መጽሐፈ ታሪክ ወግሥ

አዘጋጅ:-

መምህር አፈወርቅ ተክሌ

የቅኔ መምህርና ሰባኬ ወንጌል

1997 ዓ.ም አዲስ አበባ

«አባቶች ሆይ ከመጀመሪያ የነበረውን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ:
ጉበዞች ሆይ ክፉውን አሸንፋችኋልና እጽፍላችኋለሁ::
ልጆች ሆይ አብን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ» 1ዮሐ. 2÷12

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ እትም 1997 ዓ.ም

የመጽሐፉ መታሰቢያነት

የዛሬ ማንነቴና የሕይወቴ ትርጉም ለሆነችኝ ምስጢርን አመስጥሬ እንዳውቅና ትምህርተ ሃይማኖትን እንድረዳ የዕውቀት ፈር ቀዳጅ ለሆነችኝ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቆሙ ትምህርት ቤት እንዲሁም የጉባኤ መምህራንና ተማሪዎች ትሁንልኝ።

ምሥጋና

ይህን መጽሐፍ ከረቂቅ ጀምሮ ለሕትመት እስከበቃበት ዕለት ድረስ የተለያዩ መጻሕፍትን በማንበብና መረጃዎችን በማሰባሰብ እንዲሁም የኮምፒውተር ሥራው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በጥራት እንዲከናወን በማድረግና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ባለው በቂ ዕውቀትና ችሎታ ከጐኔ ሆኖ ላንባብያንና ለተማሪዎች በቂ ዕውቀት ሊሰጡ የሚችሉ ጠቃሚ ቃላቶች በመጽሐፉ ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ በአጠቃላይ ከረቂቅ እስከ ሕትመት ድረስ ጊዜውን ሰውቶ ጉልበቱን ዕውቀቱንና ምክሩን ለለገሰኝ ለሊቀ ዲያቆናት ፍስሐ ስንደቁ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ከዚህ በታች በሚከተለው ገጽ የተጻፉት የቃላት ማሳጠሪያ ቃሎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት እንዳሉ ሆነው የቀሩትን እንደሚከተለው እናሳያለን።

ስንክ	ማለት	ስንክሳር
መስ	»	መስከረም
ጥቅ	»	ጥቅምት

ወራቱን በዚህ ዓይነት ዝለቅ

ፍነ	ማለት	ፍትሐ ነገሥት
ፍት.መን	»	ፍትሕ መንፈሳዊ
መጽ.ምሥ	»	መጽሐፈ ምሥጢር
ሃይ.አበ.	»	ሃይማኖተ አበው
መዝ.ሃይ	»	መዝገበ ሃይማኖት
ድር.ማህ.	»	ድርሳነ ማህየዊ
ዲዲ.	»	ዲዲስቅልያ
ግን.	»	ግንዘት
ቀሌ	»	ቀሌምንጦስ
ቅዳ.አፈ	ማለት	ቅዳሴ አፈወርቅ
ቅዳ. ማር	»	ቅዳሴ ማርያም

ቅዳሴዎችን በዚህ ዓይነት ዝለቅ

አረጋ.	ማለት	አርጋኖን
ፊልክ.	»	ፊልክስዩስ
ፈላ.	»	ፈላስፋ
ገድ.ተክ.ሃይ.	»	ገድለ ተክለሃይማኖት
ገድ.ጊዮ.	»	ገድለ ጊዮርጊስ

ገድላትን በዚህ ዓይነት ዝለቅ

ክብረ.ነገ	ማለት	ክብረ ነገሥት
አረ.መን.	»	አረጋዊ መንፈሳዊ
ፈመ፡	»	ፈውስ መንፈሳዊ

እንዲሁም የግሡን አወጣጥ በዚህ አይነት እናሳያለን።

ው	ማለት	ውስጠ ዘ.
መ	»	መስም ውስጠ ዘ
ግ	»	ግብር ቅጽል
ስ	»	ስርዋጽ
ባ	»	ባዕድ
ባ.ሙ.	»	ባዕድ ሙሻ ዘር
ባ.ከ.ም.	»	ባዕድ ከ ምዕላድ

ምዕ.	»	ምዕላድ
ሳ.	»	ሳቢ ዘር
ዘ.	»	ዘር
ጥ.	»	ጥሬ
ጉል.	»	ጉልት
መድ.	»	መድበል
በብ.	»	በብዙ
የብ.	»	የብዙ ብዙ
አሀ.	»	አሀዝ ቅጽል

ቃልንም ከቃል በየንባቡና በየስልቱ በየብልቱ ለይተው ነጥለው ዘርዝረው ደምረው አንድ ፈርጅ አድርገው የሚያሳዩ የቃል ምልክቶች አምስት (5) ናቸው። መልካቸውና ስማቸውም ይህ ነው።

መልካቸው		ስማቸው
•	.....	ነጥብ÷ አው (ወይም) ነቊጥ÷ ማጥበቂያ።
:	.....	ንውስ ነጥብ÷አው ንጻል (ነጠላ)።
፡÷	.....	ንውስ ሠረዝ ÷ አው ንጻል።
፤	.....	ዐቢይ ሠረዝ÷አው ክውብ (ድረብ)።
።	.....	ዐቢይ ነጥብ÷አው ክውብ ናቸው።

ማሳሰቢያ:- ከዚህ መጽሐፍ ከሀ እስከ ፐ ድረስ ባለው ግሥ እየጠበቁና እየላሉ የሚነበቡ (የሚገሠሡ) ቀለማቶች መኖራቸው ይታወቃል። ሆኖም አንባብያን በቀላሉ ሊረዱት እንደሚችሉ በማሰብ ጠብቀው የሚነበቡ (የሚገሠሡ) ቀለማቶችን በራሳቸው የነጥብ˚ (ይዘት˚) ምልክት የተጠቀምኩ ስለሆነ ይህ ምልክት ያለበት ግሥ ሁሉ ጠብቆ የሚነበብ መሆኑን እንድታውቁት ስል በትሕትና አሳስባለሁ።

ምሳሌ:- ቀደሰ፤ ሰብሐ፤ አሰየ።

ማውጫ ገጽ

መቅድም 1
መግቢያ 3
ትምህርት ቤት 5
ሥነ-ጽሑፍ 7
ትርጓሜ ፊደል 9
የግዕዝ ታሪክ 18
አጭር የሰዋስው ብዚል 22
ጸዋትም ቅኔ 25
ቅኔና ታሪካዊ አመጣጡ 26
ሥርዓተ ቅኔ 30
አርዕስተ ቅኔ 33
የቅኔ ዜማ ልክ 35
ፍናተ ቅኔ (የቅኔ መንገድ) 41
ሥርዓተ ንባብ 56
የግሥ አርእስት 60
ትርጓሜ ግሥ 65
የሀ ግሥ 79
የለ ግሥ 91
የመ ግሥ 104
የሰ ግሥ 116
የቀ ግሥ 144
የበ ግሥ 150
የተ ግሥ 157
የነ ግሥ 166
የአ ግሥ 181
የከ ግሥ 192
የወ ግሥ 197

ማውጫ ገጽ

የዘ ግሥ 205
የየ ግሥ 211
የደ ግሥ 222
የገ ግሥ 229
የጠ ግሥ 332
የጰ ግሥ 236
የጸ ግሥ 237
የፈ ግሥ 241
የፐ ግሥ 247
ግጥም 248
መቅድመ ክብረ በዓል 251
ልደታ ለማርያም 253
የቅዱስ ራጉኤልና የነቢዩ ኤልያስ 259
ቅዱስ ታዴዎስ 259
በአታ ለማርያም 262
ቅዱስ ፋኑኤል 270
ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ 270
አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ 273
ቍስቋም 279
ኢየሱስ 280
ግዝረት 281
ሥሉስ ቅዱስ 281
ሥላሴ በቤተ አብርሃም 283
አቡነ ኪሮስ 286
ቅዱስ ቶማስ ዘመርዓስ 289
ሚስቀል 291
አ.ያቄም ወሐና. 293

ግውጫ ገጽ

ቅዱስ ሚካኤል መቅድም 298
የሀዳር ሚካኤል 299
ሰኔ » 300
ቅዱስ ሩፋኤል 304
ደብረ ታቦር 305
አቡነ አረጋዊ 308
ቅዱስ ቂርቆስና ኢየሱጣ 315
ኪዳነ ምህረት 322
ጾመ ፍልሰታ 323
ቅዱስ አስጢፋኖስ 324
አባ ኤምስጣቴምስ 327
ቅዱስ ገብርኤል 329
ሠለስቱ ደቂት 334
ሕንፀተ ቤ/ክርስቲያን 340
በዓለ ማርያም 342
ብዙኃን ማርያም 345
ታቦተ ጽዮን 348
አስተርእዮ 350
ደብረ ምጥማት 352
ቅዱሴ ቤታ ለእግዝእትነ ማርያም 353
ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ 354
ቅዱስ ደቅስዮስ 357
ቅዱስ ኡራኤል (ሱርያል) 358
ቅዱስ ጊዮርጊስ 359
አቡነ ተክለሃይማኖት 364
ቅዱስ መርቆሬዎስ 371
ቅዱስ ቶማስ 375
መድኃኔዓለም 378

ማውጫ 7ሸ
አማኑኤል 384
አብርሃም ይስሐቅ ወያእቆብ 385
በዓለ ልደት 388
ዘጠኙ ዐዘያትና ዝኩሳን በዓላት 391
ቅዱስ ማርቆስ 393
መዓምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ 395
12ቱ ሐዋርያት 396
72ቱ አርድኢት 406
36ቱ ቅዱሳት አንስት 410
፱ቱ ቅዱሳን 414
፱ቱ ነገደ መላእክት 417
ቅዱስ መጽሐፍና አዋልድ 419
የቀድሞ የዘወትር ጸሎትና የመልክአ ድርሰት 423
ዐሥሩ ማዕርጋት 426
ዓመተ ዓለም 427
መርሐ ጉልቊ ዘመን ዘኢትዮጵያ 429

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

መቅድም የግሥና የታሪክ ወንድም

መቅድም ማለት ከመጽሐፉ ፍሬ ነገር አስቀድሞ የሚገኝ ጽሑፍ የነገሩ መሪ ፊት አውራሪ ማለት ነው። መቅድም በነቢይ ይመሰላል። ነቢይ ያለፈውንና እስከ ዕለተ ምጽአት የሚደረገውን በመንፈስ አውቆ ለሕዝቡ እንዲያስተላልፍ መቅድምም ጸሐፊው ለምን እንደተነሳሳና በመጽሐፉ ውስጥም ከገበታ እስከ ገበታ ያለውን ፍሬ ሃሳብ ለአንባቢዎች ያስረዳል፤ ያሳውቃል። ይህንን መጽሐፍ ለመጽሐፍ ያነሳሳኝና ያሳሰበኝ ዐቢይ ጉዳይ ያማርኛ እናት የቤተክርስቲያን መብራት የሆነው ግዕዝ እየጠፋ ሌላ ቋንቋ እየተስፋፋ በማየቴ ነው :: አባቱን አያውቅ አያቱን ይናፍቅ። አባትህንና ሊቃውንትን ጠይቅ /ዘዳ.32÷7/ የቋንቋ አባት የሆነውን ግእዝ ሁሉም እንዲያውቅ ያሳስባል። ያንባት መሠራት አዙሮ ለማየት እንደተባለው አግዚአብሔር ዓይናችንን ሲፈጥር አንዱን በፊት አንዱን በማጅራት አድርጉ መፍጠር ባልተሰወረውም ነበር። ነገር ግን በማጅራት በኩል በሚውለው ዓይን ፈንታ አዙሮ ማየትን አስተማረ (ፈጠረ) በፊትህ ሲመጣ የምታየውን ጣላትህን ባለህ አቅም ተከላክለህ ለመመለስ የማይቀር ነው። በኋላህ የሚመጣውን ግን ስለማታየው በብርቱ ሊያጠቃህ መቻሉን ተገንዝበህ የፊትህንና የኋላህን አስተውለህ ተመልከት። እንዲህ ያደረግህ እንደሆነ ባለታሪክ ያሰኘህል ጥንታውያንና ብሔራውያንን ልማድ አኮስሰህ ዘመናዊውን አሞግሰህ መመልከት አይኑርብህ። የግዕዝ ቋንቋ በኢትዮጵያውያን ሕያው ቋንቋ ሆኖ ብዙ መጻሕፍት ተተርጉመውበት ብዙ ድርሰቶችም ተደርሰውበት የቆየ ቋንቋ ነው ከ12ኛው መቶ ክ/ዘመን ወዲህ ግን በርሱ ፈንታ አማርኛ ስለገባበት ግዕዝ የቤተክርስቲያን ቋንቋ ብቻ ሆኖ እስከአሁን ሳይጠፋ ሲሰራበት ይገኛል። በቤተክርስቲያንም ቢሆን በንባብና በዜማ ካህናት ብቻ ይጠቀሙበታል እንጂ ከንግግር አደባባይ ከወጣ ብዙ ጊዜው ነው። የቀረው ቀርቶ በካህናቱም ዘንድ የተነበበውን ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቁት ጥቂቶች ናቸው ነገር ግን በአሁኑ ጊዜም ቢሆን አንዳንድ የሚያስደስት ነገር አለ። ርሱም ግዕዝ በዩንቨርስቲ ውስጥ ከፈተና ማለፊያ አንዱ በመሆኑ ወጣቶች እንዲማሩት ሆኖአል። ግእዝን ለማወቅ ማጥናትና ቅኔ መማር እንዲገባ በተለይ ነቢዩ

ዳዊት ራሱ ግጥም ገጥሞ ፈጣሪውን ከማመስገኑ በላይ ሌላው ሰው ቅኔ እንዲቀኝ ምሥጋና እንዲያቀርብ ሲያዝ «ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት»/ መዝ.2÷11/ ሲል ዘምሯል።አንድ ሰው ቅኔን ለመማር ሲገባ ዕድሜው የበሰለ አእምሮው የተደላደለ መሆን አለበት። ከዚህም በላይ ግዕዝ ጠንቅቆ ያወቀ መሆን ይገባዋል። ምክንያቱም ተማሪው የንባብና የዳዊት ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ የግዕዝ ቋንቋ ሳያውቅና ከዜማም ሆነ ከመጽሐፍ ትምህርት፣ ቤት ገብቼ እማራለሁ ማለት ይልቁን እንጀራ በውኃ እየፈተፈቱ እንደመመገብ የሚያስቆጥር ነው። ግዕዝ ቋንቋ በፊት አውቆ ሌላውን ትምህርት መቀበል ግን ነጭ እንጀራ በዶሮ መረቅ እየፈተፈቱ እንደመብላት ያህል ይቆጠራል። ለዚህም ጉዳይ ማስረጃ ቢያስፈልጉት የግዕዝን ቋንቋ ጣዕምና ጥቅም የቀመሱ ሁሉ ምስክሮች ናቸው። ይልቁንም ግዕዝ የአማርኛ ቋንቋችን እናት እንደመሆኑ መጠን መንፈሳዊ ሆነ ሥጋዊ ጭውውት (ንግግር) በምናደርግበት ጊዜ ወንድና ሴቱን አንድና ብዙውን ሩቅና ቅርቡን እያስለየ አማርኛችንን የሚያበለጽግ ግዕዝ የተባለው ትምህርት ነው። ይህ ግሥ ከነዘሩ ሰዋስው ከነ ነባሩ ከቅዱስ መጽሐፍና ከሌሎችም መጻሕፍት እየተጠቀሰ መጻፉ ከሌሎች የግዕዝ መጻሕፍት ለየት ያደርገዋል። ስለዚህ በውስጡ የሚገኙትን ጥቅሶች ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር እያመሳከሩ አንባብያን እንዲጠቀሙበት እናሳስባለን።

2. <u>የቅዱሳን ታሪክ</u>

ቅዱሳን ከፈጣሪያቸው በተሰጣቸው ቃል ኪዳን ፀጋና ክብርን ለሰው ልጅ የሚያሰጡ መሆናቸውን ለማስረዳት ነው። አፍ ሥራ ሲፈታ ወዳጁን ያማልእንዲሉ የዘመኑ ትውልድ ቅዱሳንን አያማልዱም እያለ የቅዱሳንን ክብርና ጸጋ ሲያቃልል ይገኛል። ነገር ግን ቅዱሳን እንደሚያማልዱ ከ1-30 ባሉት ዕለታት ታሪካቸውን ከቅዱስ መጽሐፍ በመጥቀስ ከስንክሳርና ከገድል ከተአምርና ከድርሳን ስለተዘጋጀ የተጻፈውን መመልከት ይበቃል። ታሪክ ፀሐፊው ጳውሎስ ከአቤል እስከ ሳሙኤል ያሉትን አበው ታሪክ ዘርዝሮ ሲጽፍ ሌሎችንም ሥማቸውን

ሳይጠቅስ ሥራቸውን ብቻ ሲገልጽ ጊዜን ለመቆጠብ እንዳልተርክ ጊዜ ያጥርብኛልና ብሏል / ዕብ.11÷5-33/ ስለዚህ ይህ መጽሐፍ ለጉባኤ መምህራን ማስተማሪያ ለተማሪዎችም መማሪያ ግሡን አጥንተው የዕለቱን ታሪክ አውቀው ቅኔ እንዲቆጥሩ ሰባክያንም ለምእመናን የዕለቱን ታሪክ አንብበው እንዲያሰተምሩበት ይረዳል በማለት ግዕዝ ከነጓዙ ታሪክ ከነመልኩ ሳዘጋጅ ማንኛውም አንባቢ አንብቦ ፍሬ ነገሩን እንዲረዳና ዕውቀቱን እንዲያዳብር በማሰብ ነው። ምክር ሰናይት ለኩሉ ዘይገብራ ወለዘ ያስተጋብዕ ማእረራ /መዝ.110÷10/ እንዲህ አስቀድሞ አርዕስቱን ሳያይ መቅድሙን ሳይሰማ ምክንያተ ጽሕፈቱን ሳይዝ መጽሐፍ የሚመለከት እርካብ ሳይረግጥ ወደ ኮር ድንክ ሳይረግጥ ወደ ዙፋን የሚወጣ ሰውን ይመስላል የመጽሐፉን ጠባይ የሚነግር አንቀጸ ምስጢሩን የሚከፍት በረኛው መቅድም ነውና። መቅድም የሌለው መጽሐፍ ግን ደጃፍ እንደሌለው ቤት ነው። አንባቢውም በትር የሌለው አንካሳ መሪ የሌለው ጠንባሳ ይሆናል።

<u>መግቢያ</u>

መግቢያ ማለት መሪ ምልክት ማለት ነው። አንዱን ሰው ወደማያውቀው አገር ልኮ የሚሰድ ሰው ቢያገኝ አንድ መሪ ጨምሮ ቢያጣ የመንገዱን አኳኋንና የአገሩን አቀማመጥ የሚደርስበትንም ቤት በቂ ምልክት አስጠንቶ ወይም የዚህን ካርታ ሰጥቶ ቢሰደው መልእክተኛው ያለችግር ካሠበው ቦታ ይደርሳል እንግዳ ድርሰት የሚጽፍ ሰውም ተመልካቾች ከመካከሉ ሲገቡ የመጽሐፉን አኳኋን ለማወቅ እንዳይቸገሩ መግቢያ በተባለው አርእስት ላይ የመጽሐፉን ጸባይ የአጻጻፉን ድርጅት ብቻ ዘርዝሮ ማሳየት ይገባል። እንደዚህ የሆነ እንደሆነ ተመልካቾች ያለ አንድ ችግር የመጽሐፉን ጸባይ በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ። የመጻሕፍት አጻጻፍ ሥርዓትም 5 ወገን ነው። 1ኛ አንቀጽ 2ኛ አንቀጽ እያለ በአንቀጽ ብቻ ወይም 1ኛ ምዕራፍ 2ኛ ምዕራፍ እያለ በምዕራፍ ብቻ ወይም 1ኛ ክፍል 2ኛ ክፍል እያለ በክፍል ብቻ ወይም 1ኛ 2ኛ እያለ በቍጥር ብቻ ወይም በእንተ እገሌ እያለ በበእንተ ብቻ ሊከፍለው ይችላል። ሆኖም አንቀጽ የሚባለው መክፈያ አንቀጽ በእንተ እገሌ ሲባል እገሌ ስለተባለው የሚዘረዝረው ነገር ሳይፈጸም ሌላ አያገባም ስለዚህም ጠቅላላው ዐቢይ አንቀጽ ነው። በርሱ ውስጥም ምዕራፍና ክፍል ቍጥር

ይውላሉ። እያንዳንዱ ራሱን ችሎ ከላይ እንዳለው መክፈያ ሲሆን ግን ዐቢይ አንቀጽ ንዑስ እየተባለ ርስ በርሱ የበላይና የውስጥ ይሆናል። የዚህ መጽሐፍ አጻጻፍም ይህን ሥርዓት የተከተለ ነው። ስለ አንቀጽ እናት ግሥና ዘር ሲጀምር ዐቢይአንቀጽ ነባር አንቀጽን ንዑስ አንቀጽ ስለ ታሪክ ከ1-30 ያሉ ዕለታትን ምዕራፍ 1 ምዕራፍ 2 በማለት ስለሚቆጥር የቅዱሳንን ዝርዝር አንድ ሁለት በማለት በእንተ እገሌ ስለሚለውም የዕለቱን ታሪክ ከልደት እስከ ሞት ይተርካል። ስለ ክፍል ከመግቢያ እስከ ግስ ድረስ ያሉትን ክፍል 1 ክፍል 2 በማለት ይጨርሳል።

ይህ መጽሐፍ የግእዝና የአማርኛ ንባብ መልመጃ የታላቁ ሰዋስው በር መግቢያ፣ መግለጫ፣ መክፈቻ የግዕዝን ቋንቋ ሕጉንና ሥርዓቱን አመልካች በግዕዝ ቋንቋ በተጻፉት ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት ምግባርንና ሃይማኖትን ሥጋዊ ታሪክንና መንፈሳዊ ታሪክን በጠቅላላው እጆቿን ለምጽዋት ሃሳቧን ለጸሎት ወደ እግዚአብሔር የዘረጋች ቅድስት ሃገራችን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊነቷ በጥንታዊ ቋንቋዋና በጥንታዊ ሃይማኖቷ መሆኑን ለማወቅ ለጀማሪዎች መንገድ ጠራጊና መሪ ስለሚሆን ነው። ጣፎችና አታሚዎች የፊደላትን ዘር በብራና ማሕፀናቸው በወረቀት ሰፋ ድላቸው። ከመምህራን እየተቀበሉ ፀንሰውና አምጠው በቀለም በብእር የሚወልዱት የጥፈትና የመጻሕፍት መልክ ድርሰቱ መድበሉ ከምሉ በከፊሉ ይህ ነው። ይህ የጣፍነው ሁሉ መልክ ታትሞ ተጠርዞ ታፍፎ ድጉሱና ማህደሩ ተከናውኖ ግዙፍና ምእዙን ሆኖ ሥራው ካለቀለት በኋላ መጽሐፉ በጽላት ማህደሩ በታቦት ዙሪያው መስምንቱ ማዕዘን ይመሰላል። ከዚያውም ዘንድ ቀኝ የምሥራቅ ግራው የምዕራብ ራሱ የሰሜን እግሩ የደቡብ 4ቱ ቀር በዚህ ውስጥ ያለው የንዑስ ማእዘን ምሳሌ ነው። ጥሩ መስታወት ከሌለ ፊትን በዓይን ማየት እድፋን ጉድፋን መክላት እንዳይቻል የትምህርት የጥፈትም ሥራ እንዲህ ነው። ጥሩ መምህር ጥሩ መጽሐፈ ግ ካልተገኘ ጥሩነት የለውም። መምህርና መጽሐፍ የተማሪቤት እነዚህ ሦስቱ በጥሩ ምንጭና በፈላሽ በወራጅ ተማሪና ጣፊም በውኃ ቀ

ይመሰላሉ በጥፈትና ባነጋገር የፊደል ጥንቃቄ ከሌለ ምንጩ ደፈረሰ ማለት ነው።

ትምህርት ቤት የሐዋ.19÷9 ዳን.1÷18/

ከአሁን ቀደም ንጉሥ ጳጳስ ስለ ሕዝብ በየወረዳው ያቆሙት ታላላቅ ጉባኤ ሰፋፊ የተማሪ ቤት ከሌለ ዘንድ ከአባትና ከእናት ቤት ኮብልሎ አገር ለአገር ዞሮ በልመና እንጀራ የሚማሩት ትምህርት እንደ ቅምሻና እንደ ጉርሻ የማያጠግብ ስለሆነ በሽመታና በቧገታ በራቻና በሸት ይመሰላል ከዚህ ምሳሌ የተነሳ ጥፈትና ትምህርት እየቅል ሆኖ ጥፈት አዋቂዎች ከሰዋስው ትምህርት የራቁ መጽሐፍ አዋቂዎችም ጥፈት የማያውቁ ስለሆኑ በዚህ ምክንያት የግዕዝ አዝመራ የትምህርቱ ሰብል በመምህራን ማጭድ በበሊጎ አእምሮ ተለቅሞ ታጭዶ ነዶው ታስሮ ተሰብስቦ ተከምሮ በታላቅና በሠፊው በትምህርት አውድማ ተጥሎ ምርቱና ግርዱ ተንጣሎ ገና አልታፈሰም፤ አልተዛቀም ሥፍሩና ቍጥሩ ውጤቱ አልታወቀም :: አዝመራው በዝቶ ሠራተኛው አንሷል። ከብዙ በጥቂቱ የተሠራ ቢኖር ተፈጭቶ ያልተነፋ ዱቄት ተበራይቶ ያልተመረተ ምርት ይመስላል የግሡና የፊደሉ እብቅ ቁንዱና ግርዱ የጥፈቱ ፍሬና ገለባ በትምህርት ነፋስ አልተለየም።

የጥንቱ የቆሎ ተማሪ

የቆሎ ተማሪ ማለት ጥሬ ቆርጥሞ ውኃ ጠጥቶ በችግር የተማረ ማለት ነው። አንድ ተማሪ ከዘመዶቹ ተለይቶ ዕውቀትን ለመማር ወደ ት/ቤት ሲሄድ ኮፈዳና ቅምጫና ይዞ ይጓዛል። የልብሱ ዓይነትም የበግ አጉላ ወይም ደበሎ /ኤር.43÷12 ማቴ.7÷15/ የፍየል ሌጦ ዕብ.11÷37/ በርኖስ /2ጢሞ.4÷13/ እነዚህንና ሌሎችንም ውሳጣዊ ልብሶችን ለመግዛት ቀርከሃና ሠሌን እየነገደ ልፋፈጽድቅና ልሳነ ሰብዕ እየጻፈ ይጠቀማል። ልዩ ልዩ መድኃኒትነት ያላቸውንም ዕፀዋትና አሥራው እየቀመመ በሽተኞችን አክሞ ይፈውሳል። / ሕዝ.47÷12 ራዕ.22÷2/ በትምህርት የደከሙትን ባልንጀሮቹን ዘኪያገድፍ (ፍቱን የትምህርት አብነት) እየሰጠ ይረዳቸዋል። /ኩፋ.10÷6 ጥበብ 7÷17-21 1ነገ.4÷33/ የምግቦች ደረጃዎችም የልመና ጥሬ ውጥንቅጥ / ድብልቅ/ እንደ ሕዝቅኤል ይመገባል። /ሕዝ.4÷9-12/ እንዲሁም ቁራሽ እንጀራና ጭብጥ ገብስ

/ሕዝ.13÷19/ እንደ ዳዊትና እንደ እስራኤል የተቆላ ጥሬ ይመገባል። /ኢያ.5÷11 2ሳሙ.17÷28/ እንዲሁም ሳይቆላ ጥራጥሬውን እንደ ዳንኤል ይመገባል። /ዳን.1÷12/ መምህሩም እንደሳሙኤል እንደ ኤልሳዕ ያስተምራል 1ሳሙ.19÷19 2ነገ.6÷1 ዳን.12÷3 የተማሪውንም ስም በነቢያትና በሐዋርያት ስም ይሰይማል። /ዳን.1÷6 ማቴ.10÷1-4/ ግንብ ሠሪ ደንጊያና ደንጊያውን ለማያያዝ በመካከሉ ጭቃ እንዲያደርግ በግንብ ሠሪ ደቀመዝሙሩን በደንግያው ሰዋስውን በጭቃው አገባባትን በግንብ ቅኔውን ሊቃውንት መስለውታል።

ተማሪው በልመና ጊዜ ከውሻ ጋር ያለው ጦርነት

ተማሪና ውሻ ምነው አይስማሙ፣
እስከ ዕድሜ ልካቸው አሉ እንደተዳሙ።
ምን እነሱ ብቻ ፍጥረቱ በሙሉ፣
በዚቺ በእንጀራ አይደለሞይ ጥሉ።
እናቴ ባየሽ እህቴ ባየሽ፣
በቁራሽ እንጀራ ሲያባርረኝ ውሻ።
ከአህት ከወንድምም ከእናት ከአባት መርዶ፣
እጅግ ያሳዝናል ያከፋዳ ባዶ።
እንዲህ መከራ አይቶ ለፍቶ የተማረ፣
ይኖራል በየትም እንደተከበረ።

የተማሪው ሠርግ

አንዲት ሴት በጐረቤቷ አንድ ተማሪ ሚስት ሲያገባ በሠርጉ ቀን ተጠርታ ሄዳ ስትዘፍን ከዚህ የሚከተለውን ገጠመች ይባላል።
የተማሪ ወዳጅ ቢቀር ምናባቱ ፣
ዱላ ሲያነሱበት ይላል ባዛኙቱ።
ከዚህ በኋላ አንዲት የቄስ ሚስት ከመካከል ተነሥታ የሚከተለውን መልስ ሰጠች ይባላል
እንኳን ባዛኙቱ ይበል በሥላሴ፣
እኔ እወደዋለሁ እስኪወጣ ነፍሴ።

አንቺ ባለ ጠላ ሁልጊዜ ቅራሪ፣
እኔስ እሞታለሁ ለዚያ ለተማሪ።
ነጋዴ ቢያገቡት ቅመም ቅመም ይላል፣
ገበሬ ቢያገቡት አፈር አፈር ይላል፣
ወታደር ቢያገቡት ባሩድ ባሩድ ይላል፣
ከሁሉም ከሁሉም ተማሪ ይሻላል፣
ቀድሶ ሲወጣ ዕጣን ዕጣን ይላል።

ተማሪው ከተጋባ በኋላ የማይፋታ መሆኑን አጥብቆ ያሳስባል/ሚል.2÷16 1ቆሮ.7÷38/

መማር እንደዚህ ነው ፈተና ማለፍ፣
የኋላውን አውቆ ሚስቱን የማይነቅፍ።
በሲኦል ከመኖር በብዙ ሥቃይ፣
ይሻላል መታገስ የአንዲት ሴት ጠባይ።
ብዙ ሴቶች ማግባት ክልክል ነው በጠና፣
ላዳም ሔዋን ብቻ ተፈጥራለችና ።
በትዳር ዓለም ሲኖር ክህነትን ጠብቆ ይኖራል የሌላውን ሚስትም እንደ ዮሴፍ የማይመኝ ነው። /ዘፍ.39÷7-20/ ቢሳሳት ግን ክህነቱ አይሠራም ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ እንዲሉ።

ሥነ ጽሑፍ

ጽሕፈትና የጽሕፈት መሣሪያዎች ከየት መጡ ለሚለው ራሱ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ጽፎ ያሳየው ነው። በዚሁም ሥርዓት ነቢያትና ሐዋርያት ከትውልድ ወደ ትውልድ አስተላልፈዋል። በመጀመሪያ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሙሴ እንደጻፈ። /ዘፀ.31÷18፣34÷1 ዘዳ.9÷10/ በአዲስ ኪዳንም ለጸሐፍት ፈሪሳውያን እንደጻፈ /ዮሐ.8÷6/ ነቢያትም ይህንን አብነት በማድረግ ጽፈዋል። ሙሴ

/ዘጎ.33÷2/ እያሱ / ኢያ.8÷32/ ሳሙኤል /1ሳሙ.10÷25/ ዳዊት /2ሳሙ.11÷14/ ኢሳይያስ / 2ዜና 26÷22/ ዕዝራ / ዕዝ.8÷34/ እንዲሁም በጸሐፊነት ሙያ የሰለጠኑ ሰዎች ነበሩ::/1ዜና.2÷55፣24÷6/ በአዲስ ኪዳንም /ሉቃ.1÷1 ዮሐ.21÷24/ ጳውሎስ /ገላ.6÷11/ ብዙውን ጊዜ ደራሲዎች በጸሐፊዎች ያጽፉ ነበር:: ኤርምያስ በባሮክ /ኤር.36÷4/ ጳውሎስ በጠርጤሞስ /ሮሜ.16÷22/ ጽሕፈት እጅን ንባብ አፍን እንደሚፈታ /ሉቃ.1÷63/ ጽሑፍ በዓለት ላይ በሰሌዳ በጡብና በብራና በወረቀት ይጻፍ ነበር:: /ኢዮ.19÷24 ኢሳ.30÷8 ሕዝ.4÷1 2ጢሞ.4÷13/ ለመጻፊያ በብዕርና በቀለም ይጠቀሙ ነበር:: /ኤር.8÷8 3ዮሐ.13/ የቀለም ቀንድ /ሕዝ.9÷2/ የእግዚአብሔር ቃል በጽሑፍ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ስለሆነ አይሁድና ክርስቲያኖች ምንጊዜም ልጆቻቸው ንባብንና ጽሕፈትን እንዲማሩ ለማድረግ በብዙ ጥረዋል:: /ዘዳ.6÷4-9፣4÷9 ሚራ.8÷8፣30÷1-6 መሳ.1÷8፣4÷10/ ከጥንት አባቶች ሲያያዝ የመጣው ሥርዓት አሁንም በቤተክርስቲያኒቱ ይገኛል:: ይህውም ተማሪው በጽሑፍ ራሱን ለመቻል የሚገለገልባቸው የጽሑፍ መሥሪያዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. የሸክላና የብረት ምጣድ ጥላት ከሙጫና ከስንዴ ሕራር በቀንጠፋ አበባ በውኃ ተበጥብጦ የተሰራ ቀለም

ለ. ከላም ወይም ከጉሽ ቀንድ የተሰራ የቀለም ቀንድ

ሐ. ከሸንበቆና ከቀርከሃ የተቀረጸ ብዕር

መ. ክፍየል ከበግ (ከፈረስ) ቆዳ የተሰራ ብራና

ሠ. የብራናው መወጠሪያ የሚሆኑ 2 ጫፋቸው የተበሳና 2 የሾሉ 4 እንጨቶች

ረ. በብራና ጫፍ እየገቡ ከመዋጥሩ ጋር የሚያያይዙ ቀጫጭን እንጨቶችና መገተሪያ ገመዶች

ሰ. የብራና መራመሚያ ዓይናማ ድንጋይ

ሸ. የብራናው ሰግላጥ (ሥጋ) መሰቅሰቂያ ቍልፍ ቢለዋ::

ቀ. ብራናው ከደረቀ በኋላ ጠጉሩ የሚፋቅበት ትንሽ መጥረቢያና የመጽሐፉ ገበታ ተጠርቦ የሚስማማበት አንድ ምሳር

በ. ብራናው በደረቀ ጊዜ መቅጠጫ መቀስ

ተ. የብራናው ማሥመሪያ ከቀርከሀ የተሠራ

ቸ. ለመሥመሩ ምልክት መሥጫ ከብረት የተሠራ ወስፌ (መሳፍኽ)

ኀ. በሚጽፍበት ጊዜ የብራናው ማለስለሻ የሚሆን ከገል ወይም ዓይነ በጉ ከሆነ ድንጋይ የተሠራ መድመጽ

ነ. የመጽሐፉ መጠረዣና የማጎደሩ መሰፊያ ጅማትና ሲር

ኘ. መጽሐፉ ገበታ ከገባለት በኋላ ልዩ ልዩ ሐረግ ያለው መደጎሻ ናቸው::

ታሪክ እና መቅድም ስለ ፊደል ተረክቦ እና ጥንት ስለ ትምህርታዎ ሰማያዊነት 1ኛ የአብራይስጥ ፊደል

ክፍል አንድ

ፊደልና ጥፈት ለአዳም ልጆች የተገለጡ እና የተሰጡ በአዳም ዕድሜ ነው:: ከዚያም በሣብዓይ ምዕት በሣልሳይ ትውልድ በሄኖስ ዘመን እንደሆነ ታውቋል ሄኖስን እንደ ሙሴ ስቦ በባለሟልነት አቅርቦ ረቂቁን ሕግና ትዕዛዝ አግዝፈው አጉልተው የሚያሳዩ የዓይነ ልቡና መነጽሮች ፊደላትን ሰጠው:: 22 ቱን አሌፋት በ22ቱ ሥነ ፍጥረት አምሣል ኩፋ 3÷9 በጸፍፀፈ ሰማይ ጥፎ አሳይቶ ወዲያው በልቡ እየሳለ ሥነ-ፍጥረትን 10ቱ ቃላትን በቃል በፊደል ያስተምራቸው ዘንድ ያለፈውን ታሪክ እና ዜና ተረስቶ እና ተዘንግቶ እንዳይቀር ለቅሞ ሰብስቦ ይጥፍላቸው ዘንድ ሥራውን እና አሠራሩን ነድፎ አሳይቶታል ፊደላትም ቢስማቸው እና በቁጥራቸው የፈጣሪ እና የፍጥረት ምሣሌ እንደሆኑ ምስጢራቸውን አስረድቶ የጥፈት እና የትምህርት አበጋዝ የአውራን ዓይን ያንካሳን ምርኩዝ የሰው ሁሉ መገሥጽ፣ መናዝዝ አድርጐታል መናዝዝነቱም የአዳም ተስፋ ዳግማይ አዳምን በአርአያ ፊደል ስሉ መስሉ ስሙንም አሌፍ፣ወታው ብሎ በማሳየት እና በመስበክ ነው:: የኋላ ልጆች ነቢያት ይልቁንም ዳዊት ፣ኤርምያስ አቡቀለምሲስ ርሱን መስለውና ተከትለው ከባለቤቱም አፍ ተቀብለው ፊደላዊ ስሙን በፊደል እንደ ሰበኩ:: የጽርእ ፊደል

በአልፋ ዠምሮ በዖሜጋ ስለ ጨረሰ ቀድሞ ለሄኖስ አነ ውእቱ አሌፍ ወታው ያለውን ኋላ ለዮሐንስ አልፋ ወየ ብሎ መድገሙ የራእያቸውን አንድነት ያሳያል። መዝ.118÷1 ሰቈ.2÷1-22 ራእ.1÷8፤ 22÷12 ተቀባዩና ሠራተኛው ሄኖስ ብቻ ሲኾን ይህን የሄኖስን ሥራ ገድለ አዳም ለአዳም ብቻ ፈላስፋው ቀሪጦን ለሴት ብቻ ሰጥቶ ይተርካል ባለቤትነት ግን ከሄኖስ አይወጣም።

ሄኖስ ማለት ፍጹም ሰው ነፍስና ሥጋ ነባቢ ለባዊ ሕያው ማለት ነውና ስሙ ከግብሩ የተስማማ የደብር ቅዱስ ሰው ሄኖስም እንዲህ ከፈጣሪው ተሹሞና ቀሰ የሚያዝ የሚናዝዝ የታቦተ ሕጉ ዐቃቢና ገበዝ የመሲሑም ጸሐፌ ትዕዛዝ ስለ ኽነ አውታረ ልቡናዉ በድሕንግ መንፈስ ተቃኝቶለት ፊደሉን ከቋንቋ ቋንቋውን ከፊደል አስማምቶ ቀኝ እጁን በነፍስ ግራ እጁን በሥጋ ዐሥር ጣቶቹን ባሠርቱ ቃላት መስሎ አነጻጽሮ ባንደበቱና በጣቱ እያነበበና እየጣፈ የፊደልን ሥራ ከሕግና ከትእዛዝ ጋር አምልቶ አስፍቶ አስተምሯል። ሕግ አታድርግ አታድርግ ትእዛዝ ግን አድርግ አድርግ የሚለው ቃል ነው የ2ቱም ራስና ቀንድ በፍጹም ልቡና እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ ናቸው። በመሐላም ጊዜ የግዚአብሔርን ስም ብቻ እንዲጠሩ አጠራሩንም እንዲፈሩና እንዲያከብሩ እንደቀድሞአቸው ግን ደመ አቤል ያጥፋን እያሉ በሩቅ ብእሲ እንዳይምሉ አስጠንቅቋቸዋል። ወውእቱ ዘአጎዘ ይጸወዕ ስመ እግዚአብሔር እንዳለ (ኩፋሌ) 5÷18 ልጁም ቃይናን እንደ ሰሎሞን ንጉሥና ነቢይ ወዲህም ፈላስፋ ነበረና ሕዝቡን እንዳባቱ በቀና መንገድ መርቷቸዋል። ከርሱም በኋላ እስከ ላሜኽና እስከ ኖኅ ተያይዞና ተከታትሉ የሚመጣው ኹሉ ተገልጦለት ለነመላልኤል ለልጆቹና ለሕዝቡ በሰላድወ አብን እየጣፈ ከቤተ መዛግብት እንዳኖረው የአይሁድ ኩፋሌ በዕብራይስጥ ቃል ይተርካል።

በዚህም በሄኖስና በቃይናን ሥራ ግራዝማች ዲያብሎስ ቀንቶ ተመቅኝቶ ጥሩውን ትምህርት ለማደፍረስ በስንዴውም ፊደል መካከል ክርዳድ ለመዝራት ለመነስነስ ፔንሙ የሚባል 4ኛውን ያጋንንት አለቃ ጸሐፌ ትእዛዝ አድርጎ በጠላትነት አስነሥቷል በሙሴ በአሮን

እነኢያኔስን እንዳስነሣ ፔንሙም ከእግዚአብሔር በተገኘው በቅዱሱ ፊደል ሌላ ርኩሰት ትምህርት ጥንቍላና ሻርት ስመ አጋንንት እንዲጥፉና እንዲያነቡ ያስተምራቸው ዘንድ ጌታ ለሄኖስ እንዳሳየው ኹሉ ርሱም በምትሀቱ ቀለምና ከርታስ በእጁ ይዞ ርኩስ ትምህርቱን እየጣፈና እየጠለሰመ መጽሐፍ አድርጎ አሳይቷቸዋል። በቃሉም ጩኸ እየሰበከ ሳይጮኽም ቀርቦ እንደ ባለቅኔ እያሾለኮከ ምስጢሩን ኹሉ በጉሯቸውና ባይናቸውም አጥግቧቸዋል። ይልቁንም ጽልሙታን ከዋክብት የተባሉ የደቂቀ ሴትን አለቆች አነስማዝያን ማሩን አምርሮ ወተቱን አጥቁሮ በመንገርና በማሳየት እንደናታቸው እንደ ሔዋን እያስጉመዠ ማርኳቸዋል። ሕዝቡንም ባለቆቹ ዐድሮ እየሳበ ጭፍራ አድርጎቸዋል። ዛሬም የርሱን አሠር ተከትሰው በቅዱሱ መጽሐፍ በዳዊት በወንጌል በጉልቁ ፊደል የሚያሻርቱ ርሱንም እንደሐረግ በገዛ አስማቱ የሚስቡ የሚጉትቱ ምስጢሩንም በጉራቸው ሰምተው እያዜሙ ለጠየቋቸው የሚያሰሙ ሰዲያብሉስም መልክ ደርሰው ጠላታቸውን ለመጉዳት በዳዊት ፈንታ መልኩን የሚደግሙ የሰብአ ትካት ቁራጮች ብዙ ሰዎች አሉ። ጌታም በወንጌል ወሰበ ይነውሙ ሰብኡ መጽአ ጸላኢ ወዘርዐ ክርዳደ ማእከለ ሥርናይ ወጎለፈ ያለው ከአዳም ከሄኖስ እስከ ርሱ ድረስ ለነበረው መጽሐፍና ትምህርት ላለፈው ኹሉ ነው እንጂ ከርሱ በኋላ ወደ ፊት ለሚመጣው ብቻ አይደለም (ማቴ 13 ÷25-30)።

ከዚህም ቀጥለን ላለፈውና ለሚመጣው ከመጽሐፈ ሔኖክ እንጠቅሳለን (ሔኖ 19÷22-25) ወራብዕ ስሙ ፔንሙ ዝ ውእቱ ዘአርአየ ለውሉደ ሰብእ መሪረ ወመዐርጊረ ወአርአዮሙ ኩሎ ኅቡኣተ ጥበቦሙ (ለአጋንንት) ወአለበዎሙ ውእቱ ለሰብእ መጽሐፈ በማየ ሕመት ወበክርታስ። ወበእንተ ዝ ብዙኃን ይስሕቱ እምዓለም ወእስከ ለዓለም ወእስከ ዛቲ ዕለት እስመ ኢተወልደ ሰብእ ለዘከመ ዝ ግብር ከመ ያጽንዑ ሃይማኖቶሙ በቀለም ወበረቅ እስመ ኢተፈጥረ ሰብእ ዘእንበለ ከመ መላእክት ከመ ይኩኑ ጻድቃነ ወንጹሐነ። ወሞት ዘኩሉ ያማስን እምኢገሰሶሙ አላ በዝ አእምሮቶሙ ይትህጐሉ ወበእንተ ዝ ይበልዐኒ ኅይል እንዳለ።

ኅጢአት የባሕርያችን ናት ለሚሉም አለመኾኗን ሲያጠይቅ መሐልኩ ለከሙ ኃጥአን ከመ ኢኮነ ደብር ገብረ ወኢይከውን ወኢወግር አመተ ሰብእሲት

ከማሁ ኃጢአትኒ ኢተፈነወት ዲበ ምድር አላ ሰብእ እምርእ ሶሙ ፈጠርዋ ወለመርገም ዐቢይ ይከውኑ እለ ገብርዋ ብሉባቸዋል።

ሐተታ

የአዳም ኃጢአት ካባት ወደ ልጅ መውረዱ አዳምን መስለው ተከትለው በሚሠሩት ብቻ ነው እንጂ በማይሠሩትና በሚነቅፋት እንደ ሄኖክ በሚጸየፋት በልጆቹ ኹሉ አይዶለም ይኸውም ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ በተባሉት በናትና ልጇ ይታወቃል። ጽድቁም እንደ ኃጢአት ነው ከባሕርይ ተከፍሎ በመወለድ አይወረስም አባትን መስሎ በመሥራት ብቻ እንጂ (ሕዝ 18÷4ና 20) በዘርም እንዳይወርድ የአዳም ኃጢአት የነፍስ ነው እንጂ የሥጋ አይዶለም ነፍስም እንደ አዳም ነፍስ ከፈጣሪ እፍታ በንጽሐ ጠባይዕ ተገኝታ ካባት ከናት በተከፈለው በዘርና በደም ታድራለች እንጂ ርኳ አትከፈልም (ኢሳ 42÷5 ዘካ 12÷1)

ትርጓሜ ፊደል የሰዋሰው ቡቃያና ተክል

ክፍል 2

መቅድመ ሰዋሰው ወግስ ጸያሔ ንባብ መብእስ ወመርትዔ ነገር ሐንካስ ለዘውስተ ኃይል እምኀይል የሐውር ወይገይሥ። ጸዋትወ ፊደል በበ ማዕረግ ወበበ ክፍል እስመ ለሊሃ ፊደል እመ መቅድመ ቃል ከዊነ ሰዋሰው ዘትክል ለዘእምታሕቱ የዐርግ ሃበ ላዕል

ፊደል ማለት የቋንቋና የቃል ያነጋገር ኹሉ ምልክት አምሳል ወይም መግለጫ ማስታወቂያ ማለት ነው የሰው ኹሉ መልክ በጥሩ ሥዕልና መስታወት ታይቶ ተለይቶ እንዲታወቅ የማይታየውም ሣቡዕ ንባብ ረቂቅ ሐሳብ በቀለም ገዝፎ በክርታስ ተጥፎ በፊደሉ መልክ ታይቶ ተለይቶ ይታወቃልና ስለዚህ ምልክት አምሳል መግለጫ ማስታወቂያ አሉት። በግእዝም ፊደል ብሎ ጣፊ ቆጠረ ለየ መረጠ ይላልና ፊደለ ከዚህ ይወጣል ልዩ ምርጥ ማለት ነው። ቅንጣትነቱን የቃል ዘር መኾኑን ያሳያል። ዐረቦች ሐርፍ ዕብራውያን አት ይሉታል በተገናኘ ምልክት ማለት ነው።

መላው የግእዝ ፊደል ከነ አበጋዙና ከነንዙ ከነአጋዙ

የግእዝ ፊደል	26	x 7 =	182
ተረፍ (ዲቃላዎች)	4	x 5 =	20
አማርኛ ፊደል	7	x 7 =	49

ከግእዝና ከአማርኛ የሚገኙ የራብዕ ዲቃሎች

ራብዖች ብቻ 21 ድምር 272

ስለ ሰባቱ ፊደላት

ክፍል 3

ይኸውም ሊቃውንት ከጥንት ከአበው በተገኘ ከውሉድም የተሰናኘ ትርጓሜ ፊደል የአባ ሰላማን ትጋትና ሥራ ሲተርክ ወአምጽአ ለነ ሰላማ ጳጳስ ፊደለ እምሕርክትያኖስ ወሜጦሙ በአሀዱ ልሳን ወአሙንቱ ስበዑቱ ፊደላት ብሎ ይመሰክራል። ሰባቱ ማለቱ ከግእዝ ጋር ነው። ከሰባቱ ደግሞ ስድስቱ ከነዚያውም 2 :2ቱ ግእዝና ሳድስ፣ካዕብና ሳብዕ ሣልስና ኃምስ ሱቱፋን ናቸው ይወራረሳሉ። ይኸውም በገቢር አንቀጽ ሞአ ፀረ ወጸላኤ ሐነጸ ቤቶ ወጽርሑ ያለውን በተገብሮ ተሞአ ፀር ወጸላኤ ተሐንጸ ቤቱ ወጽርሑ እያለ መኼዱን መናገር ነው። ራብዕ ግን ኃምስና ሳብዕ ሳይቀሩ ከሁሉም ተፈቃቃሪ ነው መልኩን ድርድሩን ሳይለውጥ ሁሉን ይከታል ይህም በልአ ሥጋ ወመና ተበልዐ ሥጋ ወመና ማለቱን ያሳያል ኃምስ ሳብዕ ደግሞ እንደ ራብዕ ናቸው ቀሠመ ጽጌ ወፍሬ ተቀሥመ ጽጌ ወፍሬ አኃዘ ዶርሆ ወእንቆቅሐ ተእኅዘ ዶርሆ ወእንቆቅሐ እያሉኙ ገቢር ተገብሮ ይከታሉ። 6 ያልናቸው 3 መዋርስቶች ባይንና በጉሮ ባፍንጫ ይመሰላሉ፣ራብዕ በአፍ ይመሰላል ባለቅኔዎች ግን ሰባቱን ኹሉ በሰባቱ ዕለታትና በሰባቱ ሀብታት በሰባቱ ምስጢራት ይመስሏቸዋል። ኪ.ወ.ክ.መ.ሰ.ወ ገጽ 29

ክፍል 4

መላው 26ቱ ፊደላት በ5 ጸታ ተከፍለው በ5ቱ ሕዋሳተ አፍ በጉሮሮና በትናጋ በምላስና በከንፈር በጥርስ ይነገራሉ ጸታቸውና ክፍላቸውም ይህ ነው። 1 በጉሮሮ የሚነገሩ 5 ናቸው። እነርሱም አ፡ሀ፡ሐ፡ኀ፡ዐ ናቸው።

እነዚህ 5ቱ ከመላላት በቀር መጥበቅ የላቸውም።

2 በትናጋ የሚነገሩ 4 ናቸው እነርሱም ገ፡የ፡ከ፡ቀ ናቸው

3 በምላስ የሚነገሩ 5 ናቸው እነርሱም ደ፡ጠ፡ለ፡ነ፡ተ ናቸው፡፡

4 በከንፈር የሚነገሩ 6 ናቸው እነርሱም በ፡ወ፡መ፡ፈ፡ጰ፡ፐ ናቸው

5 በጥርስ የሚነገሩ 6 ናቸው እነርሱም ዘ፡ሠ፡ጸ፡ፀ፡ረ፡ሰ ናቸው

አኃዝ ቅጽል

ክፍል 5

ጸዋትወ ቅጽል ወአኃዝ የሰዋሰው ባለቤትና ጓዝ

አኃዝ ዘርና ነባር ስለ ኾነ በዘርነቱ ከዘር ቅጽሎች እንዲስማማ በነባርነቱም ከነባር ቅጽሎች ከንዑስ ከደቂቅ ይስማማልና ቁጥሩ ከ2ቱም ነው፡፡ ዘርነቱም በዝርዝር ፊደል ሲጣፍ ነው፡፡ አኃዝ ካንድ እስከ ምእልፊት ያለ የቁጥር ኹሉ ጠቅላይ ስም ነው አኃዝ ማለት መያዣ ዐረቦን ወይም ኾምርና ውጥን ማለት ነው፡፡ መያዣው አንዳንድ ቅንጣት ፊደል (1፡2፡3-አ፡በ፡ገ) ውጥኑም ቃል ነው አንድ ኹለት ሦስት ማለት፡፡ ከ7 እስከ 1000 ምንም በየክፍሉ ፍጹም ቢሆን ያንዱ ቤት ላሥር ያሥሩ ለመቶ የመቶው ለሺሕ የሺሑ ለአልፍ የአልፍ ለምእልፊት ውጥን ይባላል 10ሩ የርባታ መደብ ለ80ው መደብ ውጥን እንዲባል፡፡ አኃዝ ሲባል ኹሉም ውስጠ ዘና ውስጠ ብዙ ስም ነው ስፍን ስፍናዊ ብሎ ለሚጠይቅ ወይም ለሚያስብ የብትኖችን ማነስና መብዛት ስንትነትና ስንተኛነት ዘርዝሮ ደምሮ ለማሳየት ከባለቤት በፊት እየገባ ዐብሮ የሚነገር ባለቤትም ባይኖር ርሱ ራሱ በቂ ስለኾነ ቅጽል ይባላል፡፡ ርስ በርሱም ይቀጻጸላል፡፡ ካንድ እስከ ምእልፊት ያለ አኃዛዊ ቁጥር ባንድ ረዥም ገመድ ሲመሰል ቤቱና ክፍሉ 5፡5 ይኾኑለታል ቤት 1፡10፡100፡1000፡10000፡፡ ክፍል መዘርጋት መተርተር መክፈል ማጠፍ መጠቅለል ናቸው፡፡ መዘርጋት ብዛትንና ስንትነትን እንደ ነዶና እንደ ችቦ አስሮ ሰብስቦ የሚያሳይ የጅምላ ቁጥር ነው፡፡ ምሳሌ 1፡2፡10 እንዲሁ፡፡ መተርተር ስንትነታቸው ከታወቀ ከብዙዎች ማኸል ስንተኛነትን ለይቶ የሚያሳይ የተራ ቁጥር ነው፡፡ ምሳሌ 1ኛ 2ኛ 10ኛ እንዲሁ፡፡ መክፈል

የክፍሎችን ስም እንደ ተራ ቁጥር እየለየ በየማዕረጉ የሚያሳይ ክፍላዊ ቁጥር ነው፡፡ ምሳሌ መንፈቅ ሣልሲት ራብዒት ወከማሁ ማጠፍ ጅመላውን ቍጥር ዐጥፎ ደርቦ እያሳየ በመንታ መንገድ የሚወስድ የአጸፋ ቍጥር ነው፡፡ አሐዳት አው ካዕበተ አሐዱ 1 ዕጽፍ፡፡ክልኤታት አው ካዕበተ ክልኤቱ 2 ዕጽፍ 4 ነጠላ ወከማሁ፡፡ መጠቅለል እንዳራቱ ክፍሎች አኃዝ ሳይኖረው በቅጽልነቱ ማነስና መብዛት ሕጸጽና ምልአት የሚያሳይ የአኃዝ ቅጽሎች ሰብሳቢና ከታች የሚኾን መድበል ቁጥር ነው ያውም ጎዳጥ ብዙኅ ኵሉ ይህን የመሰለ፡፡

ሥራቸውንና ጫፋቸውን በገመድ ዘይቤ ስበን ጐትተን መዘርጋት መተርተር ያልናቸው ጅምላና ተራ አካኼዳቸው እንደ የዋህና እንደ መሠሪ ርባ ስለ ኾነ ስማቸው የዋህ ቁጥርና መሠሪ ቍጥር ይባላል የዋሁ ጅምላ መሠሪው ተራ ነው የቀሩትም ሦስቱ መክፈልና ማጠፍ መጠቅለል ያልናቸው ከፋይና ዐጣፊ ጠቅላይ ይባላሉ፡፡ ጅምላና ተራ ከአንድ እስከ ኻያ ወንድና ሴት እየለዩ ከዚያ በላይ ግን ሳይለዩ ዕሥራ ሠላሳ በማለት እያስተባበሩ ይኼዳሉ ይኸውም ምእላድ ሳይኖር ነው ምእላድ ሲኖር ግን ዕሥራ ሠላሳ ያለውን ዕሥራዊ፣ ዊት ሠላሳዊ፣ ዊት ያሰኛልና ከመለየት በቀር ማስተባበር የለም፡፡ የጅምላ ቍጥር አጣጣፍና አፈታት 2 ዓይነት ነው አጣጣፍ በአኃዝ በፊደል አፈታት እንደ ንባቡ አንድ አንዱ ኹለት ኹለቱ እያለ በሳድስ በካዕብ መጨረስ ነው፡፡ የሴቶችም ቍጥር ከአንድ እስከ ኻያ ከፊደል እንጂ ከአኃዝ ጋር አይስማማም ዱባና ቅል ነው፡፡ ስለዚህ አሐተ፡ አሐቲ ክልኤ፣ ክልኤቲ ሠላስ፣ አርባዕ፣ ኀምስ፣ እያለ በፊደል ብቻ ይጣፋል፡፡ አኃዝ ቅጽል ዘርና ነባር ስለ ኾነ ርባታውና ዝርዝሩ እስከ 10 መደብ ነው፡፡

የወንዶች ጅምላና የሴቶች ጅምላ ቁጥር

፩	አሐድ ዱ	አንድ ዱ	አሐ(ድ) ት፡ቲ
፪	ክልኤ፡ ት፡ ቱ	ኹለት፡ ቱ	ክልኤ፡ቲ
፫	ሠለስት፡ ቱ	ሦስት፡ ቱ	ሠላስ
፬	አርባዕት፡ ቱ	አራት፡ ቱ	አርባዕ
፭	ኀምስት፡ ቱ	ዐምስት ቱ	ኀምስ
፮	ስድስት፡ ቱ		ስሉ
፯	ሰብዐት፡ ቱ		ሰብዑ

፮	ስምንት፡ ቱ		ሰማኒ፡ ኒቱ
፱	ተስዐት፡ ቱ	ዘጠኝ፣ኙ	ተስዑ
፲	ዐሥርት፡ ቱ	ዐሥር፡ ሩ	ዐሥሩ
፲ወ፩	ዐሥርት ወአሐድ ፡ዱ		ዐሥር ወአሐት ፡ቲ
፲ወ፪	ዐሥርት ወክልኤት ፡ቱ		ዐሥር ወክልኤ፡ቲ
፲ወ፫	ዐሥርት ወሠለስት ፡ቱ		ዐሥር ወሠላስ
፲ወ፬	ዐሥርት ወአርባዕት ፡ቱ		ዐሥር ወአርባዕ
፲ወ፭	ዐሥርት ወኀምስት ፡ቱ		ዐሥር ወኀምስ
፲ወ፮	ዐሥርት ወሰድስት ፡ቱ		ዐሥር ወስሱ
፲ወ፯	ዐሥርት ወሰብዐት ፡ቱ		ዐሥር ወሰብዑ
፲ወ፰	ዐሥርት ወሰምንት ፡ቱ		ዐሥር ወሰማኒ ፡ኒቱ
፲ወ፱	ዐሥርት ወተስዐት ፡ቱ		ዐሥር ወተሰዑ
፳	ዕሥራ ኻያ ካያ ካዕበተ ዮድ		ዕሥራ 2 ጊዜ 10
በወንዶች ዕሥራ ወአሐድ፡ ዱ በሴቶች ወአሐተ፡ ቲ እያለ እስከ 29 እንዲሁ ተጫፍሮ ይኼዳል			
፴	ሠላሳ	በቁሙ	ሦስት ዐሥር
፵	አርብዓ	አርባ	አራት ዐሥር
፶	ኀምሳ	ዐምሳ	ዐምስት ዐሥር
፷	ስ(ድ) ሳ	በቁሙ	ስድስት ዐሥር
፸	ሰብዓ	ሰባ	ሰባት ዐሥር
፹	ሰማንያ	ሰማንያ	ስምንት ዐሥር
፺	ተስዓ	ዘጠና	ዘጠኝ ዐሥር
፻	ምእት	መቶ	ዐሥር ዐሥር
፻፩	አምአት አው ዐሥርቱ	ምእት	ዐሥር መቶ ፩ ሺህ
፳፻	ዕሥራ ምእት	ኹለት ሺህ	
፴፻	ሠላሳ ምእት	ሦስት ሺህ	
፵፻	አርብዓ ምእት	አራት ሺህ	
፶፻	ኀምሳ ምእት	አምስት ሺህ	

፷፻	ስሳ ምእት	ስድስት ሺህ	
፸፻	ሰባዓ ምእት	ሰባት ሺህ	
፹፻	ሰማንያ ምእት	ስምንት ሺህ	
፺፻	ተስዓ ምእት	ዘጠኝ ሺህ	
፼	አልፍ (መቶ ጊዜ መቶ)		ዐሥር ሺሕ
፲፼	ሀሥርቱ አልፍ አው አእላፍ		መቶ ሺሕ
፳፼	ዕሥራ አልፍ ሠላሳ አልፍ እያለ እስከ ፺፼፼ ይኼዳል		
፻፼	አእላፋት መቶ አልፍ ወይም ፲፼ ሺህ (ሚልዮን)		
፲፻፼	ትአልፊት ሺህ አልፍ ወይም አልፍ ሺህ (፲ ሚሊዮን)		
፳፻፼	ዕሥራ ምእት አልፍ እንዲህ እያለ እስከ ፺፻፼ ይኼዳል		
፼፼	ምአልፊት	አልፍ ጊዜ አልፍ (፻ ሚልዮን)	

ሐዲስ ሐሳብ እንግዳ ቁጥር በምአልፊት ላይ የሚጨመር የቢልዮንና የትሪልዮን አንጻር::

ምአልፊትን ደግሞ እንደ አልፍ ፲፡፻፡ ፲፻፡ ፻፻ አያሉ በ 4ቱ ቅጽሎች ሲያበዙት አንድ የነበረው ፼ ምአልፊት ይኾናል:: ኹለተኛም በሚሊዮንና በቢልዮን ተራ ሲያወርዱት ትሪልዮን ከሚባላው ቍጥር ይስማማል:: ከአልፍና ከአእላፍ በላይ ያለ ቍጥር በውሳኔም አለውሳኔም ይነገራልና ውሳኔው ይህ ነው:: ያለውሳኔ ግን ሲነገር አእላፈ አእላፋት ወትአልፊተ አእላፋት ምአልፊት ይላል ብዛቱ እንዳሸዋና እንደ ኮከብ ሰፍሮ ቁጥሮ ሊያውቁት የማይቻል ከፈጣሪ በቀር ሰፋሪ ቈጣሪ ልክና መጠን የሌለው የብዙ ብዙ ማለት ነው አባይን በጭልፋ እንዲሉ ዘፍ 13÷16 : 15÷5

መዐዛ ሰዋስው ፊደል የግጥም ስብክት

ክፍል 6

ላንቀጹ ፍልሰታ ለርባታው ሑዳዴ፡ የተለቀመውን ጥሩ ፊደል ስንዴ
በቀለም ገበያም ጣፊው ብር ሲቀረጥ ፡ፊደሉ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ
ነቢያት የዘሩት የፊደላት ገብስ፡ ስሙ ልጅ አልቅሶ ቶሎ የሚደርስ
እግዚአብሔር የወሰነው በሕዝቅኤል አፍ፡ ሰባት ዓመት ብሉ መንፈቅ ሳያተርፍ

ይህም ሰባት ዓመት ዘመነ ማእረር፡ ከበጉ ዐይንና ቀንድ የሚተባበር
አብዝቶም ሲጠጡት በሽልም ፊደል፡ ሆድ ስላላሞቀ ጠላ ነው ብንል
ፊደሉ ብረሃን ዘእምብርሃን- ሰባት ቁልጭልጭ የእግዚአብሔር በግ ዐይን
የፊደሉ ምንጭ ዐይነ ውሃው-ከላይ ነውና የፈለቀው
ከሣር ከቅጠል በዝቶ ጊዜዋ-አሮጊት ስትሆን በተፈጥሮዋ
እንደ ሔኖክ ንስር ሕዋሳቶች-በተሐድሶ ስለኖረች
ዐይንና ጥርሷ ብሉይ ሐዲስ-ነጭና ጥቁር የሚያጣቅስ
ዝርባዋም ንባብ እንደ ሰሎሜ- ጌታን ያዘለው በሰው ትርጓሜ
ጌታም ለሄኖስ ሲድራት ባርኮ-ስላረገዘች የርሱን አምልኮ
ከአልፍ እስከ ታው መልኩ ፊደል- የሥነ ፍጥረት ጠቅላይ መድበል
የመልኩም ድርሰት በማሕልይ -ተጥፎለታል ደግሞም ለሚያይ
መስለናታል በጥሩ ዐይናማ- ከወጣቶች ልብ እንድትስማማ
ዐይናማነቷም እንደ ንስር- የወረደ ነው በፊደል ዘር
ምንም ቢያጅቧት መኳንንቶች - ዐይኗና ልቧ ከተማሮች
እኔም ልጨፍር ቃሌን ላንሳው - ተማሪን ሁሉ ደስ እንዲለው
በሽብር ወንዶቿም ነገደ ሴም - የተሠራጩት በምድረ ካም
ታሪኩም ቈንጆ ስሙ ብርሃነ- በምስራቅ ቋንቋ የሰለጠነ
በተራራም ላይ የሠሩት ግፍ- አይሰወርም ከታሪክ አፍ
ቅዱስ መጽሐፍም በርሱ አማርኛ- ከእግዚአብሔር ተልኮ መጣ ዳግመኛ
የትምህርቷን ወንዝ አለወረፋ -ኹሉ እንዲቀዳ እየተስፋፋ
ርሷም ጣይቱ መሐንዲስ ኹና- እየቀየሰች የሰው ልቡና
ወጣት ወጣቱን ለመቀበል- አዘጋጅታለች ቤቷን ፊደል
ሊፕም እንዳይኾን ትርጓሜው ኹሉ- ትምርቱን ማብሰል በየሌዱ

2ኛ የግእዝ ታሪክ

ክፍል 1

ግዕዝ ማለት ምን ማለትነው ግዕዘ ተጓዘ ከሚለው ግሥ የወጣ ነው
ከወዴትስ መጣ? መቼ? ግዕዝ ማለት ስመ ተጸዎዖ የቋንቋ ወገን ል
ክፍል ማለት ነው:: የግዕዝ ምሥጢሩ አነጋገሩ ብዙ ልዩነት ያሳያል

ግዕዝ ሲባል አርነት መውጣት፣ ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ መሸጋገርና ከባርነት ወደ ነፃነት መውጣትን ያመለክታል:: ስለዚህ ኢትዮጵያን ብሔረ አግዓዚ(አግዓዝያን) ሲል በብዙ ሥፍራ ይገኛል:: ግዕዝ ራሱ ዓይነት/ነፃነት/ ሰጭ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል:: አግዓዝያንም ተብለው ቋንቋቸውን ግዕዝ አሰኙት የተባለበት ምክንያትም ደቡብ ዓረብ ከክርስቶስ በፊት ኤርትራን ተሻግረው በሰሜን ኢትዮጵያ ተበታትነው የተቀመጡት የኛ የግዕዙ ታሪክ ነገሥት ነገደ ዮቅጣን ይላቸዋል:: ኖህ ለአዳም አሥረኛ ትውልድ ሲሆን ዮቅጣን ደግሞ ለኖህ ልጅ ለሴም አራተኛ ትውልድ ነው:: / ዘፍ .10:25/ የአገራችን ታሪክ ፀሐፊዎችም እንደሚተርኩት አገር ነባር የሆነውን የኢትዮጵያን የነገደ ካሙን መንግሥት አሸንፎ የወረረውን የሕንድ ንጉሥ ራማን እነዚህ ነገደ ዮቅጣን አሸንፈው አገሪቱን ነፃ ስለአወጡ ነገደ አግዓዝያን ነፃ አውጭዎች ተባሉ:: ሳባ ትግሬን ሲይዝ፣ ወንድሞቹ አባል የአዳልን አገር አፌር ውጋዴንን መያዛቸውን ይገልጻሉ::

እነዚህ ሰዎችም የመጡበት ዘመን፣3ሺህ 36 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በዮቅጣን ልጅ በሳባ ሳባውያን ተብለው የነርሱ ገዥ ሴት ስትሆን ንግሥተ ሳባ ወንድ ሲገዛ ንጉሠ ሳባ ይባል ነበር::

ዛሬ የተጣራው ታሪክ በደቡብ ዓረብ ሳባውያን ሀበሻን፣ሂሚያራት ሐማሪት እንደነበርና እነዚህም የሴም ወይም የዮቅጣን ነገዶች ውስጥ የኤርትራን ባሕር ተሻግረው በኢትዮጵያ ሰሜን በየአውራጃው ተሰማርተው የአክሱምን መንግሥት አቁመው ይተዳደሩ እንደነበር ከማስረጃውም በአክሱም ሐውልቶች ላይ የሚነበበው የሳባውያን ፊደል የጨረቃ አምላካቸው ከነምልክቱ የነገሥታት አስተዳደርና ልማድ በደቡብ ዓረብ ከሚገኘው ጋር ፍጹም አንድ ወይም ተመሳሳይ በመሆኑ ነው::

የአማልክቱም ሥም ሚስረም፣አስታር፣ አለመቅህ፣ ህውብስ... እያለ በደቡብ ዓረብ የተገኘው በኢትዮጵያ ሰሜን ተገኝቶአል:: ስለሆነም በዔቦር ዕብራውያን ተብለው ቋንቋቸው ዕብራኒ ወይም እበራይስጥ እንደተባለ በግዕዝ አግዓዚ / አግዓዝያን/ ተብለው ቋንቋቸው ግዕዝ አገራቸውን አግዓዚት አሰኙ:: ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ግራኝ መሐመድ ወረራ በሚል መጽሐፋቸው ምዕ.2 ገጽ 7-8

ክፍል ሁለት

1. ግእዝ የቋንቋ ሴማዊ አዳማዊ ቋንቋ የዕብራይስጥ ወንድም ከዐረብ ከሱርስት የሚገጥም ዘይቤው አልፍ እንደ ማለት አንድ መኸመሪያ ምስጢሩ ጥንታዊ አዳማዊ ልሳን ማለት ነው:: ዘፍ 11:1

2ኛም እንደ ሌላው ቋንቋ ብዙ ድካም ስለሌለበት ቅን ገር ብለው ይፈቱታል:: ተተርጕመ እምልሳነ ቅብጢ ለዐረብ ወዕም ዐረብ ለግዕዝ እን. ሃይ. አበ.1

2. ግዕዝ የፊደል ስም አንድ ወጣት አንድ ቅንጣት አንድ በቀል ዕዝል ቅጥል ነቍጥ ምክትል ዋየል አጋማሽ ኹለተኛ ፈርጅ
3. ግእዝ፣ የዜማ ስም አንደኛ ስልት መጀመሪያ ዜማ 2ኛው ሠለስቱ ዜማ ዘውእቱ ግእዝ ወእዝል ወአራራይ ወእምዝትብል ጸሎተ ዘእምዳዊት በዜማ ግእዝ ህየንተ ዕዝል ዘነግህ ግዕዝ (ስንክ ግን 11 ግንዘ፡ፍኅ) ኪ.ወ.ክ 924

ግእዝ ስለማለትና ስለመባል

ክፍል 3

ግእዝ ማለት ዋሕድ ማለት ነው ጉንድ እንደማለት ጉንድነቱም ዐጽቅ ተብሎ በተቋመ ወርቅ ይመሰላል ግእዝ የቋንቋና የፊደል ስም ሲሆን ከጌታችን ልደት በፊት በዘመነ ብሉይ ኋላም በዘመነ ሐዲስ እስከ አብርሃ ወአጽብሐ ዘመን ድረስ ካዕብ ሣልስ፣ራብዕ፣ ኀምስ፣ሳድስ፣ ሳብዕ ሳይኖር ግእዝ የተባለ ስለዚህ ነው::

ሁለተኛ የሌለው ቀንጃ ነጠላ ፊደል (ኮንሶን) ከሀ እስከ ፐ ያለ ከሰላማ በፊት ከካዕብ እስከ ሳብዕ ድረስ ሳይኖረው ርሱው ራሱ ግዕዙ ብቻ ነበረና:: ቋንቋውን ግዕዝ ያሰኘው ይህ ነው ይባላል:: ከዚያ ወዲያ ግን ከካዕብ እስከ ሳብዕ ላሉት በኩር ግንባ ቀደም ባለ ወንድም ስለሆነ አንደኛ ወይም መጀመሪያ ይባላል:: አ

ግእዝ ቡ: ካዕብ ጊ: ሳልስ ዳ: ራብዕ ሄ: ኃምስ ው: ሳድስ ዞ: ሳብዕ እንዲሉ ግእዝ አንድ አንደኛ መባሉ በአ ምክንያት ነው:: ግእዝ የንባብ ስም መጀመሪያ ንባብ ሕፃናት የፊደልን ቍጥር እጅ እግሩን ከለዩ በኋላ ከነቁጣ እስከ ነቁጣ እየጐተቱ የሚያግዙት ማጋዝ:: ለንባበ ትምህርት በየስልቱ 4 ስም አለው:: ግእዝ፣ ውርድ፣ ዐቢይ ድጋም::

በጥንታዊ ፊደል ተጥፎ ከአክሱም ሐውልት የሚገኘው ጥንታዊ የግእዝ ንባብ ያስረዳል::

መዐዛ ሰዋስው ግእዝ

ክፍል 4

ሠርቶ ያቀረበው የግእዝ ወጥ ቤት: ላስነባቢው ምሳ ላንባቢው እራት
አስተውል ተመልከት ጸሐፊና አንባቢ: ያማርኛ ግዕዝ የግዕዝ ዐቃቢ
የግእዝን ትምህርት አባይን በጭልፋ: ቀድቶ የሚጨርስ ማነው ባለተስፋ
ቀድቶም ሳይጨርሰው ከርሱ ለሚጠጣ: ለሚሻገረውም እየተቀናጣ
ዐዞውም ስንፈት ተማሪ እንዳይነጥቅ: ዋናተኛው መምህር ተግቶ ይጠብቅ
የግእዝም ፊደል በሰባትነቱ:ከትንቢት እስከ ራእይ ወየው መስማማቱ.
ጊዜ ባስረገጠው ትምህርት አውድማ: ተንጣሎ ነበረ የግእዝ ምርትማ
ሥለ ሥጋ ጥበብ ስለ ደመወዝ: ኮኛኩ ይሻላል ከጠጁ ግእዝ
ዘርፉና ቅጽሉም ባዕድ አታላይ ስም: የማይስማማ ከግእዝ ቀለም
ልጅ ዐዋቂውን ከግእዝ: እንደ ድጐስና እንደ ጥራዝ
የሚያጠብቅና የሚያያይዝ ሢራ 13÷1
ግእዝ ግእዙ ወርቅ ቀለም-ባለ 6 ዐጽቅ ጉንደ ተቋም
ስድስቱም ዐጽቆች ግራና ቀኙ-ከሱራፌል ክንፍ የተሰናኙ
ከኪሩቤልም ካራቱ ኹሉ - በራብዕ ትውልድ ይመደባሉ
ልሳኑም ጥዑም የወይን እሸት- እየተሻሙ የሚበሉት
ከአዳም ከኖኅ ካባት ከናቷ - ለሴም የታጨች ስለውበቷ
ከንጉሡም ከእግዚአብሔር ከባለቤቱ - ስለተሰጣት እቴጌነቱ
እንዲህ ብታይዋት ድኻ መስላችኹ - ባለጸጋ ናት ግእዝ ቋንቋችኹ
የግእዝን ጣዕም ብትቀምሷትማ - አትይዙም ነበር ሌላ ውሽማ

ለአንግዲሁ ግን ውሸማ አታብዙ - ርሷን አቅፋችኹ ቀድሞ ሳትይዙ
ብትጨምሩ ግን በርሷ ላይ ደግሞ - ዕዳው ገብስ ነው መቸ አረማሞ
በዚህስ ነገር ሐሜት ሳትፈሩ - እንደ ያዕቆብ ብትጨማምሩ
ስንኳን ነቢያት እነዳዊት - አይነቅፋችኹም ሐዋርያት
ያማርኛም ቃል የግእዝ ሥጋ - ስለግእዝ ነፍስ ሬሳ ባልጋ
ሬሳውን ቃል የሚሸከሙ - በግእዝ ቋንቋ ሲፈታ ይስሙ
ሥሮ ነገሩ ግእዝ ሳይጸድቅ - ፍሬ አያፈራም አማርኛ ዐጽቅ
ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ - የተባለውን እስኪ መርምሩ
እነማናቸው ዛፉን ሳያወቁ - ፍሬውን በልተው የሚጨነቁ
ዛፉንም አውቀው ሳይገላልጡ - ሾላ በድፍን የሚያላምጡ
አለበትና ብዙ ቁጫጭ - ሆድ የሚያሳምም የሚያበሳጭ
ቁስ ኹኜ ቢኾን ወይም ዲያቆን- እጠራው ነበር ስማቸውን
አፍ አለገሮሮ ቢያዜም ቢያነብ - አይታነጽም ሽካራው ልብ
መርጌታ ኹኖ አቡን ሲቃኝ - እንዲህ እንዳሉ አምጃር ዘፋኝ
ውስጡን ለቁስ ለሚናዝዝ - ቁሱም ግእዝ
ስሙ ፋና ወይም መብራት - የነፍስ አባት
አማርኛውም የንብ እንጀራ - በላስቶች ቀፎ ቀድሞ ሲሠራ
ካረብ ከሱርስት ከዕብራይስጥ - የተቀመመ እንዲጣፍጥ

3ኛ ክፍል 1

አጭር የሰዋስው ብዚል

የመምህራን ዐይን ያዕቆብ እንደ ረዥሙ አጥርቶና ቀምሎ ያላየው ቀርቦም እንደ ሐኪም ያልዳሰሰውና ያልፈወሰው:: ዘፍ.28÷10

ሰዋስው ማለት ዘይቤው መሰላል ማለት ነው:: እሙን ትርጓሜው ግን የግእዝ ቋንቋ ዐዋጅ ያሰካኩና ያጣጣፉ ያነጋገሩ ፈርጅ የንባቡ ኹሉ እጅና ፈንጅ አስተሳሰሩና አፈታቱ ተለይቶ የሚታወቅበት የትምህርት ደንብ ፍርድና አገባብ ማለት ነው:: ፍትሐ ነገሥት እንደ ማለት ኹሉ:: አዝመራ ታጭዶ ሲሰበሰብ ብዙው እንደ አንድ እስር ነዶ ብዙው ነዶ አንድ ሙሉ ዕቅፍ ብዙው ዕቅፍ፡ እንደ ጉቶ ብዙው ጉቶ

እንደ ታላቅ ክምር እንዲኾን የሰዋስውም ክፍል እንዲህ ነው:: ምዕራፍ በታላቅ ክምር ይመሰላል ብዙው ብትን ቃል እንደ ሥነ-ፍጥረት በየወገኑና በያይነቱ ሲሰበሰብና ሲለቀም ነዶውና ዕቅፉ ጉቾው በሦስት አይነት ቁጥር ተቈጥሯል::

ክፍል 2

የሰዋስው አዋጅ ርባ ቅምር

የፍጥረት ኹሉ ዐይነት 2:2 ብቻ እንደኾነ ያውም ወንድና ሴት ተባትና እንስት እንዲባል ሰዋስው ተብሎ የሚጠራም የቋንቋ ዐይነት 2 ነው ዘርና ነባር ወይም ስምና ግብር ወንድና ተባት ሴትና እንስት አንድ ወገን ኹነው በ2 እንዲታዩ እነዚህም 4ቱ ስሞች ዘርና ግብር ነባርና ስም አንድ አንድ ወገን ናቸው:: 2ኛም የመሰላል እርከን ብዙ ሲኾን በ2 አዕማድ እንዲወሰን የቋንቋም ትምህርት ስሙና ክፍሉ ስልቱና ባሕሉ ብዙ ሲኾን ዐይነቱና ሕብሩ አርእስተ ነገሩ በነዚህ በ2ቱ ብቻ ተወስኗል:: ከስምና ከግብር አይወጣም ሲዘረዘሩ ግን አንቀጽና ርባታ ዝርዝር ቅጽልና ጥሬ አገባብ ሠምና ወርቅ ሙሻዘር ፣ ሠረዝ፣ እንቈር ተብለው 10 ይኾናሉ:: ዝርዝር ከርባታ አገባብ ከጥሬ ሲደረቡ ግን 8 ብቻ ኹነው ይቀራሉ የሰዋስውን ክፍል ዝቅ ብለው 3ና 4:6 ከፍ ብለው 12 ና 15 የሚሉ አሉ::

ክፍል 3

ሰዋስውን ሊቃውንት በ10 ምሳሌ መስለውታል በምንና በምን ቢሉ በመሸጋገሪያ፣ በመሰላል፣ በድልድይ፣ በመርከብ፣ በተራራ፣ በመንገድ፣ በገበያ በፊት እና በመስተዋት፣ በአትሮንስ መስለዋቸዋል:: ሰዋስው ስለምን መሰላል ተባለ ቢሉ በመሰላል ከታች ወደላይ ይወጡበታል ከላይ ወደታች ይወርዱበታል በሰዋስውም በአግረ ሕሊና ሰማየ ሰማያት መጥቆ ዕመቀ ዕመቃት ወርዶ በዓይነ ልቡና ምጵጢረ ሥላሴን ያዩበታል መሸጋገሪያ ያለው ምነው ቢሉ በመሸጋገሪያ ከወዲህ ወዲያ ከወዲያ ወዲህ ይሸጋገሩበታል ይመላለሱበታል:: በሰዋስውም እምጽማዌ ውስተ ጥበብ እምኢያእምሮ ውስተ አእምሮ ይመላለሱበታልና ስለዚህ ሰዋስው ተባለ ይላሉ::

ክፍል 4

መዐዛ ሰዋስው የግጥም ስብክት

መዐዛ ሰዋስው ዕጣን ወጼና ትምህረት ከርቤ፡ ለአለ ያጼንው ምክረ ወይሰምው ዘይቤ

የግጥም ስብክት ወይም ይባቤ

በዶሮ ሥጋ አምሳል ምስጢሩ እንዲጥም ፡ዐጭሬ ረዥሜ ይባላል ግጥም
ዐጭሬ ሰዋስው ረዥሜው ግስ፡ የሦስት ፊደል ሥጋ የርባ ቅምር ነፍስ
ለልጆች እንዲተርፍ ያዋቆች መብል ፡ ያቡን ወጥ በሚሉት በቲማቲም ቃል
ለወጣቶች ኹሉ ከታች ወደላይ ፡ ሰዋስው እንጂ ነው መንገደ ሰማይ
ያዕቆብና ዕዝራ የእግዚአብሔር ጉበኖች ፡ ቀድሞ የሰለሱት ከላይ እስከታች
የሰዋስው ትምህርት ሥጋውና አጥንቱ፡ ባጭሬው ተከቷል ረጅሜነቱ
ከምርቱ ቆንጥረን ይህንን ሰዋስው ፡ ስሙን ለኋላ ልጅ ዘር ይኹን አልነው።
አለ ሰዋስው አለ ጥፊት፡ትምህርት አይጠራም ምንም ቢያጥቡት
የትምህርት ዕንቅርት አለመጣፍ-አለመስማትም ጆሮ ደግፍ
ዐንገት ላለው ሰው ዞሮ ለሚያይ፡ አንድ ሽክም ነው እንደ ድንጋይ
ካፍሪቃ ወንዞች ወርቅና አልማዝ ፡እንደሚያስገኘው እንዳባይ ወንዝ
ተርፎን እንዲፈስ ትምርቱ ንግድ ፡ በዚህ ሰዋስው ጥርጊያ መንገድ
ይልቅኑ እንውጣ ወደገቢያ፡ገበያችንም ኢትዮጵያ
መደብሮቿ የተዘጉቱ ፡ባራቱም ማእዘን እንዲከፈቱ
ልጆቿን በእውቀት እያሳደገ፡መንገዶቿንም እያስጠረገ
እግዚአብሔር ያቆማት ከማኸል ቦታ፡ በውጭ አገር ሰው እንዳትፈታ
ያፍሪቃ ደንደስ ሻኛና ጫንቃ፡ ጦቢያው እንጂ ናት ምሥራቅ አፍሪቃ
የሰማይ ምድር የምድር ሰማይ፡ የተከበበች በነጭ አባይ
ዐዳም ሲመሰል በገነት ዐይን፡ነጩ አባይ መደብ ጥቁሩ ብሌን
ባስተያየትም ሲመረመሩ ፡ ማየት አይችልም ነጩ አለጥቁሩ

ነጩ ሲፈተሽ ውስጠ ጥቁር፡ጥቁሩም ሲፈተሽ ውስጠ ነጭ ዘር
ነጭና ጥቁር የዓለም ዓይን፡ ኹሉም ተገልጦ የሚከደን
መከደኛውም ሞት ወስከንቢያ ነው፡ያዳም ሌባ ጣት የሰፋችው።
ቋንቋ ካልጠራ በሰዋስው ፡አነጋገሩ የለት ጉሽ ነው
ስሙ ፕራቲክ የድምጫ ቋንቋ፡ የኮረፌ አይነት ወይም የድቋ
ጆሮ ሲቀምሰው ከዋንጫው አፍ ፡ ያሰኛል እና እንትፍ እንትፍ
በጥሩ መጠጥ በሃገር ፍቅር ፡ራሱ ዞሮ ስቀባጥር
አጭሬ ግጥም ቁመተ ዶሮ ፡ የሚንጠራራ ወደ ሰው ጆሮ
ቸብ ቸቦው ዜማም ሳይቆረጥ፡በየመስመሩ የሚያስረግጥ
ቧልተኛ አዝማሪም መስሎ ሲያስቅ ፡ እንደ አቤ ሴሉም ልብ የሚሰርቅ

4ኛ ክፍል 1

ጸዋትዎ ቅኔ የሰምና የወርቅ ኩርንችት

ቀነየ ፡ቅኔ ማዜም ማጉረምረም መግጠም መምራት መቀኘት መሪ ባለቅኔ መሆን ረከብዎ ለአባ ዮሴፍ እንዘ ይትቀነይ ምስለ አሐዱ መነኮስ ካህናት ይትቀነዩ ዘንተ መዝሙረ በዜማ ወእምዝ በል ወተቀነይ ሃሌ ሉያ ወአኃዘ ይትቀነይ በሠለስቱ ዜማ ስንክ ጥቅ 23 ግንዘት ድጓ ።።

ቅኔ በቁሙ የፍትሐት የልቅሶ ዜማ ማኅሌት ማኅሌተ ቅኔ የዜማ ቦታ ሦስተኛ ክፍል ከመቅደስ ቅኔ ማህሌት ቅኔ አገዛዝ ባርነት ቅኔ እኩይ በዝጎ ቅኔሃ አው ተቀኔ ኢሳ.14÷3 ሰቆ.1÷3 ገላ. 5÷1 ንግድ ተግባረዕድ አገልግሎት ቅኔ እደዊነ ኢናጽርእ እምቅኔ እደዊሃ ትሁብ ለነዳያን ሥርዓተ ቅኔ ቤተክርስቲያን ዲድ 13 ና 4 ኪዳ። መዓልትን ቀን ማለት አማርኛው ከዚህ ወጥቷል የሥራ ጊዜ ማለት ነው።

ቅኔን የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ነው። ያሬድ የድርሰቱ መነሻና መድረሻ ቅኔ ሲሆን በድርሰቱ ግን ቤት እየመታና ሳይመታ የቃኛቸው ክብር ይእቲና እጣነ ሞገር በድጓው ተጽፈው ይገኛሉ ቅኔን እንደደረሰ ምቅናይ በሚባለው ድርሰቱ ይታወቃል። የርሱ ደቀ መዛሙርትም እስጢፋና እስክንድር ሐዊራና መንክራ እንዲሁም ብሑር ይባላሉ ከነዚህ የተማሩ ሊቃውንትም ቤት እየመቱ ተቀኝተዋል።

ለምሳሌ አጭር ዘይእዜ ተትሕተ ያሬድ ዘኢተትሕተ፡ ለቅኔያቲሁ ደቂቅ
እስመ ኢሐነፀ ቤተ፡፡
መወድስ ደቀ እስጢፋ ዓድቅ አመ እስክንድር፡
በመንፈስ ቅዱስ ነበበ ሐሳበ ነቢያት ቅኔያተ፡
እምቅኔያቲሁ ለያሬድ ዘእንበለ ያትርፍ፡ ምንተ፡
ወከመ ኢይጎድሩ ውስተ አፍአ ለቅኔያቲሁ ሐነፀ አብያተ፡
ሰብአ ወሰማኒተ፡ ወጠፈረ እሎን አብያት እስክነ ይእዜ ኢተነስተ
ለዓለም
ሐዊራሰ ወመንክራ ዘተጋብዑ ድረገተ፡
ዘምስለ ብሑር ወእስክንድር አስተጋብኦ ምሰጢራተ፡፡
መንክራተሂ መተሩ ወተመሰሉ መጥባሕተ፡
ለመጥባሕት እስመ ልማዱ ከፊሎተ ዋሕድ አርባዕተ፡፡

ክፍል 2

ቅኔና ታሪካዊ አመጣጡ

ቅኔ ማለት ቅኑየ መንፈስ ቅዱስ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ በልዩ ልዩ ዓይነት ግጥም የሚቀርብ ጽሑፍ፡ ወይም ድርሰት ነው፡፡ ቅኔ እንደ ማንኛውም ግጥም ቤቱን ማስያዝ ብቻ ሳይሆን ምስጢር ሰምና ወርቅ ጎብር ያለው ነው፡፡ መሳ 5÷1 መዝ 32÷3 2ሳሙ 1÷17 ኢሳ 5÷1 ኤፌ 5÷19 ካህናት ምስጢር ባለው ቅኔ በመሰንቆ ያዜሙ ነበር፡፡ 1ኛ ዜና 15÷20 በሐዋርያት ዘመንም ብዙ ባለቅኔዎች ነበሩ የሐዋ. 17÷18 ቅኔ ራሱ ምሰጋና ይሆናል ራዕ.14÷3 ቅኔ በየቀኑ ሊደርስ የሚችል አዲስ እየሆነ የሚቀርብ ነው መዝ 149÷1 አንዳንድ ሊቃውንት ቅኔን የደረሰው ዮሐንስ ገብላዊ እንደሆነ ይናገራሉ ነገር ግን አደራረሱን ቅዱስ ያሬድ ጀምሮት ቢያይ ጌታ እንደገለጸለት አውቆ በደብረ ታቦር ሱባኤ ገባ ምስጢሩን ከነቤቱ ለመወሰን አስቦ ሱባኤ ቢገባ እንደአሰበው ምስጢሩ ከነቤቱ ተገልጾለታል፡፡ ከቅዱስ ያሬድ አያይዞ ወስኖ ደርሶታል ከዚያም በኋላ ለአባ ወልደ ገብርኤል አስተምሯል፡፡ አባ ወልደ ገብርኤል ለሠምረ ክርስቶስ ሠምረ አብም ይባላል፡፡

ሠምረ አብ ጉባኤ ሠርቶ በሚያስተምርበት ዘመን ንጉሡ በእደ ማርያም ይባል ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ ንጉሡ አንስቶ ለሠምረ አብ አንተና አባትህ እንዲያው ትቀባጥራላችሁ እንጂ ከማን አግኝተኸዋል ይህን ቅኔ አለው፡፡ በዚህ ጊዜ መምህር ሠምረ አብ አንስቶ ይህን ካልህ አሁን ሱባኤ አንገባምን? አለው፡፡ ንጉሡም እሺ ብሎ ተያይዘው ሱባኤ ገቡ፡፡ ለሁለቱም መንፈስ ቅዱስ ገለጸላቸው፡፡ንጉሡም መንፈስ ቅዱስ ልቡናውን መታው ቀኑም ቃና ዘገሊላ ነበርና፡፡ ሁለት ቤት (ስንኝ) ያለው ምስጢረ ቅኔ ገለጠለት፡፡ ይኸውም
« ድኅረ ተሰብረ አጽንኦ ለሰብዕናነ ልህኩት
ኢየሱስ ክርስቶስ በማየ ሐዲስ ጥምቀት፡፡» ብሎ ደረሰ ጉባኤ ቃና ማለት የፈጣሪ ጉባኤ ምንኛ ተቃና ማለት ነው፡፡ ይህስ አልታወቀም ብሎ በቃና ለተደረገ ጉባኤ የሚገባ ነው ማለት ነው፡፡ የቅኔው ትርጉም፡- « ኢየሱስ ክርስቶስ እንሰራ ሰውነታችንን ከተሰበረ በኋላ በአዲስ ጥምቀት ውሃ አጸናው» ማለት ነው፡፡

ዘ አምላኪየ ለመምህሩ ደረሰው፡፡ ዘአምላኪየ ማለት የአምላኬ ነገር ምን ይደንቅ ማለት ነው፡፡ በዘጠኙ በዓላት በአደራረሰ ጊዜ የሚደርሱ እኒህ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ንጉሡ ከቅዱስ ያሬድ ገብቶ እግዚኦ ሚበዝኁ ብሎ ተናግሯል፡፡ ሚበዝኁ ሦስት ቤት ያለው ቅኔ ነው፡፡ ሚበዝኁ ማለት የሥላሴ ምሥጢር ምንኛ ይበዛ ማለት ነው፡፡

ዋዜማ በተራ ለመምህሩ ተገለጸለት፡፡ ይህም የሰርክ መስዋዕት በሰርክ የሚደረግ መስዋዕት ማለት ነው፡፡ ዋዜማ አምሰት ቤት አለው፡፡

ሥላሴ ለንጉሡ ተገለጸለት፡፡ ይህም በቸርነት በሥስተኛ ሥላሴ ደረሰኝ ማለት ነው፡፡

ዘይእዜ ለመምህሩ ተገለጸለት፡፡ ይህም የዛሬ ነገር ምን ያምር ማለት ነው፡፡ መወድስ ለንጉሡ ደረሰው ይኸውም የአሁድ ምሥጋና ነው፡፡
አሰረ ክህነት ላለው ለመምህሩ « ክብር ይእቲና እጣነ ሞገር» ተገለጸለት አሠረ ክህነት የሌለው አይናገረውምና፡፡ ድጓን መሪውም ተመሪውም ይጮኹበታል፡፡ ይህም እጣነ ሞገርን መሪ እየተናገረ ተመሪ ብቻ ይጮኸዋል፡፡
እጣነ ሞገር ቅኔ አድራጊው ለተመሪው መናገሩ ክብረ ፍጥረተ መላዕክትን ሞተ ሰማዕታትን ሞተ ጻድቃንን ሞተ ክርስቶስን ለሰው ማስረዳቱ ለራሱ እያወቀ

ማለት ነው:: ይኸውም አንድ ሰው ሲሞት ለዘመዱ እንደሚያረዱት ሲሆን ተመሪው መጮሁ የተረጁ (የአልቃሽ) ምሳሌ ነው::

ክብር ይእቲ ቅኔውን የሚያደርገው በድርገት ጊዜ እራሱ መጮሁ ሞተ ክርስቶስ ራሱ አስቦ ማልቀሱ ነው:: ክብር ይእቲ በሞተ ወልደ እግዚአብሔር በእለተ ዓርብ በክርስቶስ መስቀል ምክንያት የተፈጸሙትን ተዓምራት ብቻ በሚስጢር ያወሳል እንጂ ሌላ አይገባም:: በሌሎቹ የቅኔ አገባቦች ግን በዕለቱ የተፈጸሙትን በዕለቱ የዋለውን ሰማዕት፣ ጻድቅ ወይም ወንጌላዊ ሥራ መግለጫ ነው:: ክብር ይእቲውን ካህኑ ሲጨርስ ሃሌ ሉያ ማለቱ ሎቱ ስብሐት ሲል ነው:: ክብር ይእቲ ካህኑ የያዘው ሥልጣን ሲሆን እጣነ ሞገሩ ማሳረጊያ ነው::

ስለ ቅኔ ስንኝ (ቤት) ና ምሳሌዎቻቸው

ጉባኤ ቃና መጀመሪያ ነው ሁለት ቤት መሆኑ የመርዓዊና የመርዓት የመለኮት ና የትስብእት ምሳሌ ነው::

ዘ አምላኪየ 3 ቤት ነው:: ይኸውም የሦስትነቱ በአንድ ስብሐተ ነግህ መመራቱ የእግዚአብሔር የአንድነቱ ምሳሌ ነው::

ሚ በዝኁ ሦስት ቤት መሆኑ በሦስት ምዕራፍ የመድረሱ ሲሆን ሁለት ሐረግ መኖሩ በተሠሃለኒ የመደረሱ ምሳሌ ነው::

ዋዜማ አምስት ቤት ነው:: ይህም በአምስት ቤት መወሰኑ

1ኛ በዘ ንዜከር-ካህናት ጸሎት የሚያዘክሩበት አስርቆት ነው::

2ኛ በአንቀጸ ብርሃን 3ኛ በቅዱስ

4ኛ በድጓው 5ኛ በእግዚአብሔር ነግሠ ልክ የመደረሡ ምሳሌ ነው

ሥላሴ ቅኔ ስድስት ቤት መሆኑ በይትባረክ የመድረሱ ምሳሌ ነው::

ሥላሴም መባሉ በሦስቱ መደረጉ ነው

1. በዋዜማ 2. በስብሐተ ነግህ
3. በአርያም የመደረሱ ምሳሌ ነው::

ዘይእዜ 5 ቤት መሆኑ የ5ቱ አእማደ ምስጢር ምሳሌ ነው::

መወድስ ስምንት ቤት ሲሆን ስምንት መሆኑም

1. መዝሙር በዕለተ ሰንበት ካህናት የሚያቀርቡት ነው
2. አምላኪየ 3. ሚ በዝኁ

4. ቃልየ 5. ጸኒሐ
6. ብፁዕ ዘይሌቡ 7. ከመ ያፈቅር
8. ፍታሕ ሊተ:: በነዚህ የማኅሌት ዜማዎች የመደረሱ ምሳሌ ነው::

እነዚህ ከዳዊት መዝሙር የተውጣጡ በጣዕመ ዜማ ካህናት በቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡዋቸው ናቸው::

ሁለት እጣነ ሞገር ሁለት ክብር ይእቲ አለ ይኸውም ዕዝል በሚቀደስበት ጊዜ ዕዝል ግዕዝ በሚቀደስበት ጊዜ ግዕዝ ይሆናሉ:: እጣነ ሞገር ዕዝሉ አስራ አንድ ቤት ሲሆን ግዕዙ ሰባት ቤት በድምሩ አስራ ስምንት ይሆናል:: እዝል ክብር ይእቲ 4 ቤት ግዕዙም አራት በድምር 8 ይሆናል:: አስራ ስምንቱ እጣነ ሞገርና አራት ስንኝ (ቤት) ክብር ይእቲ 22 ይሆናሉ:: የሃያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት ምሳሌ ነው:: እንዲህ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሆነውን ምስጢር ሠምረ አብ ለልሄብ ልሄብ ለኤልያብ ኤልያብ ለተዋናይና ለድድቅ ወልደ ማርያም አስተምሯቸዋል:: ከዚህ ሲደርስ በሃገራችን ግራኝ በዚህ ዘመን ነገሠ በቤተ ክርስቲያን መጥፋትና በሊቃውንት እልቂት አገራችን ስትቸገር ድድቅ ወልደ ማርያም ወደ ጨረቃ ዳውንት ተሰደደ ተዋናይ ደቅ እስጢፋ ወደ ጣና ውስጥ ተሰደደ:: ተዋናይ ከሰው ተለይቶ ነበርና ቅኔውን ይዞት አገባቡን አጥፍቶ ወጣ የጐንጅ ቅኔ ዛሬ አገባቡ ማነሡና እርባ ቅምር አለመኖሩ ለዚህ ነው ይላሉ ሊቃውንት:: ድድቅ ወልደ ማርያም ግን ከሰው አልተለዩምና አገባቡን ከነእርባ ቅምሩ ይዘው እንደወጡ ሊቃውንት ይናገራሉ:: በዚህም በጨረቃ ዳውንት ድድቅ አልፈዋል:: በስደቱ ጊዜ የድድቅ ጉባኤ ሰፍቶም ስለነበር በኋላም ሰባት አዋጅ ሰባት እርባ ሰባት አገባብ ተናግረዋል:: ድድቅ ለልዕልና ወልደ ማርያም ልዕልና ወልደ ማርያም ለማዕበል ወልደ ሕይወት ማዕበል ለጌቴ ገሞራ ጌቴ ገሞራ ለገብረ ኢየሱስ ገብረ ኢየሱስ ለቡሩኬ ቡሩኬ ለመርዓዊ አስተማሩ እንዲህ እያለ አሁን ካለንበት ዘመን ደረሠ:: ይኸንን የቅኔ መንገድና ታሪካዊ አመጣጥ በዚህ ዘመን ያለውን ለቅኔ ፍቅር የሚያሠጥና ትኩረት እንድንሰጠው የሚገፋፋ ስለሆነ ቅኑየ መንፈስ ቅዱስ የሆነውን ይህን ምስጢር ሁላችን የማወቅ መንፈስ እንዳይነሳን ይገፋፋል::

ክፍል 3

ሥርዓተ ቅኔ

ጉባዔ ቃና ማለት ቃናን ቀዳሚ ተዓምር ይለዋልና ጉባዔ ቃናም መጀመሪያ ስለሆነ ጉባዔ ቃና አለው ቤቱ ሁለት ነው ይዘመማል እንጂ አይጸነጸልም አይጸፋም ቤቱ 2ት መሆኑ ስለ ማይና ስለ ወይን ነው በቃና ገሊላ ውሃውን ወይን አድርጎ እያደነቁ መጠጣታቸውን ያሳያል ጥሚም አንከረ ሊቀ ምርፋቅ እንዲል ተመልሶ ከመካከል መቅረቱ የፊተኛው የሰርጉ ቤት ወይን አቋርጦ ለማለቁ ምሳሌ ወይንኬ አልቦሙ አልቀኬ ወይኖሙ እንዲል የሚደረሰውም ምህላ የጀመረበት ቀን በመሆኑ አርብ እና ረቡ ነው። ጉባዔ ቃና ሁለት ቤት ዘአምላኪየ ሦስት ቤት መሆኑ በሥምአ ክልኤቱ ወሰለስቱ ይቀውም ኩሉ ነገር እንዲል። አንድም ጉባዔ ቃና ሁለት ቤት መሆኑ የመለኮት እና የትስብእት አምሳል ቀለሙ አለመለወጡ የተዋህዶ ምሳሌ ነው ከሐረጉ ጋራ አራት ይሆናል የአራቱ ፀወርተ መንበር ምሳሌ ነው። በኪሩቤል ላይ አድሮ የሚመሰገን ጌታ ከሰርግ ቤት ተጠርቶ ውሃውን ጠጅ ማድረጉን ሲያመለክት ነው። በጾም በግዕዝ በዓቢይ ስብሐተ ነግህ በዕዝል ዓርብና ረቡ ይደርሳል። አባባሉ በመሪ አንድ ጊዜ በዜማ አንድ ጊዜ በዝማሜ ሁለት ጊዜ በአንሽ ከማሁ ድምር 4 ይሆናል። ምሳሌው ከላይ እንደተጠቀሰው ነው። ዘአምላኪየ ማለት አምላኬ ብሎ የሚመራ ስለሆነ ነው። መዝ.62÷1 ሦስት መሆኑ የሦስትነት ምሳሌ ነው። ቀለሙ አለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ ነው። ሐረጉን ሲጨምሩት አምስት ይሆናል። የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ ነው። ስብሐተ ነግህ ሰኞ ማክሰኞ ሐሙስ ቅዳሜ እሁድ ሲቆም ይባላል። አባባሉ እንደ ጉባዔ ቃና ነው ወደ ኋላ ተመልሶ መጨረሱ ደግሞ ምጽአቱን ያመለክታል። ጉባዔ ቃና አርብ እና ረቡዕ መሆኑ ረቡዕ ምክረ ሞቱ ተፈጽሞበታል። አርብ መለኮት እና ትስብእት አንድ ሆነው መከራ ተቀብለውበታል። ተዓምራቱ አንድ ወገን ነው። የቀረው እየራሱ ነው የቀዳም ስዑር መስቀሉን ተሸክሞ ለሴቶች ታይቷል እንዲሁም አርፎ ውሏል እሁድ ተፀንሷል

ተነስቷል። የሆሳዕና ቤተ መቅደስ ገብቷል ሰኞ ገበያ ፈትቷል ማክሰኞ ተጠምቋል ሐሙስ አርጓል።

ሚበዙኑ ቤቱ ሦስት ነው የሥላሴ አምሳል ሐረጉን ሲጨምሩት ስምንት ይሆናል። የስምንቱ ብሔረ ኦሪት ምሳሌ ነው። አምስት ጊዜ መባሉ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር ምሳሌ ነው ይዘመማል እንጂ አይመረገድም አይጸፋም

ዋዜማ አምስት ቤት ነው የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ ነው ሐረጉን ሲጨምሩት 9 ይሆናል። በዘጠኙ ከተማ ያሉ የዘጠኙ ነገደ መላእክት ምሳሌ ነው አንድም የዘጠኙ ሰዓተ መዓልት ምሳሌ ነው። በዘጠኝ ሰዓት ትኩስ ደም ጥሩ ውኃ እንደ ለ ፊደል ሆኖ ፈሷል መረግዱ እና ጽፋቱ አሥራ አንድ ነው ይሁዳ በሰርክ ሐሙስ ማለትም በ11 ሰዓት ከ11ዱ ወንድሞች ሐዋርያት ተለይቶ ወጥቷል ዋዜማም ከጉባዔ ቃና ከዘአምላኪየ ከሚበዙኑ ተለይቶ በሰርክ መዓልት 11 ጊዜ መመርገዱ የ11ዱ ሰዓተ መዓልት ምሳሌ ነው ወይም የ11ዱ ሐዋርያት ምሳሌ ነው። 12ኛው ከይሁዳ በኋላ የተተካው የማትያስ ምሳሌ አንድም እግዚአብሔር ወልድ ይህንን ሁሉ መከራ የመቀበሉ ምሳሌ መሆኑን ያሳያል። በዋዜማ ከሦስት ላይ በዓርያም ከአንድ ላይ በመወድስ ከሁለት ላይ ይባላል።

ሥላሴ ቤቱ 6 ነው የ6ቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌ አንድም የፅዪህ ምሳሌ ነው። በ6ተኛው ሺህ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ሰው የመሆኑ ምሳሌ ነው ሐረጉን ሲጨምሩት 11 ይሆናል አንዱ የአንድነት ምሳሌ አሥሩ የአሥሮቱ ቃላተ ኦሪት ምሳሌ 15 ጊዜ ይመረገዳል ይጸፋል የ15ቱ ነቢያት ምሳሌ አንድም በ15ቱ ሰዓት ስለሚጸለየው ጸሎት ሐተታው እንደ አርያም ነው።

ማህልከ፡ ቤቱ 3ት ነው የሥላሴ አምሳል 22ት ጊዜ መባሉ ስለምን ነው ቢሉ ስለ 22ቱ ሥነ-ፍጥረት ምሳሌ ነው። በ22ቱ ሥነ-ፍጥረት ላይ ሳሰለጠንከው ንጉሥ ምስጋና ይገባዋል ለማለት አሠረ ንጉሥም እነዚህን ያስገዛልን ጌታ ይመስገን እያልን እናመሰግናለንና ስለዚህ ነው።

የዘይእዜ ቤቱ 5ት ነው ሐተታው ከመ ዋዜማ ጉባዔ ቃና ዘአምላኪየ ዘይእዜ ወደ ኋላ ተመልሰው መጨረሻቸው ዳግም ምጽአቱን ያሳያል ዘይእዜ 15 ጊዜ ይመረገዳል ይጸፋል በ15ቱ ነቢያት ምሳሌ ሐተታው እንደ ሥላሴ ነው።

መወድስ ቤቱ 8 ነው የ8ቱ ብሔረ አሪት ምሳሌ ታሪክ ካህናት መወድስ ቆመው ሳሉ በ8ት ሰዓተ ሌሊት አጼ እስክንድር መጡ ያን ጊዜ ተናግረውታል ይባላል መረግዱ እና ጽፋቱ 42 ይሆናል 36ቱ ቅዱሳት አንስት በዕለተ ዓርብ እንባ እንደጉርፍ ያፈሰሱለት አምላክ ኃያላን ፈጣሬ ፍጡራን በፍጡራን እጅ ተይዞ ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ ሲያዳፋት 36 ጊዜ ለመውደቁ ምሳሌ ነው። 6ቱ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር ለማደሩ ምሳሌ ነው።

ኩልክሙ ቤቱ 9ኝ ነው የዘጠኙ ሰዓተ መዓልት ምሳሌ በዘጠኝ ሰዓት አባ አመሐፅን ነፍስዬ ካለ በኋላ ኩልክሙ የተባሉትን ለማዳኑ ምሳሌ አንድም በ9ኝ ሰዓት የተጸለየውን ጸሎት ለመቀበሉ ምሳሌ ነው። ክብር ይእቲ ግዕዙም ዕዝሉም 4ት ቤት ነው። 4ት ቤት መሆኑ ስለምን ነው ቢሉ የ4ቱ ቤት ጭፍራ ሮማውያን በሌሊተ ዓርብ ይዘው ለሞት አሳልፈው ሰጥተውታል እና ለዚያ መታሰቢያ ነው። አባባሉ ከመ ጉባዔ ቃና ወዘአምላኪየ ነው። ከዚህ አያይዞ ክብር ይእቲ ዛቲ የሚለውን የዳዊት መስመር መነሻ በማድረግ ሰብሀም ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ ይባላል። ይህ ቅኔ ከመባሉ አስቀድሞ 150 ዳዊት 15ቱ ነቢያት እንዲደገም የተሰራ ሥርዓት መኖሩ ይነገራል ነገርግን በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ 150 ዳዊት 15 ነቢያት ለመድገም ባለመቻሉ ሰብሀም የፊደሉ ቁጥር 150 በመሆኑ ፸150ው ዳዊት መደብ ገብቷል ክብር ይእቲ ዛቲ ለኩሉ ዓድቃኑ የፊደሉ ቁጥር 15 በመሆኑ በ15ቱ ነቢያት መደብ ገብቷል።

ግዕዝ ዕጣነ ሞገር ቤቱ 7ት ነው 7ት መሆኑ ስለምን ነው ቢሉ የ7ቱ ባሕርያተ ሰብእ ምሳሌ ነው እሊህም 4ቱ ባሕርያተ ሥጋ 3ቱ በሕርያተ ነፍስ ናቸው ከእሊህ ባሕርያት የተፈጠረ ሰው እውቀቱን በ7ቱ ፊደላት

አዘጋጅቶ በምሥጢር አጣፍጦ ለፈጣሪው የሚያቀርበው መሆኑን ያመለክታል አባባሉም ሆነ ሐተታው ከመ መወድስ ነው።

ዕዝል ዕጣነ ሞገር ቤቱ 11ነው 11ድ መሆኑ ሊቃውንት ነው ቢሉ ወሪደ መቃብር የወረደበት የ11ዱ ሰዓተ መዓልት ዘአርብ ምሳሌ ነው አባባሉ 24 ጊዜ ነው 24 ጊዜ መባሉም ቀን እና ሌሊት ባለማቋረጥ 24ቱ ካህናተ ሰማይ የሚያመሰግኑትን የምሥጋና ባለቤት የሰው ልጆችም ደግሞ በ24ቱ ሰዓት ልናመሰግነው ይገባልና ስንል ነው።

ክፍል 4

አርዕስተ ቅኔ

በቅኔ ውስጥ 7 አባባሎች ይገኛሉ እነዚህም ቤት፣ ሐረግ፣ መንደርደሪያ፣ ቧዒ ለዓለም፣ አሠረ ንጉሥ፣ መጽፊያ ናቸው የቅኔ ቤት ማለት የምስጢሩ ወይም የንባቡ የዜማው መጨረሻ ማለት ነው። ቤት የተባለበት ምክንያት ለሰው ማረፊያው እና ማደሪያው ቤቱ እንደሆነ ለቅኔም የሚስጥሩ የንባቡ የዜማው መጨረሻ ቤት ተባለ። በመልክዓ ማርያም በመልክዓ ኢየሱስ ይህንን በመሰለው ድርሰት ሁሉ በምስጢሩ በንባቡ በዜማው መጨረሻ ያለው ስንኝ ይባላል። ስንኙ የተባለበት ምክንያት ስንኙ የተባለው ቃል ተሰነአወ ካለው አንቀጽ የወጣ ነው የተባለ እንደሆነ ተሰነአው ማለት ነው። ንባቡ ከምስጢሩ የሚስማማበት እና የሚጋጠምበት ወይም ግጥም ማለት ነው። ስንኝ የተባለው ቃል ሰነየ አማረ ካለው አንቀጽ የወጣ ነው የተባለ እንደሆነ ስን ማለት ደምግባት ውበት ነውና ሚስጢሩን ንባቡን የሚያሳምረው ማለት ነው። ስንኝ የተባለው ቃል አጥብቆ ስኝ ማለት ነው ስን ከተባለው ነባር የወጣ ነው የተባለ እንደሆነ ስን ማለት ጥርስ ማለት ነውና ጥርስ በተራ የተተከለና የተጋጠመ ስለሆነ ደስ እንዲያሰኝ ይህም በተራ በየስንኙ ሲነገር ደስ የሚያሰኝ ስለሆነ ነው። የቅኔ ቤቶችም የሚሆኑበት ከሀ ጀምሮ እስከ ፐ ያሉት ፊደሎች ናቸው እነዚህ ፊደሎች ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ በግዕዝ ቋንቋ መልካቸው እና ቅርጻቸው የተለየ አነጋገራቸው የገጠመ ሆኖ የተደነገጉና የተወሰኑ ሆነው የሚኖሩ አንዳንድ ፊደሎች ይገኛሉ። እነዚህም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፉት 9 x7 =63 ናቸው።

1. ሀ. ሦስት መልክ እና ቅርፅ አለው ሀ፡ ሃሌታው ሀ ሐ፡ ሐመሩ ሐ ኀ፡ ብዙኃኑ ኀ
2. ሠ፡ ሁለት መልክና ቅርፅ አለው የመጀመሪያው ንጉሡ ሠ፡ ሁለተኛ ው እሳቱ፡ ሰ ፡ይባላሉ
3. አ፡ ሁለት መልክና ቅርፅ አለው የመጀመሪያው አልፋ፡ አ፡ ሁለተኛ ው ዓይኑ ዐ ይባላሉ
4. ጸ፡ ሁለት መልክ እና ቅርፅ አለው የመጀመሪያው ጻድቁ ጸ፡ ሁለተኛ ው ፀሐዩ ፀ ይባላሉ እነዚህም መልካቸውና ቅርፃቸው የተለየ አንድ አንድ ፊደሎች በየሥፍራቸው በየንግግራቸው ሳይፃፉ ቀርተው በሌላ ስፍራና በሌላ ንግግር እየገቡ የተፃፉ እንደሆነ ፀያፍ ነው ይባላል። ፀያፍነቱም ንጉሥ በሚልበት ሥፍራ ንጉስ፡ ሀገር በሚልበት ሥፍራ ሐገር ኀገር ተብሎ መጽአ በሚልበት ሥፍራ፡ መፅዐ ተብሎ ጻድቅ በሚልበት ሥፍራ ፃድቅ ተብሎ ተጽፎ የተገኘ እንደሆነ ነው ነገር ግን ብዙ ሊቃውንቶች ይህንን አለማስተዋልና አለመጠንቀቅ ያሳያሉ ቅኔ ሲቀኙ ቤቱ ሀ ከሆነ ሐመሩንም ብዙኃኑንም ኀ ሳይለዩ ጸያፍ ቃል እያገቡ ይቀኛሉ ሠ እና ሰ እና ዐ ፡ጸና ፀ እንዲሁም ሳይለዩ ቤት እያደረጉ ይቀኛሉ ይኸውም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው።

የሐ ጸያፍ ወሰባ ማርያም ኃርየት ዘኢይትሐየድ ፍስሓኃ ትሰርጎ ማርታ ነፍሶሙ ለጻድቃን ብዙኃ

የሠ ጸያፍ አምጣነ የሐሥሥ ኪሮስ ለሠርጉ ልብሱ፡ ወይሔሌ ማትያስ ለክርሡ።

የአ ጸያፍ ባዕልሰ ይትፌሣሕ ሶበ ዜና ረጎብ ሰምዓኃ ወመቃብረ ይከሪ ለወርቁ እንዘ በድነ ቢጹ በአፍአ።

የጸ ጸያፍ ወበስመ ኮ ኮሕ ጴጥሮስ ኢይሰመይ ቢጾኃ በድንጋፄ እስመ ኮነ ዕፀ ይህንን የመሰለ ሁሉ ጸያፍ ይባላልና ቅኔ የሚቀኙ ሰዎች ሁሉ የነዚህን ፊደሎች መልክና ቅርጽ እየተከተሉ ቢሄዱ የሚያስመሰግናቸው ይሆንላቸዋል።

የቅኔ ዜማ ልክ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አመምላክ ብለን የሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት ንባባትን እንጀምራለን።

የሰማንያ አሐዱ መጽሐፍት ንባባት 4 ወገን ናቸው ማን ማን ናቸው ቢሉ ተነሽ ተጣይ ሰያፍ ወዳቂ ናቸዉ።

ተነሽ በ5 ፊደላት ይነገራል ተጣይና ሰያፍ በአንድ ሳድስ ይነገራሉ ወዳቂ በ7 ፊደላት ይነገራል።

የተነሽ ምስክር በግዕዝ ሐመ ወሞተ ውቱቀብረ ይላል በካዕብ ጸመ ወርኀቡ ወተመንደቡ ይላል በሳልሥ ሐሪ በዕንግዳኪ ወብልኢ መሬተ ይላል በራብ ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተሰአማ ይላል በሳብዕ እግዚኦ ኩነኔከ ህቦ ለንጉሥ ይላል የተጣይ ምስክር በሣድስ ሲነገር በስም ጊዮርጊስ አስጢፋኖስ ፋሲለደስ የሰያፍ ምስክር በአንቀጽ የሐውር ይቀውም ይገይስ ይላል በስም ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስ ይላል። የወዳቂ ምስክር በግዕዝ ሲነገር አሀደ ክልኤተ ሠለስተ ይላል በካዕብ ሐብቱ ንብረቱ ቤቱ ይላል በሣልስ ማኒ ጠሊ ኢሎፍሊ ይላል በራብዕ ሐና ሶልያና ህልቃና ዕዝራ ይላል በሐምስ ሙሴ አውሴ ቅዳሴ ይላል በሳድስ ግን አንድ ዝ ብቻ ነው።

በሳብእ ክበሮ መሰንቆ ደማስቆ ይላል የግዕዝ ጉባኤ ቃና መደብ መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ 2-4 ሰያፍ ከ 3-5 ወዳቂ ከ 1-3 የተነሽና የሰያፍ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 2፡2 ሰያፍ 3፡፡3 የተጣይ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 2ም 3ም ሰያፍ 3ም 4ም የወዳቂ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 3፡3 ሰያፍ 4፡4 ወዳቂ መደብነት እንጂ ተቀባይ አይሆንም ሐረግ የለውም። የቤት መምቻው መደብ መጀመሪያ ተነሽ ከ 5-7 ሰያፍ ከ 6-8 ተጣይ ከ 6-7 ወዳቂ ከ 5-6 የ5ቱ ተነሽ የ6 ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ 3ቱ ንባባት ሁሉ እንበለ ሰያፍ 3፡3 የ6ቱ የ7ቱ ተነሽ የ7ቱ የ8ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ 3ቱ ንባባት ሁሉ እንበለ ሰያፍ 2፡2 የ6ቱ የ7ቱ ተጣይ መደብ ተቀባይ 3ቱ ንባባት ሁሉ እንበለ ሰያፍ 2ም 3ም የ5ቱ የ6ቱ ወዳቂ መደብ ተቀባይ 3ቱ ንባባት ሁሉ 3፡3 እንበለ ሰያፍ 2ኛው መደብ እስከ ቤት መምቻው ተቀባይ ድረስ ከማሁ።

<u>የዕዝል</u> ጉባኤ ቃና መደብ መጀመሪያ ሰያፍ ከ 3-8 6ን አይነካም ተነሽ ተጣይ ከ 2-7 5ን አይነካም ወዳቂ ከ 1-6 4ን አይነካም የተነሽና የሰያፍ መደብ

ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 2:2 ሰያፍ 3:3 የተጣይ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 2 ም 3ም ሰያፍ 3ም 4ም የወዳቂ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 3:3 ሰያፍ 4 :4 ወዳቂ አልቦ ሐረግ ተነሽ ተጣይ ሰያፍ ከ 4-5 ወዳቂ ከ 3-5 የቤት መምቻው መደቡ እስከ ተቀባዩ እንደ ግዕዝ ጉባኤ ቃና ነው ሁለተኛው ቤት መደብ እስከ ተቀባዩ እንደመጀመሪያው ነው ሐረጉ ግን ወዳቂ 3:3 ብቻ ነው ቤት መምቻውም ከነተቀባዩ እንደ ግዕዝ ጉባኤ ቃና ነው::

<u>የዘአምላኪያ</u> መደብ እስከ ተቀባዩ እንደ ዕዝልም እንደ ግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው የቤት መምቻውም ከነተቀባዩ እንደ ጉባኤ ቃና ነው:: የዘአምላኪያ ማንደርደሪያ በረጅም ሲሆን መደብ መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ 2-4 ሰያፍ ከ 3-5 ወዳቂ አልቦ ተቀባዩ በተናባቢ 3ቱ ንባባት እንበለ ሰያፍ 6:6 የዘአምላኪያ የማንደርደሪያ የቤት መምቻ መደብ መጀመሪያ ተነሽ ከ 3-4 ሰያፍ ከ 4-5 ተጣይ 4:4 ወዳቂ 3:3 የ3ቱ ተነሽ የ4ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ እንበለ ሰያፍ 3:3 የ4ቱ ተነሽ የ5ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ እንበለ ሰያፍ 2:2 የ4ቱ ተጣይ መደብ ተቀባይ 2ም 3ም የ3ቱ ወዳቂ መደብ ተቀባይ 3ቱ ንባባት እንበለ ሰያፍ 3:3 በአጭር ሲሆን የማንደርደሪያ መደብ መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ 2-4 ሰያፍ ከ 3-5 ወዳቂ ከ 1-3 የ2ቱ የ3ቱ ተነሽ የ3ቱ የ4ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ፍጹም ወዳቂ 3:3 የ4ቱ ተነሽ የ5ቱ ሰያፍ መደብ ተቀባይ ፍጹም ወዳቂ 2:2 የተጣይ መደብ ተቀባይ ፍጹም ወዳቂ 2ም 3ም የወዳቂ መደብ ተቀባይ ፍጹም ወዳቂ 3:3

የሦስተኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ እንደ ግዕዝም እንደ ዕዝልም ጉባኤ ቃና ነው ሐረጉ ፍጹም ወዳቂ 3:3 ቤት መምቻው ከነተቀባዩ እንደ ጉባኤ ቃና ነው::

<u>የሚበዙት</u> መደብ መጀመሪያ እንደ ግዕዝም እንደ ዕዝልም ጉባኤ ቃና ነው በጉንጅ ግን በረጅም ብቻ ይጀምራል ቀጥሎ ያለው መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻው እስከ ተቀባዩ እንደ ጉባኤ ቃና ነው በልውጥ ሲሆን ተነሽ ተጣይ ከ 2-7 5 ን አይነካም ሰያፍ ከ 3-8 6ን አይነካም ወዳቂ ከ 1-6 4ን አይነካም የተነሽና የሰያፍ መደብ ተቀባይ 4ቱ ንባባት

ሁሉ 4:4 የተጣይ መደብ ተቀባይ 4ቱ ንባባት ሁሉ 4ም 5ም የወዳቂ መደብ ተቀባይ 4ቱ ንባባት ሁሉም 5:5 ሁለተኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው በለውጥ ሲሆን እንደ መጀመሪያው ቤት መምቻ ነው:: 3ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው ቀጥሎ ያለውም መደብ ከነተቀባዩ ከማሁ ለውጥ ሲሆን ተቀባዩ ወዳቂ 29ም3ም ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው::

<u>የዋዜማ</u> መደብ መጀመሪያ እንደ ግዕዝም እንደ ዕዝልም ጉባኤ ቃና ነው ወዳቂ አልቦ ተቀባዩ 4ቱ ንባባት ሁሉ 4ም 5ም ነው በጉንጅ ግን 5:5 ብቻ ነው ቀጥሎ ያለው መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው ማንደርደሪያው በአጭርም በረዥሙም እስከ ቤት መምቻው እንደ ዘአምላኪያ ነው የሦስተኛው ቤት መደብ መጀመሪያ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው:: ተቀባዩ በለውጥ ሲሆን ፍጹም ወዳቂ 2ም 3ም ቤት መምቻው መደብ ከነ ተቀባዩ እንደ መጀመሪያው ቤት መምቻ ነው፣ መጽፊያው መደቡ እስከ ተቀባዩ እንደ ግዕዝም እንደ ዕዝልም ጉባኤ ቃና ነው በለውጥ ሲሆን መደቡ ተነሽ ተጣይ 4:4 ሰያፍ 5 ወዳቂ 3 የተነሽ የሰያፍ ሐረግ ወዳቂ 2:2 የተጣይ ሐረግ ወዳቂ 2ም3ም የወዳቂ ሐረግ ወደቂ 2ም 3ም ተቀባያቸው ተነሽ ተጣይ 3:3 ሰያፍ 4:4 ወዳቂ አልቦ የ4ኛው ቤት መምቻ መደብ መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ 2-4 ሰያፍ ከ 3-5 ወዳቂ ከ 1-3 የተነሽና የሰያፍ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 2:2 የተጣይ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 3:3 ሰያፍ ተቀባይነት አልቦ በተናባቢ ሲሆን ተነሽ ተጣይ 6:6 ወዳቂ 4ም 5ም ሰረገላው በተናባቢ ተነሽ ተጣ/ ወዳቂ እንበለ ሰያፍ 4:4 የቤት መምቻው መደብ ተነሽ ከ3-4 ሰያፍ ከ4-5 ተጣ/ 4:4 ወዳቂ 3:3 የ3ቱ ተነሽ የ5ቱ ሰያፍ ተቀባይ እንበለ ሰያፍ 2:2 የተጣ/ ተቀባይ እንበለ ሰያፍ 2ም 3ም የወዳቂ ተቀባይ እንበለ ሰያፍ 3:3

<u>የሥላሴ መደብ</u> መጀመሪያ ተነሽ ተጣይ ከ 2-4 ሰያፍ ከ 3-5 ወዳ አልቦ ተቀባይ 4ቱ ንባባት በሙሉ 4ም5ም በጉንጅ ግን 5:5 ብቻ ነው:: በተናባ ሲሆን 3ቱ ንባባት ሁሉ 6:6 ወዳቂ 5ም 6ም የአጉበሩ መደብ ተነሽ ተጣይ ከ 4 ሰያፍ ከ 3-5 ወዳቂ ከ 1-3 የተነሽና የሰያፍ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 2 ሰያፍ 3:3 የተጣይ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 2ም 3ም ሰያፍ 3ም 4 የወዳቂ መደብ ተቀባይ ተነሽ ተጣይ 3::3 ሰያፍ 4:4 መድረሻው 4ቱ ንባባ

በሙሉ 5:5 በረጅም ሲሆን ተነሽ ተጣይ ከ 6-7 ሰያፍ ከ 7-8 ወዳቂ ከ 5-6 የተነሽና የሰያፍ መደብ ተቀባይ 4ቱ ንባባት በሙሉ 4 4 የተጣይ መደብ ተቀባይ 4ቱ ንባባት ሁሉ 4ም 5ም የወዳቂ መደብ ተቀባይ 4ቱ ንባባት ሁሉ 5:5 ቀጥሎ ያለው መደብ እስከ ተቀባዩ እንደ ዕዝልም እንደ ግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው ሐረጉ ፍጹም ወዳቂ 3:3 ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው ማንደርደሪያው በአጭርም በረጅም እስከ ቤት መምቻው እንደ ዘአምላኪየ ነው። 3ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻው መደብ እስከ ተቀባዩ እንደ መጀመሪያው ነው። የመጽፊያው መደብ እስከ ተቀባዩ እንደታችኛው አጉበር ነው። 5ኛው ቤት መደብ እስከ ተቀባዩ እንደ ዋዜማው መጽፊያ ነው ቤት መምቻው ከዋዜማው ተለይቶ በተናባቢ ሰያፍ 6:6 ይሆናል ሰረገላው እስከ ቤት መምቻው እንደ ዋዜማው መጨረሻ ነው።

የዘይእዜ መደብ መጀመሪያ መደቡ ከነተቀባዩ ግዕዝ ጉባኤ ቃና ነው። ሐረጉ 4ቱ ንባባት ሁሉ በተናባቢ 5:5 ነው ቀጥሎ ያለው መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። ቧሄውም መደብ ከነተቀባዩ እንደ ሚበዝኑ ተለዋጭ ነው ሁለተኛውም ለውጥ እንደ መጀመሪያው ዘይእዜ እስከ ሐረጉ ይሆናል ሁለተኛውም ቤት በረጅምም በአጭርም እስከ ቤት መምቻው የዘአምላኪየ ማንደርደሪያ ነው 3ኛው ቤትም መደብ ከነተቀባዩ እንደ ግዕዝም እንደ ዕዝልም ጉባኤ ቃና ነው ቤት መምቻውም መደቡ ከነተቀባዩ እንደ ሚበዝኑ ተለዋጭ ነው። 4ኛው ቤትም መደብ ከነተቀባዩ እንደ ግዕዝም እንደ ዕዝልም ጉባኤ ቃና ነ... ቤት መምቻውም ተነሽ ተጣይ ሰያፍ በተናባቢ 6:6 ነው ወዳቂ 5ም 6ም 5ኛው ቤትም መደቡ ከነተቀባዩ ቤት መምቻው እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው።

የመወድስ መደብ መጀመሪያ ከነተቀባዩ እንደ ዕዝልም እንደ ግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው ሐረጉ 4ቱ ንባባት ሁሉ በተናባቢ 6:6 ቀጥሎ ያለውም መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። በለውጥ ሲሆን መደቡ ከነተቀባዩ እንደ ሚበዝኑ ተለዋጭ ነው። 2ኛው ቤትም መደቡ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ

እንደ መጀመሪያው ቤት ነው። በተለዋጭ ሲሆን 4ቱ ንባባት ሁሉ በተናባቢ 6:6 ቧሄውም እንደ ዘይእዜ ቧሄ ነው ማንደርደሪያውም እስከ ቤት መምቻው ከማሁ ቧሄውም መደብ ከነተቀባዩ እንደ ሚበዝኑ ተለዋጭ ነው። ቀጥሎ ያለውም መደብ ከነተቀባዩ እንደ ዕዝልም እንደ ግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው። ቤት መምቻውም ጉባኤ ቃና ነው በተለዋጭ ሲሆን መደቡ ከነተቀባዩ እንደ ሚበዝኑ ተለዋጭ ነው ለዓለሙም መደብ ከነተቀባዩ እንደ ሚበዝሁ ተለዋጭ ነው ቤት መምቻውም መደቡም እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። በተለዋጭ ሲሆን እንደ ሁለተኛው ቤት ነው 6ኛው ቤት መደቡከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ እንደሚበዝኑ ተለዋጭ ነው 7ኛው ቤትም መደቡ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። በለውጥ ሲሆን 4ቱ ንባባት ሁሉ በተናባቢ 6:6 8ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ የሚበዝኑ ተለዋጭ ነው ኩልከሙ ሲሆን 9ኛው ቤት መደቡ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። ቤት መምቻው በለውጥ ሲሆን በተናባቢ 4ቱ ንባባት ሁሉ 6:6 ይሆናል።

<u>የግዕዝ ክብር ይእቲ</u> መደብ መጀመሪያ እንደ ግዕዝም እንደ ዕዝልም ጉባኤ ቃና ነው። የቤት መምቻው መደብ እስከ ተቀባዩ የሚበዝኑ ተለዋጭ ነው። 2ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። 3ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ እስከ ቤት መምቻው ከማሁ 4ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ የቤት መምቻ መደቡም እስከ ተቀባዩ እንደመጀመሪያው ነው።

<u>የግዕዝ ዕጣነ ሞገር</u> መደብ መጀመሪያ ከነተቀባዩ እንደ ግዕዝና ዕዝል ጉባኤ ቃና ነው። በጉንጅ ግን በረጅም ብቻ ነው። ቀጥሎ ያለው መደብ ከነተቀባዩ በአጭርም በረጅምም ይሆናል። ሐረጉ ተነሽ ተጣይ ሰያፍ ከ4-5 ወዳቂ ከ3-5 ነው የቤት መምቻ መደቡ ከነተቀባዩ እንደ ሚበዝኑ ተለዋጭ ነው።

የ2ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ የቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። የ3ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ እስከ ቤት መምቻው ከማሁ 4ኛው ቤት በረጅምም በአጭርም እስከ ቤት መምቻው እንደ ዘአምላኪየ ማንደርደሪያ ነው።

የአሠረ ነጋሲ መደብ ከነተቀባዩ እንደ ዕዝልም እንደ ግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው። ሐረጉም እንደታችኛው ሐረግ ነው የ5ኛው ቤት መምቻው መደብ እስከ ተቀባዩ የሚበዝኑ ተለዋጭ ነው። 6ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ በረጅምም በአጭርም ይሆናል። ሐረጉም ፍጹም ወዳቂ 3:3 ነው የቤት መምቻ መደብ ከነተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። 7ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ እንደረዥም ዘአምላኪየ ማንደርደሪያ ነው። ቤት መምቻውም 4ቱ ንባባት ሁሉ 4:4 ብቻ ነው።

የዕዝል ክብር ይእቲ መደብ መጀመሪያ ከነተቀባዩ እንደ ዕዝልም እንደ ግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው። ሐረጉ ተነሽ ተጣይ ሰያፍ ከ4-5 ወዳቂ ከ3-5 ቤት መምቻውም መደብ ከነተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። 2ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻው መደብ እስከተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። 3ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ በአጭርም በረጅምም ይሆናል በለውጥ ሲሆን የ5ቱ ተነሽ የ6 ሰያፍ ተቀባይ ወዳቂ 3:3 የ6 ፡የ7 ተነሽ የ7 የ8 ሰያፍ ተቀባይ ወዳቂ 2:2 የ6 የ 7 ተጣይ ተቀባይ ወዳቂ 2ም 3ም የ5 የ6 ወዳቂ ተቀባይ ወዳቂ 3:3 ቤት መምቻው መደብ ከነተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። 4ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ ሐረጉም ቤት መምቻው መደብ እስከ ተቀባዩ እንደ መጀመሪያው ነው።

የዕዝል ዕጣነ ሞገር መደብ መጀመሪያ ከነተቀባዩ እንደ ዕዝልም እንደ ግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው። በጉንጅ ግን በረጅም ብቻ ነው ቤት መምቻው መደብ ከነተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። 2ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ በረጅምም በአጭርም ይሆናል ቤት መምቻውም 3ቱ ንባባት ከ4-6 ወዳቂ ከ4-5 በጉንጂ ግን 4ቱ ንባባት ሁሉም 5:5 ነው 3ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ እንደሚበዝኑ ተለዋጭ ነው ቤት መምቻውም መደብ እስከተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው። 4ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ የሚበዝኑ ተለዋጭ ነው። 5ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ እንደ ዕዝልና ግዕዝ ጉባኤ ቃና ነው። ሐርጉ ፍጹም ወዳቂ 3:3 ቤት መምቻው መደብ ከነተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው 6ኛው ቤት በረጅምም በአጭርም እስከ ቤት መምቻው ድረስ የዘአምላኪየ ማንደርደሪያ ነው። አሠረ ነጋሲው መደብ ከነተቀባዩ እንደ ዕዝልም እንደ ግዕዝም ጉባኤ ቃና ነው ሐረጉ ተነሽ

ተጣይ ሰያፍ 4ም 5ም ወዳቂ ከ3-5 ቤት መምቻው መደብ እስከ ተቀባዩ ጉባኤ ቃና ነው 8ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ ሐረጉም ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ እንደ 5ኛው ቤት ነው።መጽፊያዉም በረጅምም በአጭርም እንደ ሥላሴ አጉበር ነው። 10ኛው ቤት መደብ ከነተቀባዩ ቤት መምቻውም መደብ እስከ ተቀባዩ እንደ ሥላሴ ነው።

11ኛው ቤት ሠረገላ እስከ ፍፃሜው የሥላሴ ፍፃሜ ነው። **አጭር ዋዜማ** ከዋዜማ ማንደርደሪያ ጀምሮ እስከ 3ኛ ቤት ነው። **አጭር ሥላሴ** (ተወረወ) ከመጽፊያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ያለው ነው።

አጭር ዘይዕዜ ኒቆዲሞስ ቆመ ከመ ይሚስቄምህሮ ወንጌል ወይነ ለእንግዳሁ ክርስቶስ

ግህልከ በዘይዕዜ ጀምር ሐረጉን ቤት መተህ በማንደርደሪያ ጨርስ

አጭር መወድስ ወይም ኩልክሙ መደቡ በመወድስ ሁለተኛ መደብ ጀምረህ እስከ ማንደርደሪያ ጨርስ

የኒቆዲሞስ ሰኞ እና ማክሰኞ የሚደረግ ክብር ይእቲ እና ዕጣነ ሞገር

ክብር ይዕቲ ሐዋርያቲሁ ከበበ ዕፃረ አርዲኢሁ ሐፀበ፡ኮኖሙ አበ ወእመ ወመሐሮሙ ጥበበ

እጣነ ሞገር ሕንፂሃ ወሱራሬሃ አዳም፡እም አስካለ ወይን ጉርዔሃ ጥዑም፡ በኒቆዲሞስ ሰኞና ማክሰኞ እንዲሁም አርያም በሚቆምበት ጊዜ ይደረጋሉ፡ የቅኔ ዜማ ልክ በዚህ ይፈፀማል።

ፍኖተ ቅኔ (የቅኔ መንገድ)

የቅኔ ጉባኤያት 3 ናቸው። እነርሱም 1. ጉንጅ 2. ዋሽራ 3. ዋድላ በመባል ይታወቃሉ። እነዚህም በ2 ታላላቅ ክፍል ይከፈላሉ። 1ኛው ሰምና ወርቅ ሲባል 2ኛው ጉዳና ይባላል። ይህም መቅለሉንና መክበዱን ለማሳየት እንጂ ሁሉም በሰምና በወርቅ የሚነገር ነው። ሰምና ወርቅ ማለት እንደ ወንድማማቾች በምስጢር መንታ ሲሆኑ በንባብ ሳይጫፈሩ በ6 ነገሮ ተባብረው ተጣምረው አንድ ወጥ ቃል መስለው የሚነገሩ ተመሳሳዮች ማለት ነው። በተረትም ሰምና ወርቅ እንጀራና መረቅ ይባላል። ሰምና ወርቅ ሲመሰሉ ሰም እየቀደመ ወርቅ ቢከተል ከአልተናበበ ጸያፍ አይባልም። ሲናበብ ግን ግንባር

ጸያፍ ይባላል። ሰም ሰወርቅ 6 ነገር ያተርፍሰታል። ፩ነገር ማትረፉም እንደሚከተለው ነው። እመ ርኅራኄ ቤተክርስቲያን ትወግዕ ጥዑመ ሥጋዌ ሐሊበ እግዚእነ ለደቂቃ ምእመናን በይነ ዘአእመረት ከመ ይኩኖሙ ሕይወተ ኃይለ ሥጋ ብሎ ትወግዕ በማለት ማሰሪያ ማትረፉን ጥዑመ በማለት ቅጽልን ሐሊበ እግዚእነ በማለት ተናባቢን ሥጋዌ ወተትን በማለት አፈታትን በይነ ዘአእመረት በማለት አንቀጽን ለደቂቃ በማለት ዝርዝር ማትረፉን ያሳያል ለዚህም ምሳሌ አለው። ብር ሠሪ ጭቃውን ሠርቶ ሰሙን በላይ ይቀርጸዋል። ወርቁን በሰሙ ላይ ሲያፈሰው የሰሙን ኅብር ወርቁ ይዞ ሰሙ ሲቀልጥ ወርቁ ይጠናል ሰምና ሰም አለመመሰሉ ስለዚህ ነው። የቅኔው ዜማም እንዳይሰብር የሚያቀኑ አገባባት አሊህ ናቸው። እንተ፣ እለ፣ ዘ፣ በገቡበት ይሰባሉ ይስማማሉም ሲገቡ ብእሲ ዘከብረ ይላል። ይህውም ምሳሌ አለው። ገበሬ ድግር ሲሰፋበት እርፍ ሲላላበት እንጨት ያደርግበታል። ደቀ መዝሙርም ዜማ ሲሰብርበት ዘከብረ ብሎ ያቀናል። ስለዚህ ሺብልቅ ይባላል። ዘ፡ በውእቱ እንደተሳበ አስተውል።

የቅኔ ጕዳና ከሺህ በላይ ሲሆን በጉባኤያት የሚነገሩ 300 ናቸው ከነዚህም ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን።

ጸሎት ሁሉ በበስመአብ እንደሚጀመር ቅኔም ጉባኤ ቃናውን በሥላሴ ስም ይጀምራል ቃልየ አጽምእ እግዚኦ በሚለው የሚገባ መዝ.5÷1

1. <u>መንታ ሰረዝ መንገድ</u>

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አኮኑ። ውእቱ ዮሴፍ ወዮሳ ወሶልያና እፎኑ።

<u>ትርጓሜ</u>:- አብ ዮሴፍ ነውና ወልድም ዮሳ ነውና፡ መንፈስ ቅዱስም ሶልያና ነውና እንዴት ነው።

2. <u>ዓመጸኛ ዳኛ መንገድ</u>

ማርያም ወይን ስኩራነ አበው ሥላሴ : ህልወ ፍቅረ ሰብእ ጣዕም ጥዕምተ ልሳን ውዳሴ።

<u>ትርጓሜ</u>:- የሰው ፍቅር ጣዕም ያላቸው ሥላሴ፡ አባቶች የስከሩባት ማርያም ወይን ለእንደበት ምስጋና የጣፈጠች ናት።

3. <u>የአገባብ ድርድር መንገድ</u>

ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን በመከራው ሰዓት ሳይሸሽ እስከ አግረ መስቀል የተከተለ ሐዋርያ ነው። እንዲያውም በዚች በዕለተ ዓርብ ያየው የጌታ መከራ ትዝ እያለው ተረፈ ዕድሜውን የፈጸመው በዕንባ ነው። የተጠራው ገና በወጣትነት ዕድሜው ሲሆን በዚህ ምድር ላይ የኖረው ለ99 ዓመታት ያህል ነው።

ቅዱስ ዮሐንስና እመቤታችን

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን እስከ እግረ መስቀሉ በመከተሉ ለክርስቲያኖች የእመቤታችንን እናትነት ከጌታ ተቀብሎአል። ዮሐ 19÷25-27። እመቤታችን ከዮሐንስ ጋር 16 ዓመት ተቀምጣ በ49 ዓ.ም ዐርፋለች። ከዚያም በኋላ በሦስተኛው ቀን እንደ ልጇ ተነሥታ ዐርጋለች ቅዱስ ዮሐንስ ርቆ ያልሄደው ርሷን የመጠበቅ አደራ ስለነበረበት ነው።

ቅዱስ ዮሐንስና የጌታ ሥዕል

ለጌታ ሥዕል ምንጭ ከሆኑት አንዱ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው። ጌታ በተሰቀለበት ዘመን የሮማ ንጉሥ የነበረው ጢባርዮስ ቄሣር ከ14-37 ዓ.ም ልጁ በሽተኛ ስለነበር የጌታን የማዳን ሥራ እየሰማ እነ ጲላጦስ የጻፉለትንም ደብዳቤ እየተመለከተ ከዚያ ደግ ሰው መቃብር ልጄን ወስዶ ማን ባዳነልኝ እያለ ይመኝ ነበር። በመጨረሻም ልጁን ወስደው በጌታ መቃብር ላይ ሲያኖሩት ከሕመሙ ስለተፈወሰለት ለጌታ ያለውን ፍቅር ለመግለጥ የጌታን ስዕል የሚስልለት ሰው ሲያፈላልግ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድን ተገናኘ ልክ በዕለተ ዓርብ እንዳየው አድርጐ ሥሎ ሰጠው።

ዮሐንስ ወንጌላዊ እመቤታችን ካረፈች በኋላ ወደ ታናሺ እስያ ሄዶ አስተምሯል ዋና መንበሩን በኤፌሶን አድርጐ በተለይ በዚያ ዘመን ከአውሮፖ ወደ መካከለኛው ምስራቅ በሚወስደው መንገድ ዳር በተቆረቆሩት ከተሞች እየተዘዋወረ አብያተ ክርስቲያናትን በማስተከል ጳጳሳትን በመሾም የወንጌልን ብርሃን አብርቶላቸዋል።

በመጨረሻም በጭካኔው በሚታወቀው በንጉሥ ድምጥያኖስ ዘመን ከ81-96 ዓ.ም ወንጌል በማስተማሩ የተነሣ በጣዖት አምላኪዎች ተከሶ ለፍርድ ከቀረበ በኋላ በፍል ውሃ ተሰቃይቶ በፍጥጥም ደሴት ግዞት ተፈረደበት ራዕዩን ያየውና የጻፈውም በዚያ ቦታ ነው ቅዱስ ዮሐንስ ድምጥያኖስ (በ96 ዓ.ም) ሲገደል ከግዞት ተመልሶ ሦስቱን መልእክታቱንና ወንጌሉን እንደጻፈ ይነገራል።

ቅዱስ ዮሐንስ ከሐዋርያት ሁሉ ይልቅ ረዥም ዕድሜ (ወደ 99 ዓመት) በምድር ላይ የቆየ ሐዋርያ ነው። ከሐዋርያት ቀድሞ ያረፈው ታላቅ ወንድሙ ቅዱስ ያዕቆብ ሲሆን ከሐዋርያት መጨረሻ ከዚህ ምድር የተለየው የቅዱስ ያዕቆብ ወንድም ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው። አስቀድሞ ጌታ በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት (ዮሐ 21 ÷22) ዮሐንስ ሞትን አልቀመሰም ። ነገር ግን እንደነ ኤልያስና ሄኖክ ሞትን እንዳያይ እግዚአብሔር ወደ ብሔረ ሕያዋን ወስዶታል። መስከረም 4 ልደቱ 29 ኤፌሶን ገብቶ ያስተማረበት 30 ከወንድሙ ያዕቆብ ጋር የተመረጠበት ጥር 4 ያረገበት ነው የሐዋርያው ረድኤትና በረከት በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ምዕራፍ 5 ቁጥር 7

መጋቢት 5 ቀን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕረፍት

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አገራቸው ግብጽ ልዩ ቦታቸው ንሂሳ ይባላል። አባታቸው ስምኦን እናታቸው አቅሌስያ ናቸው አባትና እናታቸው የተገኙት ከደጋጐቹ ምእመናን ነው ልጆቻቸው እንደ አያቶቻቸው በእግዚአብሔር ፊት ደጋጐች ነበሩ። የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እናት አቅሌስያ መካን ሆና ልጅ ስለአጣች እያለቀሰች ሠላሳ ዓመት ኖረች ንጽሕናን የሚወድ ልጅ ስጠኝ እያለች በሥዕለ ሥላሴ ተማፀነች እግዚአብሔርም ክብሩ ከፍ ያለ ልጅ ትወልጃለሽ አላት። ከዚህ በኋላ አቅሌስያ በመጋቢት 29 ቀን ፀነሰች በታኅሣሥ 29 ቀን ደም ግባቱ ያማረ ልጅ ወለደች ኢሳ.65÷22፣49÷6 መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም በሰው አምሳል መጥቶ የዚህ ልያሽ ስሙ ገብረመንፈስ ቅዱስ ይሁን አላት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መልአኩ እንዳወጣላቸው ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብለው ተጠሩ። በዚያም ቀን ሕፃኑ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተነሥተው ከእናታቸው ጭን ወርደወ ለእግዚአብሔር ሦስት ጊዜ ሰገዱ ምስጋናም አቀረቡ ከአምስት ዓመት በኋላ እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ሕፃኑን ከእናቱ ክንድ ተቀበል ብዙ ገዳማውያን ወደ አሉበት ገዳም ውሰድና አብረህ አስቀምጠው

አበምኔቱንም (የገዳሙ አለቃ) ሕፃኑን ከበር አንስተህ ከእናንተ ዘንድ አኑረው ስለ ልብሱ ስለ ምግቡ አታስቡ ሕፃኑ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነውና ምግቡም መንፈሳዊ ነው ብለህ ንገረው ብሎ አዘዘው መልአኩም ሕፃኑን ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ ከእግዚአብሔር ቡራኬ እንዲያገኙ አደረጋቸው::

ከዚያም መልአኩ ከእግዚአብሔር እንደ ታዘዘው አባ ዘመደ ብርሃን ወደ ሚባል መምህር ዘንድ ወስዶ አስቀመጣቸውና ከዘመደ ብርሃን መዝሙረ ዳዊትንና ሌሎችን የቤተክርስቲያን መጻሕፍት እየተማሩ አደጉ ትምህርታቸውንም ከጨረሱ በኋላ አባ አብረሃም ከሚባሉ ጳጳስ ዲቁና ተሾሙ ከዚያም አመነኮሱዋቸውና የቅስና ስልጣነ ክህነት ተቀበሉ በዖም በጸሎት በብዙ አገልግሎት ተወስነው በገዳም ብቻቸውን ኖሩ እንደ ሐዋርያትየተአምራትና የፈውስ ሀብት ተሰጣቸው ስለዚህም አጋንንትን ሲያወጡ ድውያንን ሲፈውሱ ለምጻሞችን ሲያነጹ መኖራቸው ተጽፎዋል በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በበረሀ ሲኖሩ አንበሶችና ነብሮች አብረዋቸው ሲኖሩ ነበር አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕድሜያቸው 300 ዓመት ሲሆን ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሂድ በዚያ ከደይን የምታወጣቸው ነፍሳት አሉ አላቸው ከዚያም በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጡ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል እየተመሩ አክሱም ደረሱ ያን ጊዜ ንጉሥ ላሊበላ ጋር በላስታ ሮሃ ተገናኝተው ላለ ንጉሡ አብያተ ክርስቲያናትን እየባረኩና የሀገሩን ሕዝብ እያስተማሩ ይቀመጡ ቢላቸው እግዚአብሔር ያዘዘልኝ ቦታ የደብረታቦር አምሳል በሆነው በዝቋላ ነው ብለው ተነሱ ንጉሡም ከርሳቸው ጋር አብሮ ሄደ ከደረሱም በኋላ በጣታቸው እየአመለከቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም አዳዱ በተባለው ቦታ ከቋጥኝ ድንጋይ ቤተክርስቲያን ሰርተህ ተመለስ በኋላ ዘመን በስምህ ቆፍቱ በሚባል ቦታ ላይ ቤተ መቅደስ ይሰራል ብለው ነገሩት ንጉሡም ቦታቸው ዳሩ እሳት መካከሉ ገነት እንዲሆን ወስኛለሁ ብሎ ተመለሰ በ97 ዓመቱ ሲያርፍም ጸሎተ ፍትሐት አድርገው የቀበሩት እርሳቸው እንደሆኑ

ታሪክ ያስረዳል አባታችንም በዚህ ቦታ ወደ ባሕርም ተወርውረው ተዘቅዝቀው ቆመው አርባ ቀን በጸሎት ቆዩ ስምህን የጠራውን መታሰቢያህን ያደረገውን እምርልሃለሁ የሚል ቃል ወደ አባታችን ወደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መጣ ርሱም በመላ ኢትዮጵያን ካልማርክልኝ ከዚህ ባሕር አልወጣም ብለው ለመልአኩ ነገሩት መልአኩም ከርሳቸው ዘንድ ከሔደ በኋላ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዚያ ባሕር ውስጥ 1 ዓመት ኖሩ ከዚህ በኋላ ጌታችን ወደርሳቸው መጥቶ ከባሕር ዳር ቆመና ተነሥ ውጣ መላ ኢትዮጵያን ምሬልሃለሁ አላቸውና ወደ ምድረ ከብድ ላካቸው በዚያም ሰባት ዓመት ቆመውና ወደ ሰማይ አንጋጠው ሲጸልዩ ሰይጣን በቁራ ተመስሎ መጥቶ ዓይናቸውን አወጣውና አሳወራቸው ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልከው መጥተው ዓይናቸው ላይ እፍ አሉባቸውና ዓይናቸው እንደ ቀድሞው አየ መላእክቱም ወደ ዝቋላ ሔደህ ጠላቶችህ አጋንንትን ተበቀል አሉዋቸውና ወደ ሰማይ ዐረጉ እርሳቸውም ወደ ዝቋላ ሲመለሱ እግዚአብሔር ለአብርሃም በመምሬ አጸድ በአንድነቱ በሦስትነቱ እንደተገለጠለት ለርሳቸው ተገለጠላቸው (ዘፍ.18÷1-5) በራዕይም እስከ ሦስተኛው ሰማይ አወጣቸው ገነትንም አስጐበኛቸው በዝቋላም ሰባቱ ሊቃነ መላእክት እየረዱአቸው ጠላቶቻቸው ሰይጣናትን በመብረቅ አጠፏቸው እንደገናም ወደ ምድረ ከብድ ተመልሰው በአራዊት መካከል ሆነው ሲጸልዩ መንፈስ ቅዱስ የጠራቸው ሦስት ቅዱሳን ወደርሳቸው መጡ እነዚህም የዋልድባው አባ ሳሙኤል የአዘሉው አባ ሕንበስ ከላዕላይ ግብጽ የመጣው አባ ብንያም ናቸው በአንበሶቻቸው ታጅበው ወደ ምድረ ከብድ መጡ ለጊዜው አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ስለተሠወሩባቸው ሰባት ቀን በሱባኤ ጸለዩ ከዚያም ተገናኝተው ሰላምታ ሰጥዋወጡ ከእነዚህም እንግዶች ጋር ከተሰነባበቱ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ከነሳስቶአቸው ክርስቶስን የካዱ ሰዎች ወደ አሉበት ወደ ምዕራብ ሀገር ሔዱ ከዚያም ጣዖት አምላኪው ንጉሥ በተአምራት አጋንንት ያደረባቸውን ጣዖታት ስለ ሰበሩበትና አጋንንቱም ስለጠፉ እንደ ሠለስቱ ደቂቅ በነደደ እሳት ውስጥ እንዲጣሉ አደረጋቸው እሳቱም ውሃ ሆነላቸው እንደገና

አበምኔቱንም (የገዳሙ አለቃ) ሕፃኑን ከበር አንስተህ ከእናንተ ዘንድ አኑረው ስለ ልብሱ ስለ ምግቡ አታስቡ ሕፃኑ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነውና ምግቡም መንፈሳዊ ነው ብለህ ንገረው ብሎ አዘዘው መልአኩም ሕፃኑን ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ ከእግዚአብሔር ቡራኬ እንዲያገኙ አደረጋቸው::

ከዚያም መልአኩ ከእግዚአብሔር እንደ ታዘዘው አባ ዘመደ ብርሃን ወደ ሚባል መምህር ዘንድ ወስዶ አስቀመጣቸውና ከዘመደ ብርሃን መዝሙረ ዳዊትንና ሌሎችን የቤተክርስቲያን መጻሕፍት እየተማሩ አደጉ ትምህርታቸውንም ከጨረሱ በኋላ አባ አብረሃም ከሚባሉ ጳጳስ ዲቁና ተሾሙ ከዚያም አመነኩሱዋቸውና የቅስና ስልጣነ ክህነት ተቀበሉ በየም በጸሎት በብዙ አገልግሎት ተወስነው በገዳም ብቻቸውን ኖሩ እንደ ሐዋርያትየተአምራትና የፈውስ ሀብት ተሰጣቸው ስለዚህም አጋንንትን ሲያወጡ ድውያንን ሲፈውሱ ለምጻሞችን ሲያነጹ መኖራቸው ተጽፎዋል በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በበረሀ ሲኖሩ አንበሶችና ነብሮች አብረዋቸው ሲኖሩ ነበር አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕድሜያቸው 300 ዓመት ሲሆን ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሂድ በዚያ ከደይን የምታወጣቸው ነፍሳት አሉ አላቸው ከዚያም በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጡ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል እየተመሩ አክሱም ደረሱ ያን ጊዜ ንጉሥ ላሊበላ ጋር በላስታ ሮሃ ተገናኝተው ሳለ ንጉሡ አብያተ ክርስቲያናትን እየባረኩና የሀገሩን ሕዝብ እያስተማሩ ይቀመጡ ቢላቸው እግዚአብሔር ያዘዘልኝ ቦታ የደብረታቦር አምላል በሆነው በዝቋላ ነው ብለው ተነሱ ንጉሡም ከርሳቸው ጋር አብሮ ሄደ ከደረሱም በኋላ በጣታቸው እየአመለከቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም አዳዱ በተባለው ቦታ ከቋጥኝ ድንጋይ ቤተክርስቲያን ሰርተህ ተመለስ በኋላ ዘመን በስምህ ቆፍቱ በሚባል ቦታ ላይ ቤተ መቅደስ ይሰራል ብለው ነገሩት ንጉሡም ቦታቸው ዳሩ እሳት መካከሉ ገነት እንዲሆን ወስኛለሁ ብሎ ተመለሰ በ97 ዓመቱ ሲያርፍም ጸሎተ ፍትሐት አድርገው የቀበሩት እርሳቸው እንደሆኑ

ታሪክ ያስረዳል አባታችንም በዚህ ቦታ ወደ ባሕርም ተወርውረው ተዘቅዝቀው ቆመው አርባ ቀን በጸሎት ቆዩ ስምህን የጠራውን መታሰቢያህን ያደረገውን እምርልሃለሁ የሚል ቃል ወደ አባታችን ወደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መጣ ርሱም በመላ ኢትዮጵያን ካልማርክልኝ ከዚህ ባሕር አልወጣም ብለው ለመልአኩ ነገሩት መልአኩም ከርሳቸው ዘንድ ከሔደ በኋላ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዚያ ባሕር ውስጥ 1 ዓመት ኖሩ ከዚህ በኋላ ጌታችን ወደርሳቸው መጥቶ ከባሕር ዳር ቆመና ተነሥ ውጣ መላ ኢትዮጵያን ምሬልሃለሁ አላቸውና ወደ ምድረ ከብድ ላካቸው በዚያም ሰባት ዓመት ቆመውና ወደ ሰማይ አንጋጠው ሲጸልዩ ሰይጣን በቁራ ተመስሎ መጥቶ ዓይናቸውን አወጣውና አሳወራቸው ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልከው መጥተው ዓይናቸው ላይ እፍ አሉባቸውና ዓይናቸው እንደ ቀድሞው አየ መላእክቱም ወደ ዝቋላ ሒደህ ጠላቶችህ አጋንንትን ተበቀል አሉዋቸውና ወደ ሰማይ ዐረጉ እርሳቸውም ወደ ዝቋላ ሲመለሱ እግዚአብሔር ለአብርሃም በመምሬ አጸድ በአንድነቱ በሦስትነቱ እንደተገለጠለት ለርሳቸው ተገለጠላቸው (ዘፍ.18÷1-5) በራዕይም እስከ ሦስተኛው ሰማይ አወጣቸው ገነትንም አስጐበኛቸው በዝቋላም ሰባቱ ሊቃነ መላእክት እየረዱአቸው ጠላቶቻቸው ሰይጣናትን በመብረቅ አጠፏቸው እንደገናም ወደ ምድረ ከብድ ተመልሰው በአራዊት መካከል ሆነው ሲጸልዩ መንፈስ ቅዱስ የጠራቸው ሦስት ቅዱሳን ወደርሳቸው መጡ እነዚህም የዋልድባው አባ ሳሙኤል የአዘሉው አባ አንበስ ከላዕላይ ግብጽ የመጣው አባ ብንያም ናቸው በአንበሶቻቸው ተጭነው ወደ ምድረ ከብድ መጡ ለጊዜው አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ስለተሠወሩባቸው ሰባት ቀን በሱባኤ ጸለዩ ከዚያም ተገናኝተው ሰላምታ ተሰዋወጡ ከእነዚህም እንግዶች ጋር ከተሰነባበቱ በኋላ መንፈስ አነሳስቶአቸው ክርስቶስን የካዱ ሰዎች ወደ አሉበት ወደ ምዕራብ ሀገር ሔዱ ከዚያም ጣዖት አምላኪው ንጉሥ በተአምራት አጋንንት ያደረባቸውን ጣዖታት ስለ ሰበሩበትና አጋንንቱም ስለጠፉ እንደ ሠለስቱ ደቂቅ በነደደ እሳት ውስጥ እንዲጣሉ አደረጋቸው እሳቱም ውሃ ሆነላቸው እንደገና

ከሐዲው ንጉሥ አባታችንን አንገታቸውን በሰይፍ ሊቆርጣቸው ሲቃጣ መብረቅ ከሰማይ ወርዶ ንጉሡን ከነሠራዊቱ አጠፋቸው። አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ከዚያ ሔደው እግራቸውን በገመድ አስረው በገደል ላይ ቁልቁል ተሰቀሉ ሰይጣን መጥቶ ያቺን ገመድ ቆረጣት አባታችንም ወደ ታች ወደቁ ቅዱስ ሚካኤል ያዛቸውና በራሳቸው ቆመው ስለእነዚያ ከሐዲዎች ነፍሳት መጸለይ ቀጠሉ በጥርሳቸው ድንጋይ ነክሰው እስከ ሠላሳ ዓመት ኖሩ። ብዙ ገድልን ተጋደሉ በገድላቸው እንደተጻፈ የዝቋላ ገዳም መቅናት የጀመረ በ1414-1430 በአጼ እንድርያስ ነው ዕረፍታቸውም በዚህ ጊዜ ነበርና መጋቢት 5 እና 27 ዎም ስለሆነ ጥቅምት 5 እና 27 እንዲከበር ንጉሡ ወስኗል። ከዚህም አያይዞ አምስት አብያተ ክርስቲያናትን 1ኛ በኢየሱስ ክርስቶስ 2ኛ በአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ 3ኛ በእመቤታችን 4ኛ በቅዱስ ሚካኤል 5ኛ በቅዱስ ገብርኤል ስም መስርቷል። ይህ ንጉሥ ሲሞት በዚሁ በእመቤታችን ቤ/ክርስቲያን ተቀብሯል ጥቅምት 5 የሚከበረውም በዚህ ምክንያት ነው።

አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ የዕረፍታቸው ጊዜ ሲደርስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ የለመንኸኝን ሁሉ አደርግልሃለሁ ከእናትህ ማህፀን ጀምሮ የመረጥሁህ እኔ ነኝ ቃል ኪዳኔንም ከአንተ ጋር አቁሜአለሁ እስከ አሁን ለምነኸኝ የከለከልኩህ ነገር የለም ሁሉንም ፈጽሜልሃለሁ ይህን ያህል ዘመ ድካምን ችግርንና ፈተናን ታግሰህ በእኔ ስም ገድልህን ፈጽመሃልና አላቸ ጻድቁም እስከ አሁን የለመኑትን ሁሉ እንደፈጸመላቸው ጠቅሰው ምሥጋና በማቅረብ ከዚህ ዓለም ሥጋ በሞት ከተለየሁ በኋላ ስሜ ተደብቆ እንዳይቀር አድርግልኝ በዓለም ሁሉ ሥራዬ ገድሌ ይታወቅ አንተ ሥራዬ ከአልገለጥህልኝ ማን መታሰቢያዬን ያደርግልኛል የሰጠኸኝ ቃል ኪዳን ሁሉ የታወቀ ይሁንልኝ በስሜ ለድሆች ለጦም አዳሪዎች ለሙት ልጆች ጠዋ ለሌላቸው ሽማግሌዎች ምጽዋት በመስጠት ለጦም አዳሪዎች በማብላ በማጠጣት መታሰቢያዬን ያጸፉትን ሁሉ ማርልኝ ሥርየተ ኃጢአት ስጥልኝ አሉት። ጌታም በራሱ በመማል ስምህን የጠራውን ያስጠራው መታሰቢያህን ያደረገውን በጸሎትህ በአማላጅነትህ የተማመነው

እምርልሃለሁ ገድልህን የጻፈውን ሳይጠራጠር በፍቁም ልብ አምኖ ሲነበብ የሰማውን እኔ ስሙን በመጽሐፈ ሕይወት እጽፍልሃለሁ መታሰቢያህ በሚደረግበት ቀን ለቤተ ክርስቲያን ስንዴና ወይን ለመሥዋዕት ቅብአ ዘይት ጧፍ ሻማ ለመብራት ዕጣን ለማዕጠንት መባዕ አድርጉ የሰጠውን ኃጢአቱ ይደመሰስለታል ሺህ ዓመት እስከሚፈጸም ድረስ በምስሐ ደብረ ጽዮን አስቀምጠዋለሁ (ራዕ. 20፥1-7) ሲል ቃል ኪዳኑን ከአፀናላቸው። በኋላ ተሰወረ አባታችንም ይህን ቃል ኪዳን በገዳመ ዝቋላ ከተቀበሉ በኋላ ወደ ምድረ ከብድ ሔዱ ምድረ ከብድ ላሉ መነኮሳት ሁሉ ጊዜ ሞታቸው እንደቀረበ ነገሯቸው መጋቢት 3 ቀን ዓርብ ታመሙ በዚህም ጊዜ ፍሬ ቅዱስና ዘርዓ ብሩክ ያዕቆብና ብንያም ዮሴፍና ሌሎችም ብዙ ባሕታውያን ወደርሳቸው ቀረቡ በማግሥቱ ድካም እየተሰማቸው ወዛቸው ላባቸው እየበዛ ዋሉ። ሲመሽ መናገር እየተሳናቸው ሔደ ገብረ እንድርያስ የተባለው ለሞታቸው ምስክር እንዲሆን ለጊዜው አልነበረምና ሄደው ከአለበት ጠርተው አመጡት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚት ማታ ለእሑድ አጥቢያ መጋቢት 5 ቀን ከሌሊቱ 6 ሰዓት ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች በዚህም ጊዜ እንደ ነጐድጓድ ያለ ድምጽ ከሰማይ ተሰማ ጌታችንም ወደ አባታችን ወረደ ዳግመኛም ለአቀባበል እንደ በረዶ ነጭ የሆነ ሻማ ከሰማይ ወደ ምድር እንደ ወንጭፍ ድንጋይ ተወረወረ እንደ ፀሐይም በራ ምድር ተንቀጠቀጠች ባሕታውያኑ ሁሉ ስለፈሩ ሥጋቸውን ለመገነዝ ችላ አሉ። ነገሩ የገባቸው ግን ይህ ሁሉ የሆነ ስለ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ክብር መሆኑን ተገንዝበው አደነቁ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጁ ሰላም ለአንተ ይሁን አላቸው በሕይወት ሳሉ የሰጣቸውንም ቃል ኪዳን አፀናላቸው ይህውም እስከ 15 ትውልድ እምርልሀለሁ ነፍስህ ከሥጋህ ከተለየችበት ከመጋቢት 5 ቀን ጀምሮ መታሰቢያህን ያድርጉ አሁንም ወደ ሰማይ ከፀሐይ ሰባት እጅ ወደ ሚያበራ ወደ ብርሃን ቤት ውጣ እነሆ አሥራ ሁለት አክሊላት ሰጥቼአለሁ አላቸው። ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሚካኤል ሦስት አክሊል ቅዱስ ገብርኤል ሦስት አክሊል ሱራፌልም ሦስት አክሊል ኪሩቤልም ሦስት አክሊል ሰጡአቸው ዳግመኛም እነሆ መብራት ሰጥቼአለሁ

እንድ መቶ ሺህ በቀኝህ መቶ ሺህ በግራህ መቶ ሺህ በፊትህ መቶ ሺህ በኋላህ ይብራ አላቸው እያንዳንዱ ብርሃን ከፀሐይ ዕጥፍ የሚያበራ ነው። ከዚህ ሌላ የብርሃን ድባብ ሰጥቼሃለሁ መቶ ሺህ በቀኝህ መቶ ሺህ በግራህ መቶ ሺህ በፊትህ መቶ ሺህ በኋላ ይሁንልህ አላቸው የእያንዳንዱም የድባብ ብርሃን ከፀሐይ ብርሃን ዕጥፍ የሚያበራ ነው። አምስት መቶ ስልሳ ሁለት ዓመትም ያለ ልብስ ራቁትህን ስለኖርህ የብርሃን ልብስ እነሆ ሰጥቼአለሁ አላቸው አቡነ ገ/ መንፈስ ቅዱስም ጌታችን አቤቱ የኢትዮጵያንሕዝብ አንድ ሳታስቀር በሙሉ ማራቸው አሉት ጌታችንም ለአባታችን እነሆ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ አሥራት እንዲሆኑህ ሰጥቼሃለሁ እንደ ወደድህ ለአንተ ይሁኑህ መታሰቢያህን ያድርጉ በጸሎትህ በአማላጅነትህ ይታመኑ ደስ ብሎዋቸው ለዘለዓለም ይኑሩ አላቸው። በዓድቅ ሰው ጸሎት ሀገር ትፀናለች እንጂ አትጠፋም ሐዋርያው ያዕቆብ እንደ ተናገረ የዓድቅ ጸሎቱ ግዳጅ ትፈጽማለች (ያዕ.5÷16)

ያን ጊዜ የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች ጌታችንም ተቀብሎ ሳማት ደስታንም መላት። ለምስክርነት የቆሙና ያዩ ቅዱሳን ገዳማውያን በዚች ሌሊት ድንቅ ነገር አዩ ሰማያት ሲከፈቱ መላዕክት ከሠራዊታቸው ጋር የቅዱሱ ሥጋ ወደ አለበት እየተጨናነቁና እየተጋፉ ሲወርዱ አዩ ዳግመኛም አባታችንን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ የሚል ቃል ሰሙ። ከዚህም ሌላ የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስን በድን አንስታችሁ ወደ ኢየሩሳሌም ውሰዱ መቃብሩም ከመሠዊያው በስተቀኝ በኩል ይሁን የሚል ቃል ሰሙ ሌሎች የመላእክት አለቆችም የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በድን በአለበት በስተቀኝ ቆሙ በንጽሕት ነፍሳቸው ፊት ዕልልታና ምሥጋና እያደረጉ እንደ ውሃ ፏፏቴ መቋረጥ በሌለበት ልዩ ልዩ ምሥጋና አመሰገኑ ሥርዓቱ ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ በድናቸውን መላዕክት ሊቀብሩት እግዚአብሔር ወደአዘዘበት ቦታ ወሰዱት። እግዚአብሔር ያዘዘው ሁሉ በተፈጸመ ጊዜ እነዚያ መላእክት በምሥጋና በክብር በዕልልታ ነፍሳቸውን ወደ ብርሃን አዳራሽ አስገቡዋት በመላእክት ማህበርም ውስጥ በሰማይ ፍፁም ደስታ ሆነ።

የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዓል በየዓመቱ 3 ጊዜ የሚከበረውና መታሰቢያ የሚደረግላቸው ይህን ታሪክ በተከተለ ሁኔታ ነው የነበሩበት ዘመን ከ853-1415 ዓ.ም ድረስ ነው።

3 ጊዜ የተባለው ታህሣሥ 29 ቀን ልደታቸው መጋቢት 5 ቀን ዕረፍታቸው ጥቅምት 5 ቀን ቃል ኪዳን የተቀበሉበት ወይም የመጋቢት 5 ቀን ለውጥ ነው። የፃድቁ ረድኤትና በረከት በሁላችን ላይ ይደር። አሜን።

ሁለተኛም ሐምሌ 5 ቀን በ67 ዓ.ም የጴጥሮስና የጳውሎስ ዕረፍት ነው። ጴጥሮስን ከሐዋርያት ጳውሎስን ከአርድኢት ይመልከቱ።

ምዕራፍ 6 ቍጥር 8

ሀዲር 6 ቀን ቁስቋም

መሠረተ ቃል:- ወይወርድ እግዚእነ ውስተ ምድረ ግብጽ ተፃኢኖ ዲበ ደመና ቀሊል ጌታ በፈጣን ደመና ሆኖ ወደ ግብጽ ይወርዳል ኢሣ.19÷1 ወፍኖቶሂ ዘእምዓለም ርኢኩ አእዳኅተ ኢትዮጵያ ይደነግፃ ከጥንት የታሰበ መንገድን አየሁ የኢትዮጵያ አውራጃዎች ይደነግጣሉ እንባቆም 3÷6-7 ያፍኒ ረከበት ላቲ ቤተ ወማዕነቅኒ ኀበ ታነብር እጕሊሃ ወፍም ሰራሲ ቤት አገኘች ዋኖስም ግልገሏን የምታሳርፍበት መዝሙር 83÷3 ከዚህ በላይ ቀደም ሲል የገለጽናቸው ጥቅሶች ስለ ኢትዮጵያና ስለ ግብጽ ታላቅ ተስፋ የያዙ ናቸው ኢሳይያስ ጌታ ወደ ግብጽ መውረዱን ሲናገር ዕንባቆም ደግሞ በዚያው መንገድ ኢትዮጵያ መግባቱን ያስረዳል። ይህ የጌታ ስደት ከግብጽ የአምልኮተ ጣዖት ላህምን ያጠፋ ሲሆን ለኢትዮጵያ ደግሞ ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል ተሻገረች ለማለት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክ ልጇን በእቅፏ ይዛ አክሱምን ሌሎችንም የኢትዮጵያ አውራጃዎች ደብረ ዳሞ ዋልድባ ጣናን ምሳአለ ማርያምን ምሁር ኢየሱስንና ሌሎችንም ቦታዎች እንደጐበኘችና ሁሉ ከሚቻለው ልጅዋ አገሪቱን ኢትዮጵያን በርዕስትነት ሕዝቧንም በአስራትነት በቃል ኪዳን እንደተቀበለች ይገልፃሉ። ስለዚህም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሕፃኑን ነፍስ የሚሻት ሙቷልና ወደ አገራችሁ ተመለሱ የሚለውን ብሥራት ሰምታ በስደት

ከነበረችበት ወደ አገሯ ለመመለስ ፊቷን ያቀናችበት በገዳመ ቁስቋም ገብታ ያረፈችበት በዓል ነው ማቴ. 2÷19 ተመየጢ ተመየጢ ሱላማጢስ ተመየጢ ወንራይ ብኪ ሰላመ ሰላማዊት ተመለሽ ተመለሽ በአንቺ ሰላምን እንይ (መኃ. 7÷1) እየተባለ በየዓመቱ ጎዳር 6 ቀን ስትከበር ትኖራለች::

ዳግመኛም በኋላ ዘመን በዚህ በደብረ ቁስቋም ቅዱሳን ሐዋርያቶችን ሰበሰባቸው ታቦቱንና ቤተክርስቲያኑንም አክብሮ የቁርባን መስዋዕትንም ሠርቶ ቅዱስ ቁርባንን / ሥጋውንና ደሙን ለወገኖቹ ሰጣቸው ለዚህም የእስክንድርያ አገር ሊቀ ጳጳሳት ቅዱሳን አባቶቻችን ቄርሎስና ቴዎፍሎስ ምስክሮች ሆኑ::

ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን:: አምላክን የወለደች የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በረከቷ ከእኛ ጋር ይኑር:: ለዘለዓለሙ አሜን::

ቊጥር 9

ጥር 6 ኢየሱስ ነው

ኢየሱስ (ጽር የሱስ ዐረ የሱዕ፡ ዕብ) ስመ ተፀውኦ አማኑኤልን የመሰለ መድኀን፣መድኃኒ፣ መድኃኒት፣ ቤዛ መቤዝው (ማቴ . 1÷21 ዮሐ. 4 ÷22) ኢና፣ይ፡ አንድ ወገን ናቸው የሱስ ማለት ይበቃ ነበር ኢ፣ እንዲያው በከንቱ ተጨምሯል ምስጢር የለውም ኢያሱ ኢዮስያስ እንደ ማለት ነው ባለ አዲሶች ግን ኢን፡- አኮ መድኀኒት ሲሉ አይሁድ ጨምረውታል ብለው ያወራሉ ውሸት ነው ስምነቱም ብቻ የቃል የሥጋ ስም አይደለም ቃልና ሠጋ ተዋህደው አንድ የሆኑበት የአንድ አካል የሰግው ቃል ስም ስለሆነ ሁለት ባሕርይና ሁለት ግብር አምላክ ወሰብ እነትን ያሳያል እንደ አማኑኤል ነው ሶበሰ አምላክ ውእቱ ባሕቲቱ እምኢሞተ ሶበ ሰቀልዎ ወሶበሂ ሰብዕ ውእቱ ባሕቲቱ እም ኢያድኅነ (ሃይ፣ሃበ):: ቤዛ ሆኖ መሰቀል፣መሞት፣ምግብ ሆኖ መበላት፣መጠጣት የሰውነት ማዳን የአምላክነቱ (ዮሐ. 6÷66 የሐዋ. 4÷12) ከሥጋዌ በፊት የርሱ ምሳሌ ሊሆኑ የሱስ የተባሉ ብዙ ናቸው (1ዜና 24÷11 ነህ.12÷8) ኢያሱና ሆሴም የዚህ ጭምር ናቸው::

ግዝረት

ወንድ ልጅ ተወልዶ በ8ተኛው ቀን ሲገረዝ ስም ይወጣለት ነበር (ሉቃ 1:59-63፣ 2÷21) ግዝረት የሥጋ ሸለፈት መቆረጥ ለአብርሃም የሰጠው ቃል ኪዳን ምልክት ነው ይህም ለወንድ ልጅ ብቻ ነበር (ዘፍ.17÷7-14) ለሙሴ ዘመን ለእስራኤል ሕዝብ ምልክትና መለያ ሆነ (ዘፀ. 12÷43-45 1ሳሙ.17÷36) ፈሪሳውያን በተለይ በሙሴ እንደተሰጠ እንደ ሕዝባዊና ሕጋዊ ምልክት አድርገው ፈጥረውት ነበር(የሐዋ. 15÷1-5 ገላ 5÷2-6) ክርስቶስ እንዳስታወሳቸው በመጀመሪያ የሰጠው ለአብርሃም ነበር መንፈሳዊ ምልክት ነው (ዮሐ. 7÷22) ግዝረት የሚከተሉትን ሦስት ነገሮች ያመለክታል:: 1. እግዚአብሔር የተገረዘውን ሰው ለራሱ መርጧልና አምላኩ ነው(ዘፍ.17÷8) 2. የተገረዙት የእግዚአብሔር ሕዝብ ናቸውና ክፋትንም ከሕይወታቸው ማስወገድ አለባቸው (ዘዳ 10÷16 ኤር 4÷4) 3. እግዚአብሔር በእምነት መሠረት ስለ ተቀበላቸው የጽድቃቸው መሠረት ነው:: (ሮሜ.4÷11) ስርዓት እርሱ አያድንም ስለዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቃድ ማድረግ አለባቸው ሮሜ 2÷25-29 ዋናው ነገር የልብ መለወጥ ነውና ምእመናን በመንፈስ የተገረዙ ናቸው::(ፊልጵ. 3÷30) በአ.ኪ ዘመን ጥምቀት በግዝረት ፈንታ ገብቷል (ቆላ. 2÷11-12) ግዝረትም አሁን አይጠቅምም (ገላ. 5÷6፣6÷15) ኢየሱስ ግን በምላጭ በፍጡራን እጅ አልተገረዘም ገራገፍ ምላጭ ይዞ ሲቀርብ በመለኮቱ ኃይል /ሥልጣን/ በጁ ላይ ምላጩ ውሃ ሆኗል ምክንይቱም የመለኮቱ ደም ያለዕለተ ዓርብ የማይፈስ ስለሆነ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ተገርዞ ተግኝቷል ሉቃ 2÷21-35 ዘሌ. 12÷1-ፍፃ. ክብር ምሥጋና ለርሱ ይሁን አሜን::

ምዕራፍ 7 ቊ.10

ጥር 7 ቀን የሥሉስ ቅዱስ በዓል

በዚህ ዕለት «ኑ እንውረድ ቋንቋቸውን እንደባልቀው» አሉ ይህንን ቃል የተናገሩ ሥላሴ ናቸው የተናገሩባቸው ከጥፋት ውኃ የተረፉት በእየጊዜው

ለተራቡት ለከለዳውያን ነው። መሪያቸውም ናምሩድ ይባል ነበር ዘፍ.10÷8 እነርሱም ሥፍራቸውን እየለቀቁ ጉዞ ጀመሩ የአደረጉትም ጉዞ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ተጉዘው ነው ወደ ሰናያር ሜዳ ደረሱ ዘፍ.10÷10፣ ዳን.1÷2 በዚያም ተቀምጠው ርስ በርሳቸው ጡብ እንስራ በእሳትም እንተኩሰው ተባባሉ ጡቡም እንደ ድንጋይ ሆነላቸው ቀጥሎም ከተማና ራሱ ወደሰማይ የሚደርስ ግንብ እንስራ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው አሉና ታላቅ ግንብ መሥራት ጀመሩ ዘፍ. 11÷1-6 በዚህ ሁኔታ የግንቡ ሥራ ከቀን ወደ ቀን እያደገ ሄደ ከምድር ሆኖ ሰሚመለከተው የግንቡ ርዝማኔ ሰማይ ጠቀስ መስሎ ይታይ ነበር አንዱ ግን የአቀዱት ጉልበታቸውን በመፈተን ኃይላቸውን በማሳየት ስማቸውን በማስጠራት በትዕቢትና በትምክህት ሰማይ ጠቀስ የሆነ ሕንፃ እንሠራለን ብለው ስለተነሱና ጦር እየወረወሩ እግዚአብሔርን ወጋን ሲሉ ሰይጣን ደም ቀብቶ ይልክላቸው ነበር። ሥላሴም ሥራቸው የውድቀትና የጥፋት መሆኑን ተመልክተው መዓት ሰማውረድ ወሰኑ በጐ ሥራ የሚሠራ የለም የሚያስተውልና እግዚአብሔርንም የሚፈልገ እንዳልተገኘ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ የሰው ልጆችን ተመለከተ ብሏል መዝ.13÷2 በሥራቸው እንደረከሱና እንደጐሰቆሉ አንድም እንኳ ከመካከላቸው በጐ ሥራ የሚሠራ እንደሌለ ሥላሴ ከሰማይ ሆነው ተመለከቱ በዚህ ጊዜ « ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን እንደባልቀው» ተባባሉ ሥላሴም ወርደው ቋንቋቸውን ደባለቁት አንዱ የአንዱን ቋንቋ የማይሰማ ሆነ ድንጋይ አምጣ ሲለው ውሃ እንጨት አምጣ ሲለው ጭቃ ያመጣ ነበር በመጨረሻም ሥላሴ ቋንቋቸውን ደባልቀው ከለያዩ በኋላ እነርሱንም በታተኗቸው በትዕቢትና በትምክህት የሠሩትንም ያንን ሰማይ ጠቀስ የሆነ ታላቅ ሕንፃ በአውሎ ነፋስ በታተኑት/ አፈረሱት/ እነሱም ሥራቸውን ትተው በየአገሩ ተበታተኑ ዘፍ.11÷7-10 ሥላሴ ይህን ሕንፃ እንዲፈርስ የአደረጉበት ምክንያት ለመልካም ሥራ አገልግሎት እንዲውል መልካም ሥራ እንዲሠራበት በአለማድረጋቸው ነው። ስለዚህ ትእቢተኞችን

በልባቸው ሐሳብ በተናቸው ሉቃ 1÷51-53። እንዳለው ሐሳባቸው ግን ታላቅ ግንብ ሠርተንና ገንብተን ጽርሐ አርያም እንደርሳለን ከሥላሴ ጋር እንፈታተናለን የሚል የድንቁርና አስተያየት ነበራቸው እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ዘዳ. 6÷16 የሚለውን ቃል በመተላለፋቸው ለጥፋት ተዳርገዋል። ሥላሴ ሚራ.3÷22፣15÷17፣44÷10 ጥበ.6÷ ፮

ቁጥር 11

ሐምሌ 7 ቀን ሥላሴ ወደ አብርሃም ቤት የገቡበት

የእግዚአብሔር ባለሟል እንግዳ መቀበልን የሚወድ በሥራው ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ደገኛና ፃድቅ የሚሆን ከኖህ ልጅ ከሴም ወገን የተወለደ ስሙን አብርሃም የሚሉት አንድ ሰው ነበር የሚስቱም ስም ሣራ ይባላል እነዚህም ቅዱሳን በሥላሴ ሕግ ተጠብቀው ስደተኛውንና እንግዳውን እየተቀበሉ ያስተናግዱ ነበር።

እንግዳ ሳይዙ ወይም ሣይኖር የሰናፍጭ ቅንጣት ስንኳ ምግብ ምንም አይቀምሱም ነበር።

የበጐ ነገር ጠላት የሆነው ሰይጣንም ይህንን በተመለከተ ጊዜ ከጭፍሮቹ አንዱን እንዲህ ሲል ላከው። እንግዶች ሁሉ ወደ አብርሃም ቤት እንዳይሄዱ ሄደህ በምድያም ጐዳና ተቀምጠህ እውነቱን በሐሰት ለውጠህ ተናገር።

እነሆ ደምህ በመሬት ላይ እስኪወርድ ድረስ ራስክን በድንጋይ ፈጥፍጠው አለው።

ሰይጣኑም ይህን ትዕዛዝ ከተቀበለ በኋላ ወደምድያም ወረደና ደሙ በምድር ላይ እስኪፈስ ድረስ እራሱን በድንጋይ ገምሶ ከጐዳና ዳር ተቀመጠ።

በጐዳናው የሚያልፉ መንገደኞች ሰዎችም ወደሱ በደረሱ ጊዜ እናንተ መንገደኞች ከወዴት መጥታችኋል ወዴትስ ትሄዳላችሁ ሲል ጠየቃቸው መንገደኞችም እኛስ ወደ ደገኛው ወደ አብርሃም ቤት እንሄዳለን አሉት።

በውኑ የአብርሃም ደግነቱ በክፋት እንደተለወጠና ክፉ ሰው እንደሆነ አልሰማችሁምን? እነሆ እንግዳ ከመቀበሉ የተነሳ ደሜ በመሬት ላይ እንደውሃ እስኪፈስ ድረስ የፈነከተኝን እራሴን መጥታችሁ ተመልከቱ ይልቁንስ በኔ የደረሰ እንዳይደርስባችሁ አትሂዱ አላቸው እንግዶቹም ያ ቸርና መልካም ሰው የነበረው አብርሃም ምን ነክቶት ክፉ ሰው ሊሆን ቻለ በማለት ርስ በርሳቸው ተወያዩ።

ይህንን ከተባባሉ በኋላ ተመልሰው ወደ እየሀገራቸው ሄዱ በዚችም ዕለት አብርሃም ከቤቱ ወጥቶ በጉዳና እንግዳ ፈልጉ አጣ ከዚያ ወደ ቤቱ ተመልሶ ገባና ምንም ምን ሳይቀምስ ተኛ። በማግስቱም አምስት ሰዎች ወደ አብርሃም ቤት ሲሄዱ ያ ተንኮለኛ አገኛቸውና እንደቀድሞው እናንተ ሰዎች ወዴት ትሔዳላችሁ ሲል ጠየቃቸው ወደ አብርሃም ቤት እንሄዳለን አሉት። ሰይጣኑም መልሶ ወንድሞቼ ሆይ አብርሃም እራሴን ፈንክቶኝ ከማህል እራሴ የሚወርደው ደሜን ኑ ተመልከቱ አላቸው። እነሆ አሁንም እናንተ እንደኔ እንዳትሆኑ በሰላም ወደ ሐገራችሁ ተመለሱ አላቸው በዚህን ጊዜ እነዚያ እንግዶች እርስ በርሳቸው አብርሃም ከሚገድለንስ ወደ አገራችን ብንመለስ ይሻላል ተባባሉ። ዳግመኛም እንደልማዱ አብርሃም ወደ ጉዳና ወጥቶ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ሲጠብቅ ውሎ ምንም እንግዳ ሳያገኝ ቀረ። ከዚያም ወደቤት ተመልሶ ምንም ምን ሳይቀምስ ተኝቶ አደረ። በሦስተኛው ቀን ሦስቱ ሥላሴ የአብርሃምን ቆራጥነት የሰይጣንን ተንኮል ተመልክተው ወደ አብርሃም ቤት ሄዱ። በዚህ ጊዜ የሰይጣን ምክሩ ሁሉ ተሻረ ይዘውም ወደ መጨረሻይቱ የሲኦል ረግረግ ጣሉት። ስድስት ሰዓትም በሆነ ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ አይኑን አቅንቶ ተመለከተ ሦስት ሰዎችም በፊቱ ቆመው አየ። ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው እየሮጠ ሄደና በምድር ላይ ሰገደላቸው።

አቤቱ ከፊታችሁ ሞገስ አግኝቼ ከሆነስ ባሪያችሁን አትለፉኝ ብዬ እለምናለሁ ከዚች ዛፍ ሥር ከድካማችሁ እረፉ ጥቂትም ውሃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ ቁራሽ እንጀራ ላምጣላችሁና ልባችሁን ደግፉ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ በክብር እንግድነት ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና

አላቸው። ሥሉስ ቅዱስም እንዳልህ ወይም እንዳሰብህ እንዲሁ አድርግ አሉት። አብርሃምም ሚስቱ ሣራ ወደ አለችበት ፈጥኖ ገባና ሦስት መስፈሪያ የስንዴ ዱቄት ወስደሽ በውሃ ለውሰሽ ድፎ ዳቦ አምባሻ ጋግሪ አላት። ዳግመኛም አብርሃም የከብት መንጋ ወዳለበት እየሮጠ ሔደና እጅግ በጣም የሰባ ታናሽ ወይፈን አምጥቶ ለብላቴናው ሰጠው ወይፈኑንም አርዶ ሥጋውን በየብልቱ ፈጥኖ ያዘጋጅ ዘንድ አዘዘው ከዚያም አርጉና ወተት ማርና ያዘጋጀውንም የኮርማ ሥጋ አመጣላቸው በፊታቸውም አቀረበ እነሱም የቀረበላቸውን በሉ ጠጡ እሱም ከፊታቸው ቆሞ ያስተናግዳቸው ነበር። እግዚአብሔርም አብርሃምን እንደዛሬው ሁሉ የዛሬ ዓመት ወደአንተ ተመልሼ እመጣለሁ ሚስትህ ሣራም ልጅ ታገኛለች ስሙንም ይሥሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ ለርሱ ከርሱም በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን ከርሱ ጋር አደርጋለሁና አባርክሃለሁ የብዙ ህዝብ ወገንንና የአህዛብ ነገስታት ሁሉ ከእርሱ ይወጣሉና አብርሃምም በግምባሩ ወድቆ ሰገደና የመቶ አመት ሽማግሌ ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን ዘጠና አመትስ የሆናት ባልቴት ሣራ ልጅ ለመውለድ እንደምን ይሆንላታል? አለ። እግዚአብሔርም አብርሃምን በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? ይልቁንስ እንደዛሬው ሁሉ የዛሬ ዓመት ወደ አንተ እመለሳለሁ ሣራ ሚስትህም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ብዬ እነግርሃለሁ አለው ዘፍ 18÷1-16

ዳግመኛም እግዚአብሔር ቃል ኪዳኔን በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ለብዙ ህዝብ ወገንና አባት ለነገሥታትም ለነቢያትም ሁሉ መገኛ ትሆናለህ ዘርህም እንደ ባህር አሸዋ እንደ ሰማይ ኮከብ ይበዛል ዘፍ 22÷17 ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደተናገረው ሣራን በቸርነቱ አሰባትና ፀነሰች ወንድ ልጅም ወለደች አብርሃምም የልጁን ስም ይስሐቅ ብሎ ጠራው ሕፃኑ ይስሐቅም አድጉ ጡት ከመጥባት ባቋረጠ ጊዜ በዚያን ቀን ሚስቱ ሣራና አብርሃም ታላቅ ግብዣ አደረጉ ዘፍ.21÷1-9 የተናገረውን የማያስቀር ክብር የባህርዩ የሆነ እግዚአብሔርን ፈጽመው አመሰገኑት 2ኛም

ከአብርሃም ቤት ከወጡ በኋላ በሰዶምና በገሞራ ላይ እሳትና ዲን ያወረዱበት ቀን ነው። ዘፍ.19÷1 መዝ.10÷5 ይመልከቱ የሥላሴ ረድኤታቸውና በረከታቸው በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ምእራፍ 8 ቍጥር 12

ሐምሌ 8 ቀን የጻድቁ አቡነ ኪሮስ ዕረፍት ነው

«የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው» ምሳ.10÷7፣18÷10፣28፣12 ጻድቃን የዚህን ዓለም ምቾትና ሀብት ንቀው በዱር በገደል ዳዋ ለብሰው ድንጋይ ተንተርሰው ድምጸ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ሳይፈሩ የቀኑን ሐሩር የሌሊቱን ቁር ታግሠው ረሀቡን ጥሙን ችለውና ሌት ከቀን በጸሎት በስግደት ተጠምደው ወንጌልንም ዞረው አስተምረው ተልዕኮአቸውን በመፈጸም ከዚህ ዓለም ድካም ያርፋሉ የጻድቃን ሞታቸው ዕረፍታቸው ነውና ኋላም ከፈጣሪያቸው ፊት አብረው እንደ ፀሐይ አብርተው እንደ ጨረቃ ደምቀው ይኖራሉ የተማፀናቸውንም ሁሉ በተሰጣቸው ቃል ኪዳን አማልደው የዘላለም ዕረፍት ያሰጣሉ «የጻድቅ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው» (መዝ. 115÷6) ከነዚህም ቅዱሳን ጻድቃን አንዱ አባ ኪሮስ ናቸው። የመጀመሪያው ስማቸው ዲላሶር ይባላል። በአባታቸው ሮማዊ በእናታቸው ሶርያዊ ሲሆኑ የነገሥታት ዘር እንደሆኑ የዘር ሐረግ ታሪካቸው ያረጋግጣል። አባታቸው ዮና እናታቸው አንሠራ ይባላል። አባትና እናታቸው መንግሥታቸውን ሀብታቸውን የሚወርስ ልጅ ባለመውለዳቸው እየአዘኑና እየጸለዩ ሲኖሩ በአንድ ጊዜ መንታ ልጆች ተወልደውላቸዋል የመጀመሪያ (ታላቁ) ቴዎዶስዮስ ሁለኛው (ታናሹን) ዲላሶር ብለው ጠርተዋቸዋል ጊዜ ሞታቸው ሲደርስ ሀብታቸውን ሁለቱ ልጆቹ እኩል እንዲካፈሉ ተናዝዘውላቸው ሞተዋል ቴዎዶስዮስ በአባቱ ምትክ ነግሦ ሲኖር አባ ኪሮስ ሕገ መንግሥትን እየተማሩ አድገዋል። አባ ኪሮስ የወላጆቻቸውን ሀብት እንዲያካፍላቸው ቴዎዶስዮስን በጥሞና ቢጠይቁት ፈቃደኛ አለመሆኑን አይተው ለዚህ ዓለም አላፊ ጠፊ ሀብት መጨቃጨቅን ጠልተው የማያልፈውን ሀብት ፍለጋ አገራቸውን ለቅቀው

በምናኔ ወደ ግብጽ አገር ሄደዋል በዚያም አንድ ተራራ ላይ እንዳሉ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ኪሮስ በማለት ጠርቶ አባ በብኑዳ ወደ ሚባል መነኩሴ እንዲሄዱ አመልክቶአቸዋል ወደ ተባለው ቦታ ሄደው እንደደረሱ አባ በብኑዳ ከሚኖሩበት ዋሻ ወጥተው በክብር ተቀብለዋቸዋል አባ በብኑዳም አባ ኪሮስን አመንኩሰ የብሉያትና የሐዲሳትን ትርጓሜ አስተምሮ ቅስናና ቁምስናን አሰጥቶ የእርሱን አርአያ እንዲከተሉ አድርጉ ዘወትር በሠርክ በመልአክ እጅ የሚላክለትን ሰማያዊ ህብስትና ጽዋዕ አብረው እየተመገቡ በጸሎትና በስግደት እግዚአብሔርን እያገለገሉ ለብዙ ዘመናት ኖረዋል ከዕለታት አንድ ቀን አንድ መነኩሴ የገዳም ልብስ ለብሶ በእንግድነት ወደ እሱ መጣ አባ በብኑዳም ተቀብሎ ከየት እንደመጣ ጠይቆ አሳድሮታል ይህም እንግዳ መነኩሴ በዋሻው ውስጥ ምግብ ማብሰያ ዕቃና ጥራጥሬም ባለማየቱ እንዴት እንደሚመገቡ ቢጠይቀው እግዚአብሔር እንዲሰጠን ብሎት ሦስቱም በአንድነት የሠርክ ጸሎት አድርገው እንደፈጸሙ መልአኩ እንደተለመደው ሕብስተ መና ጽዋአ ሕይወት አምጥቶላቸው ሲመገቡ ያ እንግዳ መነኩሴ አባ በብኑዳን በምትሀት እንዳስገኙት በመቁጠር ከምግቡ ቆርሶ በመጠምጠሚያው በመደበቅ ወደ መጣበት ገዳም ሄደ የገዳሙንም መነኰሳት በደወል ሰብስቦ የአባ በብኑዳን መሠርይነት ገልጾ ደብቆ ያመጣውን ህበስት ሲያሳያቸው መልአኩ ወርዶ በክንፉ አጣፍቶ መናውን ቀምቶ አርጓል። መነኰሳቱም ይህን አይተው በመደንገጥ የማይገባ ሥራ በመሥራቱ አዘኑ ከዚያም በኋላ የተቀደሰውን ሰማያዊ ህብስት ለማይገባው ውሻ በመስጠታቸው እግዚአብሔር ተቆጥቶ ከዚያ ቀን ጀምሮ አቋርጠባቸዋል ስለዚህ አባ ኪሮስ ምግባቸውን ወደ ጫካና ገደላገደል እየሄዱ ፍራፍሬና ሥራ ሥር እየለቀሙ በማምጣት እየተመገቡ የሚኖሩ ሆነዋል አንድ ቀን እንደተለመደው አባ ኪሮስ ምግብ ፍለጋ ሄደው ሲመለሱ «የጻድቃን ሥጋቸው ለዱር አራዊት ነው» በማለት ነቢዩ ዳዊት እንደተናገረው መዝ 78÷3 አባ በብኑዳን አንበሳ በልቶት የተረፈውን ሥጋ ተበታትኖ አገኙት አባ ኪሮስ ይህን ሲያዩ ምርር ብለው በማዘን የአባ በብኑዳን ሥጋ ለቅመው በዋሻው ውስጥ አስቀምጠው ወደ ፈጣሪያቸው

እያለቀሱ ከአንተ እውነተኛ ፍርድ እስካገኝ ድረስ እንዳልነግ በሕያው ስምህ እምላለሁ በማለት በግምባራቸው ተደፍተው በመሬት ላይ ተኙ በዚያም ምስጥ ወጣባቸው ጉንዳን ወረራቸው ዝናብና ፀሐይ እየተፈራረቁባቸው 40 ዘመን ሙሉ ሣር እስከሚበቅልባቸው ድረስ ቆይተዋል ከዚህ በኋላ ጌታ ተገልጦ መከራህን አይቻለሁ ጸሎትህንም ሰምቻለሁ አባትህ አባ በብኑዳ የታዘዘውን ረስቶ የተቀደሰውን ሰውሻ በመስጠቱ ይህ ሁሉ መከራ ደረሰባችሁ አሁንም ወዳጄ ሆይ ተነሥ በቃህ በማለት አሥነስቷቸዋል አባ ኪሮስ ከተነሡ በኋላ የኃጥኣንና የጻድቃንን ነፍስ ከሥጋቸው ተለይታ የት እንደምትገባ ተገልጸላቸው ገነትን እየዞሩ አይተዋል ወደ ዋሻው ተመልሰው በጸም በጸሎትና በስግደት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ሲኖሩ አንድ ቀን ሰይጣን ሰው መስሎ መጥቶ አሳድሩኝ አላቸው ርሳቸውም ከየት እንደመጣ ቢጠይቁት የመጣሁበት ምን ያደርግልሀል አሳድረኝ አልሁህ እንጂ ሲል በትዕቢት አነጋገር ስለመለሰላቸው ሰይጣን መሆኑን አውቀው ከዋሻው ውስጥ ራቅ ባለ አንድ ክፍል ውስጥ አስቀምጠው ቢጸልዩበት ዋሻው ተደርምሶ እንዳይወጣ ተደፍቶበት እየጮኸ « ኪሮስ ሆይ ሳልቀድምህ ቀደምከኝ እስከ መቼ ነው በዚህ ተዘግቶብኝ የምኖረው ቢል እስከ ምጻት ድረስ ብለውት እስከ አሁን በዚያው እየጮኸ ይኖራል አባ ኪሮስ በዋሻ ተወስነው መኖር ብቻ ሳይሆን በግብጽ አገር እየተዘዋወሩ ወንጌልን አስተምረዋል ብዙ አህዛብንም አሳምነው አጥምቀዋል። እንደገናም ወደ ዋሻቸው በመመለስ እንደቀድሞ ሀብስት ሰማያዊ እየወረደላቸው በጸሎት ተወስነው ኖረዋል። ከዚህም ሌላ አባ ኪሮስ በዚች ጽሑፍ ያልተካተተ ብዙ ተአምራትንና ተጋድሎን ፈጽመዋል። እግዚአብሔርም ብርታታቸውንና ቅድስናቸውን አይቶ ወዳጄ ኪሮስ ሆይ በስምህ የተራበ ያበላ የተጠማ ያጠጣ የታረዘ ያለበሰ ለቤተክርስቲያንህ መባዕ የሰጠ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት ይገባልሃል በማለት ቃል ኪዳን ሰጥቶአቸዋል የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል ከክፋ ነገርም አይፈራም በእግዚአብሔር ለመታመን ልቡ የፀና ነው መዝ.111፥7 ጊዜ ዕረፍታቸው ሲደርስ አባ ባውማ የተባለ መነኩሴ ታዝዘላቸው

ታሪካቸውን እየጠየቀ እግዚአብሔር ያመለከተውንም እየጨመረ ገድላቸውን ጽፎአል ከዚህም በኋላ ሥጋ ወደሙ ተቀብለው በ270 ዓመታቸው ሐምሌ 8 ቀን አርፈዋል። አባ ባውማም ከገነሟቸው በኋላ የታዘዙ መላእክት መጥተው የነበሩበትን ዋሻ ዘግተው አስከሬናቸውን ወስደው በደብር ቅዱስ አስቀምጠውታል። ይህም የዕረፍታቸው ቀን ቤተክርስቲያናቸው በታነፀበት ቦታ ሁሉ በታላቅ ድምቀት ሲከበር ይኖራል። የጻድቁ ረድኤትና በረከት በኛ ላይ ይደር። አሜን። ሁለተኛም ጎዳር 8 ቀን ኪሩቤል ይከበራሉ ታሪካቸውም ዘፍ.3፥24 ሕዝ.1፥ 5-28፣ 10፥ 10-21 ራእ.4፥ 6-9 2ሳሙ.22፥ 11 ይመልከቱ።

ምዕራፍ 9 ቁጥር 13

ህዳር 9 ቀን ቶማስ ዘመርዓስ

በዚህ ቀን የክርስቶስ ታጋይ ምሥክሩና ሐዋርያው የሆነ የመርዓስ ኤጴስ ቆጶስ ቅዱስ ቶማስ አረፈ። ይህንም አባት ትሩፋቱንና ገድሉን ሰው ተናግሮ ሊፈጽመው አይችልም። ርሱም በጾምና በጸሎት በስግደት በቀንና በሌሊትም በመትጋት ለድሆችና ለምስኪኖች በመራራት ተጠምዶ የሚኖር ነበር። ከዚህም በኋላ መርዓስ በሚባል ሀገር ኤጴስቆጶስ ይሆን ዘንድ የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መረጠው መንጋውንም እንደ ሐዋርያት ተጠንቅቆ ጠበቀ ከሐዲው ዲዮቅልጥያኖስ በነገሠ ጊዜ ክርስቲያኖችን ያሰቃያቸው ዘንድ ከመኳንንቶቹ አንዱ ወደዚያ ሀገር ሄደ እርሱም ቅዱስ ቶማስን ወደ እርሱ ያቀርቡት ዘንድ ጭፍሮቹን ላከ። እነርሱም እየደበደቡ በምድር ላይ እየጐተቱ ወሰዱት ደሙም እንደ ውኃ ፈሰሰ ከዚያም በኋላ መኰንኑ ቅዱስ ቶማስን ለአማልክት ስገድ አለው ቅዱሱም እንዲህ ብሎ መለሰለት ከሕያው ከእግዚአብሔር ልጅ ከጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ለርኩስ ጣዖታት አልሰግድም ለረከሱ ጣዖታት የሚሰግድ ሁሉ የተረገመ ነውና መኰንኑም ተቆጥቶ እጅግ የበዛና ዕፀብ ድንቅ የሆነ ሥቃይ አሰቃየው የነዳጅ ድፍድፍ አፍልተው በአፉና በአፍንጫው ጨመሩበት እንዲህም እያደረጉበት ለብዙ ዘመናት ኖረ። የእሊህ ከሃድያን ልባቸው እንደ

ድንጋይ የጸና ስለሆነ ቅዱስ ቶማስ ቶሎ እንዲሞት አልፈለጉም። ሌሎች ብዙ ሰዎችን ያስፈራሩአቸው ዘንድ የክብር ባለቤት ክርስቶስንም ይክዱት ዘንድ የስቃዩን ዘመን አስረዘሙ እንጂ ርሱ በክብር ባለቤት በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል የጸና ነውና ማሰቃየቱን ከሐድያን በተሣናቸው ጊዜ ስለ ስህተታቸው ይዘልፋቸው ስለነበር ስለዚህ በጨለማ ቦታ ጣሉት። በዚያም ሃያ ሁለት ዓመት ኖረ ከሐድያኑም በእየዓመቱ ወደርሱ ገብተው ከሕዋሳቱ አንዱን ይቆርጣሉ። በዚያም ቦታ አፍንጫውን ከንፈሮቹን ጆሮዎቹን እጆቹን እግሮቹን ቆረጡ። መንጋዎቹ ያረፈ መስሏቸው በእየዓመቱ መታሰቢያውን ሲያደርጉ ኖሩ ነገር ግን አንዲት ክርስቲያናዊት ሴት ሲጥሉት ስለአየችው ቦታውን ታውቅ ነበር። ርሷም በሌሊት ወደ እርሱ በመሄድ ትመግበዋለች ጻድቅ ቆስጠንጢኖስ እስከ ንገሠበትና የቀናች የክርስቶስን ሃይማኖት ክብር እስከገለጡ ድረስ እንዲህ ሲሰቃይ ኖረ እጅ እግር ባለመኖሩ ደቀመዛሙርቱ በቅርጫት አድርገው የሚጭኑበት ነጭና ጥቁር አህዮች ነበሩት አህዛብ ተመቅኝተው ሌሊት የሁለቱንም አንገት ቆረጡ በነጋም ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ሊጭኑት አህዮቹን ለማምጣት በሄዱ ጊዜ አንገታቸው ተቆርጦ ቢያገኙአቸው ለቶማስ ነገሩት ቶማስም የተቆረጠውን አያይዙት ብሎ ቢጸልይ የነጩ ከጥቁሩ የጥቁሩ ከነጩ ተያይዞ ተነስተዋል። ቶማስም በጉድጓድ በተጣለበት ወቅት ንጉሡ ክርስቶስን በመታመን የታሠሩ እስረኞችን ሁሉ በሀገሮች ሁሉ በወህኒ ቤት ያሉትን ሁሉ ይፈቷቸው ዘንድ አዘዘ ይህች ሴት ሄዳ ስለ ቅዱስ ቶማስ ከእርሱ የሆነውን ሁሉ 22 ዓመት ተጥሎ እንደነበር ለካህናቱ ነገረቻቸው በውስጡም ወደ የሚኖርበት ቦታ መራቻቸው እነርሱም አንስተው ተሸከሙት እየዘመሩና እያመሰገኑ ከቤተክርስቲያን አደረሱት በቤተመቅደሱም ፊት ለፊት በወንበሩ ላይ አስቀመጡት ምዕመናን ከእርሱ እየመጡ ይባረኩና የተቆረጡ ሕዋሳቶቹን ይስሙ ነበር ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም የከበሩ የሦስት መቶ አሥራ ስምንት ኤጲስ ቆጶሳት የአንድነት ጉባዔን በኒቂያ አገር በሰበሰበ ጊዜ ይህ የከበረ ቶማስ ከእሳቸው አንዱ ነው ንጉሡም ወደ እነርሱ ገብቶ ሰላምታ ሰጣቸውና ከእርሳቸው

ቡራኬ ተቀበለ የዚህ የቅዱስ ቶማስን ተጋድሎውን በነገሩት ጊዜ ወደ ርሱ ቀርቦ ሰገደለት ሐዋሳቱም ከተቆረጡበት ላይ ተሳልሞ አዝኖና እጅግም አድንቆ ሐዋሳቱን ዳሰሰው ፊቱንና እጆቹን አሻሸው ከሐዲ አርዮስንም ተከራክሮ ከረታ በኋላ አወገዘው ለይተውም ከወገኖቹ ጋር ከቤተክርስቲያን አሳደዱት ከዚያም በኋላ መንፈስ ቅዱስ እንደአስተማራቸውና እንደመራቸው የሃይማኖትን ትምህርት በአንደበታቸው ተናገሩ ሕግና ሥርዓትን ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍርድንም ሠሩ ታሪካቸውን መስከረም 21 ይመልከቱ ከዚያ በኋላ ቅዱስ ቶማስ ወደ መንበረ ሲመቱ ሄደ ካህናቱንና መንጋውን ሁሉ ሰብስቦ አነበበላቸው እነርሱም እንዳያስወጡት እንዲጠብቁት በመጠበቅም እንዲድኑ አዘዛቸው ጥቂት ዘመን ከኖረ በኋላ በሰላም በፍቅር አረፈ የሹመቱ ዘመን አርባ ዘመን / ዓመት/ ነው ዕረፍቱ ነሐሴ 24 ስንክ ይመልከቱ የዚህ ተጋዳይ አባት ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይኑር ለዘላለሙ አሜን ::

ምዕራፍ 10 ቁጥር 14

መጋቢት 10 ቀን መስቀል

በዚህ ዕለት የክብር ባለቤት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት የከበረ መስቀል የተገለጠበትና የተገኘበት ነው። የዚህ የከበረ ዕፀ መስቀል መገለጡና መገኘቱ ሁለት ጊዜ ሆኗል መጀመሪያ የጻድቁ የቆስጠንጢኖስ እናት በሆነችው ንግሥት ዕሌኒ እጅ ነው። ርሷ ለእግዚአብሔር ተስላ ነበርና ልጇ ቆስጠንጢኖስ ወደ ክርስትና ሃይማኖት በተመለሰ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች ከእርሷም ጋር ብዙ ሠራዊት ነበር ደርሳም ስለከበረ መስቀል መረመረች ቦታውንም የሚያስረዳት አላገኘችም የአይሁድ ወገን የሆነ ስሙ ኪራኮስ የሚባል አንድ ሽማግሌ መስቀሉ ያለበትን የጉልጉታ ኮረብታ አመለከታት ከዚያም አይሁድ ኮረብታውን ይቆፍሩ ዘንድ አዘዘቻቸው ቤቱን የሚጠርግ መቃብር ላይ እንዲጥል አዝዘው ነበርና ንግሥት ዕሌኒ እስከ ደረሰችበት ጊዜ ከሁለት መቶ ዓመት በላይ ጥራጊያቸውን

ሲጥሉበት ኖሩ ኮረብታማ ሆኖ አይሁድ በቆፈሩ ጊዜ በ326 ዓ.ም ሦስት መስቀሎች ተገለጡ ክርስቶስ የተሰቀለበት የቱ እንደሆነ አላወቁም የሞተ ሰው አግኝተው አመጡ አንዱንም መስቀል አምጥተው በሞተው ሰው ላይ አኖሩት አልተነሣም በሁለተኛውም አልተነሣም ከዚያ በኋላ ሦስተኛውን መስቀል አምጥተው በሙቱ ላይ አስቀመጡት ያን ጊዜ የሞተው ሰው ተነሣ ዕሌኒም የክርስቶስ መስቀል እንደሆነ አውቃ ሰገደችለት የክርስቲያን ወገኖች ሁሉ ሰገዱለት:: ለልጅዋ የላከችው ይህ መስቀል ነው የሚል በሌላ መጽሐፍ ይገኛል:: የቀረው ግን ግንዱ በውስጡ ተተክሎበት የነበረው ከእርሱ እኩሌታውን ከቅንዋቱ ጋር ወደ ልጇ የላከችው ነው:: ከዚያም በኋላ ሥርዓታቸውና የሕንፃቸው ነገር በመስከረም ወር በ17 ተጽፎ የሚገኝ ሲሆን አብያተ ክርስቲያናትንና የከበሩ ቦታዎችን አነፀች እሌኒን ሥን.ግን. 9 ይመል. ሁለተኛ ም በሮሙ ንጉሥ በሕርቃል ዘመን የሆነው ሲሆን የፋርስ ሰዎች በግብጽ ሀገር ሳሉ ወደ ሀገራቸው ሊመለሱ ወደዱ ከሹማምንቶችም አንዱ የጦር መኰንን ተነጥሎ ወደ ኢየሩሳሌም አልፎ ደረሰ ወደ ከበረ መስቀል ቤተክርስቲያንም ገባ በመስቀሉ ላይ ታላቅ ብርሃን ሲበራ አይቶ ሊያነሣው እጁን ዘረጋ እሳት ወጥታ እጁን አቃጠለችው ከክርስቲያን በቀር ማንም ሊነካው እንደማይችል የመስቀልን ክብር ነገሩት ከዚያም መስቀሉን ሁለት ዲያቆናት አሸክሞ ማርኮ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ከዚያም ንጉሥ ሕርቃል ሰምቶ እጅግ አዘነ ስለርሱም ምእመናን እንዲጾሙ አዝዞ ወደ ፋርስ ዘምቶ ወጋቸውና ብዙዎችን ገድሎ የከበረ ዕፀ መስቀሉንም ሁለት ዲያቆናትን አሸክሞ ማርኮ ወደ ሀገሩ ተመለሰ የዚህም መስቀል ሁለተኛ የተገለጠበት / የተገኘበት/ መጋቢት አሥር ነው:: ንጉሡም መስቀሉን ወደ ቁስጥንጥንያ ወሰደው የመስቀሉም ክብር በዓመት አምስት ጊዜ ነው:: ይህም ሦስቱ በዓለም ሁለቱ በኢትዮጵያ ናቸው:: በዓለ የሚከበሩት መስከረም 16 ቀን የደመራ በዓል (ቅዳሴ ቤቱ ለመስቀል) 1 ቍፋሮ የተጀመረበት መጋቢት 10 የተገኘበት ሲሆን በኢትዮጵያ ደግሞ መስከረም 10 አጼ መስቀል (ተቀጸል ጽጌ) ወደ አትዮጵያ የገባበት 21 ግሽ ደብረ ከርቤ የገባበት ናቸው:: የመስቀሉ በረከት ከእኛ ጋር ይሁን:: አሜን::

ምዕራፍ 11 ቍጥር 15 ኅዳር 11 ቀን

የቅድስት ድንግል ማርያም አባትና እናት ኢያቄምና ሐና

መዝ. 86÷1

ሐና ማለት ሐይማኖቷ የቀና ምግባሯ የአማረች የተከበረች መልከ መልካም ደምግባት ያላት ማለት ነው የቅድስት ሐና አባት ማጣት እናቷ ሄርሜላ ይባላሉ:: ልጅ ሳይወልዱ መካን ሆነው ይኖሩ ነበር:: ነገር ግን ልጅ እንዲሰጣቸው አዘውትረው ፈጣሪያቸውን ይለምኑ ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ስምኦን የሚባል ደግ ሰው ወደ ሄርሜላ ሄዶ ወይን በማህፀንሽ ገብታ ለምልማ አፍርታ ፍሬዋን ዓለሙ ሁሉ ሲመገበው አይቼአለሁና ደስ ይበልሽ ብሎ ነገራት ርሷም የእግዘብሔር ፈቃድ ይሁን ብላ የምሥራች ተቀበለችው ከዚያም በኋላ ማጣትና ሄርሜላ አንድ ሱባዔ ወደ እግዚአብሔር ተማማሉና በሱባዔአቸው መጨረሻ ላይ ሁለቱም አንድ ዓይነት ሕልም አዩ አንድ የደረቀ ወይራ ዛፍ ከቤታቸው አጥር ወድቆ የሚኖር ለምልሞ በ3 ክፍል አፍርቶ ለሁለቱ ሲሰጣቸው አዩ በዚህም ሲደነቁ ስልዋኖስ የሚባል ሽማግሌ ከጐረቤታቸው ይኖር ነበር ያ ሽማግሌ ስለእነርሱ ሕልም አይቶ ሊነግራቸው መጣና አልጋችሁ ለምልሞ አበባ ሲያብብ አበባውም ሲያፈራ ዛሬ ሌሊት በሕልም አይቼ ልነግራችሁ መጣሁ አላቸው እነርሱም አባታችን እንደቃልህ ይደረግልን ብለው በደስታ አነጋግረው በሰላም ሸኝተው ሰደዱት ከዚያም መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል ተገልጾ እግዚአብሔር ጸሎታችሁን ምጽዋታችሁን ተቀብሎ እንደምኞታችሁ የተባረከች ደግ ልጅ ከእናንተ እንድትወለድ ፈቃዱ ሆኖአል ብሎ ነገራቸው ወደ ሰማይም ሲያርግ ታያቸው ሄርሜላና ማጣት ይህንን አስደሳች ዜና ከመልአኩ በመስማታቸው ከፍ ያለ ምሥጋና ለፈጣሪያቸው አቀረቡ ወዲያውም ብዙ ሳይቆዩ በ5420 ዓመተ ዓለም ታህሣሥ 18 በዘመነ ማቴዎስ በዕለተ ስሉስ ሄርሜላ ፀነሰች መጽነሷም በዘመዶቿና በአካባቢው ተሠማ ማኑሄ የሚባል ጋኔን የሚጥለው ሰው ነበር አንድ ቀን ሄርሜላ ከቆመችበት አጠገብ ሄዶ ቆም ሳለ ጥላዋ ቢያርፍበት ዋይ ብሎ ጮኸና ወደቀ ጩኸቱን ሰምተው ሰዎች ቢጠይቁት በዚህች

ሲጥሉበት ኖሩ ክረብታማ ሆኖ አይሁድ በቆፈሩ ጊዜ በ326 ዓ.ም
ሦስት መስቀሎች ተገለጡ ክርስቶስ የተሰቀለበት የቱ እንደሆነ
አላወቁም የሞተ ሰው አግኙተው አመጡ አንዱንም መስቀል
አምጥተው በሞተው ሰው ላይ አኖሩት አልተነሣም በሁለተኛውም
አልተነሣም ከዚያ በኋላ ሦስተኛውን መስቀል አምጥተው በሙቱ ላይ
አስቀመጡት ያን ጊዜ የሞተው ሰው ተነሣ ዕሌኒም የክርስቶስ መስቀል
እንደሆነ አውቃ ሰገደችለት የክርስቲያን ወገኖች ሁሉ ሰገዱለት።
ለልጅዋ የላከችው ይህ መስቀል ነው የሚል በሌላ መጽሐፍ ይገኛል።
የቀረው ግን ግንዱ በውስጡ ተተክሎበት የነበረው ከእርሱ እኩሌታው
ከቅንዋቱ ጋር ወደ ልጇ የላከችው ነው። ከዚያም በኋላ ሥርዓታቸው
የሕንፃቸው ነገር በመስከረም ወር በ17 ተጽፎ የሚገኝ ሲሆን አብያ
ክርስቲያናትንና የከበሩ ቦታዎችን አነፀች እሊኒን ሥ.ግን. 9 ይመል. ሁለተ
ም በሮሙ ንጉሥ በሕርቃል ዘመን የሆነው ሲሆን የፋርስ ሰዎች በግብጽ ሀገ
ሳሉ ወደ ሀገራቸው ሊመለሱ ወደዱ ከሹማምንቶችም አንዱ የጦር መኮ
ተነጥሎ ወደ ኢየሩሳሌም አልፎ ደረሰ ወደ ከበረ መስቀል ቤተክርስቲያንም
በመስቀሉ ላይ ታላቅ ብርሃን ሲበራ አይቶ ሊያነሣው እጁን ዘረጋ እሳት ወጥ
እጁን አቃጠለችው ከክርስቲያን በቀር ማንም ሊነካው እንደማይችል የመስቀል
ክብር ነገሩት ከዚያም መስቀሉን ሁለት ዲያቆናት አሸክሞ ማርኮ ወደ ሀ
ተመለሰ ከዚያም ንጉሥ ሕርቃል ሰምቶ እጅግ አዘነ ስለርሱም ምእመ
እንዲጸሙ አዝዞ ወደ ፋርስ ዘምቶ ወጋቸውና ብዙዎችን ገድሎ የከበረ
መስቀሉንም ሁለት ዲያቆናትን አሸክሞ ማርኮ ወደ ሀገሩ ተመለሰ የዚህ
መስቀል ሁለተኛ የተገለጠበት / የተገኘበት/ መጋቢት አሥር ነው። ንጉሡ
መስቀሉን ወደ ቁስጥንጥንያ ወሰደው የመስቀሉም ክብር በዓመት አምስ
ጊዜ ነው። ይህም ሦስቱ በዓለም ሁለቱ በኢትዮጵያ ናቸው። በዓ
የሚከበሩት መስከረም 16 ቀን የደመራ በዓል (ቅዳሴ ቤቱ ለመስቀል)
ቍፋሮ የተጀመረበት መጋቢት 10 የተገኘበት ሲሆን በኢትዮጵያ ደ
መስከረም 10 አጼ መስቀል (ተቀጸል ጽጌ) ወደ አትዮጵያ የገባበት 21
ደብረ ከርቤ የገባበት ናቸው። የመስቀሉ በረከት ከእኛ ጋር ይሁን። አሜን።

ምዕራፍ 11 ቍጥር 15 ኀዳር 11 ቀን

የቅድስት ድንግል ማርያም አባትና እናት ኢያቄምና ሐና

መዝ. 86÷1

ሐና ማለት ሐይማኖታ የቀና ምግባሯ የአማረች የተከበረች መልከ መልካም ደምግባት ያላት ማለት ነው የቅድስት ሐና አባት ማጣት እናቷ ሄርሜላ ይባላሉ። ልጅ ሳይወልዱ መካን ሆነው ይኖሩ ነበር። ነገር ግን ልጅ እንዲሰጣቸው አዘውትረው ፈጣሪያቸውን ይለምኑ ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ስምኦን የሚባል ደግ ሰው ወደ ሄርሜላ ሄዶ ወይን በማህፀንሽ ገብታ ለምልማ አፍርታ ፍሬዋን ዓለሙ ሁሉ ሲመገበው አይቼአለሁና ደስ ይበልሽ ብሎ ነገራት ርሷም የእግዘብሔር ፈቃድ ይሁን ብላ የምሥራች ተቀበለችው ከዚያም በኋላ ማጣትና ሄርሜላ አንድ ሱባዔ ወደ እግዚአብሔር ተማማለሱና በሱባዔአቸው መጨረሻ ላይ ሁለቱም አንድ ዓይነት ሕልም አዩ አንድ የደረቀ ወይራ ዛፍ ከቤታቸው አጥር ወድቆ የሚኖር ለምልሞ በ3 ክፍል አፍርቶ ለሁለቱ ሲሰጣቸው አዩ በዚህም ሲደነቁ ስልዋኖስ የሚባል ሽማግሌ ከጉረቤታቸው ይኖር ነበር ያ ሽማግሌ ስለአነርሱ ሕልም አይቶ ሊነግራቸው መጣና አልጋችሁ ለምልሞ አበባ ሲያብብ አበባውም ሲያፈራ ዛሬ ሌሊት በሕልም አይቼ ልነግራችሁ መጣሁ አሳቸው እነርሱም አባታችን እንደቃልህ ይደረግልን ብለው በደስታ አነጋግረው በሰላም ሸኝተው ሰደዱት ከዚያም መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል ተገልጾ እግዚአብሔር ጸሎታችሁን ምጽዋታችሁን ተቀብሎ እንደምኞታችሁ የተባረከች ደግ ልጅ ከእናንተ እንድትወለድ ፈቃዱ ሆኖአል ብሎ ነገራቸው ወደ ሰማይም ሲያርግ ታያቸው ሄርሜላና ማጣት ይህንን አስደሳች ዜና ከመልአኩ በመስማታቸው ከፍ ያለ ምሥጋና ለፈጣሪያቸው አቀረቡ ወዲያውም ብዙ ሳይቆዩ በ5420 ዓመተ ዓለም ታህሣሥ 18 በዘመነ ማቴዎስ በዕለተ ሰሉስ ሄርሜላ ፀነሰች መጽነሷም በዘመዶቿና በአካባቢው ተሠማ ማኑሄ የሚባል ጋኔን የሚጥለው ሰው ነበር አንድ ቀን ሄርሜላ ከቆመችበት አጠገብ ሄዶ ቆም ሳለ ጥላዋ ቢያርፍበት ዋይ ብሎ ጮኸና ወደቀ ጩኸቱን ሰምተው ሰዎች ቢጠይቁት በዚህች

በሄርሜላ ማህፀን ያለች ሕፃን እንደ እሳት አቃጠለችኝና ወደቅሁ አሁንም በእርሷ አምላክ አምናለሁ ብሎ ሁለተኛ ከዚህ ሰው አልደርስም ብሎ ምሎ ሰው ሁሉ እያየው በጅንጀሮ መልክ ተመስሎ ከሰውዬው ተለይቶ እንደ አሞራ ሲበር ታየ ይህንንም የአዩ ሰዎች እጅግ በጣም ገረማቸው ከዚህች ሴት ከቶ እንደምን ያለ ፍጥረት ይወለድ ይሆን (ትወልድ ይሆን) እያሉ እያደነቁ የመውለጃዋን ጊዜ በናፍቆት ይጠብቁ ጀመር ዳግመኛም ልያ የምትባል ሴት በእየሩሳሌም የምትኖር በሆዷ የተጸነሰው ጽንስ ጋኔን እንዳወጣ ሰምታ እኔም ከዚህ በሽታዬ ብታድነኝ ብላ ወደ ሄርሜላ ሄደችና ሆዷን ዳስሳ በህመም የሚያሰቃያትን የሆዷን አጥንት እሽት እሽት ብታደርገው 4 ዓመት ሙሉ አጥንት ሆኖ የኖረው ጽንስ ወደ ሕያውነት ተለውጦ ተወለደ ይህም ሕፃን ታሪኩ ብዙ በሚል ሲጠራ እንደኖረ በገድለ ሐና ተጽፎአል በሄርሜላ ማህፀን የተፀነሰው ጽንስ ሴት ይሁን ወንድ እስኪሚወለድ ድረስ ያወቀ አልነበረም ከ9 ወር በኋላ በ5421 ዓመተ ዓለም በ9 ወር መስከረም 7 ቀን በዘመነ ማርቆስ በዕለተ ሐሙስ ሔርሜላ ሴት ልጅ ወለደች በዚህም ዕለት ወላጆቿ ከፍ ያለ በዓል አድርገዋል ዘመድ አዝማድ ጐረቤቶቻቸውን ወዳጆቻቸውን ሲቀበሉ ውለዋል ልዩ ልዩ ደዌ የያዛቸው ሄርሜላ የወለደችበትን መሬት እየዳሰሱ እየተቀቡ ከበሽታቸው ተፈውሰዋል በተወለደችበት በ8ኛው ቀን ሥርዓተ ግዝረት ሲፈፀም ስሟን ሐና ብለው ጠርተዋታል ሐናም ቀስ በቀስ አድጋ 7 ዓመት ሲሆናት ወላጆቿ ሕርማናስ ከተባለው መምህር የኦሪትን ትምህርት አንዲያስተምራት አስገቧት በሰባት ዓመቷ ሥርዓተ ኦሪትንና ሥርዓተ ረበናትን በጠቅላላው ቅዱሳት መጻሕፍትን ከእናት አባቷ ሕግ ጋር አጠናቃ ተማረች ቅድስት ሐና 15 ዓመት ሲሆናት ከቤተ ይሁዳ የቅስራን ልጅ ኢያቄምን አገባች ኢያቄምም እንደ ርሷ የተማረ ነበርና ሁለቱም እግዚአብሔር የሚወደውን በኦሪት የተጻፈውን ሕግ ሁሉ በሚገባ የሚጠብቁ ፈጣሪያቸውን የሚፈሩ ለድሃ የሚራሩ ፆምና ጸሎትን የሚያዘወትሩ ደጋግ ሰዎች ነበሩ ሀብታቸው ግን በመጠኑ ነበር እንጂ ብዙ ሀብት አልነበራቸውም በእንደዚህ ያለ ቅድስና ፈጣሪያቸውን እያገለገሉ ሲኖሩ ስማቸውን የሚያስጠራ ልጅ (የዓይን

ማረፊያ) አልነበራቸውም በዚህም የተነሳ እግዚአብሔርን ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ተስፋ በአለመቁረጥ በመዓልትም በሌሊትም እያለቀሱ ይለምኑት ጀመር እግዚአብሔር ግን የወዳጆቹን የሃይማኖት ጽንዓት ለመፈተን ልጅ እንዳይወልዱ ጸሎታቸውን የማይቀበል መስሎ ለብዙ ጊዜ የሐናን ማህፀን ዘጋ ከዕለታት አንድ ቀን ሐና ከጐረቤቷ አንዲት በዝሙት አዳሪ ሴት ነበረችና እህቴ ሆይ ቤተ እግዚአብሔር ደርሼ ልመጣ ነበር ግን ይህ ልብስ ያደፈ ነው ንፁህ ልብስ ባገኝ ያንን ልብስ ለብሼ ሄጀ እግዚአብሔርን ለምኜ እመጣ ነበር አለቻት ያችም ሴት ጐረቤት በእንዲህ ያለ ችግር ለመረዳዳት አሁንም ከእኔ ብዙ ልብስ ስላለ የፈለግሽውን ለብሰሽ መሄድ ትችያለሽ አለቻት ሐናም ነገሩ መልካም ነበር ነገር ግን ይህ ልብሽ በአስበ ደነስ የተሰበሰበ ስለሆነ ይህን ለብሶ ወደ ቤተ እግዚአብሔር መሄድ አይገባም እግዚአብሔር ንጽሐ ባህርይ ነው ንጹሕ ነገር ነው የሚወደው አለቻት ይህችም ሴት በጣም ታናደደችና ሐና እኔ ለአንቺ ልጅ በማጣትሽ አዝንልሽ ነበር ለካ በዚህ ክፋትሽ ነው እንደ እንጨት አድርቆ ያስቀረሽ ብላ ሰድባ ሰደደቻት ሐናም እያዘነች ያኑ የነበራትን ልብስ ለብሳ ሄዳ መሪር የሆነ ለቅሶ አልቅሳ ተማህጽኖዋንም አድርሳ ወደ ቤቷ ስትመለስ ርግብ ወልዳ ከልጆቿ ጋር ስትጫወት አይታ ጌታዬ ሆይ ለዚህች ፅዐዛን እንስሳ ልጅ ስትሰጥ እኔን ድንጋይ የአደረግህበት ምክንያት ለምን ነው እባክህ ፈጣሪዬ ለማንም መዘባበቻ አታድርገኝ ብላ ምርር ብላ እያለቀሰች ከቤቷ ገባች የገጠማትን ሁሉ ሰቧሏ ለኢያቄም ነገረችው በዚያችም ሌሊት ሁለቱ እንደተተከለ ምሰሶ ቆመው ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ አደሩ ጠዋት ሐና ኢያቄምን እስኪ ፈጣሪያችን ቢቀበለን መባእ ይዘን ስዕለት ተስለን እንመጣ ዘንድ ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሂድ አለችው ርሱም እሺ ብሎ መባቸውን ይዘው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄዱ ከዚያም ሲደርሱ መባቸውን ለዕቃ ቤት ጠባቂና ስዕለት ተቀባይ ለሮቤል አቀረቡ ሮቤልም እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ ውሰዱ ተዋለዱ ተብለው ከተመረቁት መካኖች ተለይተው የተረገሙ ስለሆኑ እናንተም መካኖች ናችሁና መባእችሁን አልቀበልም መልሳችሁ ውሰዱ አላቸው እነርሱም እያዘኑና እያለቀሱ ጌታችን ፈጣሪያችን ሆይ ለቅሶአችንን

ተመልክተህ ወንድ ልጅ የሰጠኸን እንደሆነ አርሶ ቆፍሮ እኛን ይርዳን አንልም ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋይ እንዲሆን እናደርጋለን ሴት ልጅም ብትሰጠን እንጨት ለቅማ ውሃ ቀድታ እንጀራ ጋግራ ወፍጮ ፈጭተ ታብላን ትርዳን አንልም ነገር ግን መጋረጃ በመፍተል መሶበወርቅ በመስፋት ቤተ እግዚአብሔር እንድታገለግል እናደርጋለን ብቻ ለዓይናችን ማረፊያ ለልባችን ተስፋ የሚሆን አንድ ልጅ ስጠን ብለው ተሳሉ::

ሐናና ኢያቄም ይህን የሕሊና ጸሎትና ብፅአት በቤተ እግዚአብሔር አድርገው ሲፈጽሙ ወደ ሊቀ ካህናት ዘካርያስ ሄደው መምህራችን አባታችን ሆይ እኛ መካኖች መሆናችንን አንተ ታውቃለህ ወደፊት ፈጣሪያችን ወንድም ሆነ ሴት ልጅ ቢሰጠን ተስለናል ይህን ስዕለታችንን እንዲፈጸምልን የመሰነባበቻ ቡራኬ አድርግልን ብለው ከእግሩ በታች ወደቁ ዘካርያስም እግዚአብሔር ጸሎታችሁን ይስማችሁ ስዕለታችሁንም ይፈጽምላችሁ ለቅሶና ሀዘናችሁንም ይመልከትላችሁ ብሎ በመጸለይ አሰናበታቸው ኢያቄምና ሐናም ወደ ቤታቸው ተመልሰው በያም በጸሎት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ጥቂት ጊዜ እንደቆዩ በ5483 ዓመተ ዓለም በዘመነ ማርቆስ በዕለተ እሁድ ነሐሴ 7 ቀን ሐና ከባሏ ከኢያቄም ፀነሰች ከ6 ወር በኋላ መጽነሷ ታወቀ ዘመዶቿ ወደ ርሷ እየመጡ ከአረጀች በኋላ በመጽነሷ ሆዷን እየዳሰሱ ይረዱ ነበርና ሐና ከዘመዶቿ ወገን በርሴባ የምትባል አንድ አይና አክስት ነበረቻት ሆዷን ዳስሳ አይኗን ብትነካው ደህና ሆኖላታል ይህን ዜና የሰሙ ዕውራን እንካሳን እንዲሁም በልዩ ልዩ ደዌ ተይዘው የሚሰቃዩ ሁሉ ማህፀኗን እየዳሰሱ የሚፈወሱ ሆነዋል 2ተኛም ሳሚናስ የሚባል የጦሊቅ ልጅ ከኤዶቅ አጉቱ ቤት ሄዶ ሞተ ዘመዶቹም ለመቅበር በአልጋ ላይ አድርገው ይዘውት ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሲጓዙ የሐና የአጐቷ ልጅ ነበርና በጣም ትወደው ስለነበር አስከሬኑ ያለበትን አልጋ እየዞረች ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ተነሥቶ ስብሐት ለኪ እሙ ለፀሐየ ጽድቅ ማርያም ሆይ ለአብ መርዓቱ ለወልድ ወላዲቱ ለመንፈስ ቅዱስ ጽርሐ ቤቱ ደስ ይበልሽ ብሎ ሰገደላት ቤተ አይሁድም ከዚያው ከለቅሶው ነበሩና ምነው ምን አይተህ ነው ለዚህች ሐና የሰገድከው አሉት ሳምናስም

እኔ የሰገድኩ ከዚህች ከሐና ማህፀን የምትወለደው ሕፃን ሰማይና ምድርን ባህርና የብሱን እመቀ እመቃትን አየረ አየራትን ወዘተ የፈጠረ እምላክን ትወልዳለች እያሉ መላእክት በሰማይ ሲያመሰግኗት ሰምቼ ነው እኔንም ያስነሳችኝ እርሷ ናት ብሎ መስክሮ ተመልሶ አርፎአል ይህም ድንግል ማርያም ከተወለደች በኋላ ብዙ ታምራት እንደምታደርግ የሚያመለክት ነው:: ጸላእያነ ሠናያት አይሁድ ይህን ሰምተው በማህፀን ሳለ እንዲህ የሚፈውስና ሙት የሚያሥነሣ በተወለደ ጊዜ ምን ታምር ይሠራ ይሆን ብለው በጣም ፈሩ ተንቀጠቀጡ ክፍርሃታቸውም የተነሣ ተሰበሰቡና በድንጋይ ወግረን በእሳት እናቃጥላቸው አቃጥለን እንግደላቸው ብለው ተማክረው ሳለ በመንፈቀ ሌሊት ቅዱስ ገብርኤል ወደ ሐናና ኢያቄም መጥቶ ተነሱና ተከተሉኝ ብሎ እየመራ ወደ አድባረ ሊባኖስ ወሰዳቸው በዚህም ተራራ በ5484 ዓመተ ዓለም ከዘጠኝ ወር በዘመነ ሉቃስ በዕለተ ስሉስ ግንቦት 1 ቀን ቅድስት ሐና እንደ ፀሐይ የምታበራ እንደ አንበሳ የምታስፈራ መልኳ በጣም የምታምር ልጅ ወለደች መኃ.6÷ 9 በዚህ ጊዜ ከአድባረ ሊባኖስ ጀምሮ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ብርሃን ታየ እስከ 7 ቀን ሙሉ ከዘመዶቻቸው ከወዳጆቻቸው ጋር በደስታ ሰነበቱ ሐና ከወለደችበት ቦታ ዙሪያ ለታምራት ከአራት ቦታ ላይ ውሃ ፈለቀ ሕፃኗ በተወለደች በ8 ቀኗ ስሟን ማርያም ብለው ሰየሟት ስለምን ማርያም አሏት ቢሉ በዚህ ዓለም ሰዎች ከሚመገቡት ምግብ ሁሉ ለአፍ የሚጥም ለልብ ደስ የሚያሰኝ ልብን የሚመስጥ ማር ነው በገነት የሚገኙ ጻድቃን ከሚመገቡት ምግብ ፈጻድቃን ቅዱሳን በጣም ደስ የሚያሰኛቸው በገነት ውስጥ በጣፋጭነት ብልጫ ያለው ያም የሚባል ምግብ ነው ስለዚህ ከሁሉ የበለጥሽ ነሽ ሲሉ ማርያም አሏት ሐናና ኢያቄምም ለቤተ እግዚአብሔርም የሚገባ መብዓ አዘጋጅተው ወስደው ቢያቀርቡ በፊት አንቀበላችሁም ሲሉ የነበሩ ሁሉ በክብርና በደስታ ተቀበሉአቸው ከዚያ በኋላ በተወለደች በሦስት ዓመቷ ድንግል ማርያምን ወስደው በዚያን ጊዜ የቤተ እግዚአብሔር ኃላፊ ለነበረው ለሊቀ ካህናቱ ለዘካርያስ አስረክበውታል በሥዕለት የተወለደች ናትና ልጇ ድንግል

ማርያም 7 ዓመት ሲኾናት ህዳር 11 ቀን ሐና አረፈች ኢያቄም ሚያዝያ ሰባት አርፏል ስንክ ይመ. ጸሎታቸውና በረከታቸው በኛ ላይ ይደር አሜን::

የቅዱስ ሚካኤል መቅድም

ሚካኤል ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሚ፣መኑ ፣ካ ከመ፣ ኤል አምላክ፣ መኑ ከመ አምላክ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው? ማለት ነው ኪ.ወ.ክ ገጽ 589

ቅዱስ ሚካኤል ዲያብሎስ በትዕቢት ፈጣሪነትን ሽቶ በዓለመ መላእክት ሁከት ባነሳ ጊዜ የቅዱሳን መላእክት ፍታውራሪ ሆኖ ዲያብሎስን የተዋጋ ጽኑዕ ኃያል መልአክ ነው« በሰማይም ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉት ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውም ከዚያም ወዲያ ከሰማይ ሥፍራ አልተገኘላቸውም» ራዕ 12÷7-8 ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ነው ይሁዳ በመልእክቱ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል በማለት ሊቀ መላዕክትነቱን ገልጾአል(ይሁዲ.9) ይህችውም ቅሩበ መንበር ተደርጉ የተፈጠረው ዲያብሎስ የተዋት ክብሩ ናት ቅዱስ ሚካኤል ይቅር የሚል ከመዓትም የራቀ ነው ሄኖክ 10÷12/ ለሰው ባደረገው በጐነት ለሕዝቡ ሁሉ ታዛዥ ነው::

(ሄኖክ 6÷5) ቅዱስ ሚካኤል ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚከራከር መልአክ ነው ዲያብሎስ የሙሴን መቃብር ለእሥራኤል አሣይቶ እምልኮተ ባዕድ እንዲፈጽሙ በማስተማር በተነሣ ጊዜ የተከራከረውና እስራኤላውያንን የጠበቃቸው ርሱ ነው(ይሁዳ9) እስራኤልን ከጠላቶቻቸው መንጋጋ በማውጣት ይራዳቸው የነበር ቅዱስ ሚካኤል ነው ዳን. 12÷1) ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ በማለት ነቢዩ ዳንኤል የገለጠው በባቢሎን ምርኮ የተራዳው ቅዱስ ሚካኤል ነው ዳን. 10÷13-21 እስራኤላውያንን የመራ ዘዳ. 14÷19 የኢያሪኮን ግንብ ያፈርሱ ዘንድ የተራዳ ኢያሱ 5÷14 እሥራኤል እግዚአብሔርን በበደሉና በተማረኩ ጊዜ ስለነርሱ ያማለደና ምሕረት ያሰጠ ዘካ. 1÷12 ኢያሱን የጠበቀ ስለርሱም የተከራከረ (ዘካ 3. ÷1) ለእስራኤል

ሕግ ሰጥቶ በሲና አብሮአቸው የነበረ (የሐዋ. 7÷38) ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነው:: የሶምሶንን መወለድ ለማኑሄ ያበሰረ መሳ.13÷ 15 እስራኤልን ሊያጠፋ የመጣውን 185000 የአሦራውያንን ሰራዊት የገደለ 2ነገ.19÷ 35-37 ሎጥን ከሰዶም ያወጣ ዘፍ.19÷ 1 በአምልኮተ እግዚአብሔር በመቆየቱ ምክንያት ወደ አንበሶች ጉድጓድ ሉተጣለው ለነቢዩ ዳንኤል ስንቅ አስይዞ ነቢዩ እንባቆምን እስከ ባቢሎን ያደርሰው ተረ.ዳን.13÷ 35-38 ሊቀመላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነው::

በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዕለተ ትንሣኤ የመቃብሩን ድንጋይ ገልብጦ ለመግደላዊት ማርያም የታየው (ማቴ 28÷2) ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን ከሄሮድስ አስር ቤት ያወጣው የሐዋ. 12÷7-11) በልቡ እግዚአብሔርን ይፈልግ ለነበረው ለጸሎተኛው ለመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ በዘጠኝ ሰዓት የተገለጠለት (የሐዋ 10÷3) ቅዱስ ሚካኤል ነው / ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የተወሰደ ትምህርት/

ስለዚህ አባቶቻችን የቤተ ክርስቲያን መምህራን የመላእክት አለቃ የከበረ የሚካኤልን በዓል መታሠቢያ በየወሩ በአሥራ ሁለት ቀን እንድናደርግ አዘውናል::

ምእራፍ 12 ቍጥር 16

ህዳር 12 ቀን የቅዱስ ሚካኤል በዓል ነው

አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በዚህ ዕለት የሰማይ ሠራዊትና የመላእክት አለቃ የሚሆን የከበረ መልአክ የቅዱስ ሚካኤል በዓለ ሢመት መታሰቢያ ነው በዚች ቀን ለሰው ወገን የሚያዝን መልአክ ሁል ጊዜ ከእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ቁሞ ለሰው ሁሉ የሚማልድ መልአክ ነው የነዌ ልጅ እያሱ በንጉሥ አምላል ክቡር ገናና ሆኖ ያየው ይህ ሚካኤል ነው:: በአየውም ጊዜ ከግርማው የተነሳ ደነገጠ በግምባሩም ከምድር ላይ ወድቆ ሰገደለት ጌታዬ ሆይ ከኛ ወገን ነህን? ወይስ ከጠላቶቻችን አለው ከሰማይ ሠራዊት ወገን ከአለቆች አንዱ እኔ ነኝ አለው ኢያ. 5÷14 በዚችም ቀን አማሌቅን በእጅህ አጥለዋለሁ በኢያሪኮም ላይ

አነግሥሃለሁ አለው ሰማዕታትንና ቅዱሳንን ገድላቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ የሚያጸናቸውና የሚያስታግሳቸው ይህ መልአክ ነው።

በዚህ መልአክ ስም በየወሩ በአስራ ሁለት ቀን የበዓል የምጽዋት መታሰቢያ እንዲደረግ ተወስኗል ስለ ምድር ፍሬ ስለ ዝናም መውረድ ስለ ወንዞች ውሃ ስለምሕረት ነፋሳት ከእግዚአብሔር በቀና በፍፁም ደስታ ያስፈጽማቸው ዘንድ እሱ እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ ይለምነዋልና። 2ኛም ቅዱስ ሚካኤል እስራኤልን ያወጣበት ሚያዝያ 12 ቢሆንም። ሲቃውንቱ ታሪኩ በዚህ ቀን እንዲነገር አድርገውታል እስራኤል በግብጽ 430 ዘመን ኑረዋል ዘፀ. 12÷40 በስደት ወደምድረ ግብጽ የወረዱትም 70 ነበሩ ዘፍ. 46÷1-27 እስራኤልን አለቅም ያለው ፈርዖን ዘጸ. 7÷3፣10÷1 ፣14÷4 ሮሜ 9÷17 መልአኩ ሚካኤል ፈርዖንና ሠራዊቱን ወደ ባህር እንዳሰጠመና እስራኤልን እንዳሻገረ ዘፀ. 14÷19 -ፍፃሜ እስራኤልን በመንገድ ይጠብቃቸው ነበር ዘፀ. 23÷20 መልአኩ ያማልድ ነበር ዘፀ. 33÷1-5 ዘካ. 1÷12 መዝ.33÷7

ቁጥር 17 ሰኔ 12 ቀን የባሕራን ታሪክ

በአንዲት አገር እግዚአብሔርን የሚፈሩ ባልና ሚስት ነበሩ በየወሩ የመላእክት አለቃ የከበረ መልአክ የሚካኤልን መታሰቢያ ያደርጉ ነበር ይልቁንም በሀዳር 12ና በሰኔ 12 በዓሉን ያከብሩ ነበር። በጉረቤታቸው ምሕረት የሌለው አንድ ክፋ ባለፀጋ እነዚህን እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ይጠላቸው ነበር የከበረ የሚካኤልን በዓል በአደረጉ ጊዜ ይዘብትባቸው ነበር። እግዚአብሔርን የሚፈራ የሴትዮይቱ ባለቤት ከዚህ ከኃላፊው ድካም ያርፍ ዘንድ የሚሞትበት በደረሰ ገዜ ሚስቱንም ቸር እንድትሆን የከበረ የመላእክት አለቃ የሚካኤልንም በዓል መታሰቢያ እንድታደርግ አዘዛት ይልቁንም በሀዳር በአሥራ ሁለት ቀን በሰኔ በአሥራ ሁለት ቀን ታደርግ ዘንድ አዘዛት ያ ሰው በአረፈበት ወራትም ሚስቱ ፀንሳ ነበር ከዚህም በኋላ ያ ሰው አረፈ ወደ መንግሥተ ሰማያትም ገባ ሚስቱ ለመውለድ ደርሳ ምጥ ያዛት መከራውም ፀናባት እንዲህም አለች የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ

ሚካኤል ሆይ እዘንልኝ ስለኔም እግዚአብሔርን ለምነው አሁን ከአለሁበት ከዚህ ጭንቅ ያድነኝ ዘንድ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ባለሟልነት አለህና ይህን በተናገረች ጊዜ ያለችበት ቤት ብርሃን ሆነ ያን ጊዜ ከጭንቀቷ ዳነች መልኩ ያማረ ወንድ ልጅም ወለደች የእግዚአብሔር መልአክ ሚካኤልም ከሰማይ ወርዶ የወለደችውን ሕፃን ባረከው እግዚአብሔር ይህ ብላቴና ምህረት የሌለው የዚህን ባለፀጋ ገንዘብ ሀብቱን ሁሉ እርሻውንም ይወርሳል ብሏል አለ። በዚህ ጊዜ ያ ባለፀጋ በዚች ሴት ቤት መስኮት በኩል ሆኖ ይመለከት ነበር ይህን በሰማ ጊዜ ኃዘን ደረሰበት ብላቴናውንም ይገድለው ዘንድ ምክንያት ይፈልግ ነበር ብላቴናውን ግን በመላእክት አለቃ በከበረ መልአክ በሚካኤል ልመና እግዚአብሔር ይጠብቀው ነበር። ዕድሜው አሥር ዓመት በሆነ ጊዜ የእናቱ ገንዘብ አለቀ ያ ርህራሔ የሌለው ባለፀጋ በዚያች ሴት ላይ ምክንያት ፈጥሮ ልጅሽን ስጭኝ ይላትና እኔ አበላዋለሁ እኔ አለብሰዋለሁ ለአንቺም ሐያ ወቄት ወርቅ እሰጥሻለሁ አላት ከባለፀጋው ይህን ነገር በሰማች ጊዜ ስለችግሯ ደስ አላት እሱም ሐያ ወቄት ወርቅ ሰጣት አሷም ልጇን ሰጠችው ያንንም ሕፃን በወሰደው ጊዜ ፈጽሞ ደስ አለው ባለፀጋውም የምፈልገው ተፈጸመልኝ አለ። ከዚህ በኋላ በብላቴናው ቁመት ልክ የእንጨት ሳጥን ሠርቶ ከውስጡ አግብቶ በላዩ ዘጋበት ሳጥኑንም ወስዶ ከባሕር ጣለው እንደዚሁ የሳጥኑን መክፈቻም ከባሕር ጣለው ። በእግዚአብሔርም ፈቃድ ያ ሳጥን በውሀው ላይ ይንሳፈፍ ነበር። ኒቆ ወደተባለውች ወደ አንዲት አገር ወደብ እስኪደርስ ድረስ በዚያች አገርም በግ የሚያረባ በባሕሩ አጠገብም በጉችን አሰማርቶ የሚጠብቅ አንድ ሰው ነበር ያን ሳጥንም ባየው ጊዜ አውጥቶ ወደ ቤቱ ወሰደው ሣጥኑን እንዴት እከፍተዋለሁ እያለ ያስብ ነበር ይህን ሲያስብ እግዚአብሔር በልቡናው ወደ በሕር ይሔድ ዘንድ ሃሳብ አሳደረበት ፈጥኖም ሔደ አንድ ሰውም ዓሣ ሲያጠምድ አገኘ በግ ጠባቂውም አለ ወጥመዱን (መረብህን) በኔ ስም ከባህር ጣለው ለተያዘውም ዓሣ ዋጋውን እሰጥሃለሁ አለው። እንደነገረውም መረቡን ጣለ ታላቅ ዓሣም ተያዘለት ለዚያ ሰውም ዋጋውን ሰጠና ዓሣውን ይዞ ወደቤቱ ሔደ በእሳቱ ጠብሶ ከቤተሰቡ ጋር ይበላው

ዘንድ ጠባው የዓሣውንም ሆድ በቀደደ ጊዜ በውስጡ መክፈቻ አገኘ። በልቡናውም ምናልባት ይህ መክፈቻ የዚህ ሣጥን ይሆን? ብሎ መክፈቻውን በሣጥኑ ቀዳዳ በአገባው ጊዜ ፈጥኖ ተከፈተ የበግ ጠባቂውም ፊጽሞ አደነቀ በሣጥኑ ውስጥም ያ ባለፀጋ ሊገድለው የወደደውን ብላቴና አገኘው ባየውም ጊዜ ተደሰተ። ከባሕር ስላገኘው ስሙን ባሕራን አለው በሱም ዘንድ እንደ ልጅ ሆነ ያ ባለጠጋ ከሚኖርበት አገርም የበግ ጠባቂው እስከሚኖርበት አገር የአሥር ቀን ጕዳና ይሆናል። ከብዙ ቀን በኋላ ርሕራኄ የሌለው ያ ባለፀጋ ንግድ ሊሔድ ወደደ መንገንዱም ያ የበግ ጠባቂ ከአለበት ቦታ ፀሐይ ሲገባ ደረሰ በግ ጠባቂውንም በአንተ ዘንድ የማድርበት ቦታ አለን ዋጋህንም እሰጥሃለሁ አለው የበግ ጠባቂውም ወደቤቱ አገባው ልጁንም ባሕራን ብሎ ሲጠራ ባለፀጋው ያን ስም በሰማ ጊዜ ጠባቂውን ልጅህ ነውን ብሎ ጠየቀው ጠባቂውም አዎን ልጄ ነው ይህንን ጕልማሳ ሕፃን ሳለ በሣጥን ውስጥ ከባሕር ላይ አግኝቼ እንደ ልጄ አድርጌዋለሁ ስለዚህም ስሙን ባሕራን አልኩት አለው። ባለፀጋውም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ በልቡናው እጅግ አዘነ ያ ልጅ እሱ ሊገድለው ወደባሕር የጣለው ብላቴና እንደሆነ አወቀ በነጋውም ያ ባለጠጋ ሰይጣናዊ ምክንያት ፈጥሮ የበግ ጠባቂውን ይህን ብላቴና ከዚህ አገር ወደ ቤቴ ልላከው ስጠኝ እነሆ ለአንተም ዋጋህን ሐያ ወቄት ወርቅ እሰጥሃለሁ በቤቴ አንድ ነገር ዘንግቼአለሁና አለው የበግ ጠባቂውም ስለ ገንዘቡ ደስ አለው ብላቴናውንም ጠርቶ ልጄ ባሕራን ና ይህ የከበረ ሰው ወደቤቱ ስለሥራ ሊልክህ ነው በደህና ትመለሳለህ አለው አባቴ ሆይ እሺ ያዘዝከኝን አደርጋለሁ አለው ያን ጊዜም ያ ባለጠጋ ደብዳቤ ጽፎ ወደ ሹሙ እንዲህ ብሎ ላከ ይህች ደብዳቤ በተነበበች ጊዜ ያመጣትን ስሙ ባሕራን የተባለውን ሰው ገድለህ ከጉድጓድ ጣለው ይህንንም ማንም ማን አይወቅ በዚች ደብዳቤ ውስጥም በመካከላቸው ያለውን ምልክት ጽፎ ደብዳቤውን አትሞ ለባሕራን ሰጠው ለመንገዱም ስንቅ ሰጠው ባህራንም ወደ ተላከበት ሔደ በጕዳና ሲሔድም በሱና በዚያች አገር መካከል የአንድ ቀን መንገድ እንደቀረው እነሆ የመላእክት አለቃ ክቡር መልአክ ሚካኤል በንጉሥ መልእዕክተኛ አምሳል በፈረስ ላይ ሆኖ ወደሱ መጥቶ እንዴት አደርክ የት

ትሔዳለህ ምን ይዘህል አለው ባሕራንም ከአንድ ባለጠጋ ሰው መልእክት ይዣለሁ ወደ ቤቱ ልኮኛል አለው የከበረ መልአክ ሚካኤልም ደብዳቤውን አሳየኝ አለው ባሕራንም ፈርቶ ደብዳቤውን ሰጠው መልአኩ ግን ደብዳቤውን እፍ ብሎ በውስጡ የተጻፈውን አጠፋው መዝ.90÷ 11 እኔ ባለጠጋው እገሌ ነኝ ይህን ደብዳቤ የያዘውን ሰው ወደናንተ ልኬዋለሁ እገሊት የምትባል ልጀን አጋቡት በቤት በእዳሪ ያለውን ገንዘቤን ሁሉ እኔ ሰጥቼዋለሁ በንግድ እኔ እቆያለሁና አትጠብቁኝ በገንዘቤ ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቼዋለሁና በቤቴ የወደደውን ያድርግ በኔና በእናንተ መካከል ምልክቱ ይህ ነው ብሎ አትሞ ሚካኤል ለባሕራን ሰጠው ከባለጠጋው ቤት ሔደህ ደብዳቤ ስጥ በጕዳናም እኔ እንዳገኘሁህ አትናገር እንዳይገልህ ይህን ደብዳቤ ለውጪዋለሁ አለው። ጌታዬ ሆይ እኔ ያዘዝከኝን አደርጋለሁ ብሎ ባሕራንም መንገዱን ሔደ ወደዚያች አገርም ደረሰ የዚያን የባለጠጋ ቤትም ጠየቀ ወደዚያም አደረሱት ደብዳቤውንም ለሹሙ ሰጠው። በአነበባትም ጊዜ በውስጧ ያለውን አስተዋለ ምልክቱም እውነት እንደሆነ አወቀ። ያን ጊዜም ለባሕራን ከባለጠጋው ልጅ ጋር ታላቅ ሠርግ ደስታ እያደረጉ ዓርባ ቀን ተቀመጡ ሠርጉ ከተፈፀመ በኋላ ያ ባለጠጋ ወደ አገሩ ተመለሰ የጨዋታና የደስታ ድምጽ በሰማ ጊዜ ይህ የምሰማው ምንድን ነው? ብሎ ጠየቀ ባሕራን በሚባል በአንድ ጕልማሳ እጅ ደብዳቤህ ስለደረሰ ልጅህንም እንዲያገባት ስለአዘዝክ ለሱ ሰጥተውታል እነሆ በመዓልትም በሌሊትም ተድላ ደስታ ሲያደርጉ ዓርብአ ቀን ነው ብለው ሰዎች ነገሩት። ገንዘብህን ቤትህን ወንዶችንና ሴቶች አገልጋዮችህን ንብረትህንም ሁሉ በደብዳቤህ እንደ አዘዝክ ሰጡት አሉት ያም ባለጠጋ ይህን ቃል በሰማ ጊዜ በታላቅ ቃል ጮሆ ከፈረሱ ላይ ወደቀና ወዲያውኑ ሞተ አጋንንትም ነፍሱን ተቀብለው ወደሲኦል አወረዱት ሚሰቱም የባሏን ሞት በሰማች ጊዜ ከደርብ ላይ ወድቃ በድንጋጤ ሞተች። ያም ባሕራን የተባለ ብላቴና በየወሩ በአሥራ ሁለት ቀን የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል መታሰቢያ እያደረገ ደስ ብሎት ኖረ ባሕራንም በመንገድ የታየው በደብዳቤውም ውስጥ የተጻፈውን አጥፍቶ ለውጦ የሕይወትን መልእክት የጻፈለት የመላእክት አለቃ ክቡር መልአክ

ሚካኤል እንደሆነ ተረዳ ከዚህም በኋላ በመላእክት አለቃ በከበረ መልአክ ሚካኤል ስም ያማረ ቤተክርስቲያን ሠራ በውስጧም ሥዕሉን አሳለ። በሱም ብዙ ድንቅ ድንቅ ተአምራት ታዬ የታመሙትም ዳኑ ባሕራንም በዚች ቤተ ክርስቲያን ላይ ቅስና ተሹሞ እስከ ዕለተ ሞቱ ለመላእክት አለቃ ለከበረ መልአክ ሚካኤል እያገለገለ ኖረ እሱም አባትና እናቱም ልጆቹም የዘለዓለም ሕይወትንና መንግሥተ ሰማያትን በመላእክት አለቃ በከበረ መልአክ በሚካኤል አማላጅነት ወረሱ በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል ምልጃና ልመና የምህረት አምላክ የሕይወት ተስፋ የሚሰጥ ለነዚህ ብቻ አይደለም መታሰቢያውን ለሚያደርጉ ሁሉ ነው እንጂ የመልአኩ ረድኤትና በረከት በሁላችን ላይ ይኑር። አሜን።

ምእራፍ 13 ቁጥር 18

ታኅሣሥ 13 ቀን ቅዱስ ሩፋኤል ቅዳሴ ቤቱ

ሩፋኤል /ዕብ./ /ሩፋ/ ፈውስ /ኤል/ አምላክ ዘሥዩም ዲቦ ፈውስ / በፈውስ ላይ የተሾመ/ማለት ነው ኩፋ 10÷7 መጽሐፈ ሄኖክም በሰው ቁስል የተሾመው ከከበሩ ከመላእክት አንዱ ሩፋኤል ነው ይላል (ሄኖክ 6÷3) እንዲሁም ሰዳዴ አጋንንት መሆኑንም ያስረዳል ሄኖክ 10÷8 / ጐርጐርዮስ ዘዐቢይ በዓለ መድኃኒት ዘእግዚአብሔር ብሎታል ፈታሔ ማህፀንም ይባላል እናቶች ሲወልዱ መከራ እንዳይበዛባቸው የሚራራ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቅዱስ ፋኑ ኤል አማላጅነትና ተራዳኢነት በሰፊው ተዘርዝሮ የምናገኘው በመጽሐፈ ጦቢት ነው ከጌታችን ልደት በፊት በ3ኛው መ/ክ/ዘ በተጻፈው በዚህ ጽሑፍ ላይ ጦቢት የተባለው በፋርስ የተማረከ ጽኑ እሥራኤላዊ ዕለተ ሞቱ በደረሰ ጊዜ በሜዶን አገር ገባኤ በተባለው ሰው እጅ ያስቀመጠውን ገንዘብ ለማምጣት ወደደ ይህንንም ለልጁ ለጦብያ ነገረውና ሊልከው አሰበ ከዚያም አገሩን አላውቀውም ስላለ አብሮህ የሚሄድ ሰው ፈልግ እኔም የድካሙን ዋጋ እከፍለዋለሁ አለው መልአኩ ሩፋኤልም ሰው ተመስሎ ለጦብያ ተገለጠለትና አብሮት ወደ ሜዶን ለመጓዝ ፈቃደኝነቱን ነገረው ጦቢትም አገሩንና ወገኑን ቢጠይቀው

የታላቅ ወንድምህ የአናንያ ዘመድ አዛርያ ነኝ አለው አዛርያ ማለት አግዚአብሔር ተራዳኢ ማለት ነው። ጦቢትም ከአዛርያ ጋር ዋጋ ተነጋግረው ስንቅ አስያዛቸውና ጦብያንና አዛርያን ላካቸው። አዛርያ በመንገድ ጦብያን ይረዳው ነበር። ጦብያ ከጤግሮስ ወንዝ ሲታጠብ ዓሣ ሊውጠው መጣ። ሳይፈራም ይዞ ሆዱን ቀዶ ጉበትና ሃሞቱን ወስዶ ከዕጣን ጋር አጨሰና በዓስማንድዮስ ሰይጣን ሰባት ወንድ የገደለች የራጉኤል ልጅ ሣራን አድኖ አግብቷል። ገንዘቡን ይዘው ሲመለሱም ለአባቱ ከዓሣ ሆድ የወጣ መድኃኒት / ጦቢት ታውሮ ስለነበር/ ለጦብያ ሰጠው ጦቢትም በዚያ መድኃኒት ታሽቶ ዓይኑ በራለት። ጦብያ ለአዛርያ ዋጋውን ካመጣው ገንዘብ ግማሹን እንዲወስድ ነገረው አዛርያም ጦብያና ጦቢትን ጠርቶ ሰማያዊ ምሥጢር ገልጦ አስተማራቸው መከራቸው መልአኩ ሩፋኤል መሆኑንም ገለጠላቸውና ወደ ሰማይ ዐረገ / መጽሐፈ ጦቢት 8÷1፣ 12÷15 ጳጉሜ 3 በዓለ ሲመቱ ነው ስንክ ይመልከቱ።

ቁጥር 19 ነሐሴ 13 ቀን ደብረ ታቦር

ደብረ ታቦር ማለት ደብር ተራራ ሲሆን ታቦር የቦታው ስም ነው ከኢያቦር ወገን የነበረ ቦር የሚባል ሰው ነበርና በሱ ስም ታቦር አሉት ታቦር ማለት ትልቅ ማለት ሲሆን ታን ጨምረው ታቦር ብለውታል በዚህ ተራራ ላይ ነቢያቱ ዲቦራ ከባርቅ ጋር በመሆን የከነዓናውያን ንጉሥና የጦር መሪ ሲሳራንና ኢያቡስን በጦርነት ድል አድርገውበታል ዲቦራ ማለት ንብ ማለት ሲሆን ነቢይቲቱም ከጦርነት ድል በኋላ መስዋዕት ሰውታበታለች መሳፍንት 4÷5-24።

ታቦር ከገሊላ ባሕር በስተምዕራብ ደቡባዊ በኩል የሚገኝ ተራራ ሲሆን ከ572 ሜትር በላይ ከፍታ ያለውና የዛፉ ሽታ ከተመረጠ ሽቶ ይልቅ መልካም መዓዛ ያለው ነው። ሳሙኤልም ትንቢት ተናግሮበታል ሳኦልም ከ3 ሰዎች ጋር በተራራው ላይ ተገኝቶበታል 1ኛ ሳሙ. 10:3 1ኛ ዜና. 6÷77 በዚህ በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 3ቱን ባለሟሎች ጴጥሮስንና የዘብዴዎስን ልጆች ዮሐንስንና ያዕቆብን ይዞ ወጥቶ

ብርሃነ መለኮቱን ገለጠ አንድነቱና ሦስትነቱ ተመሰከረ በጥምቀቱ ጊዜ የተነገረው የምወደውና የወለድኩት ልጄ ይህ ነውና እርሱን ስሙት የሚል ቃልም ተሰማ በአርሞንኤምና በታቦር ተራራ ላይ ያለው በረዶ እየሟሟ ወደ ዮርዳኖስ ባሕር ይገባል በስሙም ደስ ይላቸዋል መዝ. 88÷12 ዘዳ. 4 በዚህ ተራራ ላይ ድንቅ ነገር ከመሥራቱም ሌላ ታቦር በዛብሎን ዕጣ ውስጥ ያለ ለሚራራ ልጆች የተሰጠ ቦታ ሲሆን በተራራው ማማርና ውበት ጭምር እንደነበረ ነው ጴጥሮስም በዚህ ቦታ አንድ ዳስ ለአንተ አንድ ዳስ ለኤልያስ አንድ ለሙሴ ሠርተን እንኑር በማለት ተናገረ ማቴ.17÷1 ማር. 9÷2 ሉቃ. 9÷28። ታቦር ማለት በዕብራውያን ሲሆን ጌታ ብርሃነ መለኮቱን ለሐዋርያት በገለጠላቸው ጊዜ ብርሃኑ ከታቦር ተራራ አልፎ እስከ አርሞንኤም ተራራ ድረስ ገብቶአል ተራራው የወንጌል ምሳሌ ነው ወንጌል ሲማሯት ትከብዳለች ከተረዷትና ከተማሯት በኋላ ጽድቅና ኩነኔ አበጥራ ታሳያለች ተራራውም ሁሉንም እንደሚያሳይ ወንጌልም መንግሥተ ሰማያትንና ገሐነመ እሳትን አበጥራ ታሳያለች የተራራውም ስር የኦሪት ምሳሌ ሲሆን ኦሪት ሕግን ጠብቃ አበውን አሥነሥታ ትንቢት አናግራ ስትገዛ እስከ ክርስቶስ ደርሳለችና ወደ ተራራው 3ቱን ሐዋርያት ይዞ ሲወጣ ስምንቱንና ይሁዳን ከእግረ ደብር ትቶአቸው ወጥቶአል ብርሃነ መለኮት ሲገለጽ ለ8ቱም አብሮ ተገልጾላቸዋል ይሁዳ ግን ሳይገለጽለትና ሳይታደል ቀርቶአል ብርሃነ መለኮቱን በሌላ ቦታ ተራራ ያላደረገው አስቀድሞ በነቢዩ ዳዊት ያናገረውን ትንቢት ለመፈጸም ነው። በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ሙሴና ኤልያስ ይነጋገሩት የበረው ትንቢት ጴጥሮስ የሰማው ሙሴ ባሕሩን ብከፍል የእስራኤልን ጠላት ባጠፋ በደመና ብጋርዳቸው መና ባወርድላቸው ከክፋታቸው መመለስና እነሱን ማዳን አልቻልኩም ሲል ኤልያስም እኔ ሰማይን ብለጉም እሳትንም ባዘንብ ሙትንም ባሥነሣ እስራኤላውያንን ከክፋታቸው መመለስና ወደ ሕይወት ማስገባት አልቻልኩም በማለት ከጌታ ጋር ሲነጋገሩ ጴጥሮስ ሰምቶ ነበር በዚህ ቦታ ዳስ ሠርተን እንኑር ያለው ከዚህም ሌላ ሙቶ የነበረው ሙሴና በእሳት ሠረገላ ያረገው ኤልያስ

ሲጸልይ ታይተዋል። በዚህ ምክንያት ደብረ ታቦር በቤተክርስቲያን ትመሰላለች በዚች ደብረ ታቦር ላይ ብርሃን ተተክሎ ርእሰ አበው አብርሃምና ኖህ ቀስተ ደመና ተተክሎ አይተዋል በዚህም ኖህ አይቶ መካነ ብርሃን ብሎ ጠርቶታል።

1ኛ በነሐሴ 13 ቀን ብርሃነ መለኮቱ የተገለጠበት ዕለት በዓለ ደብረ ታቦር ይከበራል በዚህም ምክንያት መብራት ይበራል ጅራፍ ይጮሐል ቡሄ ዳቦ ይጋገራል እነዚህም ሁሉ ምሳሌ አላቸው መብራት የሚበራው 12፡ ለ13 ዋዜማ ሌሊት በዋዜማው ማታ በ3 ሰዓት ሲሆን ይህም የብርሃነ መለኮቱ ምሳሌ ነው። አንዳንዶቹ በ13 ለ14 ዋዜማ በዓሉ ከአለፈ በኋላ ያበራሉ ይህም ስህተት ነው መበራት ያለበት በዋዜማ ነው 2ኛ የቡሄው ታሪክ ደግሞ በአበው አነጋገርና ምሳሌ ቡሄ ማለት በአብራይስጡ ቋንቋ ቦሃ አበራ ማለት ሲሆን በአማርኛ ቡሄ የቦካ ማለት ነው ሊቃውንት በተለያየ መልኩ ይተርጉሙታል ይመስሉታል ይህ ዓይነቱ ሥርዓት መከበር የጀመረው በሀገራችን በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ነው 3ኛ በበዓለ ደብረ ታቦር ጊዜ ዳቦ እየተጋገረ ለልጆቹ ይሰጣል ይህም ምሳሌ አለው ብርሃነ መለኮቱ ከደብረ ታቦር ተራራ እስከ አርሞንኤም ተራራ ድረስ ሲያበራ ልጆች እረኞች ቀን መስሎአቸው እዚያው ስላመሹ ወላጆቻቸው ዳቦ ይዘው ሄደው ዳቦውን አድለው ነበር አንዳንዶቹ ሊቃውንት ደግሞ ሲመስሉት ጌታ ከደብረ ታቦር ከወረደና ሐዋርያትን ይዞ ወደ ከተማ ሲገባ ምግብ የቀረበለት እርሾ ያልበዛበት ዳቦ ስለነበረና ጌታም እያነሳ ለሐዋርያት ስለሰጣቸው ጌታን እንደ አባትና እናት ሐዋርያትን እንደ ልጆች ይመስሉታል። 4ኛ የአብነት / የቆሎ/ ተማሪዎች እየለመኑና ሰምነው ካገኙት ውስጥ በዓመቱ የደብረ ታቦርን በዓል በመደገስ ሰውን በመጋበዝ እንግዳ በመቀበል ያከብሩታል ይህም ምሳሌ አለው ለደቀ መዛሙርቶቹ ምስጢሩን የገለጠ ጌታ ለእኛም ምስጢሩንና ትምህርታችንን እንዲገልጥልን በማለት ሲሆን ጌታም ሦስቱን ባሰሚሉቹን ይዞ ከተራራው ሲወርድ ከተራራው ሥር ያሉት ደቀ መዛሙርት ግብዣ በመጋበዝ እየተደሰቱ ስላከበሩ የዚህ ምሳሌ ነው። ዛሬም የአብነት ተማሪዎች / የዜማ/ በመለመን ይደግሳሉ በአዲስ አበባ

ከተማም በአንዳንድ አድባራት እየተለመነ አስቀዳሹ ይጋበዛል ድሆችም ይጋበዛሉ ምሳሌው ይህ ነው 5ኛ ስለጅራፍ ጉዳይም አበው እንደሚመስሉት ጌታ በደመናው ውስጥ ሆኖ ድምፁን ስለአሰማ ልጆቹም ከብርሃኑ የተነሳ ቀን መስሎአቸው ስለነበር ድምፁን ስለሰሙ የዚያ ምሳሌ ሲሆን ከተራራው ላይ ያሉት ድምፅ ሲሰሙ ከተራራው ሥራ ያሉትም ተገልያላቸው ድምፁን ሰምተዋል በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔር ድምፅ ቃሉ ነጐድጓድ ስለሆነ ጅራፍ የዚህ ምሳሌ ነው እግዚአብሔር በሰማያት አንጐድጉዶ ይላልና መዝ. 17÷13 ዮሐ÷12፡19 በዚህ ደብረ ታቦር ተራራ ላይ ከነቢያት መርጦ ሙሴንና ኤልያስን ያመጣበት ምክንያት ሙሴ ፊትህን አሳየኝ ብሎት ነበርና ጌታም በኋላ ሥጋ ለብሼ መስዋዕት ሁኜ በደብረ ታቦር እገለጥልሃለሁ ብሎ ነገረው ዘፀ. 33÷18-25 ዘጉ. 12÷8 2ኛም ኤልያስን በኋላ ዘመን በደብረ ታቦር ምስክር ትሆነኛለህ ሚል. 4÷5 ባለው ቃል መሠረትና የፊልጶስ ግዛት በነበረችው በቂሳርያ እኔን ሰው ማን ይለኛል ብሎ ሐዋርያትን ሲጠይቃቸው ግማሾቹ ሙሴ ነህ የሚሉ አሉ ግማሾቹም ኤልያስ ነህ የሚሉ አሉ ብለው ስለአሉት ሙሴም ኤልያስም ያለመሆኑንና ይልቁንም አምላካቸው መሆኑን ለመግለጽ ነው ማቴ 16÷13 በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ብርሃነ መለኮቱን የገለጠው ነሐሴ 13 ቀን ነበር ከፃኙ ዐበይት በዓላትም አንዱ ነው ጌታ ብርሃነ መለኮቱን በገለጠ ጊዜ ግርማ መለኮቱ ስለአስፈራቸው ኤልያስም በመጣበት ሰረገላ ሲበር ሙሴም ደንግጦ ከመሬት ወደቀ (ተነጠፈ) በዚህም ጊዜ ቀድሞ ፊትህን አሳየኝ ይለው የነበረው ስለአቃጠለው የአንተን ፊት አይቼ እንደዚህ ከመሆን ለብዙ ሺህ ዘመናት ተኝቼበት የነበርኩት መቃብሬ ትሻለኛለች ብሎ ተናግሮ ወደ መቃብሩ ተመልሷል ዘዳ. 34÷4 የአብ ረድኤትና በረከት በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ምዕራፍ 14 ቁጥር 20

ጥቅምት 14 ቀን አቡነ አረጋዊ

በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በአክሱም ነግሦ በነበረው አፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት በነበረው ሊቅ በቅዱስ ያሬድ

አማካይነት ታሪክና በምሥራቅ ትግራይ ሀገረ ስብከት ጉሎ መካዳ ወረዳ ልዩ ስሙ መዝብር በሚባል ቦታ ስለሚገኘው የጥንታዊ ገዳም ደብረ ዳሞ አመሠራረት ይዘረዝራል። ወራቱን በምዕራፍ በመከፋፈል መሠረታዊ ታሪኩን እንዲህ እያለ ጀምሯል። እንጦንስ መቃርስን ወለደ መቃርስ ጳኩሚስን ወለደ ጳኩሚስ አባ አረጋዊን ወለደ በማለት የአስኬማና የቆብን ትውልድ ሐረግ ለአቡነ አረጋዊ ይገልፀዋል በሥጋ ትውልዱም ወላጅ አባቱ ከሮም ነገሥታት ዘር ሆኖ እናቱ አድና ወንድሞቹም ቴዎድሮስና ገብረ አምላክ እንደሆኑ ያስረዳል።

አቡነ አረጋዊ ገና በወጣትነቱ ከቤተመንግሥት ወጥቶ ከሮም ወደ ግሪክ ዳውናስ ወደ ተባለ የጽርዕ ገዳም በሄደ ጊዜ አቡነ ጳኩሚስ የተባለው የገዳሙ አበምኔት ተቀበለው በዚሁ ገዳም ውስጥም ቅዱሳት መጻሕፍትን ተማረ። በአቡነ ጳኩሚስ እጅም መነኮሰ ከ4 ዓመት ቆይታ በኋላ አቡነ ጽህማ ኻአንጸኪያ አቡነ ጉባ ከኪልቂያ አቡነ አፍጼ ከሮምያ አቡነ ጳንጠሌዎን ከሮምያ አቡነ አሌፍ ከቂሳርያ ተሰብስበው አቡነ ጳኩሚስና አቡነ አረጋዊ ወደ አሉበት ዳውናስ ገዳም መጥተው ሁሉም በአቡነ ጳኩሚስ እጅ ከመነኮሰ በኋላ በአንድነት ተቀመጡ አቡነ አረጋዊ ሌሎችም ሰባት መነኮሳት ጓደኞቹ በገዳመ ዳሞናስ ሲቀመጡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ እንደ አነበቡት ሁሉ እንዲህ የሚል ህልም አዩ ወካዕበ ሰምዑ ወረከቡ እመጻሕፍት ቅዱሳት ዘከመ ወህባ ኪዳነ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዝእትነት ማርያም ከመ ይኩንዋ አሥራተ ምድረ አዜብ እለ ይገብሩ ተዝካራ ወሕዝባኒ የዋሃን እሙንቱ ነገሥታቲሃ ርቱዓነ ሃይማኖት ውእቱሰ አቡነ አረጋዊ ምስለ ጕቱ አብያዊሁ ቦኡ ወሀደሩ በአሀቲ ሌሊት ሀበ ምድረ አክሱም በማለት ገድለ አረጋዊ ይገልፃል።

አቡነ አረጋዊ በመንፈሰ እግዚአብሔር ተመስጦ ያያትን ቅድስት ኢትዮጵያን አልአሜዳ በነገሠ በስምንተኛው ዓመት መሆኑን ይገልጻል ስምንቱ ቅዱሳን በአክሱም ለብዙ ጊዜያት ከተቀመጡ በኋላ አቡነ ገሪማ /ይስሐቅ/ ዘደብረ መደራ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ መልእክት ልኮባቸው ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ተሸክሞ እንዳመጣቸው በገድለ አረጋዊም ሆነ

በገድለ አባ ገሪማ ተገልጿል ተሰዓቱ ቅዱሳን አልአሜዳ ከሞተ በኋላ ታዜና የተባለው የአፄ ካሌብ አባት እስከነገሠበት ጊዜ ድረስ አጠቃላይ ለ12 ዓመታት በአቡነ አረጋዊ ቃለ ማህበርነት በአክሱም ከተማ ቤተቀጢን ከተባለ ቦታ በአሁኑ ወቅት ከዳዕሮ ኤላ በስተሰሜን ምዕራብ በሚገኝ ስፍራ በህብረት ተቀምጠዋል። ተሰዓቱ ቅዱሳን በቤተቀጢን በአንድ ቦታ በህብረት መቀመጡ አግባብ እንዳልሆነ ከተመካከሩ በኋላ የየራሳቸውን ገዳም መሥርተው መቀመጥና በሀገሪቱ እየተዘዋወሩ ወንጌል መንግሥትን በመስበክ ማስተማርና አብያተክርስቲያናትን ማነጽ እንደሚገባቸው ተስማሙ እግዚአበሐር ወደየመራቸው ቦታም ተሰማሩ እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ጥንታውያን ቅዱሳት ገዳማት የሚባሉትን ታላላቅ ገዳማት መሠረቱ እነሱም አባ ሊቃኖስ በደብረ ቈናጽል አባ ጰንጠሌዎን በደብረ ጸማዕት አባ ገሪማ በደብረ መደራ አባ ጽሕማ በፀድያ አባ አፍፃ በየሐ አባ አሌፍ በብሕዛ አባ አረጋዊ በደብረ ዳሞ አባ ይምዓታ በገረዓልታ አባ ጉባ በጠቀራ ናቸው። ደተሰዓቱ ቅዱሳን ገዳማት ስርጭትና አመሠራረት ከላይ እንደተገለጸው መሆኑን ከተረዳን ወደዋናው ርዕሳችን የአቡነ አረጋዊ ገዳም ደብረ ዳሞ አመሠራረት ታሪክ እንመለሳለን አቡነ አረጋዊ የረማትን መንደር ደብረ መድኃኒትን ለቆ ወደ ደብረ ዳሞ አቅጣጫ ተመለከተ ገና በሩቅ አምባዋን እንዳያት ሦስት ጊዜ ሰገደና ወደዚያው ጉዞውን ቀጠለ በመንገድ ላይ አንድ የወይራ ዛፍ አግኝቶ በሥርዋ ዕረፍት አደረገ በዚያች የወይራ ዛፍ ሥር በዕረፍት ላይ እንዳለ ጋኔን የያዘው በሽተኛ ቀርቦለት በጸሎት ፈወሰው ይህች ፈውስ ያደረገባት ቦታ አውላአ ማሕበር ተብላ ትጠራለች እስከ ዛሬ ድረስ ወደ ደብረ ዳሞ የሚሄዱ መናንያንና ሌሎች ምእመናን በዚች ቅድስት ቦታ ዕረፍት አድርገው አቡነ ዘበሰማያት ደግመው ድካማቸውን ካሳለፉ በኋላ ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ።

አቡነ አረጋዊ አውላዓ ማህበር በተባለች ቅድስት ቦታ በሽተኛውን ከፈወሰ በኋላ ወደ ደብረ ዳሞ ሲገሰግስ ከአንድ ትልቅ ወንዝ ደረሰ። ያወንዝ አጠገብ አንድ በሽተኛ ሰው አጋጥሞት በፀሎት ከፈወሰ በኋላ ርሱም በወንዙ ውሃ ሰውነቱን ታጥቦ ከዛረ ጀምሮ ይህ ወንዝ ለህሙማን ፈውስ ይሁን

በማለት ወንዙን ባረከው ወንዙን ተሻግሮ አቀበቱን ሲይዝ ምስጉግ ከተባለች ነጭ አለት ደረሰ። የሰበሰውን አጽፍ በዓለቱ ላይ ዘርግቶ ቢቀመጥበት ለተአምር ይሆን ዘንድ አጽፉ ከዐለቱ ላይ ተጣብቆ ድንጋይ ሆኖ ስለቀረ እስከ ዛሬ ድረስ ይታያል። አቡነ አረጋዊ ምስጉግ ከተባለው ዐለት ላይ አጽፉን ትቶ ለመጨረሻ ጊዜ ማረፊያ እንድትሆነው ወደሚመኘው ቦታ ወደ ደብረ ዳሞ አምባ ግርጌ ተጠጋ ወደ አምባው ለመውጣት ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ እየተዘዋወረ ቢመለከት ዙሪያው ገደል ሆነበት ወደዚያ ገዳም ለመውጣት የማይቻል መሆኑን ተገንዝቦ ተስፋ በመቁረጥ ከዳሞ ተራራ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ገጽ ወደ አለችው ስቁራ በተባለችው አምባ አደረ። በአምባውም ላይ አራቱን አንድ እንጀራ አቅርቦ ቢበላ አላጠግብ አለው ይህችስ በረከተ እግዚአብሔር የተለያት አምባ ስለሆነች ክፍሌ አይደለችም ብሎ ወደ ሌላይቱ ምንግርጋር ወደተባለች አምባ ሄደ አቡነ አረጋዊ በዚች አምባም ቀን ሲጸልይ ውሎ ማታ አንድ እንጀራ ባርኮ ቢበላ አላጠግብ አለው ይህችም አምባ በረከት የተለያት ናት አለና የዘለቄታ ክፍሉ እንዳልሆነች ተረድቶ ሙሐዝ ወደ ተባለች አምባ ሄዶ ተቀመጠ እየጸለየና እየሰገደ ላለ ቅድስት አድና የተባለች እናቱ ልትጠይቀው ስለመጣች አምባ በዓተለም ብለው ሰየሙዋት።

አቡነ አረጋዊ በእነዚህ አምባዎች ለዘለዓለም መታሰቢያ የሚወጣ ገዳም ለመመሥረት እንዳልተፈቀደለት ተረዳ እንደገና ወደ ዚያች መውጪያ ያጣባት አምባ ወደ ደብረ ዳሞ ተመልሶ ሄደ እግረ ህብል ተብሎ ከሚታወቀው ቦታ ላይም ሦስት ቀንና ሌሊት እየጸለየና እየሰገደ ምህላ እያደረሰ ተቀመጠ። እግዚአብሔር ልመናውን ሰምቶለት መልአኩ ሚካኤል ተገልጾ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሆይ በዚህ ቦታ ምን ያስጨንቅሃል አለው አቡነ አረጋዊም እንደመላእክት ክንፍ አልተሰጠኝ እንደ ሐዋርያት በደመና አላርግ አለ መልአኩም መልሶ ወደዚች ተራራ ታርግ ዘንድ ሥልጣን ተሰጥቶሃልና ለጥቂት ጊዜ አረፍ በል ከጥቂት ጊዜያት በኋላም በህብል ምትክ ወደ ተራራው የሚያወጣህ ዘንዶ እግዚአብሔር ይልክልሃል ብሎት ተሰወረ።

አቡነ አረጋዊ መልአኩ የሰጠውን ተስፋ በጸሎትና በምሕላ እየተጠባበቀ እስከ ሁለት ሳምንት ድረስ በእግረ ሀብል ሰነበተ በሁለት ሰባት መፈጸሚያ ቀን ላይ ያ የታዘዘው ዘንዶ በገደሉ መሐል ጭራውን ወደታች አንዥርግጐ መጣ ወዲያውኑ መልአኩ ሚካኤል ተገልጾ ይህ ነውና የታዘዘልህ ያለምንም ፍርሃት ወደ እርሱ ተጠጋ አለው። አቡነ አረጋዊም ዘንዶውን ባየ ጊዜ ጭራህን ላክልኝ ብሎ ጭራውን ያዘ ዘንዶውም አቡነ አረጋዊን ወደአንባው ወንጭፎ ሜዳው ላይ ጣለው መዝ. ፺፫÷13። አቡነ አረጋዊም በብዙ ጸሎት ሱባዔና ምህላ የወጣበትን አምባ ባየ ጊዜ እጅግ ደስ አለው። ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ብሎ ፈጣሪውን አመሰገነ ገዳሙም ደብረ ሃሌ ሉያ ተብሎ ተጠራ። አቡነ አረጋዊ በሌሎች አምባዎች አንድ ሙሉ እንጀራ አላጠገብ ብሎት የደብረ ዳሞ ግን ግማሽ እንጀራ ጨርሶ ለመብላት አቃተው በዚህ የተነሣ ቦታው በረድኤት የተመላ አምባና የዘለዓለም ቤት በመሆኑ ተረድቶ ሃሌ ሉያ ብሎ አመሰገነ። አቡነ አረጋዊ በአምባው ላይ ከወጣ በኋላ በስተምስራቅ አቅጣጫ የምትገኝ አንዲት ዋሻ ፈልጐ አገኘ። ዋሻው በአሁኑ ሰዓት የአቡነ አረጋዊ ዋሻ ተብላ ትጠራለች በዚህች ወሻ ውስጥ ከቢተቀጢን ሲመጣ ይዟቸው ያመጣውን ንዋያተቅዱሳት የወርቅ ጻሕል የብር ጽዋዕ የሐር አልባሳት የወርቅ መሶብ ሁሉ ከታቦተ ማርያም ጋር አስቀመጣቸው። ውሎ አድሮም ከአምባው ከነበረው ዛፍ ቅጠል እየቆረጠ ትንሽ አዲስ ቤተክርስቲያን በመሥራት ታቦተ ማርያምን አስገባበት። ከዚያም በደብረ ዳሞ አምባ ትንሽ የዳስ ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ በዚያው እግዚአብሔርን እያመሰገነ ይኖር ጀመር በዘመኑ የአክሱም ንጉሥ አፄ ካሌብ ነበር። በዚያም ዘመን በየመን ይኖሩ የነበሩትን ክርስቲያኖች በፊንሐስ የሚመሩ ይሁዳውያንና ሌሎች አረማውያን ተባብረው እየጨፈጨፏቸው መሆኑን የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጢሞቴዎስ ወደ አፄ ካሌብ ንጉሠ አክሱም መልዕክት ላከበት በየመን ያሉ ክርስቲያን ወገኖቹንም ከጦር ኃይል እንዲታደጓቸው አሳሰበው። አፄ ካሌብም የሊቀጳጳሱን መልእክት ተቀብሎ ጦር ሠራዊቱን አደራጅቶ ወደ የመን ለመዝመት ተዘጋጀ። ወደ አቡነ አረጋዊም ዘንድ አባቴ ሆይ

አህዛብንና አይሁድን ልወጋ ወደ የመን መዝመቴ ነውና በጸሎትህ አትርሳኝ ብሎ መልእክተኛ ላከበት አቡነ አረጋዊም በበኩሉ እግዚአብሔር ግርማ መገለጥንና ኃይለ መዊዕን ሰጥቶ ጠላቶችህን በእጅህ ይጣልልህ በሰላም ግባ ብሎ መርቆና ባርኮ ላከው። አፄ ካሌብ በየመን የነበሩትን አይሁዳውያንና አህዛብ አሸንፎ ክርስቲያኖችን ነፃ በማውጣት ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ ተመለሰ ከዚያም በኋላ ወደ አቡነ ጰንጠሌዎን ገዳም ገብቶ በመመንኮስ መንግሥቱን ለልጁ ለአፄ ገብረ መስቀል አወረሰ። አፄ ገብረ መስቀልም በነገሠ ጊዜ አቡነ አረጋዊ ወዳለበት ደብረ ዳሞ ገዳም ሄዶ ቡራኬና ምርቃት ከተቀበለ በኋላ አባቴ ሆይ አዲስ ቤተክርስቲያን የምሠራበት ቦታ የት እንደሆነ አመላክተኝ በማለት ጠየቀው አባታችን አቡነ አረጋዊም እስከ ዘመናችን ድረስ የዘለቀው ቤተክርስቲያን የታነጸበትን ቦታ አመላከተውና እጅግ በጣም ውብ በሆነ የዘመነ አክሱም ግብረ ሕንጻ አዲሲቱ ቤተክርስቲያን ታነጸች አፄ ገ/መስቀል የደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያንን አሳንጾ ከጨረሰ በኋላ በአልባሳትና በንዋያተ ቅድሳት አደራጀ ወደ አክሱም ቤተመንግሥቱ ሲመለስም የሕንፃውን መሣሪያ ቁሳቁሶች ለማጓጓዝ ተብሎ የተገነባውን የአምባው መወጣጫ ደረጃ ላፍርሰው ወይንስ እንደ አለ ይሁን? ብሎ ጠየቀው አባታችንም መወጣጫ ደረጃውን አፍርሰው «ዳህምሞ» በእርሱ ምትክ ግን ለትውልደትውልድ መታሰቢያ የሚሆን መወጣጫ ሀብል አድርግልኝ በማለት ለንጉሡ መለሰለት ንጉሡም ጻድቁ በጠየቀው መሠረት የሠራውን ደረጃ አፍርሶ ሰዎች እየተንጠለጠሉ የሚወጡበት ሀብል አበጅቶ ወደ አክሱም ተመለሰ በዚህ ምክንያት ደብረ ዳሞ ተባለ። በእንዲህ ያለ ሁኔታ የታነፀው የደብረ ዳሞ አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን ዙሪያው ገደል የሆነውን አምባ ጋሻ መከታ አድርጐ ለአንድ ሺ አራት መቶ ዘመናት ቅርፁና ይዘቱ ሳይለወጥ የመቃጠልና የመፍረስ አደጋ ሳያጋጥመው በዘመናችን ሳይቀር በግብረ ሕንፃ ሥራውና በውስጣዊ ሥነ-ጥበባዊ ይዘቱ ተመሳሳይና ተወዳዳሪ ሳይገኝለት ከመላ ዓለም የተውጣጡ ሀገር ጐብኚዎች በአንክሮና በአድናቆት ሲጐበኙት ይኖራሉ። ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ይህችን አዲስ ቤተክርስቲያን ለመሳለምና በመንፈሳዊ ዝማሬ ፈጣሪውን ለማመስገን

ሲል ከአክሱም ተነሥቶ ወደ ደብረ ዳሞ ገሰገሰ በደብረ ዳሞ ተራራ ግርጌ ካለው ወንዝ ሲደርስ ማትያስና ዮሴፍ የተባሉትን የአቡነ አረጋዊ ቀደመዛሙርት በወንዙ ዳር ተቀምጠው ዓሣ ሲያጠምዱ አገኛቸው ገና በቤተ ቀጢን አክሱም እያሉ ያውቃቸው ነበር። « ዳህንኑ ዝዝኩ አረጋዊ አቡክሙ. ብሎ ቢጠይቃቸው « ደሕና ነው» ብለው መለሱለት በዚህ ታሪክ የተነሳ የወንዙ መሻገሪየ እስከ ዛሬ ድረስ ዳህንኑ እየተባለ ይጠራል ቅዱስ ያሬድ ወደ ደብረ ዳሞ ወጥቶ ከአቡነ አረጋዊ ጋር ከተገናኙ በኋላ አዲስቷን ቤተክርስቲያን አይቶና አድንቆ በጥኡም ዜማው እንዲህ ሲል አወደሳት« ይሔውፅዋ መላእክት እለ በሰማያት እስመ ማህደረ መለኮት ይዕቲ ኦድክዋ ኦድክዋ ወርኢኩ ሥነ ህንፃሃ ለቅድስት ቤተክርስቲያን» አቡነ አረጋዊ በደብረ ዳሞ አምባ መጀመሪያ በዳስ በኋላም አፄ ገብረ መስቀል ቤተክርስቲያን አሳንጸለት ሲቀመጥ ከአራቱ መዓዝናተ ኢትዮጵያ የታመሙ በሽተኞች ለመፈወስ የመነኑ መነኮሳት ቆብና አስኬማ ለመቀበል ወጣት ኢትዮጵያውያን ትምህርትና ዕውቀት ለመቅሰም በየጊዜው ይጉርፉ ነበር መነኮሳቱም ቁጥራቸው 6000 ደረሱ። መጋቢ በመሾምና ለእያንዳንዱ መነኩሴ የሥራ ድርሻ በመስጠት ምግብ የሚያበስሉ እንጨት የሚሰብሩ ውሃ የሚቀዱ ጥራጥሬ የሚፈጩ አትክልት የሚተክሉ አዝርዕት የሚዘሩ ብሉያትንና ሐዲሳትን የሚያስተምሩ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚጽፉና የሚጠርዙ ማህደረ መጻሕፍት የሚሰሩና የሚደጉሱ አስኬማና ቅናተ ዮሐንስ የሚሠሩ መነኮሳት በየሙያቸውና በየችሎታቸው መድቦና ደልድሎ በሕግና በሥርዓት የሚመራ ገዳም አደረገው አቡነ አረጋዊ የደብረ ዳሞን ገዳም መሥርቶ በነገሥታቱ ረዳትነት የሚያስፈልገውን እየረዱት በቅድስት ድንግል ማርያም ስም አዲስ ቤተክርስቲያን አሳንፆና ማህበረ መነኮሳቱን በሚገባ አደራጅቶ ከፈፀመ በኋላ ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሲሞላው እለተ ህልፈቱ መድረሱን አወቀ ደቀ መዛሙርቱን ሁሉ ሰብስቦ እኔ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ መሄዴ ነውና በእኔ ምትክ ማትያስ አባት ይሁናችሁ ካላቸው በኋላ ከረፋዱ በሦስት ሰዓት ወደ አንድ ዋሻ ሄዶ ለዘለዓለሙ ተሰወረ አቡነ አረጋዊ ከሮም ጀምሮ እስከ ደብረ ዳሞ ድረስ ለፈጸመው

ገድል እና መንፈሳዊ አገልግሎት ከፈጣሪው ዘንድ ምን ጊዜም የማይፋቅ ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ተሰጥቶታል። በየወሩ በ14ኛው ቀን በስሙ የዘከረ በደብረ ዳሞ የተቀበረ በእግሩ ደብረ ዳሞን የረገጠ ገድሉን ያነበበ የተረጐመ በደብሩ ቆሞ የጸለየ በስሙ ያበላና ያጠጣ ከመሬቷ ጠበል የተቀባ በስሙ የጸለየ ጠበሉን ተሸክሞ የዞረ በስሙ ቤተክርስቲያን ያነፀ ጠበሉን የጠጣ በጠበሉ የታጠበ መጽሐፈ ገድሉን ቤቱ ያስቀመጠ በስሙ መባዓ ያቀረበ አልባሳት የሰጠ በተለይም ቤተ መቅደሱን የደብሩን አጥር ያጠረ ከማንኛውም ተላላፊ ክፋ በሽታ ሁሉ ይፈወሳል በአማላጅነትህ የሚያምነውን ሁሉ እስከ አሥራ አምስት ትውልድ ድረስ እምርልሃለሁ ብሎም ፈጣሪው ቃል ኪዳን ገብቶለታል።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ አቡነ አረጋዊን እንደሌሎች ቅዱሳን ሁሉ ያከብራል በየዓመቱ ወደ ደብረ ዳሞ እየሄደ በመሳለም የቃል ኪዳኑን በረከት ተካፋይ ይሆናል የአባታችን ረድኤታቸውና በረከታቸው አይለየን። አሜን።

ምእራፍ 15 ቍጥር 21 ጥር 15 ቀን የቅዱስ ቂርቆስና የእናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ገድልና ዜና ዕረፍት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

የቅዱስ ቂርቆስና የእናቱ ኢየሉጣ ገድል ታሪካዊ ዜና እረፍት ማቴ.10÷32 ዕብ.12÷1 አባቱ ቆዝሞስ ይባላል። በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ክርስቲያኖች ላይ በተነሣው ሁከት ምክንያት ክርስቲያኖች ሁሉ ከአገራቸው ሲሰደዱ ቅዱስ ቂርቆስን እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ይዛው ተሰዳ ነበር ሐሳውያን ከአለችበት ሀገር መጥተው ይዘው ለጣዖት እንዳይሰግዱ ሕዝቡን ትሰብካለች ሲሉ ለአገረ ገዢው አለእስክንድሮስ አቀረቧት አገረ ገዢውም ብዙ ጥያቄና ክርክር አድርጐ ለጣዖት እንድትሰግድ ቢያዛት አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነውና ለረከሰው ጣዖት አልሰግድም ስትል አጥብቃ ከተከራከረች በኋላ ለጣዖት ካልሰገድሽ ብዙ መከራ እንዲያገኝሽ አደርጋለሁ ብሎ ስለአስጠነቀቃት የ3 ዓመት ልጁ ይጠየቅና ርሱ በተናገረው አመልካለሁ

ስትል ምክንያት ሰጠች ሀገረ ገዢውም ሕፃኑን ልጅ ፈልገው እንዲያመጡት አዘዘ የቅዱስ ቂርቆስ መልኩ በጣም የአማረ በመሆኑ አንተ ደስ የምታሰኝ ሕፃን እንደምንዋልክ በማለት አሞግሶ ሃይማኖቱንና ስሙን ቢጠይቀው ለአንተ ደስታ ሳይኖርህ እኔን ታመሰግናለህን? ብሎ ገሰፀውና ሃይማኖቱ ክርስቲያን ስሙ ቂርቆስ መሆኑን ሲገልጽለት ሀገረ ገዢውም ይህን እንድትናገር ማን ይሆን የመከረህ ይልቅስ ሹመትና ብዙ ወርቅ እሰጥሃለሁና ለጣዖት ስገድ እያለ በማታለል ቢጠይቀው ቅዱስ ቂርቆስ የሚናገረው ከእግዚአብሔር በተሰጠው መንፈስ መሆኑን ገልጾ ሃይማኖቱን ለሹመት ለገንዘብ ብሎ የማይክድ መሆኑን ጭምር በማስረዳት መለሰለት ከዚያም በኋላ ገዢው ጭፍሮችን በአምበት አለንጋ እየተፈራረቃችሁ ግረፉት ብሎ ሲያስገርፈው ቅዱስ ቂርቆስ ግን ወደ ፊጣሪው ይጸልይ ነበር የገረፉት አካሉ ምንም ሳይቆስል ሳይጐዳ በማየቱ ገዢው በጣም እያደነቀ እንደገና ለጥያቄ አቀረበው እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ግን ከግርፋቱ ብዛት ቃሉን የሚለውጥ ስለመሰላት አቡቱ ጌታዬ ሆይ ልጄን አድንልኝ እያለች ወደ ጌታ ስትጸልይ አይዞሽ ይህ ልጅሽ ከቅዱሳን ሁሉ የሚበልጥ ነው ይልቅስ አንቺን ከዚህ ከሚመጣው ሥቃይ ስትፈሪ የሚያጽናናሽ ነውና አታስቢ የሚል ቃል ስለሰማች ደስ አላት ከዚያም ልጄ ማንን ትፈራለህ አምላክስ ማን ነው? ብላ ብትጠይቀው እናቱ በጥምቀት የማያልቀውን ልበሰ ሃይማኖት ከአለበሰኝ ከኢየሱስ ክርስቶስ አልለይምና አይዞሽ አትፍሪ አላት መኮንኑም ሐይማኖታችሁ እያልክ የምታወራው ወደ ገሐነመ እሳት የሚወስደውን ነው የእኛ ሃይማኖት ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሲል ለመኮንኑ በድፍረት ቃል ስለመለሰለት መኮንኑ በርበሬ ጨው ሰናፍጭ ጨምሮ በጥብጦ በአፍንጫቸው ቢጨምርባቸው ቅዱስ ቂርቆስ ይህ ትዕዛዝ ከማርና ቅቤ ከስኳር ይልቅ ጣፈጠኝ አሁን በምታደርግብን መከራ ሃይማኖታችንን ጌታችንን የምንክድ ይመስልሃልን? እኛ ግን አንፈራም ሲል መለሰለት ገዢውም ተቆጥቶ አሥራ አራት /14/ ብረቶች አግሎ እንዲቃጠሉ በአፋቸው በአፍንጫቸው በጆሮአቸው ቢያገባባቸው ቅዱስ ቂርቆስ ወደ ጌታ በመጸለይ ግለቱ ሳይቀዘቅዝ ወደ ፊት የሚያደርገውን እስኪመክር በወህኒ

ቤት አሥሮ አቆይቶአቸዋል ቅዱስ ቂርቆስ ጸሎቱን በማዘውተር ሳለ ቀናተኛ ዲያብሎስ መላክ ብርሃን መስሎ ጸሎትህ ተሰምቷል አለው ቅዱስ ቂርቆስም አንተ የክፉ መካሪ ሽፍታ ከቅዱሳን ክፍል የለህምና ከእኛ ተለይ ቢለው አንተ በዚህ ብታሸንፈኝ ክብር የምታገኝበትን መከራ እንዳያዝ የንጉሡን ልብ እዘጋለሁ እናትህም ከመከራው እንድትሸሽ እንድትፈራ አደርጋለሁ ብሎት እንደጢስ በኖ ጠፋ ከዚያም በኋላ ቅዱስ ቂርቆስን ወደ ገዢው ስለአቀረቡት ለጣዖት መስገድህ ይቅርና አምናለሁ ብለህ በቃልህ ተናገር ቢለው እኔስ ይህን ጣዖት እንዲያፈርሱት እንጂ እንዲያጥኑት አላዝም ብሎ ሲናገር ወዲያው አንድ ሺህ አንድ መቶ የጣዖት ቤትና ጣዖታት ተሰባብረው ወደቁ ስለዚህም ቅዱስ ቂርቆስ እየሳቀ የእኔ አምላክ ጽኑእ ኃያል በመሆኑ ጣዖታቶችን ቀጠቀጣቸው እያለ ስለቀለደበት ገዢው ተናደደ ከዚያም ገዢው ቅዱስ ቂርቆስ የሚሰቃይበትን ለማዘዝ በፊት ሠራተኛ አስጠርቶ ነበር ነገር ግን ይህን ሥራ ብሎ ለመናገር በአለመቻሉ ቅዱስ ቂርቆስ ቀድሞ ዲያብሎስ እንደነገረኝ ምንም እንዳይናገር የገዢውን ልብ ስለደፈነበት ማዘዝ አልቻለምና እኔ ልንገርህ ብሎ ከበፊት ሠራተኛው ጋር ከተስማማ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ነግሮታል 2 ክንድ የሆነ 4 ምላጭ የራስ መደብደቢያ መዶሻ የአንገት መተብተቢያና መቁረጫ ብልትን የሚቀድ ጉጠትና ሹካ መጠረቂያ የጆሮ መብሻና መደቅደቂያ የምላስ መቁረጫ 3 ቀዳዳ ያለው የናስ ወንበር 3 የብረት ችንካር በቁመቴ ልክ ሠርተህ በወንበር 3 ቀዳዳ ያለው 3 ብረት በ3 በኩል እንዲገባ አድርገው በችንካሩ ላይ ሥላሴ ከሚያምኑብህ አትለይ ብለህ ድፋበት 2 ረኻጅም መቁረጫ 9 የአካል መሰንጠቂያ መጋዝ የሰውነት መቀቀያ 4 ብረት ምጣድ ትልልቅ የብረት ጋን በጋን ውስጥ የሚተረትር በሆድ ውስጥ ያለውን እየቦረቦረ የሚያጣምም እጅ ያለው ብረት የሚመስል እነዚህን ሥራ ብሎ እስከ 24 ቁጥር የመሣሪያ አይነቶች እንዲሠራ ነገረው ብረት ሠራተኛውም በቅዱስ ቂርቆስ አነጋገር የተነሣ ደንግጦና ተደንቆ ጥበበኛ አስመጥቶ ሥራው ተጀመረ ሥራው እስከሚፈጸም ድረስም ቅዱስ ቂርቆስ በወህኒ ቤት ነበር በዚህን ጊዜም 434 ሰዎችን አስተምሮ አሳምኗል ከዚህም በኋላ የብረቱ ሥራ በ40 ቀን ስለተፈጸመ ገዢው ቅዱስ ቂርቆስንና

ቅድስት ኢየሉጣን አደባባይ አስቀርቦ በእኔ ዘንድ ቀልድ የለም ይኸው ተሠርቶ ስለተፈጸመ ብሎ ገዢው ቢያስፈራራው አንተ በደለኛ ኃጥእ እኔ ነግሬው በአሠራሁት መሣሪያ ተአስፈራራኛለህን ብሎ በኃይለ ቃል ስለመለሰለት የአሠራው በኢየሉስ ደም የሚያሸንፍ መሆኑን አውቆ ነው በማለት ገዢው ተናዶ የቅዱስ ቂርቆስንና የቅድስት ኢየሉጣን የእራሳቸውን ጠጉር በማስላጨት ቆዳቸውን አስገፍፎ የእሳት ፍህም ቢያፈስባቸው እሳቱ ከቤቱ ክፍል ሆኖ አብርቶ ስለታየ ወህኒ ቤቱ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተከፍቶላቸው 334 ሰዎች ከወህኒ ቤት ወጥተው ለዚህ አክሊል ስንጸልይ 50 /ሃምሳ/ ቀኖች ነበሩና በዚህ ሕፃን አምላክ አምነናል ስለአሉ ገዢው ተቆጥቶ በሰይፋ አስፈጅቶአቸዋል። ከዚያም በኋላ ትልቅ ረጅም ወንበር ከብረት አሰርቶ ከትክሻው እስከ ሰኮናው የሚተክል በትክሻው አልፎ በሰኮናው የሚተክል በትክሻው አልፎ በራሱ የሚወጣውን ስድስት ችንካሮች በአለበት ወንበር ላይ አስቀምጦ አስጨንቆ ይዞ እስኪ አምላክህ ያድንህ እያለ በዘበተበት ጊዜ ቅዱስ ቂርቆስ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ የታዘዘ መላክ መጥቶ ችንካሩን ከቅዱስ ቂርቆስ ላይ ሲነቅለው ከሀገረ ገዢው አንገት ላይ ተተክሎ ቢያስጨንቀው ቅዱስ ቂርቆስን አድነኝ ብሎ ቢለምነው ቅዱስ ቂርቆስም አንተስ አታምንም ነገር ግን ሌሎች አይተው ያምናሉ ብሎ እጁን ወደ ገዢው ትክሻ ላይ ስለዘረጋ ችንካሩ ተነቅሎ ወድቆለት ጣዖቱን አመሰገነ ከዚያም ቅዱስ ቂርቆስ ለአሁኑ ብታታልለኝ ደግሞ ለመለመን ትመጣለህ ሲል ተናገረው ከዚያም በኋላ ገዢው አንገትን የሚሰብር ድቡልቡል ብረት አሠርቶ በወንጭፍ አድርጐ በአንድ ጊዜ ሊገድለው ሲወረውረው ተመልሶ ራሱን አፉን አፍንጫውን ግንባሩን ስለመታው ቅዱስ ቂርቆስም የሚያሰቃዩኝ እራሳቸው ወደቁ ሰይፋቸውም ከልባቸው ተሰካ ጸብ ክርክራቸውም ተቀጠቀጠ ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነ ከዚያም በኋላ የቅዱስ ቂርቆስንና የቅድስት ኢየሉጣን ሥጋቸው በመጋዝ ከሦስት ተሰንጥቆ ከቅባት ጋር በብረት ምጣድ መኰንኑ አዞ ተቆልቷል ሥጋቸውም እንደ አመድ ሆኗል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለእነ ቅዱስ ቂርቆስ ስለዚህ መከራቸው የሚያገኙትን የመንግሥተ ሰማያት ክብር ከአሳያቸው በኋላ

ከሞት አሥነሥቶ ኃይል አሳድሮ ሄደው ንጉሡን እንዲያስፈራሩት ሰለላካቸው ቅዱስ ቂርቆስን እናቱ አዝላው ሲሄዱ ዲያብሎስ አሥራ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ የሚሆኑ አጋንንት አሰልፎ እንደ ሰው በመንገድ ቢቆያቸው ሕፃኑ ሰማዕት ቂርቆስ ከእናቱ ጀርባ ወርዶ ሲያማትብባቸው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተበታትነዋል ከገዢውም ዘንድ ቀርበው እኛን ታውቀናለህ ብለው ቢጠይቁት እኔ አላውቃችሁም ከፊቴ ወግዱ አላቸው ቅዱስ ቂርቆስም አንተ የሰይጣን የግብር ልጅ ሌላ እንዲያምን ነው እንጂ አንተ የገደልከን መድኃኒታችን ያሥነሣል መሆናችንን አጥተኸው አይደለም ብሎ ሲናገር አደባባይ የነበሩ አሥራ አንድ ሺህ / 11000/ ሰዎች በእውነት አምላክ ነው ብለው በአንድ ድምጽ ጮኸው አምነዋል ንጉሡ ግን ይህ ሁሉ የምትሉት ነው አትታወኩ እውነት ከሞት ከተነሣ ይህ ጫማዬ እንደቀድሞ ሕያው ይሁን ብሎ በተናገረ ጊዜ ቅዱስ ቂርቆስ ወደ ፈጣሪው ቢጸልይ የመኰንኑ ጫማ ከእግሩ ወልቆ በሬ፣ የጫማ ማሠሪያ ክሩ ከበሬው ሻኛ ላይ ፍየል ሆኗል ቀጥሎም ሣር አም ጡላቸው ይብሉ ብሎ በሬውም ፍየሉም ሣሩን በመብላታቸው መኰንኑ በእግዚአብሔር አላምንም በማለት አሳርዶ በእግዚአብሔር አምነናል ላሉት አሥራ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰዎች አብልቶ ጠግበው 4 ቅርጫት ስለተረፈ ሌሎች አይተው እንዳያምኑ ከባህር ውስጥ አስጨምሮታል ከዚህ በኋላ የዚህን ሕፃን ንግግር መስማት አልቻልሁም በማለት ምላሱን ቢያስቆርጠው አንተና አባትህ ሰይጣን መቁረጥ የማትችሉትን ከመንፈስ ቅዱስ የእሳት ምላስ ተሰጠኝ እያለ ሲናገር ሰምተው አውሳብዮስና ዲሜጥሮስ የተባሉ መኰንኖች በእግዚአብሔር አምነዋል ከዚህም ቀጥሎ መኰንኑ ለጣዖት ማጠን ይቅርና መስዋዕቱን በልተህ ከመከራ ዳን ቢለው ቅዱስ ቂርቆስም ርኩስ ነገር በአፌ አልገባም ስለ አለው በግድ ከፍቶ ጨምሮ ከእንግዲህ በእግዚአብሔር ዘንድ ነገር ተስፋህ ጠፋ ቢለው አንተ የዲያብሎስ ዳኛ በፈቃዴ በአደረግሁት ነውን? ይልቅስ አንተ ገሐነመ እሳት ስታገኝ ለእኔ የክብር አክሊል አስገኝቶልኛል ብሎ በድፍረት ተናገረው ከዚያም በኋላ የብረት ጋኑ ፈልቶ ድምፁ እንደመብረቅ ሲጮህ የእሳቱ ወላፈን አርባ ክንድ ወጥቶ ሲውሰበሰብ ቅዱስ

ቂርቆስና ቅድስት እየሉጣ ወደ ውስጥ ሲጣሉ ተይዘው ሲሄዱ ቅድስት እየሉጣ ከመከራው ጽናት የተነሣ ፈርታ ለጊዜው ስለተሰቀቀች ቅዱስ ቂርቆስ ያለፉትን ቅዱሳን ከደረሰባቸው መከራ እግዚአብሔር እንዳዳናቸው እየጠቀሰ ቢያጽናናት መፍራትን በአለመተዋ ለይተህ እንዴት ታስቀርብኛለህ ብሎ ጌታዬ ልቦናዋን አጽናልኝ እያለ በመረረ ሐዘን ወደ እግዚአብሔር ጸለየ / ለመነ/ በጸለየም ጊዜ በእየሉጣ ፊት እንቅፋት ሊሆን የተደቀነው ዲያብሎስ ስለተወጎደላት ልጇ ለመንግሥተ ሰማያት አባት ሆንኽኝ ብላ ተያይዘው ከእሳቱ ገብተው ምንም ሳይነካቸው በውስጡ ይዋኙ ጀመር መዝ.65÷12 ኢሳ.43÷1 እስከ ዚህች ቀን ያሳታቸውን የክፋቱን መጠን እየጠቀሰ በእግዚአብሔር ኃይል ድል ለማድረግ በቃሁ እያለ ስለጸለየ ዲያብሎስ በሰው ተመስሎ ወይኔ በነንኩ ጠፋሁ ይህ የሦስት ዓመት ልጅ ሕፃን ድል ስለአደረገኝ መሳቂያ ሁኜ ቀረሁ በሰይፉ ይገድለው ዘንድ ንጉሡን እመክረዋለሁ እንጂ በእየ ጊዜው ሲያሸንፈኝ አይኖርም እያለ ሲጮህ መኰንኑ ሰምቶ ይህን የሚያደርግ በሥራዩ ነው ስለ አለ ቅዱስ ቂርቆስ ከዚያው በፈላው ቅባት በእጁ እየዘገነ በእግዚአብሔር ስም በአመኑት 11900 ሰዎች ጥምቀት ይሁናችሁ ብሎ ሲረጫቸው በሌሎች በአላመኑት ላይ ጠብታው ቢያርፍባቸው 40 / አርባ/ የሚሆኑ ሰዎችን አቃጥሏቸዋል መኰንኑ ገን በጥንቆላ ይህንን ያደርጋል ብሎ ስለ ቅዱስ ቂርቆስ በተናገረ ጊዜ ቅዱስ ቂርቆስ በ3ቱ ጣቶቹ ከፍላቱ አጥቅሶ በመኰንኑ አንገት ላይ ጠብ ቢያደርግበት አጥንቱ እስኪታይ ስለተሰወጠ እባክህ ፈውሰኝ እያለ ወደ ቅዱስ ቂርቆስ ቢጮህ ሌሎች አንተን አይተው እንዲያምኑ ነው እንጂ አንተስ አታምንም ሲል ጸልዮ ፈውሶታል። ከዚያም በኋላ ሁለት ሰዎች ማነቃነቅ የማይችሉትን ድንጋይ በብረት ሰንሰለት ተብትቦ ተፈንቅሎ ወድቆ እንዲገጫቸው ቢያደርግ መልአከ እግዚአብሔር መጥቶ ስለአዳናቸው እንግዲህ በሰይፍ ከአልገደልኳቸው አላርፍም ብሎ ቁርጥ ሐሳብ አደረ ከዚህ በኋላ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ቂርቆስን በልቡ የአሰበውን አውቆ የፈቀደውን ለምነኝ እሰጥሃለሁ አለው ቅዱስ ቂርቆስም ሥጋዬን በምድር አትቅበራት ቤተክርስቲያንን በስሜ የሠራውን ዕለ

መታሰቢያዬን በማድረግ ድሆችን አብልቶ አጠጥቶ ደስ ያሰኘውን ጸሎት እየጸለየ በስሜ የተማጸነውን በቤተክርስቲያኔ መጥቶ ስለ ኃጢያቱና ስለ ደዌው የለመነውን የተቸገሩትን የሚረዳውን ለቤተክርስቲያኔ መባ የሰጠውን ዋጋውን በሰማይ ሰጥተህ ደስ አሰኘው በቤተክርቲያኔ መጥቶ የተማጸነውን ሰው በፍጹም ርህራሄ ማርልኝ ቤተ መቅደሴ በታነጸበት ስሜ በተጠራበት ሀገር ሁሉ የሰውና የእንስሳት መቅሰፍት የእህልና የውሃ ችግር አይገኝበት የእግዚአብሔር ምሥጋና ጉልቶ ይታይበት ይነገርበት እንጂ አይጉደልበት ክፋዎች አጋንንትም አይድረሱበት ብሎ ስለለመነው ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም የለመንከውን ሁሉ የሚፈጽሙልህ ከዚህም ጋር በቤተ ክርስቲያንህ የሚቀርበውን መስዋዕትና ጸሎት እየጻፉ የሚያቀርቡ 500 ጠባቂ መላእክት አዝልሃለሁ ከዮሐንስ መጥምቅ በቀር እንደ አንተ ያለ አላገኘሁምና ከሰባቱ ከመላእክት አለቆች ጋር በቀኜ ትኖራለህ ሥጋህንም በኤልያስ ሠረገላ አሳርግልሃለሁ ብሎ የጠበቀ ቃል ኪዳን ሰጥቶ አረገ ስለ ቅዱስ ቂርቆስ ክብር ኃጥአንን ከሲኦል ያወጡ ዘንድ መላእክቱን አዞአቸዋል። ጊዜው ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ነበረና ታላቅ ብርሃን መልቶ ታይቷል ጥር 15 ቀን ሐሙስ ጠዋት ቅዱስ ቂርቆስ፡ለአርብ አጥቢያ በ3 ሰዓት ጥር 16 ቀን ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ከእናቱ ኢየሉጣ ጋር በሰይፍ ተከልለው ከዚህ ዓለም መከራ ስለአረፉ ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋግረዋል በቅዱስ ቂርቆስ ስብከት ያመኑ 11441 ሰዎች ከቅዱስ ቂርቆስ ጋር በሰይፍ ተገድለው ሰማያዊ ክብር ተቀብለዋል። ቅዱስ ቂርቆስም ስለ መንፈሳዊ አርበኝነት ተጋዳይነቱ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 3 የብርሃን አክሊል ተሸልሟል ከዚያ ቀን ጀምሮ ቅዱስ ቂርቆስ በመንበረ ጸባዖት በቀኝ በኩል እነሆ ለእኛ ክርስቲያኖች ምህረትና ይቅርታን እንድናገኝ ሲለምንልን ይኖራል ይህን ለቅዱስ ቂርቆስ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠውን ጽኑእ ቃል ኪዳን እንደሌሎች መናፍቃን ሳንጠራጠር ተሰፋ በማድረግ ወደ ፈጣሪያችን የምናቀርበው ልመና ሁሉ የሚፈጽምልን መሆኑን ማመን አለብን ሐምሌ 19ኝም ክብረ በዓላቸው ነው።

የቅዱስ ቂርቆስና የቅድስት ኢየሉጣ ጸሎታቸውና በረከታቸው በኛ ላይ ይኑር። አሜን።

ምእራፍ 16 ቁጥር 22 የካቲት 16 ቀን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእመቤታችን ቃል ኪዳን የገባላት ዕለት ነው

ኪዳነ ምሕረት መሠረተ ቃል (ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ) ከመረጥኩአቸው ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ (መዝ. 88÷3) ዝየ አሐድር እስመ ሐረይክዋ መርጫታለሁና ከዚያ አድራለሁ (መዝ 131÷14) እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታ ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ ካረገ በኋላ በዚህ ዓለም እስካለች ድረስ በየቀኑ ጸሎት የምታደርግ ከጌታ መቃብር ጕልጕታ ላይ ነበር ስለዚህም የካቲት 16 ቀን ስምዋን ለሚጠሩ መታሰቢያዋን ለሚያደርጉ በእርስዋ አማላጅነት ለሚማፀኑ በልጅዋ ቸርነት ለሚታመኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ ልጅዋ ባደረገችው ምልጃ በስምዋ ጸሎት የሚያቀርቡ ምጽዋት የሚሰጡ ለቤተክርስቲያን መባ የሚያቀርቡ በጕውን ነገር ሁሉ የሚያደርጉ በምድር በረከቱን በሰማይ የዘለዓለም መንግሥቱንና ሕይወቱን እንደሚወርሱ የምሕረት ቃል ኪዳን ሰጥቶአታል ይህም ተስፋ በነሐሴ 16 ቀን ተደግሟል። የምህረት ቃል ኪዳን የተገኘበትን ተስፋ መሠረት በማድረግ ኪዳነ ምሕረት እያሉ ይጠሩአታል (ኢሳ 59÷20-21) ይወጽእ መድኅን እምጽዮን ወያአትት ኃጢአተ እም አስራኤል ወዛቲ ይእቲ ኪዳናሙ እንተ እምኀቤየ ይቤ እግዚአብሔር መድኅን ከጽዮን ይወጣል ከአስራኤልም ኃጢአትን ያርቃል ከእኔ ዘንድ የምትሆነው ኪዳናቸው ይህቺ ናት አለ እግዚአብሔር ይላልና መድህንን የወለደች እመቤታችን የሕዝቡን ኃጢአት ለማራቅ በአማላጅነትዋም ድህነት እንዲያገኙ ለማድረግ በገባላት ቃል ኪዳን መሠረት ኪዳነ ምሕረት ተብላ መጠራትዋ ቦታውን ያገኘ አጠራር ነው ለማለት ይቻላል።

ቍጥር 23 ነሐሴ 16 ቀን ጾመ ፍልሰታ

በኢትዮጵያ ከፍ ብሎ የሚታየው በብዛት ልጆች ተሳትፎ የሚያደርጉበት የፍልሰታ ጾምና በዓል ነው። ፍልሰታ የሚለው ቃል የእመቤታችን ሥጋ ከጌቴ ሴማኒ ወደ ገነት መፍለሷን ኋላም በገነት በዕፀ ሕይወት ሥር ከነበረበት መነሣቱን ለማመልከት የሚነገር ቃል ነው ታሪኩ እንደሚገልጸው እመቤታችን ከአረፈች በኋላ ሐዋርያት በሐዘን ላይ እንዳሉ ለጊዜው በኢየሩሳሌም ያልተገኘውና በሀገረ ስብከቱ የነበረው ቅዱስ ቶማስ ከሀገረ ስብከቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ መላእክት ሥጋዋን ወደ ገነት ሲያፈልሱ አይቶና ደርሶ ነገሩንም ከመላእክት ተረድቶ ለወንድሞቹ ለሐዋርያት ነግሮአቸው ነበር። ሐዋርያትም ከእመቤታችን በመለየታቸው እያዘኑ ምስጢሩን ለማወቅ ይጓጉ ስለነበር ጌታ ተገልጾላቸው እናቴን አሳያችኋለሁ የሚል ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር። በዚህ ተስፋ ላይ ሳሉ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ከነሐሴ 1 ጀምረን በጾም እመቤታችንን እንዲያሳየን ፈጣሪያችንን እንጠይቀው አላቸው እነሱም ሐሳቡን ተቀብለው ከነሐሴ አንድ ቀን ጀምሮ ሁለት ሱባዔ ከጾሙ በኋላ ነሐሴ 16 ቀን ጌታ መላውን ሐዋርያትን ወደ ገነት አውጥቶ በገነት በእፀ ሕይወት ሥር በነበረው መቃብር እመቤታችንን ነፍሷን ከሥጋዋ አዋህዶ አንሥቶ ትንሣኤዋንና ዕርገቷን አሳይቶ ለዓለም ይህንኑ እንዲያስተምሩ አዘዛቸው ይላል።

መሠረቱ በመዝሙር 131 ÷8 ላይ ያለው ነው ይኸውም አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነስ አንተ የመቅደስህም ታቦት የሚለው ነውና ወዳጀ ሆይ ተነሽ ውበቱ ሆይ ነዪ መኃ.2÷10-12 እንግዳ ነገር ሊሆን አይችልም ከቀደሙ ሰዎች ታሪክ ከእስራኤል መስፍን ከ 7ቱ አንዱ ለሆነው የዮፍታሔ ልጅ መታሰቢያ ልጆች ወይም ደናግል በእየዓመቱ በዓል ሲያከብሩ እንደነበር ተነግሯል መሳ. 11 ÷40 እንዲህ ከሆነ ዘንድ የኢትዮጵያ ቆነጃጅትና ሕፃናት ኢትዮጵያውን ጕልማሶች የእናታችን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን መታሰቢያ በየዓመቱ ሲያከብሩ የበለጠ ነገር ፈጽመዋል ማለት ነው የጾመ ፍልሰታን መታሰቢያ በመፈጸም ልጆችም ወላጆችም ይተባበራሉ

ጸሙ በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 ከተዘረዘሩት ከ7ቱ አጽዋም አንዱ ነው ጾመ ከፍቅር ጋር የሚፈጸም ስለሆነ ልጆቹም ወላጆቹም የሚጾሙት በጉጉት ነው ወላጆች ኩባድ ምክንያት ከአላጋጠማቸው በስተቀር ከአልጋ ወርደው ከመሬት ላይ ተኝተው ወይም ከቤታቸው ወጥተው በቤተ አግዚአብሔር ዙሪያ ማሪፊያ አሰናድተው ከነሐሴ አንድ እስከ አሥራ አምስት ድረስ ጥሬ በመብላት ውሃ በመጠጣት ሌሊት በሰዓታት ቀን በጸሎት ውዳሴ ማርያም ቅዳሴ ማርያም በመስማት ቅዳሴ በማስቀደስ በምጽዋት ከፍተኛ በሆነ ሥርዓት ይጾሙታል ልጆችም ረሃብ ሳይሰማቸው ውሃ ጥም ሳያሸንፋቸው ከ7 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ያሉ ወንዶችም ሴቶችም ሕፃናት እየጾሙ ይቆርባሉ በመጨረሻም ነሐሴ 16 ቀን በሥነ-ሥርዓት ያከብሩታል።

አሸንዳ የሚባል ሣር ዓይነት ቅጠል አለ ሁኔታው ቀጭን ቢሆንም ቁመቱ ረዘም ያለ ሆኖ ቅርጹ ሬባ ዓይነት ነው ሲነቅሉት ሥሩ ነጭ ነው ዛጐል ይመስላል በልዩ አሠራር ሠርተው በቀሚሳቸው ላይ ይታጠቁታል እንደዘርፍም ሆኖ ወደታች ይወርዳል በሚጫወቱበትና በሚዘፍኑበት ጊዜ ዙሪያውን ሲነሣ ክንፍ ይመስላል በዚህ ዓይነት ሥርዓት በዓሉን ሲያከብሩ ይኖራሉ በተለይ በገጠር ላሉ ሴቶች ሕፃናት ቆነጃጅት ልዩ በዓላቸው ነው። አሸንዳ ከሚባለው ሣር ዓይነት ቅጠል በልዩ ዓይነት አሠራር ሠርተው የሚታጠቁትና ሲጫወቱ ሲዘፍኑ ዙሪያው የመነሳቱ ሁኔታ መላእክት እመቤታችንን ክንፍ ለክንፍ ገጥመው እያመሰገኑ ማሳረጋቸውን ያሳስባል ኢሳ. 6÷3 በዓሉንም የአሸንዳዬ በዓል ይሉታል።

ስለዚህ ነው የኢትዮጵያ ቆነጃጅትና ጉልማሶች በእመቤታችን በእየ ዓመቱ ከ1-16 የሚያደርጉት ጾምና ጸሎት የበለጠ ያደርገዋል የተባለው የእመቤታችን ረድኤትና በረከት አይለየን።አሜን።

ምዕራፍ 17 ቁጥር 24

ጥር 1 ቀን የቅዱስ እስጢፋኖስ ዕረፍት

እስጢፋኖስ ማለት በግሪክ ቋንቋ « አክሊል» ማለት ሲሆን ከአባቱ ከስምዖንና ከእናቱ ከሐና ነገደ ብንያም ከሆኑት የተወለደው ሐኖስ የተባለ ሥፍራ ነው

በማኅበረ ምዕመናን መካከል በአረማውያንና በአይሁድ ሴቶች ጠብ የተነሳ መነቃቀፍ ተጀመረ። በዚህም ምክንያት ምእመናንን በሚገባ የሚያስተዳድሩ ዲያቆናት ለቤተክርስቲያኗ አስፈለጓት። ቅዱስ እስጢፋኖስም ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን አገልጋይነት ከተሾሙት ሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ነበር። የሐዋ.6÷1-6

ቅዱስ እስጢፋኖስ የሌሎች ስድስት ዲያቆናት አለቃ (ሊቀ ዲያቆናት) በመሆን ምእመናንን ከማገልገል ባሻገር ድውያንን በመፈወስ ትምህርተ ወንጌልን በማስፋፋት የበረታ ከመሆኑ በተጨማሪ ዲዳ ደንቆሮ ባገኘ ጊዜም ካለበት ሄዶ ይፈውስ ነበር።

እንዲያውም አንድ ጊዜ ናኦስ የሚባል ጠንቋይ ወደ አንድ በሬ ሄዶ በጆሮው ሹክ ቢለው ከሁለት ክፍል አለ። ቅዱስ እስጢፋኖስም በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ የሞተውን አሥነሥቶ የተከፈለውን ገጥሞ « ናኦስን ጠርተኸው ና» ብሎ አዘዘው በሬውም የበለዓም አህያ እንደተናገረች ዘጎ. 22÷30 በሰው ልሳን እየተናገረ ጠንቋዩን ናኦስን ቅዱስ እስጢፋኖስ ይፈልግሀል እያለ መጣራት ጀመረ።

አስቀድሞ በዚህ መሠረት ተታሎ የነበረው ሕዝብ ቅዱስ እስጢፋኖስ ባደረገው ተአምር እየተገረመ አምኖ ተጠመቀ። ይህም አይሁድን በቅንዓት በቅዱስ እስጢፋኖስ ላይ እንዲነሣሡ አደረጋቸው።

በዘመነ ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ብቻ 480 ምኩራባት ነበሩ እነዚህ ምኩራባት በተለያዩ ሀገሮች የሚኖሩ አይሁድ ለራሳቸው በኢየሩሳሌም ማረፊያ ይሆናቸው ዘንድ ያሰሩአቸው ሲሆኑ ልጆቻቸውን በመላክ የሚያስተምሩባቸው ትምህርት ቤቶችም አብረው ነበሩአቸው። ከነዚህ መካከል አምስቱ ምኩራባት ተባብረው በእስጢፋኖስ ላይ ተነሡበት። እነርሱም።

1. በሮም የነበሩና በኋላም ከባርነት ነፃ የወጡ አይሁድ ያሠሩት
2. የቀሪና አይሁድ
3. የእስክንድርያ አይሁድ
4. የኬልቅያ አይሁድ

5. የታናሿ እስያ አይሁድ ናቸው።

እነዚህ አይሁድ ወደ ቅዱስ እስጢፋኖስ መጥተው ምን እንደሚጠይቁት ይከራከሩት ነበር(የሐዋ. 6÷8) ከማለት በቀር መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ነገር የለም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግን በድርሳኑ እንዲህ ይላል።

አንተ ጐበዝ እሰኪ ንገረን ይህን የዋህ ሕዝብ የማይሆን ነገር እያስተማርክ የማረክ ተአምር እያደረክ ለምን ታስተዋለህ አምላክ ነው ብለህ የምታስብ ከሆነ እስኪ ንገረን ? ከማርያም የተወለደ፣ የእንጨት ጠራቢ ዮሴፍ ልጅ ዓለምን መፍጠር የሚችል ይመስልሀልን የተወለደው በቤተልሔም እየተማረ ያደገው በናዝሬት መሆኑ ጠፋህ እንዴ? በተወለደ ጊዜ ከድህነቱ ብዛት የተነሣ የሚጠጋበት እንኳን አጥቶ በጨርቅ ተጠቅልሎ ከበረት የተወረወረ ፣ ንጉሥ ሄርድስን ፈርቶ የሸሸ ኃጢአቱን ሊያጣራ በዮርዳኖስ የተጠመቀ የሚራብ የሚጠማ የሚደክም የሚተኛ ሲያዝ ማምለጥ ለተከሰሰበትም ፍርድ መከላከል ያልቻለ ሲሰቅሉት ሲወርድ ያቃተው ነገር ግን የተረገመውን ሞት በመስቀል የሞተ ርሱን በመቃብር እንዳልቀበርነው በሰማያት የሚኖር ብለን እንመንልህን? እስቲ አስበው እግዚአብሔር እንዲ የሚሰቃይ ይመስልሀል? ነበር ያሉት።

ቅዱስ እስጢፋኖስም ለጠየቁት ሁሉ የሚገባቸውን መልስ እየሰጠ ስለ አሳፈራቸው በክርክር ሊያሳምኑት አለመቻላቸውን ሲያውቁ በቁጣ ተነሣሥተው ያለ አንዳች ፍርድ ከከተማዋ በስተሰሜን ወደ ቄዳር ከሚወስደው መንገድ አጠገብ በድንጋይ ወግረው ገደሉት።

ያረፈው በተወለደበት ዕለት ጥር 1 ቀን በ35 ዓ.ም፣ሲሆን አይሁድ ከተበተኑ በኋላ የኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ሥጋውን ሌሊት በድብቅ በሠረገላ ወስደው ከኢየሩሳሌም ሀያ ምዕራፍ ርቀት ላይ በምትገኝ (ቃፓርጋማል የግመል ከተማ ማለት ነው) በተባለች ቦታ ቀበሩት የሐዋ.7÷56-60፣22÷20 ጥቅምት 17 ቀን ቅዳሴ ቤቱ መስከረም 15 ፍልሰተ ዓጽሙ ነው የሰማዕቱ ረድኤትና በረከት በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ምዕራፍ 18 ቁጥር 25

መስከረም 18 ቀን የአባ ኤምስጣቴምስ ዕረፍት

ሲራ.1÷13 ጥበብ 4÷16

የእኒህም ቅዱስ ያባታቸው ስም ክርስቶስ ሞዓ የእናታቸው ስም ስነ ሕይወት ይባል ነበር ሁለቱም ባልና ሚስቶች እግዘብሔርን የሚፈሩ በሕጉና በትዕዛዙ ፀንተው የሚኖሩ ደጋግ ሰዎች ነበሩ ከዚህ በኋላ ይህን ሕፃን በፈቃደ አምላክ በብስራተ መልአክ ወለዱት ስሙንም ማዕቀበ እግዚእ (አልፋ) ብለው ሰየሙት ባደገም ጊዜ እንደ ጥንታዊው ልማድ ዳዊት አስደገሙት ከዚህ በኋላ የቤተክርስቲያንን መጻሕፍት ሁሉ ብሉይና ሐዲስ ሌሎችን አዋልድ መጻሕፍት ሁሉ አስተማሩት ከዚህ በኋላ የእናቱ ወንድም አባ ዘካርያስ ወደ ነበረበት የገርአልታ ገዳም ወሰዱት አባ ዘካርያስ የእግዚአብሔር ፀጋ ያደረበት ልጅ እንደሆነ ተረድቶ የምንኩስናውን ሥነ-ሥርዓት አስተምሮ አመነኮሰው እሱም በጾምና በጸሎት በስግደት ተወስኖ ጽሙድ እንደ በሬ ቅኑት እንደ ገበሬ ሆኖ በልዩ ልዩ ትሩፋት ሲጋደልና በአጋንንት ሲፈተን ኖረ ከገድሉም ጽናት የተነሳ የገዳሙ መነኮሳት ሽማግሌዎች ሁሉ እስኪያደንቁ ድረስ ይመሰገን ነበር። እሱም ከጥቂት ቀን በኋላ ዲቁና ተሹሞ እንደሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስ በቅን ሲያገለግል ቆየ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር ተገልጦ መጥቶ ባረከው። ቀጥሎም ወዳጁ ኤምስጣቴምስ ሆይ እኔ ከእናትህ ማህፀን ጀምሮ መረጥሁህ ከኢትዮጵያ እስከ አርማንያ ድረስ ለብዙዎች ሕዝብ መምህር ሐዋርያ አደረኩህ እንግዲህ ያለፍርሃትና ያለ ድንጋጤ ወንጌልን ትሰብካለህ አንተን የሰማኝኔን ሰማ አንተን እምቢ ያለ እኔን እምቢ አለ ብሎ ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ አረገ። ከዚህም በኋላ አባ ኤውስጣቴምስ ወደ ጳጳሱ ሄዶ ቅስና ተሾመ ቀጥሎም ወንጌልን ማስተማር ጀመረ ሕዝቡም እየተሰበሰቡ ስብከቱን እየሰሙና እየመነኮሱ ደቀ መዛሙርት ሆኑ። ከእነዚያም የሚበልጠው የመጀመሪያው ትልቁ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ አባ አብሳዲ እያስተማረ ብዙዎችን ከክህደታቸውና ከክፋታቸው ክርስቶስን ወደ ማመን

መለሳቸው ኤጲስጣቴጵስ በግብጽ ቆይታው በዓላትም እንዲያከብሩ እንዳደረገ ገድሉ ያስረዳል እሱም ከሐዋርያት ሕግና ስርዓት ሳይወጣ ቀኝ ግራ ሳይል ፀንቶ ኖረ ሁለት ጊዜ ኢየሩሳሌም ሄዶ ተሳልሞ ተመልሷል ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ልዩ ልዩ የተአምራት ሥራ አድርጉለታል። ይህውም ዕውር በማብራት ለምጽ በማንፃት፣ ጕባጣ በማቅናት፣ ሕመምተኞችን በመፈወስ፣ አጋንንትን በማውጣት ይህን በመሰለ ነው ከዚህም በኋላ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ስላሰበ መነኮሳቱን ሁሉ ሰብስቦ አደራ የመነኮሳቱን ሕግና ሥርዓት ጠብቁ ቀላል አታድርጉት ብሎ መክሮ በመጨረሻ እንዲህ አለ ይኸውም መንፈሳዊው የመጀመሪያ ልጁ አብሳዲ አበምኔት ይሁናችሁ ብሎ ወደ አባቶች ሄዶ ነገረ ኃይማኖትን ለመረዳት በ1327 ዓ.ም ወደ ግብጽ ወረደ። ከዚያም ከአባ ብንያም / ከ1327-1339/ ተገናኝቶና ተባርኮ ስለሃይማኖትም ጉዳይ ተነጋግሮ ከግብጽ ተነሥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ። ከዚያም ቅዱሳት ቦታዎችን ተሳልሞ በዮርዳኖስ ተጠምቆ ተመልሶ ወደ አርማንያ ጉዞውን ቀጠለ ከገሊላ ባሕርም ደርሶ የመርከብ ቀዛፊዎቹን አባካችሁ አሻግሩኝ ቢላቸው ገንዘብ አምጣ ብለው እምቢ አሉት በዚህም ጊዜ የለበሰውን የዳባ ዓጽፍ አውልቆ ከባሕሩ ላይ ጥሎ ወወገረ ዓጽፎ ውስተ ባሕር ይላል በሥላሴ ስም ትምህርተ መስቀል ባርኮ ዘሎ ከዓጽፋ ላይ ተቀመጠበት ተማሪዎቹም አብረው ተቀመጡ አራት መላእክት እንደቀዛፊ ሆነው ጌታም እንደመርከብ አለቃ አላፊ ሆኖ አይዟችሁ አትፍሩ እያለ ከማዕበሉና ከሞገዱ ያበረታታቸውና ያጽናናቸው ነበር ነገር ግን እሱ ልጆቹ ሆይ ከቂም በቀል ከክፋትና ከተንኮል ተጠበቁ በልባችሁ ቂም በቀል አትያዙ እያለ መከራቸው ነገር ግን ከእናንተ መካከል አንዱ ከባሕር ሠጥሞ ይጠፋል አላቸው ወዲያው ነገሩን ከአፉ ተናግሮ ሳይጨርስ ከተማሪዎች መካከል አንዱ በቅኔ ቤት ስሙን የማነ ብርሃን ይሉታል ከዓጽፋ ውስጥ ሾልኮ ከባሕር ገብቶ ሰጥሞ ቀረ ይህውም ተማሪ ልዩ የቂም የበቀል የክፋትና የተንኮል መዝገብ ነበረና ይለዋል ነገር ግን ጸልየው አውጥተውታል አባ ኤጲስጣቴጵስም በፈቃደ እግዚአብሔር ባሕሩን በተሻገረ ጊዜ ቆጵሮስና አርማንያ የተባሉ ተራራዎች ሰግደውለታል።

ከአርመኑ ሊቀ ጳጳሳት ተገናኝና ታላቅ ደስታ ተደሰተ አባ ኤጲስጣቴጵስም ለአሥራ ዓራት ዓመታታ የአርማንያን ሰዎች የሐዋርያትን ቀኖና የሲኖዶስን ስርዓት እያስተማራቸው ተቀመጠ ከዚህ በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት የሚለይበት ዕለት በደረሰ ጊዜ ጌታችን ተገልጾ ስሙን ለሚጠራ ዝክሩን ለሚዘክር ገድሉን ለሚጽፍ ቃል ኪዳን ሰጠው። ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ባረፈ ጊዜ ጳጳሳትና ካህናት አጥበው ገንዘው በታላቅ ክብር በሰማዕቱ በቅዱስ መርምህናም ቤተክርስቲያን ቀበሩት ዛሬም በዚያ አገር ስሙ የሚዘከርበት ቤተ መቅደስ አለ የጻድቁ ረድኤትና በረከት በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ምዕራፍ 19 ቁጥር 26

ታህሣሥ 19 ቀን ቅዱስ ገብርኤል

በሱባኤ ያስቆጠረው በነቢያት ያናገረው ሊደርስ ሲፈጸም የማያደርገውን የማይናገር የተናገረውን የማያስቀር አምላክ ገብርኤልን ከአመቤታችን ዘንድ አዝዞ ልኮ ሰደደው። ወበሳድስ ወርኅ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ አሐቲ ሃገር ዘገሊላ እንተ ስማ ናዝሬት ኀበ ድንግል እንተ ተፍኅረት ለብእሲ ዘስሙ ዮሴፍ ዘእምቤተ ዳዊት ወስማ ለይእቲ ድንግል ማርያም።

ቅዱስ ሉቃስ ወበሳድስ ወርኅ ያለው ከመቼ ዝምሮ ነው ቢሉ ኤልሳቤጥ ዮሐንስን በጸነሰችበት በስድስተኛው ወር ነው። አንድም ዓለም በተፈጠረ በስድስተኛው ሺህ ነው።

ስለምን በስድስተኛው ሺህ መጣ ቢሉ በስድስተኛው ቀን የተፈጠረ አዳም አምላክነትን ሽቶ በለስን በልቶ ከገነት ወድቆ ነበርና ርሱን ወደ ገነት ለመመለስ ስለዚህ በስድስተኛው ሺህ መጣ ገብርኤልም ከእመቤታችን ዘንድ መጥቶ ተፈሥሒ ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ባንቺ አድራለሁ ብሏልና ደስ ይበልሽ አላት። ወርእያ ደንገጸት እምቃሉ እንዳለ። እርሱዋም ገብርኤልን አይታ ከቃሉ የተነሣ ደነገጠች አንድም ሰሚዓ ማለት ነው።

ርእየን ሰምዓ የሚል ምን ምስክር አለህ?

ሄኖክ ምን ብሏል። ኦ ወልድየ አድንን እዘነከ ለርእየ ህልመ አቡከ ወውእቱኒ ርእዮ ህልመ አቡሁ ገብአ ብሏል። ስለምን ደነገጠች ቢሉ ሰምታው የማታውቀውን ቃል ብትሰማ ደነገጠች ወይቤላ መልአክ ኢትፍርሂ ማርያም አስመ ረከብኪ ሞገሰ በህበ እግዚአብሔር ወናሁ ትጸንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትሰምይዮ ስሞ ኢየሱስ እንዳለ። ገብርኤል አይዞሽ እመቤቴ ሆይ እኔም እንደ ዲያብሎስ የማስት መልአክ አይደለሁም አንቺም እንደ ሔዋን የምትሳሳች ሴት አይደለሽም ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና እነሆ ትጸንሻለሽ ልጅም ትወልጂያለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ አላት። ርስዋም ስትመልስለት ትቤሎ ማርያም ለመልአክ እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ እንዳለ።

ምድር እንበለ ዘር ሴት እንበለ ወንድ ትጸንስ ትወልድ ዘንድ ይህ በምን ይቻላል አለችው። እንዲህም ማለቷ እንደ ዘካርያስ ተጠራጥራ እንደ ኒቆዲሞስ ተከራክራ አይደለም ነገሩን እረዳው ብላ ነው እንጂ። ገብርኤል ሲመልስላት አስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር እንዳለ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለ ትያለሽ ሁሉም እንጂ ይቻለዋል። ርሱዋም ስትመልስለት «አወን ለእግዚአብሔርስ የሚሳነውም ነገር የለም ሁሉም ይቻለዋል።» ትቤሎ ማርያም ለመልአክ ነየ ዓመቱ ለእግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ እንዳለ። «እነሆ ለእግዚአብሔር ባርያው አለሁ አንተ እንዳልኸው ይሁንልኝ» አለችው። ወበሳድስ ወርኅ ካለው ጀምሮ እስከ ዚህ ድረስ ገብርኤልና እመቤታችን እየተመላለሱ የተነጋገሩበት ነገር ነው። ሉቃ.1÷26-39።

ገብርኤልስ የት ሳለች አበሰራት ከዮሴፍ ቤት ምን ስታደርግ አገኛት ቢሉ ለእመቤታችን ትሕትና ልማዷ ነበርና ውኃ ስትቀዳ። አንዱ መጽሐፍ ከዮሴፍ ቤት ይላል አንዱ መጽሐፍ ውኃ ስትቀዳ ይላል አንዱ መጽሐፍ ከቤተ መቅደስ ይላል አይደለምን ቢሉ አይደለም ይላሉ እንዴት ነዋ?

እንዲሁ ውኃ ስትቀዳ ደርሶ ሳይታይ «ተፈሥሒ ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ» አላት። ቀንታ ወዲህ ብታይ ወዲያ ብታይ አጣች። ምን መጣብኝ ብላ ደንግጣ ተነሥታ ወደ ቤት ሄደች ከቤትም እንደ

ቀድሞው ሁሉ ደርሶ ሳይታይ «ተፈሥሒ ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ አላት።» ወዲህ ብታይ ወዲያ ብታይ አጣችው። ወትሮ እንደልማድዋ ወደ ቤተ መቅደስ እየሔደች ሐሩን ወርቁን እያስማማች እየፈተለች ለቤተ መቅደስ መጋረጃ ለካህናት ልብስ ትሰጥ ነበረችና እንደ ወትሮዋ ሁሉ ተነሥታ ወደ ቤተ መቅደስ ሔደች እነሆ ዛሬ ሰው ለልማዱ ወደ ቤተ ክርስቲየን ሔዶ ስሞ አስተብርኮ መጽሐፍ ቢያገኝ አንሥቶ ገልጾ እንዲመለከት ሁሉ እርስዋም መጽሐፈ ኢሳይያስን ከቤተ መቅደስ አወጣችና አንሥታ ገልጻ ስትመለከት «ናሁ ድንግል ትጸንስ ወትወልድ ወልደ» ከሚለው አንቀጽ ደረሰች። ኢሳ.7÷14 ወዲያው «ከዚህች ዘመን ደርሼ እንጨት ሰብሬ አሙቂያት ውኃ ቀድቼ አጠጥቼአት ጫማዋን ይገር ተከትያት የእግርዋን ትቢያ አጥቤ ጠጥቼ» እያለች ትመኝ ጀመረች። አንድም ቀድሞ ስትመለከተው ነበረችና በልቡናዋ ታወጣው ታወርደው ጀመረች አንድም መጽሐፈ ኢሳይያስን በአትሮንስ ላይ ዘርግታ እየተመለከተች ሐሩን ወርቁን እያስማማች ስትፈትል ወእንዘ ትፈትል ወርቀ ወሜላተ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ እንዳለ ደርሶ ከፊቷ ቁሞ «ተፈሥሒ ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ» አላት።

በምን አርአያ ታያት ቢሉ። በአምሳለ ወሬዛ አንድም በአምሳለ ወሬዛ የታየቷት እንደሆነ ትደነግጣለች ብሎ በአምሳለ አረጋዊ አራሱ ሽብቶ ፊቱ በርቶ ሸንበቆ ተሸርኩዞ ታያት አንድም የብርሃን መስቀል ይዞ ታያት ይላሉ።

ስለምን ሦስት ጊዜ ተፈሥሒ ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ አላት ቢሉ ለአጽንኦተ ነገር። አንድም ለአጠይቆተ ሥሉስ ቅዱስ ነው ይላሉ።

ስለምን ሥጋዌን ለብሥራት አደረገው ቢሉ እመቤታችን እንዲያው ደርሳ ፀንሳ ብትገኝ ምን መጣብኝ ብላ ትደነግጥ ነበርና ስለዚህ ሥጋዌውን በብሥራት አደረገው። አንድም መናፍቃን ሥጋዌውን ምትሐት ነው ብለው እንዲነሱ ባወቀ ገንዘቡ ስለዚህ ሥጋዌውን በብሥራት አደረገው። አንድም

ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ብላ ያለችውን እምነት ምክንያት አድርጉ ሥጋ ለመልበስ ስለዚህ ሥጋዌውን በብሥራት አደረገው።

ብዙ ሊቃነ መላእክት ነበሩ ስለምን ገብርኤልን ለብሥራተ መረጠው ቢሉ። ቀድሞ ሚካኤልን መጋቤ ብሉይ አድርጉት ነበር ኋላም ገብርኤልን መጋቤ ሐዲስ ለማድረግ ስለዚህ ገብርኤልን ለብሥራት መረጠው። ዳግመኛም መላእክትን መቶ አለቃ መቶ ነገድ አድርጉ ፈጥሮዋቸው ነበር ከዚያው ከመቶው አለቃ ዲያብሎስን ለዘጠና ዘጠኙ አለቃ አድርጉ ፈጥሮት ነበር። ስሙንም ሳጥናኤል ይሉት ነበር። ሳጥናኤል ማለት ቅሩቦ እግዚአብሔር አጋዜ መንጦላዕት ማለት ነው። ኋላ ግን ቢስት ዲያብሎስ አለው። ዲያብሎስም ማለት ጥንብ፣ ግም፣ ሻጋታም ማለት ነው። ሰይጣንም አለው ሰይጣን ማለት መስህት መስተቃርን ማለት ነው። ጌልሆርም አለው። ቤልሆርም ማለት ርሑቅ እምአምላኩ ማለት ነው። ጋኔንም አለው ጋኔን ማለት ዕቡይ ማለት ነው።

መላእክትስ ሲፈጥራቸው እንዴት ፈጠራቸው ቢሉ። በድፍን ጨለማ ፈጥሮ ተሰወራቸው ወተሐውኩ ማኅበረ መላእክት እንዘ ይብሉ መኑ ፈጠረነ ለሊነኑ በርእስነ ተፈጠርነ እንዳለ አረግማን ፈጠረን ይሆን? እኛን በእኛ ተፈጣጠርን ወይ ፈጣሪያችንን አግኝተነው ሰጊድ ሰግደንለት ምሥጋና አቅርበንለት ብለው ተመኙ ያን ጊዜ ዲያብሎስ ቢያዳምጥ ድምጽ አጣ። ሁሉ ከርሱ በታች ሆኑ አነ ፈጣሪሆሙ ለፍጡራን እንዳለ የፍጡራን ፈጣሪያቸው እኔ ነኝ አለ። ያን ጊዜ ወጸርሐ ገብርኤል በዓቢይ ቃል ወይቤ ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ ብሎ ስለ አጸናቸው ስለዚህ ገብርኤልን ለብሥራት መረጠው። ዳግመኛም አዳምና ሔዋን ገነት በወጡ ጊዜ ረድቶአቸው ነበርና። ስለዚህ ገብርኤልን ለብሥራት መረጠው ዳግመኛም አይዞአችሁ እምራችሁአለሁ ብሎዋችኋል ብሎ የምሥራች ቃል ነግሮአቸው ነበርና ስለዚህ ገብርኤልን ለብሥራት መረጠው ዳግመኛም በስዓ ይተባበረዋል። ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ እግዚእ ወገብር ማለት ነው አማኑኤልም ማለት አምላክ ወሰብእ እግዚእ ወገብር ማለት ነው ስለዚህ ገብርኤልን ለብሥራት መረጠው ዳግመኛም ወለራብዕሰ ይመስል ገጹ ከ

ገጸ ወልደ እግዚአብሔር እንዳለ ናቡከደነጾር ዳን. 3 ÷ 24 በመልክም ይመስለዋልና ስለዚህ ገብርኤልን ለብሥራት መረጠው ዳግመኛም ጥንት አብሳሪ ነው። ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን ኢያቄምንና ሐናን አብስሮ ነበርና ስለዚህ ገብርኤልን ለብሥራት መረጠው ስንክ መስ. 26 ነሐ 7 አንድም ርሱ ባለቤቱ ገብርኤልን መልአኩን መስሎ አብስሮ አደረ ለልዱ አብሰርክዋ ለድንግል በአምሳለ ገብርኤል መልአክ እንዳለ ዳግመኛም «ቃል በቃሉ ተናገራ ወውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ» እንዳለ መጽሐፈ ጉዳንም በአምሳለ ገብርኤል ሊቀ መላእክት አስተርአይክዋ ለማርያም ወልባ ተወክፈ ዘተናገርክዋ አምነት ወሰሐቀት ወቃል ውስቴታ ቦእኩ ወሥጋ ኮንኩ ወለልየ ላእከ ኮንኩ ለርእሰየ እንዳለ ከዚህም በኋላ አብ ለማጽናት ወልድ ሥጋ ለመልበስ መንፈስ ቅዱስ። ለማንጻት ሦስቱ አካላት በማኅጸነ እግዝእትነ ማርያም አደሩ።

አብ ከምን ያጸናታል ቀድሞ ጽንዕተ ሥጋ ወነፍስ አልነበረችምን ቢሉ ምንም ጽንዕተ ሥጋ ወነፍስ ብትሆን ለማይና ምድር የማይችሉትን አምላክ አትችልም ነበርና እንድትችል አደረጋት። መንፈስ ቅዱስስ ከምን ያነጻታል ቢሉ ወኢረኩሰት እምዘፈጠራ ብሎ የለም ዳግመኛስ ወፈጠራ እምጽቡር ንጹሕ ብሎ የለም ዳግመኛስ ዓቀባ መንፈስ ቅዱስ ለማርያም እምከርሠ እማ ብሎ የለም ዳግመኛስ መንፈስ ቅዱስስ ከምን ያነጽታል ቀድሞ ንጽሕተ ሥጋ ወነፍስ አልነበረችምን ቢሉ ምንም ንጽሕተ ሥጋ ወነፍስ ብትሆን የአምላክ እናት ለመሆን አትበቃም ነበረና እንድትበቃ አደረጋት። ዳግመኛም እንበለ ሩካቤ እንበለ ዘርእ በድንግልና እንድትወልድ አደረጋት። ውእቱሰ ንጹሕ እምሠለሥቱ ግብራት ዘውእቶሙ ዘርእ ሩካቤ ወሰስሎተ ድንግልና እለ ሰሩአን በወልደ እጓለ እመ ሕያው ወእሙራት ቦሙ እንዳለ።

መንፈስ ቅዱስስ እንዳነጻት ምን ምስክር አለህ(ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ) ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ምን ብሏል። መንፈስ ቅዱስ ዘቀደሳ ወአንጽሐ ሥጋሃ ለማርያም ወረሰያ ድሉተ ለተወክፎ ቃለ አብ ብሎዋል። መንፈስ ቅዱስ ምንና ምን አደረገ አነጻ ፈጠረ ፈጠረም ማለት ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ

ከፈለ ማለት ነው። ያን የከፈለውን ሥጋ የት አደረገው ቢሉ ከአካለ ወልድ አዋሐደው አብን ለማጽናት ስለምን ፈለገው እርሱ አጽንቶ ባደረ ቢሉ ወልድ ሥጋ ለብሶ አዳነን ተቤዥን አብ ምን አደረገልን ብለው ምእመናን ከልቡናቸው ፍቅር ይከፍሉ ነበርና ስለዚህ አብ አጸና መንፈስ ቅዱስ ምን አደረገልን ብለው ምዕመናን ከልቡናቸው ፍቅር ይከፍሉ ነበርና ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ አነጻ ወልድ ሥጋ ለብሶ ተዋሀደ ሦስቱም ፈጠሩ ሦስቱም ከፈሉ ሦስቱም አዋሀዱ። አብ መንፈስ ቅዱስ ግን ከሥጋ ጋር አልተዋሀዱም ወልድ በተለየ አካሉ ከሥጋ ጋራ ተዋሀደ። ታሪኩ መጋቢት 29 ቀን የሚነገር ሲሆን ሊቃውንት በአብሣሪው ገብርኤል እንዲነገር ወስነውታል።

ቍጥር 27 ታህሣሥ 2 ቀን ሠለስቱ ደቂቅ

የዳንኤል እናት እህት ልጆች ሠለስቱ ደቂቅ እና ኢኮንያን የኤልያቄም ልጆች ናቸው ሁለቱ ነገዶች ሲማረኩ አብረው ተማርከው ሄደዋል። የእሥራኤልም መማረክ ሦስት ጊዜ ነው ኤር.52÷28-31 ስለምን ፃድቃንን ከኃጥአን ጋር ያስማርካቸዋል ቢሉ ስለ 3 ነገር 1/ ተማርከው በሄዱበት አገር ወደ ኃጢአት ወደ ጣዖት እንዳይሄዱ ይመክሯቸዋል፣ ያስተምሯቸዋልና 2/መስፍን ሆነው ይገዟቸዋልና እንደ ኤርምያስ እንደ መርዶክዮስ እንደ ጦቢት 3/ መከራ ከበዛ ዘንድ ፀጋ ክብር ይበዛልና። የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በነገሠ በ3ኛው ዘመን ናቡከደነጾር ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ባለሟሉ አስፋኒዝን ተማርከው ከመጡ ከነገሥታቱ ልጆች መልከ መልካም የሆኑትን፣ ጥበብ የሚስማማቸውን፣ እዉቀት ያላቸውን ቢቆሙ የማይታክቱትን ምረጥልኝ አለው።

ወይምሐሮሙ መጽሐፍ ወነገረ ፋርስ መጽሐፍ ፍልስፍና ጥንቆላ የመጽሐፍ ወግታሪክ ቋንቋ ያስተምራቸው። እኔ ከምበላው ከምጠጣው እየሰጡ ወይም ሐረዎሙ 3ተ ዓመተ ሕሙማ መብልዕ የሐምማ ልበ እንዲል ያልሆነ ምግብ ልቡናን ያደነቁራልና፣ እኔ ከምበላው እኔ ከምጠጣው እየሰጡ 3 ዓመት ይንከባከቧቸው አለው። ያን ጊዜ ብዙ ልጆች ተመረጡ። 3ቱ ደቂቅም አብረው ተመርጠዋል። ወወለጠ አስማቲሆሙ ሊቀ

ሕጽዋኒሁ ለንጉሥ፣ የንጉሥ አዛዥ ቢትወደዱ የሚሆን አስፋኒዝ ስማቸውን ለወጠ ስማቸውንም በአንጻር በአንጻሩ ያወጣል። ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሐር ፍትሐ እግዚአብሔር ማለት ነው ብልጣሶር አለው አምኃ ዳጎን ማለት ነው። አናንያ ማለት ደመና ማለት ነበር ሲድራቅ አለው ሰቃዩ አትክልት (አትክልት አጠጪ) ማለት ነው። አዛርያ ማለት ረድኤት ማለት ነበር። ሚሳቅ አለው ጸሐቂ፣ተጋሒ (ትጉ፣ ታታሪ፣ ፍንው ለግብረ መላእክት ማለት ነው ሚሳኤል ማለት ስምአኒ እግዚአበሔር ማለት ነበር አብደናጎ አለው ገብረ ዳጎን ማለት ነው ዳንኤል በልቡ ጥሬ እንብላ ብሎ ጨከነ። አስፋኒዝ አሜላድን ተወራጅ ሹሞላቸዋል። ዳንኤልም ማለደው እንዲህም አለው። ጥሬ ባቄላ ስጠን ስለምን? ቢሉ በተድላ በደስታ ከተማሩት ትምህርት በመከራ የተማሩት ትምህርት ይጠቅማል ብሎ እንዲሁም መከራ ከበዛ ዘንድ ፀጋ፣ክብር ይበዛልና ከንጉሥ ግብር ከሚበሉ ሰዎች ተለይታችሁ ከስታችሁ ንጉሥ ያየ እንደሆነ ከታች ባቴን፣ ከላይ አንጉቴን ይቀጣኛል ብዬ ለራሴ እፈራለሁ አላቸው እኛን ባሮችን ፈትነን አሉት የእነርሱን ድርጎ ራሱ እየተቀበለ ለእነዚያ ጥሬ እየሰጠ አስር ቀን ተቀመጠ ከአሥር ቀን በኋላ የንጉሡን ግብር ከሚበሉ ይልቅ ሰውነታቸው አምሮ፣ መልካቸው ጠርቶ ታየ ከዚህ በኋላ የእነርሱን ድርጉ ርሱ እየተቀበለ ለእነዚያ ጥሬ እየሰጠ ተቀመጠ ዳን. 1÷1-17 ከሦስት ዓመት በኋላ ንጉሥ አስመጥቶ ቢጠይቃቸው ወዘሐሰሰ ንጉሥ ምክረ ወጥበበ ረክበ በጎቤሆሙ ትስዕርተ እደ እምኩሉ ሰባ ሰገል ወእምኩሉ ሰብአ እስራኤል አለሀለው ውስተ መንግሥቱ በሚገዛው አገር ሁሉ ሥር ከሚምሉ ቅጠል ከሚበጥሱ ይልቅ ንጉሥ የፈለገውን ሁሉ ምክሩን፣ ጥበቡን ከእነዚያ ዘንድ አሥር እጥፍ በልጦ አገኘው አስመጥቶ ቢጠይቃቸው በአራተኛው ዘመን ንጉሥ ሕልም አይቶ ሕልሙም ትርጓሜውም ተዘነጋው። ስለምን ቢሉ የዳንኤልን ክብር የሚገልጽ መንፈስ ቅዱስ አዘንግቶታል። ከሚበላው አብልቶ፣ ከሚጠጣው አጠጥቶ የሚያኖራቸው ጠቢባን መፈክራነ ሕልም ነበሩት፣ አስመጥቶ ሕልም አይቼ ሕልሙም ትርጓሜውም ተዘንግቶኛልና ንገሩኝ አላቸው። ሕልሙን ንገረን ትርጓሜውን እኛ እንነግርሃለን አሉት አንተስ ከፈርኦን ታንሳለህን? እኛስ

ከዮሴፍ እንበልጣለን? ፈርኦን ሕልሙን ነገረው ዮሴፍ ተረጉመለት ዘፍ.41÷25 አሉት እኔስ ነገሩ ተዘንግቶኛል አላቸው። ባይሆንም ቀን ስጠን አሉት ኋላ ልቦለድ ነገር ትነግሩኛላችሁ አሁን ጊዜው ሳያልፍ ትዝ ትዝ ብሎኝ ሳለ ንገሩኝ አላቸው ይህም እንደምን ይሆንልናልና? አሉት እንግዲያው ከምበላው አብልቼ ከምጠጣው አጠጥቼ የማኖራቸሁ ለዚህ ብዬ ነው እንጂ በቅሎ አይደላችሁ አላሰግራችሁ ፈረስ አይደላችሁ አልጋልባችሁ፣ ጦር አይደላችሁ፣ አልወረውራችሁ፣ ጋሻ አይደላችሁ አልመክትባችሁ ለዚህ ብዬ አይደለምን አክብሬ የማኖራችሁ? ንሳ በሰይፍ በላቸው ብሎ አዘዘ።

ወወጽአ አርዬክ ሰያፊ ይላል ወደ መካነ ምቅታሉ (አርዮክ) ይዟቸው ሲሄድ ዳንኤልም አልነበረምና ከጕዳና ተገናኙ። ዳንኤልም በይነ ምንት ወጽአ ዝንቱ ትዕዛዝ እጹብ እምአበ ንጉሥ(ከንጉሥ ዘንድ እንዲህ ያለ ጭንቅ ትዕዛዝ ስለምን ታዘዘ?) ሲል ጠየቀው ንጉሥ ሕልም አይቶ ሕልሙም ትርጓሜው ተዘንግቶት ነው አለው። ይህንስ ሕልሙንም ትርጓሜውንም እኔ እነግረዋለሁ ይዘኸኝ ግባ አለው። ይዞት ገባ ለእነዚያ የነሳውን ቀን ለእርሱ 3 ቀናት ሰጠው ወዲያው ወደ ሠለስቱ ደቂቅ ይልካል ዳር ሲፈታ መካከል ዳር ይሆናል እንዲሉ ይህ ነገር በእኛም የማይቀር ነውና ቀኖና እንግባ ብሎ ላከ ለዳንኤል ዕለቱን ተገልጸለታል። ጥሬ እንብላ በማለት ጨክኖ ነበረና ስለተገለፀለት ግን ዕለቱን አልወጣም ሱባኤ የገባ ሰው ዕለቱን ቢገለጽለት ሱባኤውን ጨርሶ መውጣት እንዲገባ ለማጠየቅ ለሠለስቱ ደቂቅ በሦስተኛው ቀን ተገልጸላቸዋል። ከዚህ በኋላ ሕልሙንም ትርጓሜውንም አግኝቸዋለሁና ይዘኸኝ ግባ አለው። ይዞት ገባ አንተኑ ብልጣሶር ዘትክል አይድዖተ ሕልምየ ወፍካሬሁ ሕልሜን ከነትርጓሜው የምትነግረኝ አንተ ነህን? አለው ሕልምን እንጂ የሚተረጉም እግዚአብሔር የገለጸለት ነው ብሎ ዳንኤል ሃይማኖቱን ይሰብክል። ናቡከደፆር እግዚአብሔርን አያውቅም ነበርና በል ንገረኝ አለው ከዕለታት በአንድ ቀን በሰገነት ስትመላለስ የሴት ወይዘሮ የወንድ መኮንን ሲወጡ ሲገቡ ሲታጠቁ ሲፈቱ አይተህ እኔ ይህን ዓለም እንደ ገል ቀጥቅጬ እንደ ሰም አቅልጬ ገዛሁት ከእኔ በኋላ የሚነሣው ንጉሥ ከእኔ የሚበልጥ ይሆን ወይስ ከእኔ የሚያንስ ብለህ ተመኘህ መንፈስ

ቅዱስ የተመኙትን መግለጽ ልግዱ ነውና በራዕይ ይገልጽልሃል። ርእሱ ዘወርቅ፣ አንገቱ ደረቱ የብር፣ ወገቡ የብረት ጭንና ጭኑ የብረት አንድ እግሩ የሸክላ አንድ እግሩ የብረት ምስል ከፊትህ ቆሞ አንተ ርሱን ርሱ አንተን ሲመለከት ሳለ ከረጅም ተራራ የሰው እጅ ሳይፈነቅለው ታላቅ ድንጋይ ወርዶ ቀጥቅጦት በዓለሙ ሲሞላ ተመልሶ ተራራ ሲያህል ያንኑ ነፋስ ጠራርጉ ሲያጠፋው አላየህምን? አለው እሙን ሕልሙ /እልሙ እውነት ነው እስኪ ትርጓሜውን ንገረኝ አለው ርእሱ ዘወርቅ የተባልከው አንተ ነህ ወርቅ መክበበ ንዋያት ነው አንተም? ንጉሠ ነገሥት ነህና አንገቱ ደረቱ የብር የተባለ ዳርዮስ ነው የብር ማዕረጉ ከወርቅ ቀጥሎ ነውና ካንተም ቀጥሎ የሚነግሥ ርሱ ነውና ጭንና ጭኑ የብረት የተባለ እስክንድር ነው። ብረት ሀያል (ጽኑዕ) ነው እርሱም ኃያል ንጉሥ ነውና የብረት ድምጽ ከሩቅ ይሰማል የእርሱም ዜና መንግሥቱ ከሩቅ ተሰምቶአልና አንድ እግሩ የብረት አንድ እግሩ የሸክላ የተባሉ እስክንድር ያነገሣቸው ነገሥታት ናቸው። በብረት የተመሰሉት በጥሊሞስ አንጥያኮስ ናቸው። በሸክላ የተመሰሉት ስልዊስ ደማጥርያኖስ ናቸው። ይህስ አይደለም ብሎ በመንግሥት ያወርዱታል። ርእሱ ዘወርቅ የተባለ መንግሥተ ባቢሎን ነው አንገቱ የብር የተባለ መነግሥተ ሜዶን ነው። ወገቡ የብረት የተባለ መንግሥተ ፋርስ ነው ጭንና ጭኑ የብረት የተባለ መንግሥተ ጽርዕ ነው አንድ እግሩ የሸክላ አንድ እግሩ የብረት ምስል የተባለ እለሕውሳን በዘርእ የሚላቸው ረጅሟ አጭር ጥቁር ቀይ ሆነው በሮም የነገሡ ነገሥታት ናቸው። ከረጅም ተራራ የሰው ልጅ ሳይፈነቅለው ታላቅ ድንጋይ ወርዶ ይህን ሁሉ አድቅቆ በዓለሙ ሲመላ ማየትህ በኋላ ዘመን ጌታ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ እነዚህን ሁሉ አጥፍቶ በዚህ ዓለም መንገሡን ይገልፃል፣ ዕሩያ መንበር ይሆናል እሙን ሕልሙ ወትርጉሜሁ፣ ሕልሙም ትርጓሜውም የቀና ነው ብሎ ለእግዚአብሔር ሰገደ ዳን. 2÷1-46 ዳንኤልንም ቢትወደዱ አድርጉ ሾመው ወግዱ በዘመኑ እንዲሉ ዳንኤል ከንጉሡ ተካስሶ አቤቱታ አቅርቦ ሠለስቱ ደቂቅን ግራአዝማችነት፣ ከንቲባነት አሹሟቸዋል። ለለምን ቢሉ እነርሱ በገጠር

እርሱ በስተማ የሚኖሩ ሆነዋል። ትምህርት እንዲስፋፋ ከዚህ በኋላ ናቡከደነጾር በነገሠ በ18ኛው ዘመን በሠለስቱ ደቂቅ ቀናን ያሉ ሰዎች ርእሱ ዘወርቅ የተባልክ አንተ ነህና 60 ክንድ ቁመቱ 6 ክንድ ደረቱ ጣዖት አቁም ሁሉ ለእርሡ ይስገዱ አሉት እንደነገሩት 60 ክንድ ቁመቱ 6 ክንድ ደረቱ ጣዖት በሀቅለ ዱራ አቆመ። በዚህ ጊዜ ለአሠራህው ለወርቅ ምስል ያልሠገዱ አምላክህን ያላመለኩ፣ በባቢሎን የሾምካቸው ሦስት ሰዎች አሉ ብለው ለንጉሡ ለናቡከደነፆር ነገሩት ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ ሲድራቅ፣ሚሳቅ፣ አብደናጎን ያመጡአቸው ዘንድ አዘዘ። አመጡአቸው ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ አብደናጐን በእውነት ፈጣሪዬን አታመልኩምን ለሠራሁት ለወርቅ ምስልስ አትሠግዱምን አላቸው አምላክህን እናመልካለን ብለን ልንመልስልህ አንወድም አሉት። እኛ የምናመልከው ፈጣሪያችን በሰማይ አለ ከአንተ እጅ እኛን ማዳን ይቻለዋል ንጉሥ ግዱን ቁርጡን ታውቅ አምላክህን አናመልክም ላሠራህው የወርቅ ምስልም አንሠግድም አሉት። ያን ጊዜ ንጉሡ ሰይፍ መዘዘባቸው፤ ጦር ነጠቀባቸው። እሳቱን እጥፍ ድርብ አድርገው ያነዱት ዘንድ አዘዘ ሃያላኑ ጽኑአኑ እጃቸውንና እግራቸውን ይዘው ከእቶነ እሳት ይጥሏቸው ዘንድ አዘዘ። እጃቸውን እግራቸውን አስረው ከነልብሳቸው ፣ ከነጫማቸውና ቍንጽል ቀሚሳቸው፣ ከነመጐናፀፊያቸው፣ ከነኩፊታቸው በተራ እየገፋ ከእሳት ጉድጓድ ጣሏቸው አላልቦ ይገድላቸዋል ብሎ እሳቱም በረደላቸው የንጉሥ ሎሌዎች ግን ነገር መሥራታቸውን አልተውም በምትሐት እንጂ አበረዱት ብለው ነገሩት ደም ደም ያለውን እንጨት፣ ቅንጭቡን፣ ቁልቋሉን፣ ድኙን፣ አይድሮማሩን ጨመሩበት ወተለለለ ነበልባል አርባ ወተሰዓተ እመተ ነበልባሉ አርባ ዘጠኝ ክንድ ከፍ ከፍ አለ በምን ታውቋል ቢሉ ከጉድጓዱ ታላቅ ዛፍ ነበር ቢሰፍሩት 49 ክንድ ሆኗል ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወዘበጦ ለነበልባለ እሳት ወረሰዮ ከመነፋስ ቆሪር ይላል መላኩ ቅ. ገብርኤል ወርዶ ነበልባሉን ቢመታው እንደጠል አቀዘቀዘው ዳን. 3÷1-ፍፃ. በዚህ ጊዜ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው አመስግነዋል። ናቡከደነፆር ሲያመሰግኑ ሰምቶ አደነቀ። ሦስት ሰዎች አሥረን ከእቶነ እሳት ጥለን አልነበረምን? እነሆ

አራት ሰዎች የተፈቱ ሆነው በእቶነ እሳቱ ሲመላለሱ አየሁ ወገዱ ለራብዓይ ይመስል ከመ ወልደ እግዚአብሔር ለአራተኛው የእግዚአብሔርን የባህርይ ልጁን ይመስላል አለ። አምን ያለ ባላጋራ ከስሩ የተነቀለ ወይራ እንዲሉ መንፈስ ቅዱስ ፊቱን ፀፍቶ አፉን ከፍቶ አናግሮታል ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ ማለት ነውና ናቡከደነፆር ከጉድጓዱ አፍ ቀረብ በሉ አንትሙ አግብርተ እግዘብሔር ሲድራቅ ወሚሳቅ ወአብደናጎ ንዑ ፃዑ ባላቸው ጊዜ እንደ ሳቢላ የወፍ ዘር ነጭ ሆነው በክንፈ ፀጋ ብር ብር ብለው ወጥተዋል። ከዚህ በኋላ አዋጁን በአዋጅ መልሶታል። እመቦ ዘነበበ ወፀረፈ ላዕለ አምላከ ሲድራቅ ወሚሳቅ ወአብደናጐ ይትበረበር ቤቱ፣ ወይትኩነን ነፍሱ ብሎ አወጀ እነርሱም ከዚህ በታች ያሉትን 6 መስመሮች ተናግረዋል ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ወይትባረክ ከመ ስብሐቲሁ ቅዱስ ቡሩክ አንተ በጽርሐ ቅድሳተ ስብሐቲከ፤ ቡሩክ አንተ ዘትሬኢ ቀላያተ ነቢረከላዕለ ኪሩቤል፣ ቡሩክ አንተ በዲበ መንበረ መንግሥትከ ቡሩክ አንተ በመልዕልተ ሰማያት ብለው አመሰግነዋል። እነዚህን 6ቱን መናገራቸው እኛ እቶነ እሳት በወደቅን በ600 ዘመን ጌታሥጋ ለብሶ ቅድስት ድንግል ከምትሆን ከእመቤታችን ይወለዳል ሲሉ ነው ብለው ሊቃውንት ተረጉመውታል። ይባርክዎ ኩሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር የሚለውንም በ33 መስመር ደርሰውታል ይሄም ከተወለደ በኋላ 33 ዓመት በምድር ላይ እንዲኖር ያመለክታል በዘመናቸው የነበረ ዳንኤል ከ490 ዘመን አለሳ? ቢሉ ዳን. 9÷25 ዳንኤል ከሚጠት እስከ ጽንስ ያለውን ቆጥሮ እነርሱ ከጹዋ እስከ ዕርገት ያለውን ቆጥረው ይኸውም በነገሥታቱ ዘመን ይታወቃል ናቡከደነፆር ንጉሠ ነገሥት የሆነበት ዘመን 25፣ የዮርማሮዴቅ 22፣ የብልጣሶር 23 ይህን ቢደምሩት 70 ይሆናል። ጌታ በዚህ ዓለም የኖረው 33 ዓመት ከ3 ወር ይህን ከ70 ቢደምሩት 103 ይሆናል። ከሴዴቅያስ 7 ዓመት አምጥተው ቢደምሩበት 110 ይሆናል። ከ 490 ጋር ቢደምሩት 600 ይሆናል 600 ዘመን ያለበት ምክንያት ይህ ነው ስለዚህ ነው ሊቁም ኢየሱስ ክርስቶስ ሞገስ ዳንኤል ነቢየ ሱሳ ድኅረ ተፈፀመ ሱባኤ ሰንበታት ስሳ፣ በምጽዓትከ ተኃትመ አበሳ ያለው የሰለስቱ ድቁቅ ረድኤትና በረከት አይለየን። አሜን።

ምዕራፍ 20 ቁጥር 28

ሰኔ 20 ቀን ሕንፀተ ቤተክርስቲያን

ጌታ ባረገ በ8 ዓመት ቅዱስ ጳውሎስ አመነ ጳውሎስና በርናባስ ፊልጵስዩስ ገብተው አስተማሩ ሕዝቡም አመኑ ተጠመቁ ከአመናችሁ ከተጠመቃችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ቤተ ጣዖት አትሂዱ አሏቸው የለመድነውንማ ከነሣችሁን መካነ ጸሎት ለዩልን አሏቸው እነሱም ነገሩ ደግ እንደሆነ አውቀው ምንስ ቢሆን ሴት ብታወቅ በወንድ ያልቅ እንዲሉ ርእሰ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ እያለ እኛ ሥራ መሥራት አይገባንም ብለው ላኩበት ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር በኢየሩሳሌም ተገኘ ሁሉን ዙረው መርምረው አስተምረው መዲናይቱን ኢየሩሳሌም አድርገው ነበር። ብዙ ሥራ ሠርተውባታልና በዚህ ያሉ ምእመናን ለመጽናትዋ ይላሉ ርሳቸውም አልቦ ዘትገብሩ ምንተኒ ዘእንበለ በትእዛዙ ወምክሩ ለእግዚእነ ኢየሱስ ይላል ብለው ላኩባቸው። ሱባኤ ያዙ ሱባኤው ሲፈጸም ጌታ ሐዋርያትን ዋሞቱትን አሥነሥቶ ያሉትን ጠርቶ በሕይወተ ሥጋ በፊልጵስዩስ ሰበሰባቸው ዮሐንስ ቅዱስ ጴጥሮስን አበዓለም ነህና የሰበሰበንን ምክንያቱን ጠይቀህ ንገረን አለው ቅዱስ ጴጥሮስም ቀድሞ በምሴተ ሐሙስ የጠየቅከው አንተ ነህና አንተ ጠይቀው አለው ዮሐ.13÷24 ዮሐንስም ጌታዬ ስለምን ሰብስበኸናል አለው ጌታም በእናቴ ስም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የአብያተ ክርስቲያንን ሕንፃ ሥራ ላሳያችሁ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ላስተምራችሁ ሰብስቤያችኋለሁ አለው። ይኸን ብሏቸው ወደ ምሥራቅ አገር ይዟቸው ወጣ ከዚያ በምሥራቅ አገር ሦስት ድንጋዮች ነበሩ ተራርቀው የነበሩትን አቀራረባቸው ጥቃቅን የነበሩትን ታላላቅ አደረጋቸው ቁመቱን ወርዱን ለክቶ ሰጣቸው ራእ.1÷1፣19 ቁመቱ 24 ወርዱ 12 ክንድ ነው 24ቱ በነገሥታት ያሉ የ24ቱ ነቢያት አንድም የ24ቱ ካህናተ ሰማይ አምሳል ነው 12ቱ ወርዱ የ 12 ሐዋርያት አምሳል ነው። ከዚህ በኋላ ሥራ ጀመሩ ሲሰሩትም ሰማእት ሲያሳዩት እንዲለመልም በጃቸው ላይ እየተሳበ ሰርተው ፈጽመውታል። ይህ የሆነው ጌታችን ባረገ በ19ኛው እመቤታችን ባረገች በ

ዓመት በሰኔ 20 ቀን ነው በ21 ኛው ቀን ጎብስት ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ መጣ እመቤታችንን ታቦት ሐዋርያትን ልውሳን አድርጉ ጌታ ዓቢይ ካህን ሆኖ ቀድሶ አቁርቧቸዋል። እምይእዜሰ አንትሙኒ ከመዝግበሩ ብሎ አዟቸው አረገ።

ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረ ከዚያ ወዲህ ነው 3ቱ ድንጊያዎች የሥላሴ አምሳል ናቸው። ከታች አቀማመጣቸው 3 ከላይ ሕንፃቸው 1 ነው ይህም ያንድነታቸው የሦስትነታቸው አምሳል ነው። በሠላስ አዕባን ገፀ ሥላሴሁ ለአምሮ ሐኒጸ ቤትኪ ድንግል ድኅረ ፈፀመ ሣርሮ እንዳለ ደራሲ ሲሰሩትም 3 ክፍል አድርገው ሠርተውታል መጀመሪያው የታቦተ አዳም ሁለኛው የታቦተ ሙሴ ሦስተኛው የታቦተ ኢየሱስ አምሳል ነው። ዳግመኛ ም ሥርዓተ ሰማይ ተሠርዓ በዲበ ምድር እንዲል የሦስቱ ዓለመ መላእክት ምሳሌ ነው። የመጀመሪያው የጽርሐ አርያም ሁለተኛው የኢዮር ሦስተኛው የጠፈር አምሳል ነው። በጽርሐ አርያም መንበረ ብርሃን ታቦተ ብርሃን መንጦላዕተ ብርሃን 4 ፀወርተ መንበር 24 አጠንተ መንበር ይኖራሉ ጽርሐ አርያም የመቅደስ መንበረ ብርሃን የመንበር መጦላዕተ ብርሃን የመንጦላዕት 4ቱ ፀወርተ መንበር የ4ቱ ሊቃነ ጳጳሳት 24ቱ አጠንተ መንበር የጳጳሳት የኤጲስ ቆጳሳት አምሳል ናቸው። ኢዮር የመካከለኛው በኢዮር የሚኖሩ መላእክት የቀሳውስት የዲያቆናት አምሳል ናቸው ጠፈር የዙሪያው በጠፈር የሚኖሩ መላእክት የንፍቀ ዲያቆናት የአናጉንስጢሳውያን የመዘምራን አምሳል ናቸው። አንድም መጀመያው ለኤረር 2ተኛው ለራማ 3ተኛው ለኢዮር አምሳል ነው በኤረር መላእክት መኳንንት ሊቃናት ይኖራሉ በራማ ሥልጣናት መናብርት አርባብ ይኖራሉ በኢዮር ኃይላት ኪሩቤል ሱራፌል ይኖራሉ እኒህ 9ኙ ነገድ የ9ኙ መዓረጋተ ቤተክርስቲያን አምሳል ናቸው መላእክት የመዘምራን መኳንንት የአናጉንስጢሳውያን ሊቃናት የንፍቀ ዲያቆናት ሥልጣናት የዲያቆናት መናብርት የቀሳውስት አርባብ የቆሞሳት ኃይላት የኤጲስ ቆጳሳት ሱራፌል የጳጳሳት ኪሩቤል የሊቃነ ጳጳሳት አምሳል ናቸው በታች የሚኖሩ ደቂቀ አዳም ወደ ላይ መውጣት እንዳይቻላቸው መዘምራን የአናጉንስጢሳውያንና አናጉንስጢሳውያን የንፍቀ ዲያቆናትን

ንፍቀ ዲያቆናት የዲያቆናትን ዲያቆናት የቀሳውስትን ቀሳውስት የቆሞሳትን ቆሞሳት የኤጲስ ቆጳሳትን ኤጲስ ቆጳሳት የጳጳሳትን ጳጳሳት የሊቃነ ጳጳሳትን ሥራ መሥራት አይቻላቸውም በላይ የሚኖሩ መላእክት ግን ወደ ታች መውረድ እንዲቻላቸው ሊቃነ ጳጳሳት የጳጳሳትን ጳጳሳት የኤጲስ ቆጳሳትን ኤጲስ ቆጳሳት የቆሞሳትን ቆሞሳት የቀሳውስትን ቀሳውስት የዲያቆናትን ዲያቆናት የአናጉንስጢስን አናገንስጢስ የመዘመራንን ሥራ መስራት ይቻላቸዋል::

መስከረም 21 ቀን በዓለ ማርያም መቅድም

ማርያም (ዕብ) ማርያም የነቢያት የሙሴና የአሮን እህት (ዘፀ 15 ÷20) ቃሉ 2 ነው ማር፣ ሚር አንድ ወገን መራራ መራጭ ያም ዮም ዕለት ዘመን መዋዕል በተገናኘ ምርርተ ዮም ወይም መራረ መዋዕል ዘመሪር መዋዕሊሃ ዘመኗ ዘመነ ልደቷ ማሩር የተባለው ማሉል ፈርኦን በእስራኤል ላይ ክፋ ምክር መክሮ ወንድ ወንዱ ለሞት ሴት ሴቱ ለትሎት ብሎ መራራ ዐዋጅ ያስነገረበት እስራኤልም ዕርር ምርር ብለው ያዘኑበት ያለቀሱበት የሐዘን የመከራ ወራት ስለሆነ አባት እናቷ ዘበመዋዕሊሃ አምረሩ ግብጸ ሕይወቶሙ እስራኤል ሲሉ እንደዚህ ያለ ስም ሰጥተዋታል ዘፀ. 1 ÷ 8-16 :: ብሊት ማርያም የብሉይ ኪዳን ጥንት እንደ ሆነች ሀዳስ ማርያምም የሐዲስ ኪዳን ጥንት ናትና አስቀድሞ በማርያም ዘመን የሆነውን ግፍና መከራ ድንቅ ሥራ ሁሉ ጎላ በድንግል ማርያም ለሚሆነው አምላል መርገፍ ሆና ተጥፋለች (ዕብ. 10÷1) ማርያሞች እንዲነጻፀሩ ፈርኦንና ሄሮድስ ሙሴና ክርስቶስ ንሴብሑና ታዕብዮ ይነፃፀራሉ(ዘፀ. 15÷1-21) (ሉቃ. 1÷46-55) ብሊት ማርያም በልደተ ሥጋ እህተ ሙሴ እንደ ተባለች ሀዳስ ማርያምም ለስግው ቃል ልጁ በልደተ ነፍስ እህት ትባላለች ማስተባበር ልማዷ እንጂ ድንግልናን ከወሊድ እንዳስተባበረች እህትነትንም ከናትነት አስተባብራለች በሰንበት ላይ ደብረ ዘይት እንዲሉ

የማርያም የስሚ ትርጉም

ማርያም ማለት እግዝእተ ብዙኃን ማለት ነው አብርሃም ማለት ኀበ ብዙሐን ማለት እንደሆነ (ዘፍ. 17÷1-5) በአኗኗርም ትመስለዋለች አብርሃም ወደ ከነዓን ዘፍ. 12÷1 እመቤታችን ወደ ቤተመቅደስ መዝ. 44÷10 ዘበዕብራይስጢ ማርያም ይላል ብሎ ማርያም ማለት ቅሉ እግዝእተ ብዙኃን ማለት ነው::

ማርያም ማለት መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው:: ምእመናንእየመራች ገነት መንግሥተ ሰማያት ታገባለችና አንድም ፍጽምት ማለት ነው ኖህ ፍፁም ነበር (ዘፍ. 6÷9) መልክ ከደምግባት አስተባብራ ይዛ ተገኝታለችና ፍፁሜው ግን ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና አንድም ማርያም ማለት ፀጋ ወሀብት ማለት ነው ለጊዜው ለእናት ለአባቷ ፀጋ ሀብት ሁና ተሰጥታለች ፍፁሜውግን ለሁላችን ተሰጥታለችና (ሉቃ. 1÷28) አንድም ልዕልት ማለት ነው አርያም ማለት ልዑል ማለት እንደሆነ እመቤታችንም መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ይላታልና አንድም ተለአኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ ማኅበረ መሃይምናን ወሕዝብ ማለት ነው:: ማርያም ማለት በምድር ማር በሰማይ ያም የሚለው ቃል ተገናኝቶ የተገኘ ስም ነው በምድር በሚኖሩ ሰዎች ዘንድ በጣፋጭነቱ የሚታወቅና በጣዕሙ ወደር የሌለው ምግብ ማር ነው እንዲሁም በገነት ቅዱሳን የሚመገቡት በብሔረ ሕያዋንና በብሔረ ብፁዓን ለሚኖሩ ቅዱሳን ብቻ የሆነ እጅግ የሚጣፍጥ ያም የሚባል ምግብ አለ የእመቤታችን ርኅራኄ እና ፍቅሯ በምድር ባሉና በሰማይ በሚኖሩ ሁሉ ዘንድ እጅግ ጣፋጭ በመሆኑ ማርያም ተብላለች ጣዕሟና ፍቅሯ የማይጠገብ ነውና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ (በዮሐ.3÷12) ስለምድራዊ ነገር ስነግራችሁ ካላመናችሁ ስለሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ እንዳለ ዛሬም በምድር ባለው በስዕሏ ክብር ጠበሏ ፈውስ ያላመኑ ሰዎች ከዚህ ከፍ ያለ ነገር መቀበል ይቸገሩ ሆናል:: እነርሱ ቢቸገሩም እውነቱ ግን ይኸው ነው ከዚህ ከተገለጠው ተጨማሪ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የስሟ አራት ፊደላት

ቀጥሎ በተመለከተው አይነት በምስጢር ተተርጕመዋል ይህም አባቶች ለእመቤታችን ላላቸው ፍቅር ሲገልጡ ነው በዚህ መሠረት ማ : ማህደረ መለኮት የመለኮት ማደሪያ መሆኗን ያጠይቃል (መዝ. 45 ÷4) ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ መዝ. 131 ÷13) አለሙ ሁሉ መጻፍ ያዘዘውን በዚህ አለ በዚያ የለም የማይባለውን የሚችለው የሌለውን ረቂቁን ባህርየ መለኮት በማህፀኗ የተሸከመች ስለሆነች የመለኮት ማደሪያ ትባላለች ር፡ ርግብዬ ይቤላ ሰሎሞን ርግብዬ ይላታል መደምደሚያም አንዲት ናት ለወላጆቿ የተመረጠች ናት። ልጆች ባዩአት ጊዜም አመሠገኑአት ነገሥታትና አባቶቿም ምሥጋና ሰጡአት ይህች ማን ናት እንደ ማለዳ ብርሃን የምትጐበኝ እንደ ጨረቃ የተዋበች እንደ ፀሐይ የጠራች።

(መኃ. 6÷9) ብሏታል እመቤታችን ርግብ ስለ ሰው ወደ እግዚአብሔር በአማላጅነት የምትላክ የሠላም መልዕክተኛ የምሥራች ነጋሪ ናትና ርግብ እንላት አለን የጥፋት የምሥራቹን ለኖህ ያበሠረችው ርግብ ናት (ዘፍ. 8÷8-12) በአዳምና በልጆቹ ላይ ታዞ የነበረው ጥፋትና የሲኦል መከራ ማክተም የሆነች ድንግል ማርያም ናት ርግብ የየዋህነት ምሣሌ ናት ማቴ. 10÷16) ምክንያቱም ጌታ ከእሷ ጋር ነውና (ሉቃስ. 1÷28) ያ፡ ማለት ያንቀአዱ ሃቤኪ ኩሉ ፍጥረት ፍጥረት ሁሉ ለምኝልን እያሉ ወደ አንቺ ያንጋጥጣሉ ማለት ነው ሰውን ከእግዚአብሔር የምታስታርቅ በሰውና በፈጣሪ መካከል የምትገኝ የፍጥረት ሁሉ አማላጅ በመሆኗ ፍጥረት ሁሉ አማልጂን እያሉ ያንጋጥጣሉ ከፈጣሪ ምሕረትና ይቅርታን የምታስገኝ ናትና ስለዚህ ሰው ከወደ በላዩ ማንጋጠጥ የተለመደ ነው ድንግል ማርያም ከሁሉ በላይ ናትና ወደ ርሷ እናንጋጥጣለን የሐዋ. 3÷3-10÷ም፡ ማለት ምስአል ወምስጋድ ወምስትስራየ ኃጢአት መስገኛ መለመኛ የኃጢአት ማስተሰሪያ ማለት ነው የሚሠገደው የሚለመነው በተቀደሰ ሥፍራ እግዚአብሔር ፀጋውንና ክብሩን ባሳደረበት ቦታ ነው። ይህን የመሰለው ስግደትና ልመና ጸሎት ኃጢአትን ያስተሰርያል (2ኛ ዜና. 7÷11-17) በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ያደረባት በቅዱስ መንፈሱ የጐበኛት በምንለምንበት ቅዱስ

ሥፍራ ሁሉ የምትመለል ቅድስት ድንግል ማርያም መስገኛ መለመኛና የኃጢአት ማስተሰረያ ትባላለች። በአማላጅነቷ ኃጢአታችንን እንድታስተሰርይልን ቅድስት ሆይ ለምኝልን እንላታለን በአጠቃላይ ማርያም ማለት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በፍፁም ፍቅሯና የዋህነት ለሰዎች ድህነት በምልጃ የምትላላክ የምታገናኝ ድልድይ መሠላል ማለት ነው። እስራኤል ኤርምያስን እንደለመኑትና ወደ እግዚአብሔር እንደላኩት እመቤታችንም ወደ እግዚአብሔር እንልካታለን(ኤር. 42÷2) ጽዮን (ዕብ) ስመ ሀገር የኢያውሴዎን አምባ ዳዊት የያዛት አገር ዳዊት ፍችው ፀወን ምልክት ማለት ነው መዝ. 2÷6 ፣ 2ሳሙ. 5÷6 የድንግል ማርያም ስም መዝ. 86÷5፣ 131÷13። ሶልያና (ጽር ሴሊኒ) ጨረቃ፡ ድንግል ማርያም ጊዜ ዕረፍታ ለሶልያና እንዳለ ድጓ በቅጽል ስሟም ድንግል ትባላለች ኢሳ. 7÷14፣ ሉቃ. 1÷27 ።

ምዕራፍ 21 ቊጥር 29

መስከረም 21 ቀን ብዙኃን ማርያም ታሪክ

መስከረም 21 ቀን የብዙኃን ማርያም እየተባለ ይጠራል። ይህ ዕለት የሚታወሰው በሁለት ምክንያቶች ነው አንደኛው ሊቃውንት በሃይማኖት ምክንያት ከሩቅም ከቅርብም የተሰበሰቡበት ሲሆን ሁለተኛው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በአምባሰል ተራራ ግሸን ደብረ ከርቤ ቤተ መቅደስ ተሠርቶ የተቀመጠ በቹ ነው። ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታቸዋለን ፴25 ዓ.ም አርዮስ የሚባል አንድ የእስክንድርያ ቄስ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ እግዚአብሔር አብ በመጀመሪያ ወልድን ፈጥሮ በወልድ አለምን ፈጠረበት ብሎ ተነሣ በዚያን ወቅት ታላቁ ቆስጠንጢኖስ አብያተ ጣዖታት ይትአጸዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትርኃዋ ብሎ አዋጅ የነገረበት ነበር ይህ የአርዮስ ክህደት በሊቃውንቱ መካከል መለያየትን ፈጠረ አርዮስም ይህንን ክህደት ትምህርቱን እንዲተው ሲመክሩት አልተውም አሻፈረኝ አለ። ታላቁና ጻድቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ጉባኤ ኒቅያ እንዲደረግ ሊቃውንቱም ሁሉ እንዲሰበሰቡ በየሀገሩ መልዕክቱን አስተላለፈ ከሚያዝያ

21 ቀን ጀምሮ እስከ መስከረም 21 ድረስ 2348 ሊቃውንት ተሰበሰቡ ለዚህ ታላቅ ጉባኤ ኒቅያ የተመረጠችው ጳጳሱን ከማህበሩ ንጉሡን ከሠራዊቱ ጋር አንድ አድርጋ አጠቃላ ለመያዝ የምትችል ሠፊና ምቹ ቦታ ለሁሉም አማካይ የሆነች ሥፍራ ስለሆነች ነው። ከተሰበሰቡት ሊቃውንት መካከል እንደ ሐዋርያት ሙታን ያላሥነሡ ፣ ለምጽ ያላነጹ ፣ አንካሣ ያላረቱ፣ የዕውራንን ዐይን ያላበሩ፣ ድውያንን ያልፈወሡ፣ ሌላም ልዩ ልዩ ተዓምር ያላደረጉ አይገኙም ነበር። እንዲሁም ስለሃይማኖት በመጋደል አይናቸው የወጣ እጃቸው የተቆረጠ ነበሩ።

ከላይ እንደተገለፀው ከሚያዝያ 21 እስከ መስከረም 21 ቀን ሊቃውንቱ ቢሰበሰቡም ክርክሩ ወድያው አልተጀመረም እስከ ጎዳር 9 ቀን በጸሎት በሱባኤ ቆይተዋል ጉባኤውን በሊቀመንበርነት የሚመራው ታላቁ ቄስጠንጢኖስ ስለ ነበር ስማችሁን አገራችሁን ሃይማኖታችሁን እየፃፋችሁ ስጡኝ አላቸው ሁሉም እየፃፉ ሰጡት ከ2348ቱ ሊቃውንት መካከል ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን ፣ ዘፅሩይ ምስለ አብ በመለኩቱ » ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮት በሥልጣን በፈቃድ በህልውና አንድ ነው ብለው ጽፈው ሰጡት ቄስጠንጢኖስም ሃይማኖት እንደ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት ይሁን ብሎ አዋጅ አስነግሯል። ምላሌዎቻቸውም ዘፍ.14÷14 ያለው ነው። እነርሱም « ነአምን በአሀዱ አምላክ» በአንድ አምላክ እናምናለን በማለት የሃይማኖት ጸሎትና ሌሎችንም የሃይማኖት መፃሕፍትን ደርሰው አዘጋጅተው ከመወሰናቸውም ሌላ አርዮስንም አውግዘው ተለያይተዋል። ምንም የሃይማኖት ጉባኤ የተደረገው ህዳር 9 ቀን መሆኑ ቢታወቅም ሊቃውንቱ የተሰበሰቡትና የተገኙት መስከረም 21 ቀን በመሆኑ ዕለቱ ብዙኀን ማርያም እየተባለ ይጠራል። በሌላ በኩል ደግሞ መስከረም 21 ቀን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል በግሸን የከበረበት ዕለት በመሆኑ ሁሉም ወደዚህ ቦታ በእግረ ሥጋና በእግረ ኀሊና ይገሰግሳል። ታሪኩም በአጭሩ እንደ ሚከተለው ስለሆነ በጽሞና እንመለከተዋለን። አፄ ዳዊት መንፈሳዊነት ያላቸው ደግ ንጉሥ ነበሩ።

በዘመናቸው በኢትዮጵያ አገር ቸነፈር ሆኖ ህዝቡ ስለተሰቃየባቸው በጣም አዘኑ በጸሎትም ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክቱ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ደግ ባህታዊ መጥቶ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል አስመጥተህ በአገርህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሠርተህ ብታስቀምጥ ረሀቡ ቸነፈሩ ሁሉ ይታገስልሃል አላቸው፤ አፄ ዳዊትም የጌታችን መስቀል ላኩልኝ ብለው ከብዙ ገፀ በረከት ጋር መልእክተኞችን ላኩ መልእክተኞቹ ወደ ኢየሩሳሌም ሂደው ከዓፄ ዳዊት የተላኩትን መልእክት ከገፀ በረከት ጋር አቅርበው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን የቀኝ እጁ የተዘረጋበትን መስቀል ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መምጣታቸውን አፄ ዳዊት ስለሰሙ ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ለመቀበል ጉዞ ጀመሩ ስናር (ሱዳን) ደርሰው ከመልዕክተኞቹ ጋር ተገናኝተው መስቀሱን አክብረው አጅበው ወደ መካከል ኢትዮጵያ ለማስገባት መስከረም 10 ቀን ሲነሡ አፄ ዳዊት ከበቅሎአቸው ወድቀው በድንገት ሕይወተ ሥጋቸው ጥቅምት 9 ቀን አለፈ። በዚህ ጊዜ ሠራዊቱ ተደናግጦ መስቀሉን በዚያ ትቶ የንጉሥ አፄ ዳዊት አስክሬኑን ይዞ ተመለሰ የጌታችንም መስቀል በስናር ቆይታል። አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከነገሠ በኋላ የጌታችን መስቀል ወደ መሃል ኢትዮጵያ አስገብተው ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ለማስቀመጥ አስበው ቦታ አላገኙም። በኤረር ተራራ ብዙ ጊዜ ካስቀመጡት በኋላ ወደ ደብረ ብርሃን ወስደው አኖሩት_ከዚያም ወደ መናገሻ ማርያም አምባ ቀጥሎም ወደ እንጦጦ ጋራ አምጥተው እንዳስቀመጡት « አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል» መስቀሌን በመስቀለኛ ተራራ ላይ አስቀምጥ የሚል ቃል በራዕይ ሰሙ ከዚያም ወደ ወሎ ሀገር ስብክትም እንዲሄዱ ነገራቸው ወሎ ሀገረ ስብክትም እንደደረሱ ወደ አምባሰል እየጠቀሰ መስቀሉን በመስቀለኛ ተራራ ላይ አስቀምጥ ስላላቸው ወደዚያው ሲያመሩ የግሸንን ተራራ ተመለከቱ ተራራው ሲመለከቱት በመስቀል አምሳል የተቀረፀ ይመስላል አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከዚያ ተራራ ላይ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል በ1446 ዓ.ም አስቀመጡ። ከዚህ በኋላ መካከሏ ገነት ዳሯ እሳት ይሁን የበረረ ወፍ የሠገረ ቆቅ አይታደንባት ድንገት ነፍስ

የገደለ ቋንጃ የቆረጠ ወንጀለኛ አይያዝባት ብለው አውጀው የታቦተ ማርያምን ጽላት አብሮ እንዲኖር አድርገዋል ስለዚህ መስከረም 21 ቀን ወደዚሁ ቦታ መጥቶ የጸለየና የተማጸነ ሁሉ እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ የምህረት ቃል ኪዳን እንደሚያደርግለት ጌታ በተባለችው መጽሐፍ ተጽፎአል::

ቁጥር 30 ህዳር 21 ቀን ታቦተ ጽዮን

በግዕዝ ግሥ ተጸወነ ማለት ተጠጋ ማለት ነው ጸወን ማለት መጠጊያ ጽዮን ማለት ጥግ ነው ለጊዜው ጽዮን የዳዊት ከተማ ፍፃሜው ግን የእመቤታችን ማርያም ምሳሌ ናት ስለዚህ ጽዮን ማለት ሁለተኛው ትርጓሜ ታቦተ አምላክ ታቦተ ሥርዓት ወሕግ ምስማክ ሥጋ ወነፍስ ማህደረ አምላክ ማህደረ መለኮት ማለት ነው የድንግል ማርያም ምሳሌ የሆነችው ይህች ታቦተ ጽዮን በድንኳን 600 መቶ ዘመን ኖራለችና ከዚያ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን የዳዊት ልጅ ቤተ መቅደሱን በ4500 ዘመን ስለሠራ በቤተ መቅደስ ተቀምጣለች 1ኛ ነገ.8÷2 ከዚያም በኋላ ጌታ በአወቀ በረቂቅ ምስጢሩ የናቡከደነጾር ምርኮ (ፄዋፄ) ሳይደርስ ሰሎሞን የሠራው ቤተ መቅደስ ሳይፈርስ ታቦተ ጽዮን አስቀድሞ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን በ4518 ዓ.ዓ ወደ ኢትዮጵያ መጥታለች ይህውም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ982 ዓመት አስቀድማ ነው::

እስራኤል ስለበደሉትና ስለአሳዘኑት ናቡከደነፆር ለቅጣትና ለጥፋት ከፋርስ ዛሬ ኤሪን ከተባለው ወደ ኢየሩሳሌም ሳያመጣው ታቦተ ጽዮንን አስቀድሞ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመጣ በማድረጉ በአክሱም ከተማ የእግዚአብሔር አምልኮና ምሥጋና ሲነገርባት ሲቀደስባት ትኖራለች:: ቀድሞ ታቦቲቱ በቅድስት ሐገር በኢየሩሳሌም ልዩ ልዩ ታምራት እያደረገችና እሥራኤልን እየተራዳች እንደኖረች 1ኛ ሳሙ. 5÷7) ተመልከት 2ሳሙ. 6÷1-23 ደግሞም መቅድመ ተአምር አመ ፭ወ፩ ለዝወርህ ጽዮን ተቅዋመ ማኅቶት ዘርአየ ዘካርያስ ይላል (ዘካ. 4÷1) በዚህ ወር በ21 ቀን ታቦተ ጽዮን ተማርካ በብሔረ ኢሎፍሊ ሄዳ ሳለች በላይ የተቀመጠ የዳጉንን ጣዖት

ጎይል አውርዳ ጥላ ቀጥቅጣ ለእስራኤል ተድላ ደስታውን ያሰማችበት ለሰብአ ኢሎፍሊ የእባጭ ቁስል ለአዝመራቸውም አይጥና ፍልፈል በመላክ 1ኛ ሳሙ. 5÷6 ጎይሏንና ታምራቷን የአሳየችበት ቀን ነው:: በኋላም ዳዊት ነግሦ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ ዘውዱን ደፍቶ እመቤታችን ታቦተ ጽዮንን ከቤተ አቢዳራ ስትመለስ በዕልልታ በይባቤ በዝማሬ በቃለ ቀርን የተቀበለበት ቀን ነው 2 ሳሙ. 6÷14 ደግሞም ዕዝራ ዘርአያ እንዲል ዕዝራ በአምሳለ ብዕሲት የአያት ዕዝ. ሱቱ. 9÷24-26 ዘካርያስ ወልደ በራክዩ ሄዶ አይቶ የብርሃን ፋና በብርሃን መቅረዝ ተቅዋመ ወርቅን የመሰለበት ነው ዘካ. 4÷1 ፍልስጥኤም ማለት በዕብራይስጥ፣ ኢሎፍሊ ማለት በፅርዕ፣ ነውና ያን ጊዜ እስራኤል ስለበደሉትና ስለተቀየመ እስራኤልን በፍልስጥኤም እጅ ጣላቸው የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በደላቸውና ክፋታቸው ስለበዛ በመጀመሪያ ጦርነት 1ሳሙ 4÷2 4000 ጀግኖች ከእስራኤል ወደቁ ሁለተኛ ደግሞ ገጥመው ጦርነት አደረጉና እስራኤል ድል ሆነው ተመተው ወደቁ ያን ጊዜ ከእስራኤል ያለቁ ብዛት 30000 1 ሳሙ. 4÷10 ጦረኞች ወደቁ ጌታም የመጣላቱ ምልክት ታቦቲቱ ተማረከች ሁለቱም የሊቀ ካህናት የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በጦርነት ሞቱ በጠቅላላ ከእስራኤል ላይ የሞቱት 34 ሺህ ናቸው አስተዋይ ልቦና ላለው ሰው እግዚአብሔር ሲቆጣ የማያዳላ እውነተኛ አምላክ ስለሆነ ታቦታቱን ታቦት ቁሱን ቁስ መቅደሱን መቅደስ ቤተክርስቲያኑን ቤተክርስቲያን ጳጳሱን ጳጳስ መነኮሴውን መነኮሴ አይለውምና ኢያኃፍሮ ለባዕል እንበይነ ብዕሉ ወኢይምህሮ ለነዳይ እንበይነ ንዴቱ ለእመ ኢከነ መሥመሪ ሎቱ እንዳለ አትናቴዎስ በቅዳሴው በእስራኤል በደልና በካህናት በአፍኒንና በፊናሐስ የእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦቲቱ ተማርካ በጠላት እጅ ገባች ታቦቲቱ በፍልስጤማውያን ዘንድ 7(ሰባት) ወር ያህል ተቀመጠች 1ሳሙ. 6÷1 ከዚያም በኋላ ከአሚናዳብ ቤት ሄዳ 20 ዓመት ከሰባት ወር በኋላ ዳዊት ደግሞ ከእስራኤል የተመረጠ 3000 ያህል ሠራዊት ሰብስቦ ከአሚናዳብ ቤት የእግዚአብሔርን ታቦት በአዲስ ሠረገላ አስቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ደብረ ጽዮን በዕብራይስጥ ቋንቋ በቅኔ

በዝማሬ፣ በበገና፣ በመሰንቆ ፣በከበሮ፣ በነጋሪት፣ በፀናጽል ድምጽ በእግዚአብሔር ፊት እያስጨበጨቡና እየዘፈኑ ሲሄዱ ሰረገላው የተጫነባቸው ጊደሮች መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እያደረጉ ሲፋንኑ አዛ የሚባል የአሚናዳብ ልጅ እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ስለያዘ ስለጥፋቱ ወዲያውኑ ተቀሰፈ:: 2ሳሙ. 6÷6 የሳኦል ልጅ ሜልኮልም ታቡቱን በመናቅ ዳዊትን ስለሰደበች መካን ሁና ቀርታለች 23:: ጽዮን የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት ኤልያስ በብሉይ በሐዲስ ዮሐንስ እንደተባለ ሚል. 4÷5 ማቴ. 17÷10 በብሉይ ጽዮን በሐዲስ ድንግል ማርያም ተብላለች:: መዝ. 9÷11 ሉቃ. 2÷6

ቊጥር 31 ጥር 21 ቀን አስተርእዮ ማርያም

በዓሉ አስተርእዮ መባሉ ግን ሁለት ጠባይ ያሳያል አንድ ወራቱን ማለት ጥር ጌታችን በጥምቀቱ ምሥጢረ ሥላሴን ከዚያም ጋር አምላክነቱን ለዓለም የገለጸበት በመሆኑ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ የአምላክ እናት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን በወለደችበት ስብሐተ መላእክትን በሰማችበትና በአየችበት የልደት ወራት አካባቢ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታ ወደሰማይ ስትወጣ በሰማይም በምድርም ለሰውም ለመላእክትም ከልጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር አብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተሰጣት ፀጋና ክብር መገለጡን ያሳያል አስተርእዮ ማለትም መታየት መገለጥ ማለት ነውና::

የኢትዮጵያ ሊቃውንት በዚህ ቃል ሐሳባቸውን ያስተባብራሉ ቅዱስ ያሬድ አምላክ ከድንግል በሥጋ መወለዱን በዚህ አካለ መጠን ለዓለም መገለጡን አስተርእዮ ብሎ ሲናገር ሌላው ደግሞ / ደራሲ ሊቅ/ የትንቢት አበባ እግዚአብሔር የእኛ ሥጋ የሆነውን ያንቺን ሥጋ ለብሶ በምድር እንደተገለጠ ለእኛም እንደታወቀ ድንግል ሆይ የመገኛችን መመኪያ ዛሬ ለእናታችን ለማርያም በሰማይ በፍጹም ደስታ መገለጥ ሆነ እያልን እናመሰግንሻለን ብሏል::

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጥር 21 አሑድ ቀን በ49 ዓ.ም በ64 ዓመቷ አርፋ ከዚህ ዓለም ወደዘለዓለማዊ ሕይወት በምትሸጋገርበት ዕለት / በዕረፍቷ ቀን ቅዱሳን ሐዋርያት የቅድስት ድንግል እመቤታችንን አስከሬን ወደ ጌቴ ሴማኒ መቃብር በሚወስዱበት ጊዜ አይሁድ ለምቀኝነት አያርፉምና ከዚህ ቀደም ልጇን ኢየሱስን ሞተ፣ ተነሣ አረገ፣ ደግሞ በክፋዎችና በበጉዎች ለመፍረድ ይመጣል እያሉ ያውኩን ነበር አሁንም ይህችን እናቱን ዝም ብንል ሞተች ተነሣች እያሉ ሊያውኩን አይደል አሁንም ኑ በእሳት እናቃጥላት ብለው ከእነሱ መካከል አንዱ ታውፋንያ ወይም ሶፎንያስ የሚባለውን ልከው አስከሬንዋን ለማቃጠል የተጠቀሰው ሰው አስከሬንዋን ለመጣል ተረማምዶ በድፍረት ያልጋውን ሸንኮር ሲጨብጥ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ከሁለት ትክሻው በሰይፉ ቀጣው ሁለቱ እጆቹም ከአልጋው ሸንኮር ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ ይህም ቅጣቱ ስለአስደነገጠውና በይበልጥም ምክር ስለሆነው ወዲያውኑ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ የባህሪይ አምላክ እሷም ወላዲተ አምላክ መሆኗን አምኖ በልጅዋ ቸርነት በእርሷ አማላጅነት ተማጽኖ ምህረትና ይቅርታን ስለለመነ በቅዱሳን ሐዋርያት ጸሎት በእመቤታችን አማላጅነት እጆቹ እንደነበሩ ተመልሰውለታል:: ሥጋዋንም ቅዱሳን ሐዋርያት ለጊዜው ጌቴሰማኒ በተባለው ቦታ አሳርፈውታል በሦስተኛው ቀን ግን መላእክት ከዚያ አፍልሰው በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አኑረውታል ከመቃብር እስከተነሣችበት ዕለት ቀን ድረስ ለሁለት መቶ አምስት ቀኖች በዚያው ቆይታል ክርስቶስ ለሚመጣበት ለ2500 ዓ.ም ምሳሌ ነው:: 200 መቶ የ2ሺህ 5ቱ የ500 መቶ በዚህ ጊዜ የሰው ሁሉ ትንሣኤ ይሆናልና:: በዕለተ ዕረፍትዋ ብዙ ፍጹም በረከት ተሰጥቷል የፈውስ ፀጋ ከደረሳቸው አንዱ ታውፋንያ ነው በዚህ ዕለት የተደረገውን ሁሉ የታሪክ መጻሕፍት በሰፊው ዘርዝረው ያስረዳሉ:: በዚህ የተጠቀሰው ግን በአጭሩ ነው::

ስለዚህ በዕረፍትዋ ምክንያት በጥር 21 ቀን የተጀመረው የበዓል መታሰቢያ በእየወሩ ሲገባ በ21 ቀን እንዲታሰብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተርክስቲያን ሥርዓት ስለሆነ ወሩ በገባ በ21 ቀን የዕረፍቷ

መታሰቢያ በ29 ቀንም አምላክን የመወለዷ መታሰቢያ ይከበራል። ይህ በቀድሞ በመባቻ በዓል ፈንታ የገባ ነው ያ ጥላ ምሳሌ ስለነበር አማናዊ ተተክቶበታል።

ቍጥር 32 ግንቦት 21 ቀን ደብረ ምጥማቅ

ጌታችን በዳዊት አገር በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ መልአክ ለዮሴፍ በህልም ብላቴናውን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ ግብጽ ሂድ አለው። /ማቴ.2÷13/ ርጉም ሔሮድስ ይገለው ዘንድ ይሻዋልና ያን ጊዜም ዮሴፍ ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዞ ወደ ግብጽ አገር ደረሱ በምድረ በዳም አደሩ በውስጧም አምስት ቀን ተቀመጡ ከዚህም በኋላ ጌታችን በከበረ አንደበቱ ክብርት እናቱ ማርያምን በዚህ ቦታ ላይ ባንችና በኔ ስም ቤተክርስቲየን ይሰራል እኮ አላት ለመነኩሳትም ገዳም ይሆናል ከሱም ተአምራት ይገለባሉ ለህዝቡም ሁሉ በእየቋንቋቸው ብዙ ምሥጢር ይደረጋል ክርስቲያኖችም እስላሞችም ሁሉ ተገልጸ ያዩታል ይሽውም በግንቦት 21 ቀን ጀምሮ እስከ 25 ቀን ድረስ በስምሽ በሚሠራ በዚህ ገዳም አንቺ ትገለጫለሽ የመላእክት አለቆች ንውሐን የሚሆኑ ሚካኤልንና ገብርኤልን አንዱ በቀኝሽ አንዱ በግራሽ ይሆኑ ዘንድ አዛቸዋለሁ ከአንች ሰው ለመሆኔ ክብር ምሥጋና ይገባኛል በእኔ ስም አምነው የሞቱ በሥጋቸው የኔን መከራ የተቀበሉ የምወደውን ፍለጋየንም የተከተሉትን ሰማዕታትን ሁሉ እንዲያገለግሉሽ አደርጋቸዋለሁ እነርሱም ወደዚህ ወደ ከበረ ቦታ መጥተው በውስጡ ያድራሉ ለክብርሽም ይሰግዳሉ ይደረግልኛል ብሎ አምኖ አንቺን በኔ ስም የለመነ ሰው ቢኖር ከሰማዕታትና ከቅዱሳን ወገን ቢሆን የፈለገው ይደረግለታል በቀናች ሃይማኖት ከሞቱ ከምእመናን ወገን ሌሎች ወደ አንቺ ይመጣሉ አንቺን አስነሽልን ብለው የለመኑትን ሰው ያያሉ የሚያዩ ሁሉ በማየታቸው ደስ ይላቸዋል ለእናቱ ተስፋውን እንደነገራት አስቀድመን በተናገርነው ቦታ የከበረች ቤተክርስቲያን በተሠራች ጊዜ ይህ ምልክት እስከ ዓለም ፍፃሜ የተገለፀ ይሆናል በሷም ዘንድ መነኮሳት ተሰበሰቡ ታላቅ ገዳም ሆነች ደብረ ምጥማቅም ተባለች በዚህ በዓል ከ21 ጀምሮ- 25 ቀን ድረስ በአመት በአመት ከኢትዮጵያና ከግብፅ

ሰዎች ከአርማንያና ከሶርያ ከእስክንድርያና ከአፍሪካ ከሮምና ከጽር ከምሥራቅ ከምዕራብ ወደዚህ ገዳም ተሰብስበው በእመቤታችን ምክንያት ድንቅ ታምራትን ያያሉ መዝ. 44÷12 መኃ. 6÷10 ሚል. 4÷2-4 ራዕ. 12÷1፤ 21÷24)

ቍጥር 33 ሰኔ 21 ቀን ቅዳሴ ቤታ ለእግዝእትነ ማርያም መዝ.45÷4

በዚህች ዕለት የአዳምና የዘሩ ድኅንነት የተደረገበት አምላክን የወለደች የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የታላቅ በዓል መታሰቢያና በዓለም ሁሉ የቤተክርስቲያን መታነጽ መታሰቢያ ነው ከሁሉ አስቀድሞ ይህች ቤተክርስቲያን በሐዋርያት ዘመን ብቻዋን ታነፀች ይሽውም ጳውሎስና በርናባስ በአህዛብ አገር በፊልጵስዩስ በአስተማሩ ጊዜ ክብር ይግባውና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ህዝቡ አመኑ ከሰዎች ቤቶች በቀር ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበሉበት ቤተ ክርስቲያን አልነበራቸውም ነበር። ስለዚህም ወደ ጴጥሮስና ወደ ሐዋርያት ሁሉ ስቤተክርስቲያን መታነጽ ጉዳይ እየለመኑ ላኩ ሐዋርያትም እንደዚህ ብለው መለሱላቸው ክብር ይግባውና ያለጌታችን ፈቃድ እኛ ምንም አንሠራም ነገር ግን የምንሠራውን እሰኪያስረዳን ድረስ ወደ እግዚአብሔር እየጸለዩና እየማለዱ አንድ ሱባዔ ይጸሙ ዘንድ ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት የተመለሱ አህዛብን እናዛቸዋለን አሉ። እንዲሁም ለአዘዙአቸው በሱባኤው ፍጻሜ ክብር ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገለጸላቸው ሐዋርያትንም ሁሉ ከአየአገሮች እስከ ፊልጵስዩስ በደመና ሰበሰባቸው ከእርሳቸውም ጋር ጳውሎስና በርናባስ ነበሩ ጌታችንም ባረካቸው እንዲህም ብሎ ነገራቸው ይህች ዕለት በእናቴ በማርያም ስም በአራቱ ማእዝነ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ የፈቀድኩባት ናት። ይህንንም ብሎ ከከተማዋ በስተምስራቅ በኩል አወጣቸው የቤተ ክርስቲያኒቱንም ቦታና መሠረቷን ወሰነላቸው ከእርሳቸውም ጋር የእግዚአብሔር ኃይል ነበር የቤተክርስቲያኗ ሕንፃም እስከ ተፈጸመ ድረስ ደንጌያዎች በሐዋርያት እጆች ውስጥ ይለመልሙ ነበር ጌታችንም ንዋየ

ቅድሳቷንና አልባሳቷን መሠዊያዋን አዘጋጀ ከዚህ በኋላ ጌታችን እጹን በጴጥሮስ ራስ ላይ ጭኖ በአራቱ ማእዝነ ዓለም ውስጥ አርሳይሮስ ብሎ ሾመው ይህም ሊቀጳጳሳት ማለት ነው ለሐዋርያት አለቃ ጴጥሮስ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የጳጳሳት አለቃ ይሆን ዘንድ ይገባዋል ይገባዋል ይገባዋል አያሉ ሰማያውያን መላእክትና ምድራውያን ሰዎች ሦስት ጊዜ አስምተው ተናግረዋል። ከዚያም በኋላ ጌታችን የቁርባን ሥርዓተ ቅዳሴ ሥርዓት ያከናውኑ ዘንድ ለሕዝቡ ሥጋ ወደሙን ያቀብሏቸው ዘንድ አዘዛቸው እንዲህ የሚል አለ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ቀድሶ ሥጋውና ደሙን ለሐዋርያት አቀብሏቸዋል እንዲህም አሳቸው በዚህች ቀን የእጃቸውን ሥራ እንዳይሠሩ ሕዝቡን ሁሉ አዘዛቸው ይህም በሰኔ ወር 21 ቀን ነው ከዚህ በኋላ መድኃኒታችን ከእርሳቸው ዘንድ በታላቅ ክብር ወደ ሰማያት በክብር በምሥጋና አረገ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤትና በረከት አይለየን ::አሜን::

ቁጥር 34 ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ

አያሌ ሴቶች በዚህ ስም ይጠራሉ

1. **ማርያም ድንግል** የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ወላጆችዋ በመጽሐፍ ቅዱስ በስማቸው አልተጠቀሱም ሆኖም ከዳዊት ዘር ተወለደች ለዮሴፍም ታጨች (ማቴ. 1÷1-18 የሐ.13÷22 ሮሜ.1÷3) በናዝሬት ሳለች መልአኩ ገብርኤል ወደ እርስዋ ተላከ ወንድን ሳታውቅ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ቅዱሱን የእግዚአብሔር ልጅ በድንግልና እንደምትወልድ አበሠራት ቃሉን አምና ወደ ዘመድዋ ወደ ኤልሳቤጥ ሄደች (ሉቃ.1÷26-40) ማርያም ወደ ዘካርያስ ቤት በገባች ጊዜ ኤልሳቤጥ ማርያም ጌታን እንደምትወልድ በመንፈስ ቅዱስ ተርድታ « ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ» አለች ደግሞም ማርያም የእግዘአብሔርን ቃል በማመኗ ብጽዕት እንደሆነች ኤልሳቤጥ ገለጸች (ሉቃ.1÷40-45) ማርያምም መልሳ ብሉይ ኪዳንን እየጠቀሰች እግዚአብሔርን አመሰገነች (ሉቃ.1÷40-55) ሦስ

ወር ያህል በኤልሳቤጥ ዘንድ ተቀመጠች (ዮሐንስ አስኪወለድ ድረስ ይሆናል) ወደ ቤትዋ ተመለሰች (ሉቃ.1÷56) ዮሴፍ ግን እንደ ፀነሰች አይቶ ሊተዋት አሰበ ነገር ግን የጌታ መልአክ ርስዋን ለመውሰድ እንዳይፈራ በሕልም ነገረው:: ዮሴፍም ታዝዞ እጮኛውን ማርያምን ወሰደ የበኩር ልጅዋንም አስክትወልድ ድረስ አላወቃትም (ማቴ.1÷18-25) በመንግሥት ትዕዛዝ ምክንያት ዮሴፍና ማርያም ወደ ቤቴልሔም ሄዱ በዚያም ኢየሱስን ወለደች (ሉቃ. 2÷1-20) እንደ ሙሴ ሕግ ወደ ቤተ መቅደስ በሄዱ ጊዜ ስምዖን አገኛቸው በአንቺ ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል ብሎ የሚደርስባትን ኃዘን ተነበየ (ሉቃ.2÷22-35) ሰብአሰገል (ጠቢባን) ከሄዱ በኋላ ከዮሴፍና ከልጅዋ ጋር ወደ ግብጽ ሸሸች ከዚያም ወደ ናዝሬት ተመለሰች (ማቴ. 2÷1-23) ኢየሱስን አሳደገች የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሲሆንም ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች በዚያም ኢየሱስ የተናገረውን ምንም ባታስተውለውም በልብዋ ትጠብቀው ነበር:: ማርያም ከቤተሰብ ጋር በናዝሬት የታወቀች ነበረች (ማቴ.13÷55 ማር.6÷3 ሉቃ. 2÷41-51) በቃና ሠርግ ያደረጉ ሰዎች የወይን ጠጅ አልቆባቸው ሲቸገሩ ማርያም ለኢየሱስ አመለከተችና የመጀመሪያ ተአምር አደረገ ከዚያም በኋላ ከኢየሱስ ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደች (ዮሐ.2÷1-12) ኢየሱስ ሲያስተምር ትጉበኘው ነበር (ማቴ.12÷46 ማር.3÷31-35 ሉቃ.8÷19-21) እስከ ቀራንዮ ተከተለችው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ ወደ ቤቱ እንዲወስዳት « እነኋት እናትህ» ብሎ ለዮሐንስ ነገረው ዮሐንስም ወደ ቤቱ ወሰዳት (ዮሐ. 19÷25-27) ከትንሣኤ በኋላ ከሐዋርያት ጋር ነበረች (ዮሐ. 1÷12-14) ብፅዕናዋ (ሉቃ. 1÷28-42) እምነትዋ (ሉቃ.1÷34 -38) መታዘዝዋና ትህትናዋ (ሉቃ. 1÷38) ምሥጋናዋና የብሉይ ኪዳን እውቀትዋ (ሉቃ.1÷47-55) ተጠቅሷል::

2. ማርያም የሙሴ እህት ሙሴ በወንዝ ዳር በተጣለ ጊዜ እህቱ ማረያም በእርሱ ላይ የሚሆነውን ለማወቅ ትመለከተው ነበር። በጥበብም የፈርኦንን ልጅ አነጋገረቻትና እንድታጠባው የገዛ እናቱን ለሞግዚትነት ጠራች (ዘፀ.2÷4-8) እስራኤላውያን የኤርትራን ባሕር ከተሻገሩ በኋላ ነቢይት ማርያም ሴቶችን በመዝሙርና በምሥጋና መራች (ዘፀ. 15÷20-21) በኋላ ግን ማርያም የሙሴን የበላይነት ካለመውደዷ የተነሳ ኢትዮጵያዊት ሚስቱን ምክንያት አድርጋ አማችው እግዚአብሔር ግን በለምጽ ቀጣት (ዘኁ.12÷1-15 ዘዳ.24÷9) ገና በጉዞ ሳሉ ሞተች በቃዴስም ተቀበረች (ዘኁ.20÷1) ዕረፍቷ ታኅሣሥ 16 ቀን ነው።

3. ማርያም የዮቴር ልጅ የዕዝራ የልጅ ልጅ (1ዜና. 4÷17)

4. ማርያም የማርታና የአልዓዛር እህት (ዮሐ. 11÷1) ከኢየሩሳሌም አጠገብ ባለው ቢታንያ በተባለው መንደር ትኖር ነበር ኢየሱስ ወደየቤታቸው እየሄደ ይጠይቃቸው ነበር ቀርባ ቃሉን ስለ ሰማች ኢየሲስ አመሰገናት(ሉቃ. 10÷39-42) ወንድምዋ ከሙታን በተነሣ ጊዜ ከኢየሱስ ጋር በሰፊው ተነጋገረች (ዮሐ. 11) ማርያም ኢየሱስ እንደሚሞት ስለተረዳችና በጣም ትወደው ስለነበር በናርዶስ ሽቱ እግሩን ቀባችው (ዮሐ.12÷1-8) ዕረፍቷ የካ.6 ቀን ነው።

5. ማርያም መግደላዊት ከገሊላ ከተማ ከመጌዶል መጥታ ይሆናል (ማቴ. 15÷19) ሰባት አጋንንት ከወጣላት በኋላ ኢየሱስን ታገለግል ነበር (ሉቃ. 8÷2 ማር. 15÷40) ይህች ሴት የክርስቶስ የስቅለቱና የመቀበሩ ምስክር ነበረች። (ማቴ.27÷55-56፣61 ማር. 15÷40-47 ዮሐ. 19÷25 ማቴ. 28÷1-10 ማር. 16÷1-8 ሉቃ. 24÷10) ከትንሣኤው በኋላ በአትክልት ቦታ ለርስዋ ለብቻዋ ክርስቶስ ታያት (ዮሐ.20÷1-18) ዕረፍቷ ነሐ.6 ቀን ነው።

6. ማርያም የታናሹ ያዕቆብና የዮሳም እናት ይህችም ደግሞ ለክርስቶስ ስቅለትና መቀበር ምስክር ነበረች (ማር.15÷40-47፣16÷1 ሉቃ. 24÷10)

7. ማርያም የቀለዮጳ ሚስት ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ከመስቀሉ አጠገብ ቆማ ነበር (ዮሐ. 19÷25) ይህችና ከላይ በቁ.6 የተጠቀሰችው አንድ ይሆኑ ይሆናል።

8. ማርያም የማርቆስ እናት (የሐዋ. 12÷12

ምዕራፍ 22 ቁ.ጥር 35

ታህሣሥ 22 ቀን ደቅስዮስ

ደቅስዮስ ጥልጥልያ በምትባል አገር ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ተሹሞ ሲኖር እመቤታችንን ከመውደዱ የተነሣ እመቤታችን በአፀደ ሥጋ ሳለች ከሞተችም በኋላ በየጊዜው ያደረገችውን ተአምር በማስታወስ እየጻፈ ያስቀምጥ ነበር። ከእለታት በአንድ ቀን እመቤታችን ተገልጻ የጻፈውን መጽሐፍ በእጇ በመያዝ ወዳጄ ደቅስዮስ ሆይ ይህን መጽሐፍ ወድጀልአለሁ ቀጥልበት ብላው ተሰውራለች ደቅስዮስም ይህን ራዕይ ባየ ጊዜ እጅግ በጣም ተደሰተና በሥራው ላይ የበለጠ ፍቅር አደረበት ክብሯን ያበዛ ዘንድ ያስብ ጀመር ቅዱስ ገብርኤል ድንግል ማርያምን ያበሰረበትን ታህሣሥ 22 ቀን በአሏን አከበረ በዚህ ላይ ወቅቱ ኤጲስ ቆጶስነት የተሾመበት ዘመን ነበር ደግነትን ምህረትን ቸርነትን የምትወድ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የፀናች ክብርት እመቤታችን በእጇ የሐር ልብስና ወንበር ይዛ ተገለጠችለት ገብርኤል መልአክ እኔን በአበሰረበት ቀን በዓሌን አክብረሃልና እኔም ዋጋህን ልከፍልህ እወዳለሁ አንተ በዚህ ዓለም በሰው ሁሉ ፊት እንዳከበርከኝ እኔም አከብርህ ዘንድ እወዳለሁ ይችን ልብስ ትለብስ ዘንድ በዚችም ወንበር ትቀመጥ ዘንድ አመጣሁልህ ከሰው ወገን ይችን ልብስ ይለብሳት ዘንድ በዚችም ወንበር ይቀመጥ ዘንድ የሚቻለው የለም በማለት ተናግራ ተሰውራለች ደቅስዮስ ከዚህ ዓለም በሞት በተለየ ጊዜ ድንግል ማርያም የሰጠችው ልብስና ወንበር በቤተ ክርስቲያን በክብር ቦታ

ተቀመጠ ሌላው ኤጹስ ቆጶስ በተሾመ ጊዜ ያችን ልብስ ሌለብሳትና በወንበሩም ላይ ሊቀመጥ ወደደ ካህናቱ ግን ይቅርብህ ሲሉ ከለከሉት ርሱ ግን ርሱም ሰው እኔም ሰው ነኝ አምጡልኝ ብሎ ልብሱን ለበሰ በወንበሩም ላይ ተቀመጠ ወዲያው ከወንበሩ ተገልብጦ ክፉ አሟሟት ሞተ በዚያ የነበሩ ሁሉ አደነቁ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት ድንግል ማርያምንም አከበሯት ከቀድሞው በበለጠም ሲያገለግሏት ኖሩ ይላል ተአምረ ማርያም የጻድቁ ረድኤትና በረከት በሁላችን ላይ ይደር። አሜን። በዚሁ በ22 ቀን የቅዱስ ሉቃስ መታሰቢያ ነው። ታሪኩን ከ72ቱ አርድእት ይመልከቱ።

ቊጥር 36 ጥር 22 ቀን ቅዱስ ሱርያል / ዑራኤል/

ሱርያል የሚለው ስም በአንዳንድ ድርሳናት እንጅ እምብዛም አይታወቅም ትርጉሙ ዐለቴ እግዚአብሔር ማለት ነው የዑራኤል ሁለተኛ ስሙ ነው ዑራኤል ማለት እግዚአብሔር ብርሃን ነው ማለት ነው። በቤተክርስቲያናችን በስፋት የሚታወቀው ዑራኤል ሁለተኛ የሚለው ስም ነው / ድርሳነ ዑራኤል 19÷91 ገጽ 14

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ቅዱስ ዑራኤል በስፋት የምናገኘው በመጽሐፈ ዕዝራ ስቱኤል ነው ዕዝራን ይራዳው የነበረው መጻሕፍትንም እንደገና እንዲጽፋቸው ፅዋዐ ልቡና አጠጥቶ ምሥጢር የገለጠለት ቅዱስ ዑራኤል ነው / ዕዝራ ሱቱ 2÷1 ፣9÷28 ብሔረ ሕያዋን ያሳረገውም ርሱ ነው። ዕዝ.ሱቱ.13÷9-49 መጽሐፈ ሄኖክ በመብረቅና ነጐድጐድ ላይ የተሾመ ሄኖክ 6÷2 / ይለዋል። ምሥጢረ ሰማይን ለሄኖክ ያሳየው ዕውቀትም የገለጠለት ርሱ መሆኑን ጽፏል / ሄኖክ 28÷13-14/26÷34

አመቤታችን በስደቷ ኢትዮጵያን በዞረች ጊዜ ቅዱስ ዑራኤል ያገለግላት እንደነበር በድርሳነ ዑራኤል ላይ ተጽፏል በመጽሐፈ ስንክሳርም ምስጢር የተገለጠለት የሚያረጋጋ ለኃጢአተኞችም አማላጅ ነው። ይላል / ስንክ. ጥር 27/

በቅዱሳን ገድልም ውስጥ የቅዱስ ዑራኤልን ተራዳኢነት እናነባለን በስንክሳር / የካቲቲ 9/ ጳውሎስ የተባለ የእስሙናይን ሰው በአረማዊ ንጉሥ ለሰማዕትነት በተወሰደ ጊዜ ያበረታው እንደ ነበር ተጽፏል ሐምሌ 21 ቀን ቅዳሴ ቤቱ ነው።

ምዕራፍ 23 ቊጥር 37

ሚያዝያ 23 ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ እረፍት

በዚህ በሰማዕትነት ከባድ ሥራ ፈተና ያለፋ አበው ሰማዕታት ብዙ ናቸው ከብዙዎቹም አንዱን የቅዱስ ጊዮርጊስ የሰማዕትነትን ሥራ በመጠኑ እንደሚከተለው እንመልከት የቅዱስ ጊዮርጊስ አባቱ /ዘሮንቶስ / አንስጣስዮስ ይባላል። እናቱ ትዮብስታ እንደምትባል ዜና ገድሉ ይናገራል ወላጆቹ በክርስትናቸው የታወቁ በሐብታቸው የተደነቁ ደጉች ነበሩ የአባቱ ጥንተ ነገዱ ሮም ነው ወደ እስያ ለሥራ ጉዳይ መጥቶ ንብረት አፍርቶ ልዳ በምትባል ሀገር ሴት አግብቶ ሲኖር ቅዱስ ጊዮርጊስን ወልዷል። ቅዱስ ጊዮርጊስ አሥር አመት ሲሆነው አባቱ አርፏል ከእናቱ ጋር ሲኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን ከት/ቤት ገብቶ በሚገባ ተምሮአል።

ከዚያም በኋላ እድሜው እየጨመረ ሲሄድ ከውሃ ዋና እስከ ፈረስ ግልቢያ እንዲሁም የውትድርና ሙያ በዘመኑ የነበረውን የማጎበራዊ ኑሮ ዋስትና ተምሯል። በተማረበትም የሥራ አገልግሎት መሪ ለመሆን በግብረ ገብነቱ ተወዳጅነት በጀግንነቱም በጎብረተሰቡ ዘንድ ተደናቂነትን አትርፏል። በዚህም መልካም ሥራው አረጋውያን የበለጠ እንዲያገለግላቸው መክረውና ዘክረው ከዱድያኖስ ዘንድ ሙሉ ሥልጣን ተቀብሎ እንዲመጣ ጠይቀውታል። ቅዱስ ጊዮርጊስም የአረጋውያንን ጥያቄ ተቀብሎ በአለሚሉችን አስከትሎ እጅ መንሻ አሸክሞ የአባቱን ሙሉ ሥልጣን ለመቀበል የፋርስ መሪ ወደ ነበረው ወደ ዱድያኖስ ተጉዟል። ቢደረስ አረማዊው ንጉሥ ከሰባ መሳፍንት ጋር በመሆን ለአድሎስ ሲሰግድ ስመ እግዚአብሔር የሚጠሩትን ፈጣሪያቸውን ክርስቶስን የሚያመልኩትን ሲያሳርድ በእሳት ሲያነድ አግኝቶታል። በዚህ ሰይጣናዊ ድርጊት ተደንቆ

የተማረ ነበረና መድኃኒታችን ክርስቶስን «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ® ነፍሱን ግን ቢያጐል ምን ጥቅም አለው» ያለውን በማስተዋል ማቴ. 16÷26 አባቴ ምድራዊ ሐብቱ በጊዜያዊ ሹመቱ ምን ተጠቀመ ይህን ሁሉ ትቶት ሞተ እኔስ ቢሆን እንደዚሁ አይደለም ብሎ አርቆ በመመልከት ይዞት የመጣውን እጅ መንሻ ባለሟሎቹን የሚመለከተውን በባለሟሎቹ ፤ ድሆችን የሚመለከተውን ለድሆቹ አስረክቦ ሳይሞት ሞተ ብለው ለእናቱ መርዶ እንዲነግሩለት ለባለሟሎቹ መመሪያ በመስጠት ገላ.6÷14 እንጂወርቅ በእሳት በመፈተን እኔ ክርስቲያን ነኝ በማለት ለአላውያን በአደባባይ አምልኮቱን አሰምቶ ተናገረ በዚህም ዓይነት የተጋድሎ ሥራ ጀመረ መዝ. 118÷41-48 ይህ ቀን ሚያዝያ23 ቀን ነው ከ318ቱ ሊቃውንት አንዱ ¯ቴዎዶጦስ በገድሉ እንደመዘገበልን ዱድያኖስ የአጽሎስን ውርደት በጊዮርጊስ አንደበት በመስማቱ ባለማወቅ መስሎት ጊዮርጊስን በሕዝብ ፊት ክርስቶስ ፈጣሪውን ክዶ ለአጽሎስ እንዲሰግድ ይህን ቢፈጽም ሙሉ ሥልጣን ከብዙ ሐብት ጋር እንደሚሸልመው ጥያቄ አቅርቦለታል። ጊዮርጊስም አጽሎስ አምላክ ሳይሆን የሰይጣን ቤት ሰው ሰራሽ የድንጋይ ጥርብ ነው። እኔ የማመልከው ያጽሎስ የሠሪዎቹ ሠሪ የዓለም ፈጣሪ ነው በማለት በሁለተኛ ደረጃ የአጽሎስን ወራዳነት በሚገባው ቋንቋ ነግሮታል። ዲያብሎስም የማደሪያው የአጽሎስ ሕልውና በጊዮርጊስ አማካይነት አደጋ ላይ መድረሱን / መውደቁን/ በመመልከት የግብር ልጁ ዱድያኖስን ለዓይን የሚያስፈሩ ልብ የሚያሸብሩ ከብረታ ብረት የተሠሩ አንጀት የሚጐለጉሉ ጥርስ የሚነቅሉ በአጠቃላይ ሰውነትን የሚቆራርጡ ዓይን የሚያፈርጡ መሣሪያዎች እንዲዘጋጁ አድርጓል። በመጀመሪያ ጊዜ ልብሱን ገፈው ከግንድ በማሠር በአደባባይ ሰውነቱ እስኪደቅ ሥጋው እስኪያልቅ ተገርፏል። እንደገናም የብረት ቀኖት እንደጫማ በማሠር በእግሩ አጥልቀው የውስጥ እግሩ ሥጋውን ዘልቆ አጥንቱ እንዲሰበር ተደርጓል። ይህ ሰይጣናዊ ድርጊት ጊዮርጊስን ሊበግረው አልቻለም። ሐዋርያው ለሮም በጻፈው ክታቡ ሮሜ.8÷35-39 ያለውን በመገንዘብ ምክንያቱም ብቻውን አልነበረምና ፈጣሪው ክርሱ ጋር ስለነበረ

ከዕለት ወደ ዕለት በጊዮርጊስ ታምራዊ ሥራ ግዙፉ ዱድያኖስ ከመንግሥቱ ረቂቅ ዲያብሎስ ከጣዖቱ ሁለቱም ከችግር ላይ ወድቀዋል። ሰይፉም ሆነ እሳት ማንኛውም ዓይነት ሊያስቀረው አልቻለም። በእሳት አቃጥለው አመዱን ከተራራ ላይ ለነፋስ ሰጡት። ፈጠሪው አሥነሣው በአርባ ኃያላን በሚንቀሳቀሰው የብረት ወፍጮ ፈጩት ተመልሶ ተነሣ በብረት ቀፎ ውስጥ አድርገው አሸጉት ብረቱን ሠንጥቆት ወጣ ይህን ድንቅ ሥራ ያዩት አንድ አንድ በአለሥልጣናትና ተራው ሕዝብ ዱድያኖስን እየካዱ አጽሎስን እያዋረዱ ጊዮርጊስን ተከትለው እውነተኛ አምላክ የቅዱስ ጊዮርጊስ አምላክ ነው አሉ። ዳን.3÷1-30 ያለውን ይመልከቱ።

ሰው ከተገኘ ታሪክ ይደገማል። ሐዋርያው በእምነት እነሱ መንገሥታትን ድል ነሱ በሉ ከተናገረው በሥራ ከተረጐሙት አበው አንዱ ይህ ሰማዕት ነው። ዕብ.11÷33 ጊዮርጊስን በምንም የስቃይ መሣሪያ ዓይነት መቋቋም ያልቻለው ዱድያኖስ ብዙ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ባለመድኃኒት በማስፈለግ በሥራዩ የሚታወቀው የጠንቋዮች ሊቅ የሆነውን አትናቴዎስን በጥበቡ የሚፈራ ታምራት የሚሠራ አምጥቷል።አትናቴዎስም ጊዮርጊስ ከእስር ቤት እስከሚመጣ ችሎታውን ለማስመስከር አንድ በሬ እንዲያመጡ ለሰዎች በመንገር በአደባባይ ያለምንም ስራ በጆሮው ሽክ በማለት ከሁለት ተርትሮታል። የተከፈለውንም በሚዛን ቢመዝኑት እኩል ሁኖአል ይህን ያየ ዱድያኖስ ጊዮርጊስን ለመግደል አንተ ትችላለህ ብሎ አስተያየቱን ሰጥቷል። ጠንቋዮች ከሰይጣን እያበሩ ወይም እየተመሩ ብዙ ነገር እንደሚሠሩ ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል ዘፀ.7÷8-23 1 ሳሙ. 28÷8-25 የሐዋ.19÷11-20፣8÷9-12 ይመልከቱ። ቅዱስ ጊዮርጊስ ከእሥር ቤት በወታደር እየታጀበ መጣ አቶናቴዎስም መድኃኒቱን ሞከረ አልሠራም እንደገናም ሞከረ አልሆነም ማር. 16÷16-18 የሐ.28÷3 ያለውን ልብ ይላል አትናቴዎስ መድኃኒቱ እንዳልሠራ ባየ ጊዜ ጊዮርጊስ የሚያመልከውን አምላክ ነው የማመልከው ብሎ በአደባባይ ተናገሮ ስለ ጊዮርጊስ ማንነት መሰከረ በዚህ ምክንያት በሰማዕትነት በሰይፍ ተመተረ። እውነተኛ እምነት ይህን ይሠራል ማቴ.

17÷20 1ነገ.18÷20-41 ይመልከቱ የአትናቴዎስን ወደ ጊዮርጊስ እምነት ገብቶ በሰይፋ መመታቱን የተመለከቱ ዱድያኖስና እንደራሴዎች መርዛማ መድኃኒት ሰይፍና እሳት በአጠቃላይ የስቃይ ዓይነት የማይበግረው ቢሞት ይነሣል ምን ማድረግ ይሻላል ብለው የማያምኑት እናምናለን ብለው የተቀመጡባቸውን ወንበሮች እንዲያለመልም ጠየቁት ጊዮርጊስም እንደማያምኑ ነግሮአቸው ነገር ግን የፈጣሪዬን ኃይል ተመልከቱ ብሎ ወደ ፈጣሪው በማመልከት ሥር ሰደው ቅጠል እንዲያወጡ አድርጓል። ደረቅ ነገር ማለምለም አመድ ሆኖ ከመነሣት አይበልጥም እነሡ በምድራዊ ጥቅም ልቦናቸው ተዳፍኖ አላስተዋሉም እንጂ ዘጉ.17÷1-11

1. ቅዱስ ጊዮርጊስ በዓላውያን ነገሥታት ብዙ መከራና ስቃይ በማየት ከኤርምያስና ከጳውሎስ ኤር. 38÷1-14 1ቆሮ. 11÷12-33
2. ሙት በማሥነሣት ምግብ በማበርከት ከኤልያስና ከኤልሳዕ 1 ነገ.17÷9-12 2 ነገ. 4÷1-44
3. ጣያትን በማዋረድና ይመለክ የነበረውን ዘንዶ በመግደል ቢሩታዊትን በማስጣል ከሠለስቱ ደቂቅና ከዳንኤል ዳን. 3÷1 ተረ.ዳን.13÷43
4. እሳት ከሰማይ በማውረድና መምለክያነ ጣያትን በማጋየትና በማንደድ ከኤልያስ 2 ነገ.1÷9-15
5. በሽተኞችን በመፈወስ ከጴጥሮስና ከጳውሎስ የሐዋ. 5÷12-17 ፤ 19÷11-13 ይመስላል ዜና ገድሉን ይመልከቱ
6. ቅዱስ ሚካኤል ምግብ አምጥቶለት ተመግቧል እንደ ኤልያስ 1 ነገ. 19÷5-8
7. ቅዱስ ጊዮርጊስ በበትሩ በመንካት የአንዲት ድሃ በሬ ሞቶባት ከሞት አሥነስቷል። ከአንዲት ድሃ ቤት በረሃብ ቢሞት ብለው ከምሰሶ ቢያስሩት ምሰሶው አለምልሞ ፍሬ እንዲያፈራ አድርጉታል የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ መገኘት እንጂ ይህ ሁሉ ተአምር በእግዚአብሔር እምነት መሆኑን በሙሴና እያሱ እንዲሁም በዘመነ ሐዋርያት የተፈጸመውን ልብ ይሏል ይህ ሰማዕት በሃያ ዓመቱ

ጀምሮ በሰባት ዓመቱ ሚያዝያ 23 ቀን 303 ዓ.ም ተሰይፎ አርፏል በዚህ ጊዜ ከአንገቱ ደም ውኃና ወተት ፈሷል።

መክብብ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ ያለውን በትክክል ዋጋእንዲኖረው ያደረገ ሰማዕት ነው። መክ.12÷1 ቅዱስ ጊዮርጊስ የሰማዕትነቱን ሥራ ሲጀምር ፈጣሪውን አንድ ነገር ለምኖት ነበር ይህውም እኒህን ዓላውያን ድል ሳልነሳ አትግደለኝ ብሎ ነው በዚህም ምክንያት በሰይፍ ወደ ሚቆረጥበት ቦታ ሲሄድ ወደ ፈጣሪው በማመልከት እሳት ከሰማይ ወርዶ ሰባውን ነገሥታት ከነመሪያቸው ዱድያኖስ እንዲያጋያቸው አድርጓል። ኤልያስ መቶ ሁለቱን ዓማጽያን እንዳጋየ 2 ነገ. 1÷9-13 ለሰባት አመት ጮማ እየቆረጡ ጠጅ እየመጠጡ ሲንደላቀቁ የእሳት እራት እየሆኑ አለቁ ትምህርቱን በአለመስማትና ጊዮርጊስ ለመጽደቅ ይህን ያህል እንደፈጀበት እግዚአብሔር ለቀጣዩ ትውልድ የሰማዕትነት ሥራ ምን እንደሚመስል ሊያስተምርበት ፈልጐ እንጂ ሉቃ. 23÷39-42 ይህ ፋርሳዊ መሪ የነበረበት ዘመን በሁለኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደነበር ዜና ሰማዕታት ይናገራል። የሮማዊያን ቄሣር ጋላስን የአንጾኪያውን መሪ ጋላሪስን ድባቅ መትቶ በፋርስ የነገሠ ጣያታዊ መሪ ነው።

የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል በቤተክርስቲያን

1. የደረቀውን አምድ ያለመለመበት ቤተክርስቲያን ታምር የሠራችበት ጎዳር 7.
2. ሰውነቱ ተፈጭቶ በደብረ ይድራስ የተበተነበት ጥር 18
3. ያረፈበት ሚያዝያ 23 በበዓልነት ቤተክርስቲያን ታስታውሳለች።
4. ፍልሰተ አጽሙ ነሐሴ 16 ቀን የሰማዕቱ ረድኤትና በረከት በሁላችን ላይ ይደር። አሜን።

ጎዳር 24 ቀን ሱራፌል (24ቱ)ካህናተ ሰማይ ናቸው። ታሪካቸውን ኢሳ.6÷2-5 ራእ.11÷16-19፤19÷4 በድጋሜም ስንክሣር ይመልከቱ።

ምዕራፍ 24 ቍጥር 38

ታህሣሥ 24 የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ልደትና ደብረ ሊባኖስ ገዳም

ሚራ.2÷1-10 ማቴ.19÷29 ዕብ.11÷37

ደብረ ሊባኖስ / ገዳም / በ13ኛው ምእት በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ ወረዳ ከጀማ ጅረት በላይ በአቡነ ተክለሃይማኖት የተመሠረተ ገዳም ነው። የጥንት ስሙ ደብረ አስቦ ነበር ደብረ ሊባኖስ እየተባለ መጠሪት የጀመሪው ከ15ኛው ምእት በተለይም ከዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ /1426-1460/ ጀምሮ ነው። ስለዚህ የዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ታሪክ ዘመን ወለደብሮ ሙኒ ሰመያ ደብረ ሊባኖስ ቀዳሚሁሰ ነበረት እንዘ ይብልዋ ደብረ አስቦ። /ገዳማቸውን ደብረ ሊባኖስ አሏት በፊት ደብረ አስቦ ትባል ነበረች ይላል ለምን ስሙን መለወጥ እንዳስፈለገ የዘመን ታሪኩ አያብራራም ግን እንደሚመስለው ንጉሡ የአዳልን ገዢ ለመውጋት ሲነሣ ደብረ ሊባኖሶችና ሌሎች ገዳማትም በጸሎት እንዲማልዱት ጠይቆ ነበር ጠላቱን አሸንፎ ወደ ዙፋኑ ከተመለሰ በኋላ በዚህ ስም እንዲጠራ ያደረገ ሳይሆን አልቀረም።

በአባ ሊባኖስ ገድል ግን አስቀድሞ ገዳሙን ጀምሮት ስለነበር መላኩ ተገልጸ ይህንን ቦታ ከአንተ በኋላ ለሚመጣው ተውሰት ዘጋሜል የሚለውም ስም በአንተ ስም ደብረ ሊባኖስ ይባልልህ ብሎት ተሰወረ ይላል።

1. የገዳሙ መሥራች

አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተወለዱት ጽላልሽ ቡልጋ በታህሣሥ 24 ቀን በ1200 ዓ.ም ነው። አባታቸው ፀጋ ዘአብ እናታቸው እግዚእኀረያ ይባላሉ። የክርስትና ስማቸው ፍሥሐ ጽዮን ይባላሉ የመጀመሪያውን ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በ15 ዓመታቸው ወደ ጳጳሱ አቡነ ጌርሎስ ተወስደው ዲቁና ተቀበሉ 22 ዓመት እስኪሞላቸው በእናት በአባታቸው ቤት ኖሩ 16 ዓመት በኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ አስተምረዋል። ከዚያም ዛሬ ቦረና ሳይንት ወደሚባለው ምድረ አምሐራ ሄደው አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ገብተው እያገለገሉ 10 ዓመታት ተቀምጠዋል ። ቀጥሎም ወደ ደብረ

ሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ገብተው አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ዘንድ 10 ዓመታት ኖሩ ምንኩስናን የተቀበሉት በዚህን ጊዜ ነበር። በዚያው ጉዞአቸውን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ በማምራት ደብረ ዳሞ ከአባ ዮሐኒ ዘንድ ሄደው 12 ዓመታት አበውን እየረዱ ተቀምጠዋል። አስኬማንም በዚያን ጊዜ ተቀብለዋል። ከዚያ ተመልሰው በ1267 ዓ.ም ደብረ አስቦን ኋላ ደብረ ሊባኖስ የተባለውን መሠረቱ በዚህን ጊዜ ዓፄ ይኩኖ አምላክ መጥቶ መንግሥት እንዲመሰርት ከአቡነ ተክለ ኃይማኖት ጋርም ቃል ኪዳን መሠረተ ዘመኑም የኪዳን ዘመን ተባለ። አቡነ ተክለሃይማኖት በደብረ አስቦ ዋሻ 29 ዓመታት የምንኩስናን ሕግ ጠብቀው ገዳሙን እያስፋፉ ከኖሩ በኋላ በ99 ከ8 ወር ከ1 ቀን በ1299 ዓ.ም ዐርፈው እዚያው አስቦ ተቀበሩ እረፍቱ ነሐሴ 24 ፍልሰተ አጽሙ ግንቦት 12 ስባረ እግሩ ጥር 4 ይከበራል አቡነ ተክለሃይማኖት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በግብጽ ቅዱስ ናቸው ታቦት ተቀርጾላቸዋል ገድል ተጽፎላቸዋል ከኢትዮጵያውያን ቅዱሳን መሀከል የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ በግብጽ ቤተክርስቲያን ቅዱስ የተባሉት እስካሁን አቡነ ተክለሃይማኖት ብቻ ናቸው።

2. አስተዳደር

አቡነ ተክለሃይማኖት የወንጌል መልዕክታቸውን ፈጽመው በአስቦ ገዳም ከተሰበሰቡ በኋላ ብዙ ደቀመዛሙርት መምጣት ጀመሩ እነዚህም አብዛኛዎቹ ለአቡነ ተክለሃይማኖት የሥጋ ዘመዶች የነበሩ ናቸው እነዚህም ትልልቅ የተባሉት፡-

1. ዜና ማርቆስ
2. ቶማስ
3. ስምዖን
4. ተስፋ ሕፃን
5. ኤልሳዕ
6. ይትባረክ
7. ኤልያስ
8. ክርስቶስ ቤዛነ
9. መስቀል ሞአ
10. ተስፋ ሥሉስ
11. ፊልጶስ
12. አኖርዮስ
13. ኤፎስጣቴዎስ ናቸው

አቡነ ተክለሃይማኖት ለየት ብለው በአንድ ዋሻ ሲቀመጡ ሌሎች ሴቶች ጭምር በአንድ ዋሻ ውስጥ ይቀመጡ ነበር የሥራ ክፍልፍል አድርገው ግማሹ በግብርና ግማሹ በጸሎት ተጠምደው ከዋሉ በኋላ ማታና ሌሊት የማህበር ጸሎት ነበራቸው። የሚመገቡትም አብረው በአንድ ማዕድ ነበር ደብረ ሊባኖስን ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ገዳማት ለየት የሚያደርገው ቢኖር ስብከተ ወንጌሉን ማጠናከሩ ነበር። ዓሥራ ሁለት ሰዎች በቀዋሚነት በዚህ ሥራ ላይ ተሠማርተው ነበር። ይህ ድልድል የተፈጸመው በሦስተኛው እጨጌ በአቡነ ፊልጶስ መምህርነት ዘመን ነበር በዚያን ዘመን የነበረው ጳጳስ አቡነ ያዕቆብ የወንጌል ስብከት ፍላጐት የነበረው በመሆኑ የገዳሙን ዕቅድ በሙሉ ልቡ ደግፎታል። እነዚህ 12 ሰባክያን « ንቡረ እድ» በመባል ይታወቃሉ በአጠራር ይለይ እንጂ በሥልጣን ግን የኡጹስ ቆጶስነት ሥልጣን (ማዕረግ) ነበራቸው። ኢትዮጵያውያን ጵጵስና አይሾሙ የሚል አጉል የግብጾች ፈሊጥ ስለነበር ያንን በስም ለማክበር ሲባል የተፈጠረ አጠራር ነው። በአፈፃፀም ላይ አንዳንድ ችግር እንዳይፈጠር አርቆ በማሰብ የስብከት ሀገራቸው ስፋት ተወስኗል እያንዳንዱ ሰባኪ ከዚያ ክልል እንዳይወጣ በግዝት ቆሟል ንቡራኒ እዶቹም የሚከተሉት ናቸው።

1. ፊልጶስ ዋና አስተባባሪ ደብረ ሊባኖስ
2. ዜና ማርቆስ ከእንሳሮ ወንዝ እስከ ዓባይ ፈለስ
3. ታዴዎስ ከፅጉር ወንዝ እስከ ፈጠጋር
4. ማትያስ ከጉሮ እስከ ደዋሮ
5. ላሙኤል ከአይመለል እስከ ንብ ገደል
6. ገብረ ክርስቶስ ከዳባት እስከ ጉል ወንዝ
7. መርቆሬዎስ ደራ
8. አድኃኒ ደጋ ደሞት እስከ ጉመል
9. ኢዮአስ ጉራጌ
10. ቀውስጦስ መሐግል
11. ዮሴፍ ከቆጫ እስከ ሜጫ እናርያን ጭምር
12. አናሬዎስ ሰማሌ

እነዚህ ሰባክያን ከእናት ገዳማቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንዳይቋረጥ በዓመት አንድ ወር እያንዳንዳቸው ደብረ ሊባኖስ ተቀምጠው የአቡነ ተክለሃይማኖትን ዓጽም ያጥኑ ነበር በዚህ አኳኋን ድልደላቸው እንደሚከተለው ነበር። በግንቦት ወር የአቡነ ተክለሃይማኖትን ፍልሰተ ዓጽም ለማክበር ሁሉም ይሰባሰቡ ነበር።

1. ሰኔ አኖሬዎስ
2. ታህሣሥ ላሙኤል
3. ሐምሌ ዜና ማርቆስ
4. ጥር ኢዮአስ
5. ነሐሴ ዮሴፍ
6. የካቲት ታዴዎስ
7. መስከረም ማትያስ
8. መጋቢት ቀውስጦስ
9. ጥቅምት መርቆሬዎስ
10. ሚያዝያ ገብረ ክርስቶስ
11. ህዳር አድኃኒ
12. ግንቦት ፊልጶስ

የዓሥራ ሁለቱ ንቡራኒ ዕድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱሳን ስለሆኑ ገድል ተፅፎላቸዋል :: በገድላቸው ውስጥ የፈጸሙትም ሐዋርያዊ ተልዕኮ ተዘርዝሯል።

ገዳሙ በየጊዜው ለመነኩሳቱ መርጃ እርዳታ አግኝቷል ዓፄ ይኩኖ አምላክ ከመንግሥት ሚሶ መንግሥት እንደሰጠ ይታመናል ግን ይህ በተግባር የተተረጐመ አይመስልም። ዓፄ ይስሐቅ /1399-1414/ የመጀመሪያውን ቤተክርስቲያን ከማሠራቱም በላይ ገድሉን በማጻፍ ብዙ ንዋየ ቅድሳትና መተዳደሪያ ጉልት እንደሰጠ ይነገራል ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ /1426 -1460/ ለደብረ ሊባኖስ የተለየ አክብሮትና ፍቅር ነበረው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ገዳሙ ደብረ ሊባኖስ ተብሎ የተጠራው በእርሱ ዘመን ነበር ሁለት ፀባቴዎች በእርሱ ዘመን መሾም ተጀምሮአል አንዱ በገዳሙ ሆኖ የተለመደውን የበዓላት ድግስን ማዘጋጀት ሲሆን ሌላው ከንጉሡ አደባባይ ሆኖ እያስታወሰ የገዳሙን ጉዳይ የሚያስፈጽም ነበር በዚህ አኳኋን 150 ርስትና ጉልት ገዳሙ አግኝቷል በተጨማሪም ደብረ ብርሃን ኢየሱስን ደብረ ነጐድጓድን በእጨጌ ስር እንዲሆን አድርጓል። ከዚህም የተወሰነ ጉልት ገዳሙ አግኝቷል። ዓፄ በዕደ ማርያም ከ1460 እስከ 1470 አትሮንስ ማርያምንና ደብረ ማርያምን ሠርቶ በደብረ ሊባኖስ

ሥር እንዲሆኑ አድርጓል። ዓፄ አስክንድርም 1470 እስከ 1486 ደብረ ምስጢርንና ገነተ ጊዮርጊስን አሠርቶ ለደብረ ሊባኖስ ሰጠ። በክብርም ገዳሙን ከፍ አደረገው። ቀጥሎም የንጉሥ ደብዳቤ ሲላክላቸው መነኩሳቱ ቁጭ ብለው እንዲሰሙ አደረገ የራሱን ትልቅ ድንኳን በመስጠት አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ እንዲጠቀሙበት አደረገ አጨጌው በክብር በንጉሡ ቀኝ ተቀምጦ ፍርድ እንዲፈርድ ክብር ሰጠው እናቱ ንግሥት ሮምናም ምዕራፈ ማርያም የተባለች ቤተክርስቲያን አሠርታ ለደብረ ሊባኖስ ሰጠች። ዓፄ ናኦድ ከ /1486 - 1500/ መካነ ሥላሴን በአምሐራ አገር አሠርቶ ተጠሪነቱን ለደብረ ሊባኖስ እንዲሆን አደረገ በእርሱ ዘመን ነው ቤተክርስቲያኑ ከኤላም ዝቅ ብሎ ዛሬ ካለበት ሥፍራ ላይ ወርዶ የተሠራው በቅዳሴ ቤቱም ፣ ጊዜ ከጳጳሱ አቡነ ማርቆስ ጋር ሆኖ ደብረ ሊባኖስ ወርዶ እንደ አንድ ደብተራ ሆኖ እያሸበሸበ ቅኔ እየተቀኘ አክብሯል ለአቡነ ተክለሃይማኖት ዓጽም ማሳረፊያ የወርቅ ሳጥን ሰጠ ለአጨጌውም በግራና በቀኝ ሁለት ድባብ እንዲያዝለት ትዕዛዝ ሰጠ ዓፄ ልብነ ድንግልም / ከ1500 እስከ 1533/ ተጨማሪ ቤተክርስቲያን ሠራ ከጳጳሱ ከአቡነ ማርቆስ ጋርም ደብረ ሊባኖስ ወርዶ ቅዳሴ ቤቱን አክብረ። አንጾኪያ የምትባል ቤተክርስቲያን አሳንጾ ሌሎች ነገሥታት እንዳደረጉት ርሱም በደብረ ሊባኖስ ስር እንድትተዳደር አደረገ ዓፄ ገላውዴዎስም / ከ1543 እስከ 1551/ በግራኝ የፈረሰውን ቤተክርስቲያን አሠራ ተድባበ ማረያም የምትባለውንም ቤተክርስቲያን አሳንፆ ለደብረ ሊባኖስ ሰጠ መተዳደሪያ እንዲሆን 1.000 መሬት ለደብረ ሊባኖስና ለተድባበ ማርያም ሰጠ። ዓፄ ሠርፀ ድንግልም / ከ1555 እስከ 1588/ ድብ አንበሳና የወርቅ ወንጌል ሰጥቷል ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ለማስፈፀም ወደ ንጉሡ አደባባይ የሚመጣ መነኩሴ ሳይከለከል ክቤተ መንግሥት የተላከበትን ጉዳይ እንዲያመለክት ቀዋሚ ትዕዛዝ ሠራ ይኸውም ትዕዛዝ እስከ 20ኛው ምዕት ድረስ ሲሰራበት ቆይቷል።

3. ቤተክርስቲያን

አቡነ ተክለሃይማኖት ይቀደሱባት የነበረችው ታቦተ ማርያም ዓፅማቸው ካረፈበት ዋሻ እየተቀደሰባት 57 ዓመታት ኖረች በአጨጌ ሕዝቅያስ አራተኛው እጨጌ ዘመን የአቡነ ተክለሃይማኖት ዐጽም ፈልሶ ከዋሻው በታች ካለው ሜዳ ላይ መቃኞ ተሠርቶ ታቦቷም ዓጽሙም ከዚያ 1357 ዓ.ም ዐረፈ እስከ ዓፄ ይስሐቅ / 1399 - 1414/ ዘመነ መንግሥት ደንበኛ ቤተክርስቲያን አልነበረም ርሱ ትልቅ ቤተክርስቲያን ማሠራት ጀምሮ ሳለ ፈቃዱ ስላልሆነ ፈረሰ። ከዚያ መነኩሳቱ ሌላ ቤተክርስቲያን መሥራት ጀምረው ሥራው 7 ዓመታታ ያህል ፈጀ ቅዳሴ ቤቱ ሰኔ 21 ቀን ሲከበር ዓፄ ይስሐቅ የወርቅ አልባሳትን ላከ። ይህ ቤተክርስቲያን በግራኝ ዘመን ሐምሌ 24 ቀን 1524 ዓ.ም ተቃጥሏል። ሽሐብ የሚባለው ታሪክ ጸሐፊ የግራኝን ታሪክ የጻፈ ዝርዝር ሁኔታውን ይገልፃል ግራኝ በራሪ ከሚባለው ከተማ ነበር ደብረ ሊባኖስ የሚባል ትልቅ ቤተክርስቲያን ግራርያ ውስጥ እንዳለ በውስጡም የወርቅና የብር አልባሳትና ንዋየ ቅድሳት እንደሚገኙ ወሬ ይደርሰዋል። የዚህን ጊዜ አቡበከር ቀጢን የሚባለውን አዝማቹን ወደ ደብረ ሊባኖስ 300 ፈረሰኛ ሰጥቶ እንዲዘምት ያዘዋል። ርሱም እንደታዘዘው 6 ቀን ተጉዞ ደብረ ሊባኖስ አፋፍ ይደርሳል መነኩሳቱ ይህን ሲሰሙ መልዕክተኞች ከአቡበከር ጋር ለማደራደር ይልካሉ። ቤተክርስቲያኑን እንዳያቃጥል ይህን ቢያደርግ ወርቅና ብር የፈለገውን ያህል እንደሚሰጡት ይነግሩታል ይህ አይሆንም ብሎ ቤተክርስቲያኑን ቢያቃጥል አነርሱም አብረው ለመቃጠል እንደሚመርጡ ነገሩት። አቡበከር ቀጢንም ከጦር አለቆች ጋር ምክር ያዘ። ከአነርሱ ግማሾቹ ወርቅና ብር ካገኙ ቤተክርስቲያኑን ለመተው ፈለጉ ግማሾቹ ግን ከወርቁና ከብሩ ምርጫቸው የቤተክርስቲያኑን መቃጠል እንደሚመርጡ ተናገሩ። አቡበከር ቀጢን የመጀመሪያዎቹን ደገፈና ይህንኑ ለመልዕክተኞቹ አስታወቀ እነርሱም ከውሳኔው ደስ ብሏቸው ሁለት ካባዎች እያንዳንዳቸው ላይ 150 ወቄት ወርቅ ያለበት ወዲያው ሰጡትና ይህንኑ ለገዳሙ መነኩሳት ለማብሰር ወጣ ሲሉ አራይ አቡበከር የሚባል የበለው ነገድ ውሳኔውን እንደሰማ ሲሮጥ

ሄዶ ቤተ ክርስቲያኑን በእሳት አያያዘው የዚህን ጊዜ ሸሀብ ኦዲን እንደሚለው ከጥቂቶች በስተቀር መነኮሳቱ እንደ እሳት እራት ተማገዱ በኡራይ ላይ አቡበከር ቀጢንም መሐመድ ግራኝ እርምጃ አልወሰዱም::

ከስደት በኋላ በዓፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት እቴጌ ሰብለ ወንጌል ቤተክርስቲያኑን አሠራች ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጋሎች ቤተክርስቲያኑን አቃጠሉት መነኮሳቱም ታቦቱንና የአቡነ ተክለሃይማኖትም ስባረ አጽም ይዘው ወደ ቆላው ሸሹ አመቺ በሆነ ጊዜ እየመጡ ቦታውን አጥነው ይመለሱ ነበር:: ዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ / 1674 - 1698 ዓ.ም/ ለአቡነ ተክለሃይማኖት ልዩ ፍቅር ነበረውና ቦታውን ለመሳለም ጽኑ ፍላጐት ነበረው በመጀመሪያው ሙከራው አልተሳካለትም እስከ መርሐቤቴ ዘልቆ ተመለሰ በሁለተኛው ግን በ1691 ዓ.ም ተሳክቶለት ከቦታው ደርሶአል:: ወሐዘነ ንጉሥ ዓቢየ ሐዘነ እንበይነ ተነሥቶታ በእደ ግራኝ ወከዊኖታ ሐቅለ በእደ ጋላ:: / ንጉሡ በግራኝ በመፍረሱና ከዚያም በጋሎቹ ምድረበዳ በመሆኑ ትልቅ ሐዘን ተሰማው ይላል የዘመን ታሪኩ::

የሸዋ መሳፍንት ኃይላቸው እስኪበረታ ድረስ ለደብረ ሊባኖስ ቀን አልወጣም ነጋሢ / በ1763 እስከ 1792 / ተጋንቻ መጥቶ አያበርን አቀና:: ይህ ሁኔታ ለደብረ ሊባኖስ መቅናት በር ከፋች ነበር:: ይህም ሲባል ተስፋው እየተጠናከረ ሂደ እንጂ የመቅናቱ ነገር ገና ነው:: ይህ ዕድል የተጠበቀው ለመርዕድ አዝማች ወሰን ሰገድ / ከ1800 እስከ 1804/ ነበር:: በዘመነ ማቴዎስ በወርኃ ጥር በ1804 ዓ.ም የደብረ ሊባኖስ ሥራ ያትጋፊኝ ላይ ተጀመረ:: በወርኅ ግንቦት ተፈጽሞ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ:: በ1870 ዓ.ም ዓፄ ዮሐንስ በአክሱም ጽዮን አሠራር አንድ ቤተክርስቲያን ማሠራት ጀምረው በ1876 ዓ.ም አለቀና ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ:: በ1895 ዓ.ም ዓፄ ምኒልክ ሌላ ቤተክርስቲያን ለማሠራት ራስ አባተን አዘዙት እርሳቸውም ያርጊ ከሚባል ግሪክ ጋር ኮንትራት ፈረሙ:: ሥራው በ1900 ዓ.ም ተጠናቆ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ:: አሁን ያለው ቤተክርስቲያን የታነፀው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲሆን መሠረት የተጣለው በ1952 ዓ.ም የሕንፃው ሥራ የተጠናቀቀው በ1955 ዓ.ም ነው:: የጻድቁ ረድኤትና በረከት በሁላችን ላይ ይደር:: አሜን::

ምዕራፍ 25 ቁጥር 39

ኅዳር 25 ቀን መርቆሬዎስ ሰማዕት

ጌታችን ኢየሱስ ክረስቶስ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ:: ማቴ. 10÷32 ብሎ በተናገረው አምላካዊ ቃል መሠረት በከሐድያን ነገሥታትና በኢአማንያን ሕዝብ ፊት ቁመው ስለ ክርስቶስ አምላክነት እየመሰከሩ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ሕይወታቸውን መስዋዕት አድርገው ያቀረቡ ሰማዕታት ብዙ ናቸው ከነዚህም ውስጥ በተጋድሎውና በአማላጅነቱ የታወቀው ቅዱስ መርቆሬዎስ ነው:: ቅዱስ መርቆሬዎስ የመጀመሪያው ስሙ ፒሉፓዴር ይባል ነበር ቃሉ ላቲን ሲሆን ትርጉሙ ታማኝ ሀቀኛ ማለት ነው መርቆሬዎስ ማለት ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ማለት ስለሆነ ቋሚ መጠሪያ ስሙ ሆኖአል የአባቱ ስም ሎርዮ የእናቱ ስም ክርስቲና ሲሆን በክርስትና ስም አጠራሩ ደግሞ የአባቱ ስም ኖኅ የእናቱ ታቦት የራሱ መርቆሬዎስ መሆኑን በመጽሐፈ ስንክሳርና በገድሉ ተጽፎ ይገኛል ዜግነታቸው ደግሞ ሮማውያን መሆናቸውን ይገልጻል::

ቅዱስ መርቆሬዎስ የተወለደው በ221 ዓ.ም ሲሆን በዚሁ ዘመን የቅዱስ መርቆሬዎስ አባት ትልቅ ባለሥልጣን ሆኖ በመርዶክውያን አገር ተሹሞ ያስተዳድር ነበር የመርቆሬዎስ አባት ከሞተ በኋላ በአባቱ እግር ተተክቶ ቅዱስ መርቆሬዎስ በዚያ አገር ተሹሞ እግዚአብሔርን በመፍራት በታማኝነት ያስተዳድር እንደነበር ገድሉ ይናገራል:: በዚያ ዘመን ዳኬዎስ የተባለ የሮም ንጉሥ መርቆሬዎስን በጣም ይወደው ነበር ምክንያቱም ዳኬዎስ ንጉሥ በጠላቶቹ ላይ በዘመተ ቁጥር ቅዱስ መርቆሬዎስ በእግዚአብሔር ረዳትነት በሚያሳየው ድል አድራጊነት ያደንቀው ስለነበር ነው:: የሮም ንጉሥ ዳኬዎስ ወደ ቤተ መንግሥቱ በተመለሰ ጊዜም ድል ለስገኘለት እግዚአብሔር አምላክን ዘንግቶ ለማይሰማና ለማይናገረው ጣዖት ምሥጋና መስዋዕት አቀረበ::

ቅዱስ መርቆሬዎስ ይህንን በማየቱ ሰው ድል ለሰጠው ለእግዚአብሔር ማመስገንና መስገድ መስዋዕት ማቅረብ ሲገባው እንዴት ለሰው ሠራሽ ጣዖት ይሰግዳል መስዋዕትስ ያቀርባል በማለት በጣም አዘነ በዚሁ ሀዘን ስለተሰማው ንጉሥ ዳኬዎስ ወደ አቀረበው ግብዣ ሳይሄድ ቀረ የንጉሡ ሠራዊት አለቆችም ለንጉሥ ዳኬዎስ እንዲህ አሉት እኛ ትዕዛዝህን አክብረን ላቆምከው ጣዖት ስንሰግድና በተዘጋጀው ግብዣ ስንገኝ መርቆሬዎስ ግን ትዕዛዝህን በመናቅ ለጣዖት መስገድ አያስፈልግም በማለት ሳይመጣ ቀርቶአል በማለት ለንጉሡ ነገሩት ንጉሥ ዳኬዎስም ቅዱስ መርቆሬዎስን አስጠርቶ ስለምን ለቆመው ጣዖት እንዳልሰገደና ወደ ግብዣው እንዳልመጣ ጠየቀው ቅዱስ መርቆሬዎስም የሚያመጣበትን ስቃይና ግርፋት ሳይፈራ በድፍረት እኔ ለማይሰሙና ለማይናገሩ ጣዖታትህ ልሰግድና መስዋዕት ላቀርብ ይቅርና አንተ ድል ለሰጠህ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ክብር ማቅረብ ሲገባህ ድል ላልሰጠህ ጣዖት በመስገድህና መስዋዕት በማቅረብህ በጣም አዝናለሁ እኔስ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን አመልካለሁ ለእርሱም ምሥጋናና ክብር አቀርባለሁ ብሎ መለሰለት ታጥቆት የነበረውን መሳሪያና የተሰጠውን ሽልማትም ወረወረለት ንጉሥ ዳኬዎስም በመርቆሬዎስ ሁኔታ ተደናግጦ በጣም ተናደደ በግርፋትና በእስራት እንዲያሰቃዩት አዘዘ ደሙ እንደ ውኃ እስኪፈስ ድረስም ገረፋት በዚህ ሁሉ ስቃይ ላይ ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መላኩ ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ ያጽናናው ነበር::

ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ በንጉሡ በዳኬዎሥ ትዕዛዝ በብረት አልጋ ላይ ተኝቶ ብዙ የእሳት ነበልባል እንዲያነዱበት ተደረገ ቅዱስ መርቆሬዎስ ቀደም ሲል ብዙ ግርፋት ተገርፎ ስለነበር ከሠውነቱ የፈሠሠው ደም የእሳቱን ነበልባል አጥፍቶታል ቅዱስ መርቆሬዎስ በእግዚአብሔር ኃይል በተአምራት ከእሳቱ ድኗል በእምነት የእሳትን ኃይል አጠፉ ዳን.3 ኢሳ. 43÷2-5 ዕብ.11÷33-35 በግዞት ቤት ሳለ ቅዱስ መርቆሬዎስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ ወዳጄ መርቆሬዎስ ስለስሜ ብለህ ብዙ ሥቃያትን ስለተቀበልክ ስለ አምላክ መርቆሬዎስ ብሎ ለተራበ

ላበላ ለተጠማ ላጠጣ ለታረዘ ላለበሠ በስሙ ቤተክርስቲያን ላሠራ ዕጣን ስንዴ አልባሳት ለሠጠ ሁሉ እምርልህለሁ ገነት መንግሥተ ሰማያት እንዲገባ አደርጋለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ሠጥቶታል በዚህም ቅዱስ መርቆሬዎስ ፈጣሪውን አመሰግኗል::

ቅዱስ መርቆሬዎስ ብዙ መከራና ስቃይ ከተቀበለ በኋላ በንጉሡ በዳኬዎስ ትዕዛዝ ኅዳር 25 ቀን አንገቱን በሠይፍ ተከልሎ ሰማዕትነት ተቀበለ ራእ. 2÷10፣11÷10 ስለተጋድሎውም ሦስት አክሊል ከሰማያት ወረዱለት መላእክትም ከሰማያት ወርደው የጻድቅ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው መዝ.115÷5 እያሉ ልብን በሚመስጥ ምሥጋና እየዘመሩ የቅዱስ መርቆሬዎስን ነፍስ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት አገሯት:: ሐምሌ 25ትም ቅዳሴ ቤቱ ነው::

ቂሳርያ በምትባል አገር ባስልዮስና ጉርጉርዮስ የተባሉ ቀዱሳን አበው ሌሎችም ምእመናን የሚጸልዩባት በወህኒ ቤት አጠገብ የምትገኘ የቅዱስ መርቆሬዎስ ቤተክርስቲያን ነበረች ባስልዮስና ጉርጉርዮስ ወደ ቤተክርስቲያን ገብተው በቅዱስ መርቆሬዎስ ስእል ፊት ቆመው ሲጸልዩ በቅዱስ መርቆሬዎስ ሥዕል እጅ የነበረው ጦር በደም ተነክሮ ሲንጠባጠብ አዩ መርቆሬዎስ ሆይ ያንን ከሃዲ ኡልያኖስን ገደልከው ሲሉ የቅዱስ መርቆሬዎስን ሥዕል ጠየቁት ሥዕሉም ራሱን ዘንበል አድርጐ አዎን አላቸው ስሊዚህ ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ኃበ ሥዕሉ ለቅዱስ መርቆሬዎስ ደነነ ሥዕል ከመኦሆ ዘይብል ወተፈሥሁ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ተብሎ «በቤተክርስቲያን የሚዘመረው ስለዚህ ነው ትርጉሙም ባስልዮስና ጎርጎርዮስ በቅዱስ መርቆሬዎስ ስዕል ፊት ቆመው በጸለዩ ጊዜ ሥዕሉ እሺ እንደሚል ሠው ራሡን ዘንበል አደረገ ማለት ነው:: ገላ.3÷1 እንደ ቅዱስ መርቆሬዎስ ታማኝ ሠማዕት ለሆነ ዮሐንስ በራእዩ 3÷12 እንዲሲል ጽፎለታል ድል የነሳውን በአምላኬ መቅደስ አምድ እንዲሁም አደርገዋለሁ ወደፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን

የአዲሲቱን ኢየሩሳሌም ስም በእርሱ ላይ እጽፋለሁ ብሏል በዚህ ቅዱስ ቃል መሠረት ቅዱስ መርቆሪዎስ ወደ አዲሲቱ ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ገብቶአል አዲስ ስም በስሙ ላይ ተጽፎለታል ስሙም በአዲስ መዝገብ ተመዝግቦአል ሉቃ. 10÷20 ብዙዎችን ምእመናን ቅዱስ ወንጌልን አስተምሮ በሰማያዊ መዝገብ እንዲመዘገቡና መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርሡ አድርጓል።

የገጸ ከለባት ግኝት የመርቆሬዎስ አባትና አያት አውሬ ሰማደን ሲሄዱ ገጸ ከለባት አግኝተውት አያቱን በሉት አባቱን ሊበሉ ፈልገው ሳለ መልአኩ ከርሱ የሚወጣ መልካም ፍሬ ስለአለ አትንኩት አላቸው መልአኩም ዙሪያቸውን በእሳት ከበባቸው ቢቸግራቸው ወደ ቅዱስ መርቆሬዎስ አባት መጥተው ሰገዱለት እንደ በጉችም የዋሆች ሆኑ አብረውትም ወደ መንደር ገቡ ክርስቲያኖችም ሆኑ ንጉሡም የውሸ መልክ ያላቸውን ዜና በሰማ ጊዜ ወደርሱ አስቀረባቸው እግዚአብሔርም የቀድሞ ፍጥረታቸውን መልሶላቸው ንጉሡ ያቀረባቸውን ሁሉንም አራዊት አጠፏቸው ንጉሡም ሃይማኖታቸውን ይለውጡ ዘንድ ሸነገላቸው ባልሰሙትም ጊዜ ሊያሰቃያቸው ጀመረ በዚህ ጊዜ አንዱ አምልጦ ወደ ጌታው ሄደ ሁለተኛው ግን በሰማዕትነት ሞተ በዚህ አይነት አባቱ ኖጎንና መርቆሬዎስን ሲያገለግሉ ኑረዋል። መርቆሬዎስም ከሞተ በኋላ ፈረሱ ለ15 ዓመታት ያህል ወንጌልን ለሕዝቡ እንዳስተማረ ገድሉ ይናገራል። ለአግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለሌለ መናገር ይችላል የበልአምን አህያ እንዳናገረ ዘጎ. 22÷30 የሰማዕቱ ረድኤትና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።

ምዕራፍ 26 ቁጥር 40

ግንቦት 26 ቀን ቅዱስ ቶማስ (ዲዲሞስ) ማቴ.10÷3 ዮሐ. 11÷16

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ትንሣኤ ሙታን የለም ብለው ያምኑ ከነበሩት ሰዱቃውያን ወገን እንደነበር ይነገራል። ማቴ.22÷23-33 ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን አሥሩ ሐዋርያት ሲነግሩት « የችንካሩን ምልክት በእጆቼ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጀንም በጉኑ ካላገባሁ አላምንም» ያለው በዚህ የተነሣ ነበር። ዮሐ.20÷25 በኋላ ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቶማስ በእምነቱ እንዲጠነክር አስቀድሞ አሥሩ ባሉበት እንደተገለጠው ሁሉ ዳግመኛ ቶማስ ባለበት በዝግ ቤት ውስጥ ተገልጦ ቶማስ ያለው ሁሉ እንዲፈጽምለት አደረገ። ቶማስም « ጌታዬ አምላኬ» ብሎ አምኖ መስክሮአል ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ከሐዋርያት ሁሉ ርቆ ወደ ምሥራቅ የተጓዘ ሐዋርያ ነው።

የምሥራቋ የክርስቲያኖች ከተማ

በዮሐንስ ወንጌል 12÷20-22 ግሪኮች በሐዋርያው እንድርያስ አቅራቢነት ከጌታችን ጋር እንደተነጋገሩ ተገልጦአል መጽሐፍ ቅዱስ ስለነዚህ ግሪኮች ማንነት ባይገልጥልንም በቤተክርስቲያን ትውፊት ግን እነዚህ ግሪኮች በሮማ ግዛትና በፐርሺያ መካከል ይኖሩ ከነበር አብጋር ዑካማ ከተባለ የዑር (ኤዴሳ) ንጉሥ የተላኩ ነበሩ አብጋር ጻንሆይ እንደማለት ነው ለዑር ነገሥታት ሥመ መንግሥታቸው ነው። አብጋሮች በዑር (ኤዴሳ) የነገሡት ከጌታችን ልደት በፊት 132 ዓ.ዓ. እስከ 216 ዓ.ም ድረስ ነው አብጋር ዑካማ በማይድን በሽታ ተይዞ ሲሰቃይ ከግሪክ ነጋድያን የጌታችንን ዝና በመስማቱ የሚከተለውን ደብዳቤ ለጌታ ላከለት። የተላከውም ከአብ ጋር ዑካማ ለእውነተኛው መድህን ለኢየሱስ ክርስቶስ

በኢየሩሳሌም ለተገለጥከው ሰላም ላንተ ይሁን ሥር ሳትምስ ቅጠል ሳትበጥስ ስለምታደርገው የማዳን ሥራና ስለ አንተ ዝና ሰምቻለሁ እንደነገሩኝ ከሆነ ዕውሩን ታበራለህ ሽባውን ትተረትራለህ ይህን ስትሰማ ወደ እኔ መጥተህ ከዚያ ከሚያሰቃየኝ የደዌ ዳኛ የአልጋ ቁራኛ ትገላግለኝ ዘንድ አለምንኻለሁ። ይህንንም ደብዳቤ ልኬብኻለሁ አይሁድ ባንተ ላይ እንደተነሣሡብህ ሰምቼሀለሁ ሊገድሉህም ይፈልጋሉ አሉ ምንም እንኳን ከተማዬ ጠባብ ስትሆን ውብናት ለእኔና ለአንተም ትበቃለችና ወደ እኔ ና ሲል ላከ ጌታችንም ከመልዕክተኞቹ ደብዳቤውን ተቀብሎ ካነበበ በኋላ እንዲህ ብሎ መለሰለት « አብጋር ሆይ አሁን ልጉበኘህ አልችልም ነገር ግን ከትንሣኤዬ በኋላ ከደቀ መዛሙርቴ አንዱን እልክልሃለሁ። በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት ከዕርገት በኋላ ጌታችን ቶማስን ወደ ዑር ላከው ቶማስም ከሰባ ሁለቱ አርድዕት ወገን የሚሆነውን ደቀ መዝሙሩን ታዴዎስን (አዳይ) ላከለት። ቅዱስ ታዴዎስም ኤዴሳ ገብቶ አብጋርን ፈውሶ ሀገሩን ቀደሰለት ከአብ ጋር ጀምሮም ብዙ ሰዎች በክርስትና አምነው ተጠመቁ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ተተክለ አርስዋም ምሥራቅ እስያ የመጀመሪያዋ የክርስቲያን ከተማ መሆንዋ በታሪክ ይነገራል።

ሐዋርያው ቶማስ ታዴዎስን ወደ ኤዴሳ ከላከ በኋላ በቅድሚያ ወደ ፕርሺያ ከዚያም ወደ ሕንድ ተጓዘ ቅዱስ ቶማስ ሕንድ የደረሰው በ46 ዓ.ም አካባቢ ነው።

የሰማዩ ቤተ መንግሥት

በሕንድ የማላበር ግዛት በታክሻሲላ ከተማ የነበረው ንጉሥ ጉንዶ ፓረስ በኢየሩሳሌም ስለነበረው የሰሎሞን ቤተ መንግሥት ዝና አየሰማ ርሱም በግዛቱ ይህን ዓይነት ቤተ መንግሥት ለማሠራት ይፈልግ ነበርና ነጋዴዎች በየአገሩ ሲጓዙ የታወቀ ግንበኛ እንዲያመጡለት አሟዋቸው ነበር። ይህን መልዕክት ከሰሙት ነጋዴዎች መካከል አንዱ ወደ ፕርሺያ ወረደ ቅዱስ ቶማስ ወደ ሕንድ ተጉዞ ወንጌልን ለመስበክ መንገድ ሲፈልግ ከዚያ ነጋዴው ጋር ተገናኘ ነጋዴውም የቶማስን ከኢየሩሳሌም መምጣት ሲሰማ የግንበኝነት ሙያ ይችል እንደሆነ ጠየቀው ቶማስም በኢየሩሳሌም

በነበረበት ጊዜ ሕንፃ በማነጽ ኑሮውን ይገፋ እንደነበር ለነጋዴው መለሰለት። ነጋዴውም በዚህ አጋጣሚ እጅግ ተደስቶ ቶማስን ወደ ሕንድ ማላበር ወሰደው ንጉሡም የቶማስን ሙያ ሲሰማ ነፍስ አልቀረለትም ንጉሡ ለሠራተኛ መቅጠሪያ ለድንጋይና ዕብነ በረድ፣ ለብርና ወርቅ፣ ለብረትና እንጨት መግዣ እያለ ለቅዱስ ቶማስ ያለ የሌለውን ገንዘብ ይልክለት ጀመር። ቅዱስ ቶማስ ገንዘቡን ሲያገኝ የተጓዘው ወደ ገበያ ወይም ሠራተኛ ፍለጋ ሳይሆን ወደ ድኾች መንደር ነው በዚያም ለተራቡት ምግብ ለታረዙት ልብስ በየቦታው ለወደቁት መጠለያ እየገዛ ማደል ጀመረ በሽተኞችን እየፈወሰ እና የተቸገሩትን እያጽናና ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን መስበክ ያዘ። ንጉሥ ጉንዶፓረስ ገንዘቡን በላከ ቁጥር የሚገነባው ቤተ መንግሥቱ ሳይሆን የድኾችና የደካሞች ቤት ሆነ ለቤት መሥሪያ የመደበው ገንዘብና ጊዜ እንደተጠናቀቀ ቤተ መንግሥቱን ሊጐበኝ ወጣ ጫካው አልተነካም ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ቀርቶ የወደቀ ድንጋይ የለም ንጉሡ በዚያ በኩል የሚያልፍ አንድን መንገደኛ ጠራና ቶማስ የታለ ሲል አፈጠጠበት ቶማስ የተራቡትን እያበላ የተጠሙትን እያጠጣ የታረዙትን እያለበሰ ሕሙማኑን እየፈወሰ በድኾች መንደር ይገኛል ሲል መንገደኛው መለሰለት። ርሱ ባልከፋ ታዲያ የሠራልኝ ቤተ መንግሥት የታለ? ንጉሡ መንገደኛው ላይ እንዳፈጠጠ ጠየቀው በድንጋይ የተሠራ ቤተ መንግሥት ላያዩ ይችላሉ ጌታዬ ነገር ግን በሕዝብም ገጽታ ላይ ደስታና ፈገግታ ማንበብ ይችላሉ አለው መንገደኛው በዚህ ጊዜ ንጉሡ ያ ሁሉ ገንዘብ እንደባከነበት መጠርጠር ጀመረ ወዲያው ወታደሮችን አዘዘና ቶማስን ፍለጋ አካባቢውን አጥለቀለቁት ቅዱስ ቶማስ ተይዞ እንዲመጣ ተይዞ በመጣ ጊዜም «ቤተ መንሥቴን ለምን አልሠራህልኝም ?» አለው ንጉሡ «ሠርቻለሁ ጌታዬ» ብሎ ቶማስ መለሰ «የታለ» ? «ጫካው እንኳን መች ተነሣ?» «አርግጥ በምድር ላይ የድንጋይ ቤተ መንግሥት ላያዩ ይችላሉ እኔ ግን በሰማይ ላይ ቤተ መንግሥት ሠርቼልዎታለሁ» አለው ቶማስ ለንጉሡ ያን ጊዜ ንጉሡ ተቆጣ። ቶማስን እጅ እግሩን እየቆራረጡ እንዲያሠቃዩት አዝዞ ወህኒ አወረደው በዚያች ሌሊት የንጉሡ ወንድም

የሆነው ልዑል ጋድ በድንገተኛ በሽታ መጣደፍ ጀመረ ሊነጋጋ ሲልም ነፍሱ ወጣች። የጋድ ነፍስ በመላእክት ታጅባ ወደ ሰማያት ወጣች ካጀቧት ቅዱሳን መላእክት አንዱ ብዙ አብያተ መንግሥታትን እያሳያት ትኖሪባት ዘንድ ደስ ያለሽን ምረጪ አላት የጋድ ነፍስም በአብያተ መንግሥታቱ መካከል የሚታየውን የሚያምር ቤተ መንግሥት መረጠች ይህ ቤተ መንግሥት ያንቺ አይደለም ቶማስ ለንጉሥ ጉንዶፓረስ የሠራለት ሰማያዊ ቤተ መንግሥት ነው አላት በዚህች ሰዓት የልዑል ጋድ ነፍስ ከሥጋው ጋር ተዋሐደች ጋድ ሊቀብሩት በተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ተንቀሳቀሰ ከዚያም አፈፍ ብሎ ተነሣ ልዑል ጋድ በዚያች ቅጽበት የተመለከተውን ሁሉ ለንጉሥ ጉንዶፓረስና ዕተሰበሰቡት ሁሉ ነገራቸው። ንጉሡ ይህንን ሲሰማ በቶማስ ላይ በሠራው ግፍ ሁሉ አዘነ ተፀፀተም ያ- ያሰበው ቤተ መንግሥት መሠራቱን ሲሰማ ቶማስን ከወህኒ አወጣው ርሱና ቤተሰቡም በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ ጉንዶፓረስም ሌላም ቤተ መንግሥት ሥራልኝ እያለ ያለውን ሁሉ ገንዘብ ለቶማስ ይሰጠው ጀመር የአገር ባለፀጐችም አሠረ ፍኖቱን ተከተሉ። ቅዱስ ቶማስ ከማላበር ጀምሮ እስከ ቻይና በመዝለቅ ወንጌልን ሰብኳል በመጨረሻም በ66ዓ.ም በሚላፓር ከተማ የሚገኙ አምላክያነ ጣያት ቆዳውን ገፈው ሰልቻ በመሥራት በሰውነቱ ጨው ነሥንሰው እያሰቃዩ ሰሞት አብቅተውታል። በ4ተኛው መ/ክ/ዘመን ዐፅሙ ወደ ኤዴሳ መጥቶ በክብር ዐርፎአል። የሰማዕቱ ረድኤትና በረከት በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ምእራፍ 27 ቍጥር 41

መጋቢት 27 ቀን መድኃኔዓለም

ይህን ስም እናቱ ድንግል ማርያም አውጥታለታለች ሉቃ.1÷48 ስምን መልአክ ያወጣዋል እንዲሉ በተወለደ ጊዜ መልአክ አውጥቶለታል ሉቃ.2÷11 ኋላም በመዋዕለ ስብከቱ የሰማርያ ሰዎች በዚህ ስም ጠርተውታል ዮሐ.4÷42 መላው ዓለም የተቀበለው ግን በዕለተ ስቅለት በተደረገው ድኅነት ነው።

ለኃጢአት መሞን ለጽድቅ እንድንኖር ርሱ እራሱ በሥጋው ሐጢያታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ 1ጴጥ.2÷24 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን በደል ክሶ አዳምን ለማዳን ፈቃዱ በሆነ ጊዜ ካሣውን እንጨት ላይ በመሰቀል ሰላምን አደረገ ብንል ችግሩ አዳም ላይ የደረሰው በአፀበለስ ምክንያት ነው በአፅ የገባውን በዕፅ ለመመለስ ነው። እሾህ በእሾህ ይነቀሣል ከብት በከብት ይመለሣል እንዲሉ አዳም በበደለ ጊዜም ወድቆበት የነበረው እርግማን እንዲህ የሚል ነበር አዳም የሚስትህን ቃል ሰምተሐልና ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን ዘፍ.3÷17 ብሎ ነበርና ይህንን እርግማን ከአዳም ላይ ለማንሳት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መርገመ ኦሪትን እንደተቀበለ ዘዳ.21÷22 ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሠዎች በፃፈው በምዕ.3÷13 በእንጨት የሚሠቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን ተብሏል። ስለሞቱም ጲላጦስ አይሁድን እናንተ ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት ብሏቸው ነበር አይሁድም ለእኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም ብለው መልሠዋል ኢየሱስ በምን አይነት ሞት ሊሞት እንዳለው ሲያመለክት የተነገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው ዮሐ.18÷31-32 ጌታ የሚሞት በመስቀል ተሰቅሎ እንጂ እንደ አይሁድ ሥርዓት አይደለምና ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም ብለዋል። ሔዋን በደልን ስትፈጽም በጆሮዋ ምዕዳነ አርዌን ሰምታ በአይኗ አይታ በእግሯ ሔዳ በእጇ ቆርጣ በአፏ በልታ ነው ጌታ በዚህ ሁሉ ክሶናል በጆሮዋ ምዕዳነ አርዌን እንደሠማች ዝንጉጇ አይሁድን ሰምቷል። በአይኗ እንዳየች ግርማ አይሁድን አይቷል በእግሯ ሄዳ በእጇ እንደቆረጠች እጆን እግሩን ቸንክረውታል በአፏ እንደበላች መራራ ሐሞትን ቀምሷል በዚህ ሁሉ ክሶ አድኖናል ቅዱስ ጳውሎስ ሮሜ 8÷2-4 « በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ሕይወት ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶናልና» ብሏል።

ሊቀ ካህናት እና የሕዝብ ሽማግሌዎች ክርስቶስን ለመስቀል የነሳሳቸው ምክንያት ምን ነበር?

1. እጁ የሰለሰችውን ሰው ስላዳነ ፈሪሳውያን እንዲያጠፉት ተማክሩበት ማቴ.12÷9-14
2. በሰንበትም ቀን በምኩራብ ሲያስተምር ከ18 ዓመት ጀምሮ የታመመችውን ስለፈወሰ ነው ሉቃ.13÷10 -17
3. 38 ዓመት የታመመውን መፃጉዕን ባዳነ ጊዜ ይህንን ያዳነው በሰንበት ነው ብለው አይሁድ ያሳድዱት ነበር። ሊገሉትም ይፈልጉት ነበር ዮሐ.5÷16
4. አልዓዛርን ባሥነሣው ጊዜ ሊቀ ካህናት የነበረው ቀያፋ የሚሉት ከነርሱ አንዱ «እናንተ ምንም አታውቁም ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ይሞት ዘንድ እንዲሻለን አታስቡም» አላቸው ዮሐ.11÷49 ስለዚህም የካህናት አለቆች ይይዙት ዘንድ ያለበትን ሥፍራ የሚያውቅ ሰው ቢኖር እንዲያመለክታቸው አዘው ነበር። ዮሐ.11÷57
5. «ሆነአና እየተባለለት እየሩሳሌም በገባ ጊዜ ሕዝቡ ስለሰሙ ሊቀበሉት ወጡ ስለዚህ ፈሪሳውያን ተበሳጭተው እርስ በእርሳቸው አንድስ እንኳን ልታደርጉ እንዳይቻላችሁ ታያላችሁ ዮሐ.11÷28 እነሆ ማስተማር ከጀመረ ጀምሮ ስለ ተወዛገቡ የመጨረሻውን እርምጃ ለመውሰድ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ተሰበሰቡ ኢየሱስንም በተንኰል ሊያስይዙት ሊያስገድሉትም ተማከሩ ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ ሁከት እንዳይነሣ በበዓል አይሁን አሉ»ማቴ.26÷4-5

በህማሙና በሞቱ ሰሞን ያደረጋቸው ተዓምራት

1. በለምፃሙ በስምዖን ቤት ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው የበዛ ሽቱ ቀባችው ማቴ.26÷6-13 ማር.14÷3-9 ሉቃ.7÷36-50 ዮሐ.12÷1-8
2. ሀጽበተ እግር ዮሐ.13÷1-26
3. ምስጢረ ቁርባን ዘፀ.12÷1-5 ለሙሴ የነገረው ነው ቁጥር 43 ሕግዚአብሔርም ሙሴን እና አሮንን «ይህ የፋሲካ ሕግ ነው አላቸው » ይህ የፋሲካ ሕግ ሥርዓቱ መሠረቱ የእስራኤል ከግብጽ መውጣት ሆኖ እስከ እለተ አርብ ድረስ ሲሰራበት ኖሯል። ጌታም

ይህንን ሳይለውጥ በዓሉን ለማክበር ለደቀመዛሙርቱ የሰጠውን ትዕዛዝ እንመልከት ማቴ.26÷17 ርሱም «ወደ ከተማ ከእገሌ ዘንድ ሄዳችሁ መምህር ጊዜዬ ቀርቧልና ከደቀመዛመርቴ ጋር ከእንተ ዘንድ ፋሲካን አደርጋለሁ ይላል በሉት አለ» ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ እንዳዘዛቸው ፋሲካን አሰናዱ ማር.14÷12-16 ደግሞም በሉቃስ 22÷7 የተላኩት ደቀመዛሙርት ጴጥሮስና ዮሐንስ መሆናቸው ተገልጿል እርሱም ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህንን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመኝ ነበር እላችኋለሁ የእግዚአብሔር መንግሥት እስኪፈጸም ድረስ ከዚህ አልበላም አላቸው ጽዋውንም ተቀብሎ አመስግኖም እንካችሁ ተካፈሉት እላችኋለሁና የእግዚአብሔር መንግሥት እስኪመጣ ድረስ ከአሁን ጀምሮ ከወይኑ አልጠጣም አለ ይህንን ብሎ የቀደመውን ሥርዓት ፋሲካ ወደፊት ከዚህ አልበላም ከወይኑ ፍሬም አልጠጣም ብሎ የአሪቱን ሥርዓት ዘጋ ሉቃ.22÷20 ወደ ሐዲስ ሥርዓት ሲገባም እንዲህ አለ በቊ.19 እንጀራውንም አንስቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸው ይህ ስለእናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ከአራት በኋላ ጽዋውን አንስቶ እንዲህ አለ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ የሚፈሰው ደሜ ለደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው በሉቃ.22÷39 ወጥቶም እንደ ልማዱ ወደ ደብረዘይት ሄደ ደቀ መዛሙርቱም ደግሞ ተከተሉት ወደ ሥፍራውም ደረሱ ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ አላቸው ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ ተንበርክኮም ጸለየ ሁለተኛ ሄዶ ጸለየ ሦስተኛ ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ ወደ ደቀመዛሙርቱ መጥቶ እነሆ ሰዓቲቱ ቀርባለች የሰውን ልጅም በኃጢያተኞች እጅ አሳልፎ ይሰጡታል ተነሡ እንሂድ እነሆ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቧል አላቸው ገናም ሲነጋገር እነሆ ሰዎች መጡ ከ12ቱ አንዱም ይሁዳ ይቀድማቸው ነበር ሊስመው ወደ ኢየሱስ ቀረበ ኢየሱስ ግን ይሁዳ ሆይ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጠዋለህን? አለ። ቦታውም

እንደ ማቴዎስ ጌቴ ሴማኒ ማቴ.26÷36-51 እንደ ሉቃስ ደብረ ዘይት ሉቃ. 22÷39-51 እንደ ዮሐንስ ቂድሮን ወንዝ ማዶ ዮሐ. 18÷1-12

ጌታችን አልፎ ለአይሁድ በተሰጠ ጊዜ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ፈተናዎች ሲታዩ አንዳንዶቹም እንደፀኑ እናያለን

1. ይሁዳ ጌታችንን አሳልፎ በመስጠቱ እንደተጐዳ እንመልከት ማቴ.27÷3-10 ተረ.ኤር.7÷2
2. 38 ዓመት ታሞ የዳነ መፃጉዕ በጥፊ ጌታን እንደመታ ዮሐ.18÷22
3. ሐና እንደታሰረ ወደ ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ሰደደው ዮሐ.18÷28
4. ኢየሱስንም ከቀያፋ ወደ ገዢው ወደ ጲላጦስ ወሰዱት ሉቃ.23÷1 በቁጥር 4 ጲላጦስም ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ በዚህ ሰው አንድስ በደል እንኳን አላገኘሁበትም አለ እነሱ ግን ከገሊላ ጀምሮ እስከ ይሁዳ ሕዝቡን ያውካል አሉ። ጲላጦስም ገሊላ ሲሉ የገሊላ ሰው ነውን ብሎ ጠየቀ ከሄሮድስ ግዛት እንደሆነ ባወቀ ጊዜ ወደ ሂሮድስ ሰደደው
5. ሄሮድስም ኢየሱስን ባየው ጊዜ ደስ አለው ከሠራዊቱ ጋርም ዘበተበት የጌጥ ልብስ አልብሶም ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደደው ሄሮድስና ጲላጦስ በዚያን ቀን እርስ በእርሳቸው ወዳጆች ሆኑ ቀድሞ በመካከላቸው ጥል ነበርና። ሉቃ.23÷11 እዚህ ላይ እንደምናየው የጌታን ፍርድ 1. ቀያፋ 2. ጲላጦስ 3. ሄሮድስ ሆነው በተራ እንዳዩ ነው። ከዚህም የተነሳ ነው ጲላጦስ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ ባኖረ ጊዜ በዮሐ.19÷19-20 ላይ ከአይሁድ ብዙዎች ይህንን ጽሕፈት አነበቡት በእብራይስጥ እና በሮማይስጥ በግሪክም ቋንቋ ተጽፎ ነበር ብሎ በሦስት ቋንቋ መፃፉን ተናግሯል። እብራይስጥ የሄሮድስ ሮማይስጥ የጲላጦስ ጽር የቀያፋ ስለሆነ ነው። «ጲላጦስ የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን» ቢለው ኢየሱስ መልሶ «ከዚህ ዓለም አይደለችም መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ብትሆን ኖሮ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ

ሉሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር።» ዮሐ.18÷33 -40 ዳግመኛም ጲላጦስ «ለአይሁድ አንዲት በደል አላገኘሁበትም ነገር ግን በፋሲካ አንድ አስረኛ ልፈታላችሁ ልማድ አላችሁ ኢየሱስን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን» አላቸው ሁሉም በአንድነት «ኢየሱስን አይደለም በርባንን ፍታልን እንጂ እያሉ ጮኹ» ስለ ሁከትና ሰውን ስለመግደል በወህኒ ታስሮ የነበረውን በርባንን ፈታላቸው። ኢየሱስን ግን ሰፈቃዳቸው አሳልፎ ሰጠው ዮሐ.18÷38-40 ሉቃ.23÷18-25

6. ሌሎችንም ሁለት ክፉ አድራጊዎች ደግሞ ከእርሱ ጋር ይገደሉ ዘንድ ወሰዱ ኢሳ.53÷12 ሉቃ.23÷32 በቁጥር 39 ከተሰቀሉት አንዱ አንተ ክርስቶስ አይደለህምን ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው ሁለተኛውም አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን አትፈራምን ብሎ ገሰጸው። ጌታችን ሲሰቀል የተጠቀሙት

1. ጴጥሮስ ንስሀ በመግባት ሉቃ.22÷55-62
2. ስምዖን ቀሬናዊው መስቀል በመሸከም ማር.15÷21
3. ፈያታዊ ዘየማን (ጥጦስ) አቤቱ ስትመጣ በመንግሥትህ አስበኝ በማለት ሉቃ.23÷39-43
4. ዮሐንስ እስከመስቀል በመከተሉ ዮሐ.19÷26፣28÷29

በመስቀል እያለ የተናገረው ቃል ሉቃ.23÷34፣43፣46ማቴ.27÷46 ዮሐ.19÷26-27፣28፣30

ጌታ በተሰቀለ ዕለት የተፈጸሙ ተዓምራቶች ማቴ.27÷45

1. ከ6-9 ሰዓት ምድር ጨለመች
2. የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ
3. ምድር ተናወጠች
4. አለቶች ተሰነጣጠቁ
5. መቃብሮች ተከፈቱ

ስለታምራቱ :- በሰማይ ሦስት በምድር አራት እንደሆነ ይነገራል አሁን ከወንጌል አግኝተን የመዘገብናቸው ግን አምስት ናቸው ሁለቱ በፀሐይ

መጨለም ተሸፍኖ እንደሆነ እንጂ ጨረቃ ደም እንደሆነ ከዋክብት እንደረገፉ በየቦታው ይነገራል ኢሳ.12÷10 ኢዩ.2÷30 ከጭፍሮቹም አንዱ እንደሞተ አይቶ ቀኝ ጐኑን ወጋው ያን ጊዜ ጥሩ ውኃ ፈሰሰ ዩሐ.19÷33 ዘካ.12÷10 ራዕ.1÷7 ከዚህ በኋላ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ሥጋውን ገንዘው በአዲስ መቃብር ቀበሩት ማቴ. 27÷57-61 ዮሐ.19÷38-42

ምዕራፍ 28 ቁጥር 42

ታኅሣሥ 28 ቀን አማኑኤል

ጌና (ጽር) የልደት ዋዜማ ገሀድ ወይም ልደት እንተ በኵሉ ክብርት ጌና ዘይእቱ ልደት በሥጋ ተረፈ ቁር 25 ስንክ ታኅሣሥ 28 በዓሉ በምስራቃውያን ታኅሣሥ 29 በምዕራባውያን ታኅሣሥ 15 በአርመን ቤተ ክርስቲያን ጥር 12 ቀን ይከበራል በዓሉ በቁስጠንጢኖስ ጊዜ በ325 ዓ.ም እንደተከበረ በዓለም ታሪክ እናነባለን::

አማኑኤል (ዕር) ሂማኑኤል (ዕብ.) አማኑኤል የሥግው ቃል ስም በኩነት በተዋህዶ የተሰጠው አማኑ ምስሌነ ኤል አምላክ በተገናኘ አምላክ ምስሌነ ወይም ምስሌነ አምላክ አምላክ ከኛ ጋር (ማቴ.1÷23 ኢሳ.7÷14፤8÷8) ሊቃውንት ግን አምላክ ወሰብዕ ብለው የምሥጢር አፈታት ይፈቱታል አማኑኤል ዘበትርጓሜሁ አምላክ ወሰብዕ እስመ ውዕቱ አምላክ በመለኮቱ ወሰብዕ በትስብእቱ ዘነሰአ ወዝ ስም ዘውእቱ አማኑኤል ዐቢይ ጥቀ ወኢይደሉ ፈሊጡቱ ወውእቱ ዘበአማን ምስጢር ለጽንዓ ሃይማኖት (ሃይ. አበ. ቴዎዶ. ዘአ. ሳዊ. ዘአን)

ለጌታችን ሁለት ልደት አሉት ቀዳማዊ ልደቱ ወልድየ አንተ ወእነ ዮም ወለድኩከ መዝ.2÷7 ከዚያ ወረድ ብሎ ቁ.6 ላይ አንሰ ተሰየምኩ ንጉሠ በላዕሌሆሙ በጽዮን በደብረ መቅደሱ ሲል ደኃራዊ ልደቱ ነው በኢሳ.45÷10 ላይ አባትን ምን ወልደሃል ሴትንም ምን አምጠሻል ለሚሉ ወዮላቸው ይላል ማለት አብ ወልድን የወለደበት ሰዓትና ጊዜ ለሚመራመሩ ሰዎች የተነገረ ነው:: ሴትንም ምን አምጠሻል ለሚሉ ወዮላቸው ማለት ድንግል

ማርያም እንደሌሎች ሴቶች ምጥና ጋር አግኝቷታል አያሉ ለሚጠራጠሩ ሰዎች የተነገረ ነው::

ስለቀዳማዊ ልደቱ ራሱ ሲመሰክር እኔ አብርሃም ሳይወለድ ነበርሁ ብሎ ቀዳማዊነቱን መስክሮአል:: ዮሐ. 8÷42፤58 ደኃራዊነቱም ዮሐ.5÷28 ሐዋርያውም ደኃራዊ ልደቱን ሲመሰክር ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም ብሏል ማቴ.1÷1 ዕብ.2÷16 ቀዳማዊ ልደቱን እግዚአብሔር ፈነወ ወልዶ ብሎ ደኃራዊ ልደቱን ወተወልደ እምብእሲት በማለት ያስረዳል ገላ.4÷4

ቁጥር 43 ነሐሴ 28 አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ

አብርሃም የመጀመሪያ ስሙ አብራም ነበር ዘፍ.11÷27 አብራም ማለት ታላቅ አባት ማለት ነው በኋላ ግን እግዚአብሔር ለብዙ አሕዛብ አባት ትሆናለህ በማለት አብርሃም ብሎ ስሙን ለወጠ (ዘፍ.17÷1-5) አባቱ ታራ እናቱ ኤድና ይባላሉ ኩፋ.10÷30 ኢያ.24÷1-4 እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ አነጋገረው

1. ለእስራኤል ሕዝብ አባቶች የመጀመሪያው ይሆን ዘንድ ከትውልድ አገሩ ከከለዳውያን ዑር አንዲወጣ በጠራው ጊዜ አነጋገረው (ዘፍ.12÷1-6)
2. ከሚስቱ ሣራና ከአጐቱ ልጅ ከሎጥ ጋር ሆኖ ከዑር ተነሥቶ ወደ ካራን ሄደ ከካራን ወጥቶ ወደ ከነዓን ምድር ሲገባ ያችን ምድር ለዘሩ እንደሚሰጥ በግልጥ አነጋገረው (ዘፍጥ.12÷5-7).
3. ለጥቂት ጊዜ በሴኬም በቤቴልና በአዜብ ወይም በደቡብ አገር ቆይቶ በረኃብ ምክንያት ወደ ግብጽ ተጉዞ ከዚያ ም ተመልሶ በኬብሮን ከቆየ በኋላ ከሎጥ በተለየ ጊዜ አነጋገረው ዘፍጥ.13
4. ወራሽ ልጅ እንደሌለው አይቶ ባዘነ ጊዜ በራዕይ አነጋገረው (ዘፍ.15፤1-21)
5. ስሙን አብርሃም ብሎ በለወጠ ጊዜ ተገልጦ አነጋግረው (ዘፍጥ.17)

በመምሬ የአድባር ዛፍ ሥር ተገልጦ ካነጋገረው በኋላ ወደ ቤቱ ገብቶ ሚስቱ ሣራ ልጅ እንደምትወልድለት ተስፋውን ነገረው:: በኋላም ስለ ሰዶምና ገሞራ ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ተወያየ (ዘፍጥ.18)

7. ልጁ ይስሐቅን እንዲሠዋ በፈተነው ጊዜ አነጋግሮታል(ዘፍ.22÷1-18)

አብርሃም እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ላይጠብቅ አጋር ከተባለች ግብጻዊት ገረዱ አስማኤልን ወለደ (ዘፍ.16)። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑንና ምልክት የሆነውን ግዝረት ከሰጠው በኋላ ግን የተስፋ ልጁ ይስሃቅ ከሚስቱ ከሣራ ተወለደለት (ዘፍጥ.17÷21፤21÷1-9) ሚስቱ ሣራ ከሞተች በኋላ ኬጡራ የተባለችውን ሴት አግብቶ 6 ልጆችን ወለደ (ዘፍጥ.25÷1-2) አብርሃም በከነዓን አገር በድንኳን ውስጥ ይኖር ነበር ባረፈበትም ሁሉ መሠዊያን ይሠራ ነበር። ዘሩ አገሩን እንደሚወርስ ተተነበየለት ተስፋው በምድራዊ ርስት ብቻ ላይሆን በሰማያዊ አገርም እንደሚፈጸም ተረዳ (ዕብ.11÷8-16) በ175 ዓመቱ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ2036 ዓ.ዓ ሞተና በኬብሮን ተቀበረ (ዘፍ.25÷9-10)አብርሃም የተጠራበት ምክንያት ከወገኑ ከክርስቶስ በሥጋ እንዲወለድ ነው የምድር ነገዶች በእንተ ይባረካሉ። የሚለው ተስፋ የተፈጸመ በክርስቶስ ነው። ስለዚህ በአ.ኪ መፃሕፍት ብዙ ጊዜ ስሙ ተጠቅሶአል። ለምሳሌ፡- 1. ለእግዚአብሔር ስለመታዘዙ (ዮሐ.8÷39-40 ዕብ.11÷17-19 ያዕ.2÷21-24)

2. እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ስለመቈጠሩ የምእመናን ሁሉ አባት ስለመባሉና በእርሱ ምሳሌ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ በእምነት ስለ መጽደቃቸው (ገላ.3÷6-7)
3. የዓለም ወገኖች ሁሉ በእምነት የአብርሃም እውነተኞች ልጆች የተስፋው ወራሾች ተብለው ስለመጠራታቸው (ሮሜ.4÷11፤ 12፤9÷7-8 ገላ.3÷7-9

የአብርሃም እቅፍ (ሉቃ.16፤22-23) በአይሁድ አስተሳሰብ በአብርሃም እቅፍ መቀመጥ ማለት በእግዚአብሔር መንግሥት ከአብርሃም ጋር በደስ መቀመጥ (መኖር) ማለት ነው። (ማቴ.8÷11)

በዚች ቀን ይስሐቅ አረፈ

ይስሐቅ የስሙ ትርጉም « ይስቃል» ማለት ነው። የአብርሃም የሣራ ልጅ የያዕቆብ አባት ሣራ በስተርጅናዋ ወለደች (ዘፍ.17÷15-21፤18

15፤21÷1-7) ከመወለዱ 25 ዓመት ቀደም ብሎ ለአብርሃም የተሰጠው የዘር ተስፋ በይስሐቅ ሊፈጸም ጀመረ (ዘፍ.12÷1-3 ማቴ.1÷2 ገላ.3÷16) ይስሐቅ ተገረዘ(ዘፍ.21÷4) በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል ስለ ተባለ አስማኤል ተሰደደ (ዘፍ.21÷8-14) አብርሃም ይስሐቅን ለመሥዋዕትነት አቀረበ (ዘፍ.22) ይስሐቅ ርብቃን አገባ (ዘፍ.24) መካን ነበረችና ከጸለየም በኋላ ዔሳውንና ያዕቆብን ወለደችለት (ዘፍ.25÷19-26) በዘመኑ ረሃብ በሆነ ጊዜ ወደ ፍልስጥኤም ተሰደደ እግዚአብሔርም ወደ ግብጽ አትውረድ አለው (ዘፍ.26÷1-2) እግዚአብሔር የአብርሃምን ተስፋ አፀናለት (ዘፍ.26÷3-5) ባረከውም (ዘፍ.26÷12-14) ልጆቹን ባረካቸው (ዘፍ.26÷30፤ 28÷5) 180 ዓመት ሲሆነው ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ1931 ዓ.ዓ ሞተ ዘፍ.35÷28 ጳውሎስ እንደ መንፈስ የተወለዱትን የእግዚአብሔር ልጆች የተስፋ ቃል ልጅ በሆነው በይስሐቅ መሰላቸው (ሮሜ.9÷6-9 ገላ.4÷21-31) የእምነት ሰው መሆኑ በዕብ.11÷9 ተጽፎአል።

በዚች ቀን ያዕቆብ አረፈ

ያዕቆብ የስሙ ትርጉም ተረከዝን ይይዛል ማለት ነው ርብቃ ለይስሐቅ ከወለደችለት መንታዎች ታናሹ የአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ሕዝብ ነገዶች አባት። ከልደቱ በፊት መመረጡ ተገለጠ የወንድሙን ተረከዝ ይዞ ተወለደ(ዘፍ.25÷19-26) ብኩርናውን ገዛ(ዘፍ.25፤27-34) አባቱን በማታለል በረከትን አገኘ (ዘፍ.27) ከዔሳው ለማምለጥ ሚስትን ለማግኘት ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ ሄደ (ዘፍ.27÷42-46 28÷1-9) የመሰላልን ሕልም አየ የአብርሃምም ተስፋ ተሰጠው (ዘፍ.28÷10-22) ሃያ ዓመት ለላባ አገልግሎ ልያንና ራሔልን አገባ ብዙ ልጆችንም ወለደ ብዙ ሀብትም አገኘ ዘፍ.29÷30 እግዚአብሔር ወደ ከነዓን እንደሚመለስ ባዘዘው ጊዜ ከላባ ቍጣ ዳነ (ዘፍ. 31 ከኢሳውም ቍጣ ዘፍ.32÷33 በጽኒኤል እግዚአብሔር ጠበቀው ዘፍ.32÷22-32 በቤቴልም ዘፍ.35÷9-15) ተገለጠለት ስሙንም እስራኤል ብሎ ሰየመው ብዙ ዓመት በከነዓን ከኖረ በኋላ (ዘፍ.33÷18-45) በረሃብ ጊዜ ወደ ግብጽ ሄደ (ዘፍ.46÷47) ትንቢት እየተናገረ የዮሴፍንም

ልጆች የራሱንም አሥራ ሁለት ልጆች ከባረከ በኋላ 147 ዓመት ሲሆነው ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በ1871 ዓ.ዓ ሞተ (ዘፍ. 47÷27-31፣48÷13-17፣49÷1-28) በአብርሃምም መቃብር ተቀበረ (ዘፍ.49÷30-33) ከእርሱ የተገኘ ሕዝበ እስራኤል አንዳንዱም ያዕቆብ ይባላል (ዘጎል.23÷10 ኢሳ.41÷8፣14÷21) ስለ መመረጡ (ሮሜ.9÷10-16) ስለ እምነቱም (ዕብ.11÷9-21)። ተጠቅሶአል። እነዚህ ሦስቱ አባቶች አርዕስተ አበው ይባላሉ በብሉይና በሐዲስ የራሱን ስም ዘርፍ በማድረግ በወዳጆቹ አጽፏል ዘፀ.3÷15 ማቴ.22÷31 የአበው ረድኤታቸውና በረከታቸው በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ምዕራፍ 29 ቍጥር 44 ታኅሣሥ 29 ቀን በዓለ ልደት

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ታኅሣሥ 29 በዚች ቀን የከበረና የተመሰገነ ታላቅ የልደት በዓል ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከከበረች ድንግል ማርያም የተወለደበት ዕለት ከበዓላት ሁሉ ተለይታ ከፍ ከፍ ያለች ናት። የቤተክርስቲያን መምህራን አባቶቻችን የከበረ የልደት በዓል በ2 ቀኖች ያከብሩ ዘንድ በምክራቸው ተስማሙ ከወደኋላ በ28 ሌሊቱ የልደት በዓል ነው። በ29 መዓልቱ ጳጉሜን 6 በሆነ ጊዜ በዚያች ዓመት የልደት በዓል በ28 ይከበራል። ጳግሜን 5 ከሆነ ግን በ29 ይሆናል። ስለዚህ የበዓላት ሁሉ ራስ የሆነ የከበረ የልደት በዓል በሁለቱ ቀኖች እንዲከበር አዘዙ (ወሰኑ) የበዓላት ራስ ስለሆነ የከበረ የልደት በዓል የከበረ ወንጌል እንዲህ አለ « በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በይሁዳ ዕፃ በቤተልሔም ጌታ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ እነሆ የፍልስፍና ሰዎች ከምሥራቅ መጥተው ወደ ኢየሩሳሌም ደረሱ ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና። የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው እያሉ መጡ። እሊህ ፈላስፎች ከበለዓም ወገን ናቸው። በመጻፋቸው በከዋክብት የሚፈላሰፉ ሲሆኑ በበለዓም መጽሐፍ የአይሁድ ንጉሥ ሊወለድ እንዳለው ተጽፏል አሉ። በለዓም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል ከእስራኤል ንጉሥ ብሎ ነበርና /ዘኁ.24÷17/ ይቅር ባይ መሐሪ አምላክ

ዓላማቸውን በሚያምኑበትም ሃሳባቸው እነርሱ ከዋክብትን በመጠባበቅ የሚፈላሰፉ ናቸውና። ይሕንንም ኮከብ ገለጠላቸው ባዩትም ጊዜ ደስ አላቸው መልኩ በብዙ ዓይነት ልውጥ ነውና። ሕፃን የታቀፈች ድንግል ብላቴናን ይመስላል። ርሱ በቀን ይጓዛል በሌሊት ይሰወራል ከሰው ሲገናኙ ይሰወርና ሲቆሙ በሌላ አንጻር ይገለጽላቸዋል እነርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ሲደርሱ ያ ኮከብ ተሰወራቸው እጅግ አዘኑ የሚያደርጉትንም አላወቁም ከዚያ በኋላ ከኢየሩሳሌም ገብተው ስለ ተወለደው ንጉሥ ጠየቁ የእሊህም ሰዎች ቍጥራቸው ሠላሳ ሺህ ነው ነገሥታቱ ሦስት ናቸው ለእያንዳንዱ ንጉሥ አሥር አሥር ሠራዊት አለው። ንጉሡ ሄሮድስም በሰማ ጊዜ ደነገጠ። ኢየሩሳሌምም በመላዋ ከእርሱ ጋር ደነገጠች የካህናት አለቆችና የሕዝቡን ጸሐፊዎች ሰብስቦ ክርስቶስ በየት ይወለዳል ብሎ ጠየቃቸው በይሁዳ ዕፃ በቤተልሔም አንቺ ከይሁዳ ነገሥታት አታንሽም ወገኖቼን እስራኤልን የሚጠብቅ ንጉሥ ከአንቺ ይወለዳልና ተብሏል አሉት። ሚል.5÷2 ከዚያ በኋላ ሄሮድስ ሰባ ሰገልን በጭልታ ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከእነርሱ ተረዳ ። ሄዳችሁ የዚያን ሕፃን ነገር መርምራችሁ ንገሩኝ እኔም መጥቼ አሰግድለት ዘንድ በኔ በኩል ተመልሳችሁ አስረዱኝ ብሎ ወደ ቤተልሔም ሰደዳቸው። የነገራቸውን ሰምተው ከንጉሡ ሄዱ። እነሆ ከምሥራቅ ያዩት ኮከብ ወደ ቤተልሄም እስከሚደርሱ ይመራቸው ነበር። ሕፃኑ ካለበት ዋሻ ሄዶ ቆመ። ኮከቡን ባዩት ጊዜም እጅግ ደስ አላቸው ወደቤትም በገቡ ጊዜ ሕፃኑን ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር አገኙት ወድቀውም ሰገዱለት ሳጥናቸውንም ከፍተው ወርቅ፣ ከርቤ፣ እጣን እጅ መንሻ አቀረቡለት። /ማቴ.2÷1-12/ በእግዚአብሔርም ፈቃድ ዮሴፍ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሕፃኑ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም በዚያች ዕለት ወደ ቤተልሔም መጡ። ስለዚህ ሰባ ሰገል አገኙአቸው። የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ናዝሬት በሌላ ቦታ አላደገምና ከተወለደም ሁለት ዓመት ሆኖት ነበር። አምላክ ነውና ስለ መንግሥቱ ወርቅ ገበሩለት። ክህነትም ገንዘቡ ነውና እጣን ገበሩለት። ማህየዊ ለሆነው ሞቱ ምልክትም ከርቤን ገበሩለት። ወደ

ሄሮድስም እንዳይመለሱ በህልም ነገራቸው በሌላ መንገድም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ገቡ። አምላክ በሥጋ ስለመገለጡ አዋጅ ነጋሪዎች ሰባኪዎች ሆኑ ይህቺም አለት ነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት የተናገረባት ናት። እንዲህ ብሎ « ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከኛ ጋር ማለት ነው» /ኢሳ.7÷14 ማቴ.1÷23/ ስለዚችም የከበረች ድንግል ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዲህ ብሎ ትንቢት ተናገረ « እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ ይህቺ በር ተዘግታ ትኖራለች አትከፈትም የሚገባባትም የለም የእስራኤል ፈጣሪ እግዚብሔር እንደተዘጋች ይገባባታልና ተዘግታ ትኑር አለ» /ሕዝ.44÷1-4/ ነቢዩ ዳንኤልም አለ « ሌሊት በራዕይ አየሁ የሰው ልጅ የሚመስል በሰማይ ደመና መጣ ዘመኑን ወደሚያስረጁ ደረሰ ከፊቱም አቀረቡት የዘላለም አገዛዝ ጌትነት መንግሥትም ተሰጠው ሕዝብና አሕዛብ ሁሉ መንደር መንደራው የሚኖሩት ነገዱ ነገሥታት ሁሉ ይገዙለታል አገዛዙም የዘላለም ነው። መንግሥቱም የማይጠፋ የማያልፍ ነው። /ዳን.7÷13/ ዳግመኛም ኢሳይያስ «እግዚአብሔር እንደ እኔ የሥጋ መጋረጃ በመጋረድ ተገለጠልኝ» አለ። አሁንም «አዲስ ሰማይ አዲስ ምድር እሠራ ዘንድ አለኝ »አለ። ሁለተኛም «ከእሴይ ስር በትር ትወጣለች ከእርሷም ጽጌ አበባ ይወጣል» አለ። /ኢሳ.11÷1/ «ዳግመኛም ሕፃን ተወለደልን ወንድ ልጅም ተሰጠን ይኸውም ሥልጣኑ በጫንቃው የሆነ ክርስቶስ ነው ስሙም ድንቅ መካር የዘለዓለም አባት የሠላም አለቃ ይባላል አለ» / ኢሳ.9÷6/

ኤርምያስም አለ « እግዚአብሔር እንዲህ አለ በዚያ ወራት ለዳዊት ብርሃንን አወጣለሁ በምድርም የቀና ፍርድን ያደርጋል እግዚአብሔር ያመኑበትንም ያድናቸዋል» ኤልሳም እንዲህ አለ እግዚአብሔር ከሰማይ ይወርዳል በእስራኤል ልጆች አደባባይም በመመላለስ ለሕዝቡ እውነትን ያስተምራቸዋል። ከአብርሃም ልጅነት ልዩ ከሆኑ በቀር አህዛብ ሁሉ ይታዘዙለታል»

ነቢዩም ናሆም እንዲህ አለ « እግዚአብሔር በእኔ አርአያ ይመጣል ልብሱም እንደልብሴ ነው። »

ነቢዩ ኢዩኤልም እንዲህ ተናገረ « የእግዚአብሔር ዙፋን የሆነች ብላቴና ድንግል አየሁ ርሷም እንደ እሳት ያልባት ነበር ስለሷም ይህች ማናት ብየ ኪሩብን ጠየቅሁት ከአዳም ልጆች የተመረጠች የእግዚአብሔር ዙፋን ይህች ድንግል ናት። በርሷም የተጐሳቆሉ አሕዛብ ይድናሉ ለአመነባትም ረድኤትና መጠጊያ ናት።»

ዳዊትም በመዝሙር እንዲህ አለ « እግዚአብሔር አንተ ልጄ ነህ ዛሬ በተዋሕዶ ወለድኩህ አለኝ ለምነኝ አሕዛብን ርስት አድርጌ እሰጥሃለሁ ግዛትህም በመላው ዓለም ነው » / መዝ.2÷7/ ዳግመኛም አብ አለ ቀዳማዊ ወልድ በኃይል ቀን ከአንተ ጋር ሳለሁ ከአጥቢያ ኮከብ በፊት ከሆድ ወለድኩህ እንደመልከጼዴቅ ሥርዓት አንተ የዓለሙ አገልጋይ ካህን ነህ ብሎ ማለ ከማለም አይጸጸትም» /መዝ.109÷3/ ቤዛ ይስሃቅ በግዕ ከጎቱም ዕፀ ሳቤቅ እንደተገኘ /ዘፍ.22÷13/ ለእስራኤልም ከበረሃ ውስጥ ከጎቱም አለት ውኃ እንደአፈለቀ / ዘፀ.17÷6/ የደረቀች የአሮን በትርም እንደለመለመችና እንደ አፈራች / ዘኁ.17÷8/ በሶምሶን እጅ ውስጥ ከአህያ መንጋጋ አጥንት ውኃ እንዳፈለቀ / መሳ.15÷15-20/ እንዲሁም የጌታችን ልደት በጎቱም ድንግልና ሆነ በዕፀ ጳጦስ ውስጥ አሳት እንደ ነደደች ዕፀጳጦስም እንዳልተቃጠለች እንዲሁ የመለኰቱ አሳት ድንግልን አላቃጠላትም / ዘፀ.3÷2/ ለርሱም ከቸር አባቱ ከማኅየዊ ከመንፈስ ቅዱስ ሕይወቱ ጋር ጌትነት ክብር ምሥጋና ስግደት ከርሱ ጋር በትክክልነት ይገባል። ለዘለዓለሙ አሜን።

ዘጠኙ ዐበይት በዓላትና ንዑሳን በዓላት

1. ጽንሰት ኢሳ.7÷14 ሉቃ.1÷31 5500 ዘመን በዘመነ ዮሐንስ በወርኃ መጋቢት 29 አሁድ 3:00 ሰዓት ታኅሣሥ 19 ቀን ይመ.
2. ልደት 5501 ዓ.ም በዘመነ ማቴዎስ በወርኃ ታኅሣሥ 29 ማክሰኞ 10 ሰዓት ከሌሊቱ ተወለደ። ታኅሣሥ 29 ቀን ይመ.

3. ጥምቀት በተወለደ በ30 ዓመቱ በዘመነ ሉቃስ በወርኃ ጥር ማክሰኞ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ተጠመቀ።
4. ደብረ ታቦር በተወለደ በ32 ዓመት ከሰባት ወር ከ15 ቀን በዘመነ ማቴዎስ በወርኃ ነሐሴ 13 እሁድ ቀን። ነሐ.13 ይመ.
5. ሆሳዕና በተወለደ በ33 ዓመት ከ2 ወር ከ22 ቀን እሁድ በዘመነ ማርቆስ በወርኃ መጋቢት ማቴ.21÷1 ማር.11÷1
6. ስቅለት በዚህ ዘዘመነ ማርቆስ በወርኃ መጋቢት 27 አርብ ቀን 9 ሰዓት መጋ.27 ቀን ይመ.
7. ትንሣኤ በዘመነ ማርቆስ በወርኃ መጋቢት 29 እሁድ ቀን ከሌሊቱ 10 ሰዓት ማቴ.28÷1 ማር.16÷1 ሉቃ.24÷1 ዮሐ.20÷1
8. ዕርገት በዘመነ ማርቆስ በወርኃ ግንቦት 8 ሐሙስ ቀን በ33 ዓመት ከ4 ወር ከ10 ቀን ነው። ማር.16÷19 ሉቃ.24÷50
9. ጰራቅሊጦስ በዘመነ ማርቆስ በወርኃ ግንቦት 18 በተነሣ በ50 ቀን እሁድ እለት 3 ሰዓት የሐዋ. 2÷1-15

ንዑሳን በዓላት

1. ስብከት ታኅሣሥ ከ7-13
2. ብርሃን ከታኅሣሥ 14-20
3. ኖላዊ » 21-27
4. ጌና 28 ይመ.
5. ግዝረት ጥር 6 ቀን ይመ.
6. ልደተ ስምዖን የካቲት 8 ሉቃ.2÷21-35
7. ቃና ዘገሊላ ጥር 12 የካቲት 13 ጥንቱ፡ በሊቃውንት ድንጋጌ ጥር 12 ዮሐ.2÷1-11 ፤4÷46
8. መስቀል መስከረም 17 እና መጋቢት 10 በአንድ ላይ መጋ.10 ቀን ይመ.
9. ደብረ ዘይት ማቴ.24÷1 ናቸው።

ምዕራፍ 30 ቁጥር 45 ሚያዝያ 30 የወንጌላዊ ማርቆስ ዕረፍት

በትውልዱ ዕብራዊ ሲሆን ቤተሰቦቹ ግን ይኖሩ የነበሩት በሰሜን አፍሪካ ሲሪላንካ (ቀሬና) በተባለችው በዛሬዋ ሊቢያ ምዕራባዊ ጠረፍ በተቆረቆረችው ደማቅ ከተማ ነበር ነገር ግን የሰሜን አፍሪክ ዘላን ጐሳዎች የሆኑት በርበሮች በየጊዜው በከተማዋ ጥቃት እየሠነዘሩ ሀብት ንብረታቸውን እየዘረፉ ስላስቸገሩዋቸው እናቱ ማርያምና አባቱ አርስጦቡሉስ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ኢየሩሳሌም በመመለስ ቤት ሠርተው ተቀመጡ። ቅዱስ ማርቆስ ገና በልጅነቱ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በመታደሉ በዚያን ዘመን ይሰጥ የነበረውን ትምህርት የማግኘት ዕድል ገጥሞታል። የላቲን የግሪክና የዕብራይስጥ ቋንቋዎችን አሣምሮ ያውቅ ነበር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ አውራጃዎች እየተዘዋወረ ሲያስተምር ማርቆስ ገና ሕፃን ነበረ በምሴተ ሐሙስ ለሐዋርያት ወደ ከተማ ሂዱ በማድጋ ውኃ የተሸከመ ጉበዝም ያገኛችኋልና ተከተሉት በማለት ፋሲካን ሊያዘጋጁለት የመረጠውን ቤት እንደሚያሳያቸው የጠቆማቸው ወጣት ቅዱስ ማርቆስን መሆኑን የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ይተረጉማሉ። (ማር.14÷13) በስቅለቱም ጊዜ ልብሱን ትቶ የሸሸ (ማር.14÷51-53) ይህም በዚያ ጊዜ ገና ልጅ እንደነበር ያመለክታል። የማርቆስ እናት ማርያም ባውፍልያ ትባላለች ቤቷን ለክርስቲያኖች መሰብሰቢያነት የሰጠች ደግ ሴት ነበረች። /የሐዋ.12÷12/ጌታም መጀመሪያውን የሐዲስ ኪዳን ቁርባን ለሐዋርያት ያቆረባቸው በርስዋ ቤት የላይኛው ፎቅ ላይ ነበር በዓለ ሃምሳም መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደላቸው በርስዋ ቤት ተሰባስበው ሲጸልዩ ነው በርናባስ ለቅዱስ ማርቆስ አጐቱ ነው የቅዱስ ማርቆስ አባት አርሶጦቡሉስና በርናባስ በእናት የሚገናኙ ወንድማማቾች ናቸው። ቆላ.4÷10 የእነርሱን እህት ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስ ስላገባት ቅዱስ ማርቆስ አክስቱን ለመጠየቅ ሲሄድ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ተዋወቁ 1ጴጥ.5÷13 ሐዋርያት ዓለምን ዕጣ በዕጣ ተከፋፍለው ሲወጡ

ቅዱስ ማርቆስ በበርናባስ አቅራቢነት ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በመጀመሪያው ጉዞው በ46 ዓ.ም ለስብከተ ወንጌል ወጥቶ ነበር 2ጢሞ.4÷11 ነገር ግን በጽንፍልያ ከተማ እናቴ ናፈቀችኝ ስላለ (የሐዋ.13÷13) በርናባስ ይዞት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። ከዚያ በኋላ የኖረው ከሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ነው። ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በታናሻ እስያ አድርገው እስከ ሮም ድረስ ሰብከዋል መጨረሻ በ60 ዓ.ም ወደ ሰሜን አፍሪካ መጣ በዓባይ ዴልታ በኩል አድርጉ በዘመኑ ታዋቂ የንግድ የባሕልና የፖለቲካ ማዕከል ወደ ነበረችው እስክንድርያ ደረሰ እስክንድርያ የጣዖት አምላኪዎች ከተማ ስለነበረች ቅዱስ ማርቆስ ወንጌልን እንዴት እንደሚሰብክላቸው እያሰበ በከተማዋ ውስጥ ይዘዋወር ጀመር በመጨረሻ በመዘዋወሩ ብዛት የተነሣ ያደረገው የእግሩ ጫማ ተበጠሰ ወዲያው በአጠገቡ ወደ ነበረ አንያኖስ ወደሚባል ጫማ ሰፊ አመራ አንያኖስ የቅዱስ ማርቆስን ጫማ ሲሰፋ መስፌያው እጁን ወጋው በዚህ ጊዜ ኤስታኦስ ብሎ በዮናናውያን ቋንቋ ጮኸ ትርጉሙም « አንድ አምላክ» ማለት ነው። ያን ጊዜ ቅዱስ ማርቆስ ጠጋ ብሎ ለመሆኑ አሁን የጠራኸውን አምላክ ታውቀዋለህን? በማለት ጠየቀው አንያኖስም ሲሉ እሰማለሁ እንጂ አላውቀውም ሲል መለሰለት ቅዱስ ማርቆስንም ይዞ ወደ ቤቱ በመውሰድ ቤተሰቡን ያስተምር ዘንድ ጋበዘው። የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያንም በግብጽ ውስጥ በአንያኖስ ቤት ተመሠረተች። ቅዱስ ማርቆስ በእስክንድርያ ከአስተማረ በኋላ ወደ ትውልድ ሀገሩ ሲሪናይካ (ቀሬና) በመሄድ ወንጌልን በመስበክ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አንጾአል። በ68 ዓ.ም የትንሣኤን በዓል ለማክበር ቅዱስ ማርቆስን የእስክንድርያ ክርስቲያኖች ስለጠሩት በቅድስት ባውክልያ ቤተክርስቲያን ውስጥ በቅዳሴ ላይ እያለ ግብፃውያን መምለክያነ ጣዖት ተነሱበት ያ ዓመት የግብጽ ክርስቲያኖች የትንሣኤ ዕለት ከታወቀው የግብጻውያን ጣዖት ሠራፒየም በዓል ጋር ገጠመ በዚህ የተነሣ የጣዖቱን በዓል ለማክበር የተሰበሰቡት መምለክያነ ጣዖት ቤተክርስቲያኑን ሰብረው በመግባት ቅዱስ ማርቆስን ያዙት ከሠረገላ ጋር በማሠር ቀኑን ሙሉ መንገድ ለመንገድ ሲጐትቱት ከዋሉ በኋላ ሚያዝያ 30 ቀን በዚያው ዕለት

ዐረፈ። ሥጋውንም ለማቃጠል እንጨት ሰብስበው እሳት ሊያያይዙ ሲሉ ኃይለኛ ዝናብ ዶፉን አወረደው በዚህም ጊዜ አረማውያኑ ዝናቡን ሸሽተው ወደየቤታቸው ተበተኑ የእስክንድርያ ምእመናንም ሥጋውን ደብቀው በመውሰድ በቅድስት ባውልክያ ቤተክርስቲያን ዐሳረፉት በ820 ዓ.ም እ.ኤ.አ የቬነስ ነጋድያን ዐጽሙን ሰርቀው በመውሰድ በከተማቸው በሳንማርኮ ቤተክርስቲያን አስቀመጡት።

ከወንጌላዊያንም መካከል የመጀመሪያውን ወንጌል የጻፈው ቅዱስ ማርቆስ ነው ከጥንት ዘመን ጀምሮ የቤተክርስቲያን አበው ቅዱስ ማርቆስ የጻፈው የቅዱስ ጴጥሮስን ወንጌል መሆኑን ተናግረዋል በ140 ዓ.ም የነበረው ከሐዋርያን አበው አንዱ ፖፒያስ እንደገለጠው ቅዱስ ማርቆስ የቅዱስ ጴጥሮስን ቃል በመቀበል ወንጌሉን ጽፏል። የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ከወንጌሉ ሁሉ አጭሩ ወንጌል ነው። 16 ምዕራፎችንና 661 ቁጥሮችን ይዟል ከትረካ ይልቅ ድርጊቶችን አከታትሎ ያስቀምጣቸዋል። የሐዋርያው ረድኤትና በረከት በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ቁጥር 46 ሰኔ 30 ቀን የመጥምቁ መለኮት ዮሐንስ ልደት

ሉቃ.1÷62

መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ከአዲስ ኪዳን አበው አንዱ ነው። ዮሐንስ ከመወለዱ በፊት የሥራው ዓይነት የትምህርቱ ስልት የኑሮው ሂደት ምን እንደሚመስል ፈጣሪው በንጹሐን ነብያት ትንቢት አናግሯል ኢሳ.40፣1 ሚልክ.3÷1-3 በኋላም በመላኩ ቅዱስ ገበርኤልና በአባቱ ትንቢት ስለ ሥራው አናግሮለታል ሉቃ.1÷10-20 ቁ. 76 -80 ስለዚህ ዮሐንስ ብቸኛ በአለ አምስት ማእረግ ያለው ሰው ነው ማእረጐችም ብሕትውና፣ የማይበላ የማይጠጣ ማቴ.11÷18 ፣3÷4 ሐዋርያነት ሉቃ.3÷15-17፣ ነቢይነት ማቴ.11÷11 ፈጣሪውን ያጠመቀ ካህን ማቴ.3÷13-17 ሰማዕትነት ማቴ.14÷8-13 ማር.6÷14 ዮሐንስ በምሳሌ ኤልያስ ተብሎአል ሚል.4÷5 ፍጻሜው ማቴ.17÷10 እንደ ኤልያስ ንጉሥንና ንግሥትን የገሠጸ 1ኛ ነገ.

22÷38 2ኛ ነገ. 9÷30 ማቴ.14÷4 ከመላኩ ገብርኤል ጋር ይመሰላል መላኩ ለጽንሰቱ ለልደቱ ከእግዚአብሔር ተላከ ሉቃ.1÷26 ዮሐንስም ለጥምቀቱ ለትምህርቱ ከእግዚአብሔር ኑላከ ዮሐ.1÷6 ሐዋርያት ግን ከክርስቶስ ጋር መሰሉት ማቴ.16÷13 የእግዚአብሔርም ቃል ከመጣለት በኋላ በዮረዳኖስ ወንዝ አቅራቢያ ሰበከ ሉቃ.3÷2 ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ስለአገባ ዮሐንስ ወቀሰው ሉቃ.3÷18 ጭፍሮችንም ደመወዛችሁ ይብቃችሁ እንዳለ ቁ.14 ኢየሱስ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻ ነቢይ መሆኑን መሰከረለት ሉቃ.7÷18-35፤16÷16 መስከረም 1 ቃል ኪዳን የተቀበለበት 2 የተቆረጠበት ጥር 11 ጌታችን ያጠመቀበት ነው። እድሜው በሕይወተ ሥጋ 32 ራሱ 15 ያስተማረችበት በአጠቃላይ 47 ዓመት ሲሆነው ሚያዝያ 15 ቀን አርፏል። የካቲት 30 የተቀበረበት ሰኔ 3 ፍልሰተ አጽሙ ስንክ. ይመ. የመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ረድኤትና በረከት በኛ ላይ ይደር። አሜን።

ምእራፍ 31

የ12ቱ ሐዋርያት ታሪክ

ኢየሱስ የመረጣቸው አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጴጥሮስ፣ (ስምዖን) (ኬፋ) ወንድሙ እንድርያስ፣ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ፣ ፊልጶስ፣በርተሎሜዎስ (ቶማስ) (ዲዲሞስ) ቀራጩ ማቴዎስ፣ (ሌዊ) የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ታዴዎስ የተባለው ልብድዮስ፣ቀናተኛ (ቀነናዊ) ስሞን (ናትናኤል) የአስቆሮቱ ይሁዳ ናቸው። ማቴ.10÷1-4 ማር.3÷13-19 ሉቃ. 6÷12-16 የሐዋ.1÷12-14 ማትያስ በአስቆሮቱ ይሁዳ ፈንታ ተተክቶአል። የሐዋ.1÷15-26 አሥራ ሁለቱ ነገዶች በእስራኤል እንደነበሩ፣ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትን በመንግሥቱ ሾመ ማቴ.19÷2 ምሳሌዎቻቸው ናቸውና ዮሐንስም በራእዩ ከምዕራፍ 21÷12-15 ምሳሌው በኢየሩሳሌም ሰማያዊት እንደተጻፈ ተመልክቶአል የአሥራ ሁለቱ የያዕቆ ልጆችም ምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘፍ.35÷23-27፤49÷1-29 ይመልከቱ፤

ያዕቆብ ከከነአን ወደ ሶርያ ወርዶ ከአራቱ ሴቶች እንደወለደ ኢየሱስም ከሰማይ ወደ ዓለም ወርዶ አራት ክፍል ሆና በተመደበችው በትምህርተ ወንጌል ወልዶአቸዋልና በብሉይ ኪዳን በአሥራ ሁለቱ እንደተመሰገነ በሐዲስ ኪዳን በአሥራ ሁለቱ ይመሰገናል። ድምር 24 በሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በሰማይ እንደተመሰገነ በምድርም በሃያ አራቱ ይመሰገናልና። ራዕ. 11÷16 ፣19÷4

2ኛ ምሳሌ ሙሴ የላካቸው 12ቱ የከነዓን ሰላዮች

እነዚህ ሰላዮች ምድረ ከነዓንን ሰልለው ሲመጡ ስለ አገሯም ለምነት ለመረጃ የወይን ፍሬ ተሸክመው ተመልሰዋል። ይህም ምሳሌ አለው የወይን ሐረግ የወላዲተ አምላክ የወይኑ ፍሬ የክርስቶስ ወይኑን ተሸክመው ያመጡት ከፊት ያሉት የነቢያት ከኋላ ያሉት የሐዋርያት ከፊት ያለ ቢሸከም እንጂ ወደ ኋላ መመልከት እንዳይችል ነቢያትም ስለ አምላካቸው ክርስቶስ ሰው እንደሚሆን ትንቢት ተናግረው ሰው ሲሆን በዓይናቸው ሳያዩት ሞት ቀድሞአቸው ከዘመነ ሥጋዌ ሳይደርሱ አርፈዋል። ማቴ.13÷16 ከኋላ ያለ ወደፊት ማንኛውንም ነገር መመልከት እንዲችል ሐዋርያትም ፈጣሪያቸውን ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ሲመላለስ አይተው ከቃሉ ተምረው አምላክ ሰው ሆነ እያሉ አስተምረዋል። ጽፈውማል። ዘኁ.13÷1-33 ማቴ.13÷16 ነቢያትን በክረምት በዘር ሐዋርያትን በበጋ በመከር መስሏቸዋል። በክረምት በዘር ያለውን ሥቃይ በጋ በመከር ያለውን ሲሳይ ልብ ይሏል። ዮሐ.4÷34-39 በ12ቱ አዕናቁም ይመሰላሉ። ራዕ.21÷19-22 ትርጓሜውን ይመልከቱ በ12 ሰዓተ መዓልት ብራናተ ዓለሙ ይባላሉ። ማቴ.5÷14 ሐዋርያትም የተመረጡበት ምሠረቱ 12 ሆነው እንደሚመረጡ ትንቢት ተነግሮ ነበር። ተረ.ኤር.11÷52 ጌታችንና መድኃኒታችን ጥር 11 ማክሰኞ ተጠምቆ ወዲያውኑ ወደ ምድረ በዳ ሄደ ከዚያም 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሞ ዲያብሎስን ድል ነሥቶ የካቲት 20 ቅዳሜ ቀን ወደ ቤተ ራባ ተመልሶ የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ስለመሆኑ የዮሐንስን ምስክርነት አሑድ 21 ቀን ተቀበለ። ዮሐ.1÷29 የመጀመሪያዎቹንም ደቀ

መዛሙርት አስከተለ። እነርሱም ዮሐንስና እንድርያስ ነበሩ። ዮሐ.1÷35-40 በ22 ሰኞ እንድርያስ፣ ጴጥሮስን፣ ፊልጶስ፣ ናትናኤልን ወደ ኢየሱስ አመጡ ዮሐ.1÷41-52 የኢየሱስም የመጀመሪያ ደቀመዛሙርቶች እሊህ ናቸው ከተመረጡት አንዱ ዮሐንስ ስለነበረ ትክክለኛውን ጽፏል። ሌሎች ግን ሥራቸው ዓሣ ማጥመድ እንደነበረ ይገልጻል። ማቴ.4÷18 ማር.1÷16-20

የ12ቱ ሐዋርያት ታሪክ በከፊል

1ኛ ሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስ

ጴጥሮስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ በመጀመሪያ ስምዖን ተባለ ጌኋላ ግን ኢየሱስ ኬፋ ብሎ ሰየመው። በአራማይክ ኬፋ በግሪክም ጴጥሮስ ማለት ዐለት ማለት ነው በዐረብ ኢለሀየር ይባላል። ማር.3÷16 ዮሐ. 1÷43 የትውልድ ቦታው ቤተ ሰይዳ ነበር ብዙ ትምህርት አልተማረም ማር.14÷70 ዮሐ.1÷45 ከወንድሙ ከአንድርያስ ጋር አሣ እየአጠመደ በቅፍርናሆም ኖረ አንድርያስም በመጀመሪያ ከኢየሱስ ጋር አስተዋወቀው ዮሐ.1÷41-43 በኋላም ኢየሱስ ሰዎችን እንዲያጠምድ (እንዲያሳምን) ጠራው ማር.1÷16 ሉቃ.5÷1-11 ደቀመ መዝሙር ሳለ ለሐዋርያነት ተጠራ ማር.3÷13-16 ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር እንደተገናኘ ኢየሱስ የኢያኢሮስን ልጅ ሲያስነሣ ማር.5÷35-43 በተራራ ክብሩን ሲገልጥ ማር.9÷2-8 በጌቴ ሴማኒ ሲጸልይ ማር.14÷32 ጴጥሮስ የተጠየቀውን ለመመለስ ፈጣን ነበር ማቴ.16÷13-19 ዮሐ.6÷66 ጠይቆም ይረዳ ነበር ማቴ.19÷28 ኢየሱስን ለመያዝ የመጡትን ሰዎች በሰይፍ ለመከላከል ሞከረ ዮሐ.18÷10 በኋላም ሦስት ጊዜ ኢየሱስን ካደ ተጸጽቶም በማልቀሱ ኢየሱስ ይቅር አለው ማር.14÷66-72 ሉቃ.5÷8 በትንሣኤ ዕለት ጴጥሮስ ወደ ጌታ መቃብር ሮጠ ዮሐ.20÷3-7 በኋላ ኢየሱስ ታየው ሉቃ.24÷34 ኢየሱስ በገሊላ ባሕር ዳር « ትወደኛለህን» እያለ ሦስት ጊዜ ጠየቀው «በጕቼን አሰማራ» ካለውም በኋላ እንዴት እንደሚሞት ነገረው ዮሐ.21÷1-23 ራሱ ጴጥሮስም ዕለተ ሞቱ እንደቀረበ አወቆ ጽፏል 2ጴጥ.1÷12-15 ከዕርገት በኋላ የክርስቶስ ተከታዮች መሪ ነበር የሐዋ.1÷15

22 በበዓለ ሃምሳ ሰበከ የሐዋ.2÷14-42 ከዮሐንስ ጋር ድውይ ፈወሰ ዮሐ.3÷1 የሐዋ.9÷32 በቃሉ ሐናንያና ሰጲራ ሞቱ የሐዋ.5÷1-11 ወደ ሰማርያ ሄዶ ሰበከ የሐዋ.8÷14-25 ራዕይ አይቶ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሄደ የሐዋ.10 በሄሮድስ ታሰረ በምእመናን ጸሎት በእግዚአብሔር መልአክ ተፈታ የሐዋ. 12÷1-17 ከሌሎች ሐዋርያት ይልቅ ልዩ ሥልጣን እንደተሰጠው ማቴ.16÷18 በአባቱ የሮቤል በእናቱ የስምዖን ነገድ ነው። በ67 ዓ.ም በቄሳር ኔሮን ቍልቍል ተሰቅሎ ሐምሌ 5 ቀን አርፏል። ጴጥሮስ ሁለት መልእክታትን ጽፎልናል 1ኛው መልእክት 5 ምዕራፍ ያለው ሲሆን በ63 ዓ.ም 2ኛው መልእክት 3 ምዕራፍ ያለው በ64 ዓ.ም የተጻፉ ናቸው።

2ኛ ዮሐንስ

ዮሐንስ ማለት እግዚአብሔር ጸጋ ነው ማለት ነው የያዕቆብ ወንድም የዘብዴዎስ ልጅ ማቴ.4÷21 ማር.16÷1 ዮሐንስና ወንድሙ ኃይለኞች ስለነበሩ ኢየሱስ ቦኣኔርጌስ ብሎ ሰየማቸው ማር.3÷17 ከጴጥሮስ ጋር የፋሲካ እራት አዘጋጀ ሉቃ.22÷8

- ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር የሐዋ.3÷1 ድውይ ሲፈውሱ የሐዋ.4÷13 ወደ ሰማርያም ወርደው እንዳስተማሩ 8÷14 ከጴጥሮስና ከያዕቆብ ጋር በቤተ ክርስቲያን ይሠራ ነበር ገላ.2÷9 እስከ ሕይወቱ መጨረሻ በፍጥሞ ደሴት ኖረ ራዕይ 1÷9 ቅዱስ ዮሐንስ ለማስተማር ጉዞ ያደረገባቸው ሃገሮች የሚከተሉት ናቸው 1. ሠማርያ 2. ፍልስጥኤም 3. ትንሿ እስያ / ቱርክ/ 4. ኤፌሶንና አወራጃዎቹን አስተምሮአል። የዮሐንስ ወንጌል 4ኛ ሲሆን በምዕራፎቹና በቁጥሮቹ ብዛት የሦስተኛነትን ደረጃ ይዞአል 21 ምዕራፎች ሲኖሩት 866 ቁጥሮችንም ይዟል። በተጨማሪም 3 መልዕክታት፣ 1ራዕይ፣ 1 ቅዳሴ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ለቤተክርስቲያን አበርክቶአል ነገዱም

በአባቱ ይሁዳ በእናቱ ሌዊ ነው። ነቢይም ነው ራዕይ 1÷3 ፣22÷6-10 የቀረውን ታሪክ ጥር 4 ይመልከቱ።

3ኛ እንድርያስ

እንድርያስ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ማቴ.10÷2 መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ አመለከተውና ከኢየሱስ ጋር ዋለ ጴጥሮስንም ወደ ኢየሱስ አመጣው ዮሐ.1÷35-43 ብላቴናውንና ግሪኮችን ወደ ኢየሱስ አቀረበ ዮሐ.6÷8፣12÷21 ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስ ከጠየቁት ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር ማር.13÷3 ከዕርገት በኋላ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ የሐዋ.1÷13። እንድርያስ የቍስጥንጥንያ የመጀመሪያ ሊቀ ጳጳስ ነበር በዚህ ዓለምም በቢታንያ ፣ በገላትያና በሩማንያ አስተምሯል በመጨረሻ ግሪክ ውስጥ ሲያስተምር በአካያይ አውራጃ ጳጥርሳ በተባለች ቦታ በ60 ዓ.ም ታህሣሥ 4 ቀን በሰማዕትነት አርፏል። የሀገሩም ሠዎች በጌታ አይነት መስቀል ሊሰቅሉት ሲሉ « ጌታዬ በተሰቀለበት አይነት መስቀል አትስቀሉኝ» ብሎ በእንግሊዝኛ ፊደል ኤክስን (X) የመሰለ ቅርጽ ባለው መስቀል ተሰቅሎ ሞተ። ስንክ ታኅሣሥ 4 በተጨማሪ ሐምሌ 30፣ ነሐሴ 30 ይመ. ነገዱ ከነገደ ስምዖን ነው።

4ኛ ያዕቆብ

ያዕቆብ የስሙ ትርጉም ተረከዝን ይይዛል ማለት ነው የዘብዴዎስ ልጅ የዮሐንስ ታላቅ ወንድም ማቴ.4÷21፣10÷2 ኃይለኛና ቍጡ ከመሆኑ የተነሳ ቦአኔርጌስ ተብሎ ተሰይሞአል። ማር.3÷17 ይህም ጠባዩ እሳት ከሰማይ ወርዶ ሰዎችን እንዲያጠፋቸው በጠየቀው ጊዜ ተገልጦአል። ሉቃ.9÷52-56 በሐዋርያት መካከል ከፍተኛ ማዕረግን ፈልጉ ነበር ማር.10÷35 ጌታ የኢያኢሮስን ልጅ ሴያስነሳ በተራራ ላይ ክብሩን ሲገልጥ በጌቴሴማኒም ሲጸልይ ያዕቆብ ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር አብሮ ነበር ማር.5÷35-43፣9÷2-8 በመጨረሻ ሄሮድስ በሰይፍ አስገድሎው የሐዋ.12÷2 ያዕቆብና ዮሐንስ ለሐዋርያት መጀመሪያና መጨረሻ ናቸው። ያዕቆብ የሁሉ መጀመሪያ ሰማዕት ሲሆን ዮሐንስ ደግሞ ሳይሞት ያረገ የሁሉ የመጨረሻ

ነው። ያዕቆብ ሚያዝያ 17 አርፏል። ያዕቆብ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ሲሆን ነገዱም ከነገደ ሌዊ ነው።

5ኛ ፊልጶስ

ፊልጶስ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ማቴ.10÷3 ሀገሩ ከቤተ ሳይዳ ነበር ኢየሱስ አገኘው በኋላ ናትናኤልን ወደ ኢየሱስ አመጣው። ዮሐ.1÷42-47 የኢየሱስን ኃይል ባለማስተዋሉ በተጠየቀ ጊዜ በቂ መልስ አልሰጠም ዮሐ.6÷5 ከእንድርያስ ጋር ግሪኮችን ወደ ኢየሱስ አቀረበ። ዮሐ.12÷20-22 አብን እንዲያሳያቸው ኢየሱስን ጠየቀ ። ዮሐ.14÷8-11 በኋላ ከሌሎቹ ሐዋርያት ጋር የትንሣኤው ምሥክር ሆነ የሐዋ.1÷13፣2÷14። በመጨረሻ ጎዳር 18 በመስቀል ተሰቅሎ አርፏል። ነገዱ ከነገደ ዛብሎን ነው።

6ኛ በርተሎሜዎስ

በርተሎሜዎስ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ማቴ.10÷3 በርተሎሜዎስ ማለት የተሎሜዎስ ልጅ ማለት ነው። በርተሎሜዎስ ከእርገት በኋላ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ የሐዋ.1÷13 በገድለ ሐዋርያት እንደ ምናየው እጣ የደረሠው አልዋህ የተባለ አገር ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ በርተሎሜዎስን ለማድረስ ወደ አልዋህ አብረው ተጓዙ ጴጥሮስ በርተሎሜዎስን ባሪያ አድርጉ በ30 አስታቲር ሸጡት ተመልሳል። በርተሎሜዎስም የወይን ጠባቂ ሆኖ ተሾመ ለ40 ቀናት ያህል ወይን እየጠበቀ እየተከለ በሥራ ተጠምዶ ኖረ አንድ ቀን ባለ ፀጋው የወይን ቦታ ሊያይ ሲመጣ አባብ ነድፎት ሞተ በርተሎሜዎስም ጸልዮ ያንን ባለፀጋ ከሞት አሥነሣው። በዚህም ተአምር የተነሳ ሕዝቡ አምነው ተጠመቁ። በመጨረሻም በንጉሥ አግሪጳ ተከሶ ተርቧል የሞት ፍርድም ተፈርዶበት መስከረም 1 ቀን በአሸዋ የተሞላ ከረጢት ውስጥ ከተውት ከነሕይወቱ በባሕር ውስጥ ወረወሩት። በዚያም አረፈ በበነጋውም ምእመናኑ ከባሕር አውጥተው ቀበሩት። ስንክ መስከረም 1 እና ጎዳር 19 ይመልከቱ ነገዱ ከነገደ ንፍታሌም ነው።

7ኛ ቶማስ

ቶማስ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ማቴ.10÷3 ቶማስ ሐይ ሄኖ 26÷1 በአራማይክ ዲዲሞስ በግሪክ መንታ ማለት ነው ዮሐ.20÷24 ክርስቶስን ሲከተል ተስፋ መቁረጥን የሚያስከትል ድፍረት ዮሐ.11÷8-16 አለማስተዋል ዮሐ.14÷5 ከትንሣኤ በኋላ ግን የክርስቶስን ጐን በመዳሰስ ከተረዳ በኋላ ጌታዬ አምላኬ ብሎ ወደ ሙሉ እምነት ደርሶአል:: ዮሐ.20÷26 በቤተክርስቲያን ታሪክ በፋርስና በሕንድ ወንጌልን እንዳስተማረ ይነገራል ታሪኩን ግንቦት 26 ይመልከቱ ነገዱ ከነገደ አሴር ነው::

8ኛ ማቴዎስ

ማቴዎስ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ማቴ.10÷3 ማቴዎስ የእልፍዮስ (ዲቁ) ልጅ ሲሆን ሌዊ ይባላል በቀራጭነት ሥራ ላይ ሳለ ኢየሱስ ጠራው ኢየሱስንም ተከትሎ በቤቱ ግብዣ አደረገለት ማቴ.9÷9 ማር.2÷1 ሉቃ.5÷27 ሐዋርያው ማቴዎስ ያስተማረበት ሀገር በፍልስጥኤም፣ በፋርስ በባቢሎን፣ በኢትዮጵያ እና በአረቢያ እንደሰበከ ይነገራል:: ማቴዎስ ከሌሎ ወንጌላዉያን ተለይቶ የሰባ ሠገልን ታሪክ ጽፏል እነዚህን በማስተማሩ ነ የተርሴስና፣ የደሰያት፣ የአረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀርባ መዝ.71÷10 ማቴ.2÷1-12:: ተርሴስ ደስያት/ፋርስና ባቢሎን/ /አረብና ሳ የመንና ኢትዮጵያ/ ናቸው:: የማቴዎስ ወንጌል የምዕራፍ ብዛት 2 የቁጥሮቹ ደግሞ 1068 ቁጥሮችን አካቷል:: ወንጌሉ የተፃፈው ለአይሁ በመሆኑ ከ150 በላይ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች አቅርቧል የተጻፈበት ቋን በሦስት ዓይነት ሀሳብ ቀርቧል በእብራይስጥ፣ በአረማይክ፣ በግሪክ ነው ጥቅምት 12 ቀን አንገቱን ተሠይፎ አርፏል:: ነገዱ ከነገደ ይሳኮር ነው::

9ኛ ያዕቆብ

የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ከሐዋርያት አንዱ አንድ አንድ ጊዜ ታና ያዕቆብ ይባላል ማቴ.10÷3 ማር.15÷40 ጸሎት ወዳድ በመሆኑ ለብ ሠዓታት መቆም ስለሚያበዛ እግሩ ያብጥበት ነበር:: በዚህም የተነሳ እ አሥራ አንዱ ሐዋርያት ተዘዋውሮ ለማስተማር ባለመቻሉ የኢየሩሳ

ኤጴስ ቆጶስ በመሆን ተሾመ በ50 ዓ.ም በኢየሩሳሌም የተደረገውን ሲኖዶስ በሊቀመንበርነት የመራውም ርሱ ነው የሐዋ. 15÷13:: በኢየሩሳሌምም መንበር ለ28 ዓመታት ያህል አገልግሏል:: አይሁዶችም በትምህርቱ አምጸው ለሊቀ ካህናቱ ለሀናንያ ነግረው አሠሩት ሊቀካህናቱ አይሁድን በቤተ መቅደስ ዙሪያ ከሰበሰበ በኋላ ቅዱስ ያዕቆብን ወደ መቅደስ ጣራ አውጥቶ በዚህ ሕዝብ ፊት ክርስቶስን ክደህ አስተምር ብሎ አዘዘው ቅዱስ ያዕቆብ ጌታን በመካድ ፈንታ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነቱን ቀጠለ በዚህ የተናደዱ የአይሁድ አለቆች ያዕቆበን ከቤተ መቅደስ ጫፍ ወረወሩት ከዚያም ከሥር የተሰበሰቡት አይሁድ በድንጋይ ሰባብረው ገደሉት ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን እንደ ጻፈው የካቲት 10 በ62 ዓ.ም ነው ነገዱ ከነገደ ጋድ ነው::

10ኛ ታዴዎስ

ታዴዎስ ከሐዋርያት አንዱ ማቴ.10÷3 በሉቃስ 6÷16 እና በሐዋ.1÷13 የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ተብሎ ተጠርቶአል:: ልብድዮስም ይባላል:: ሐምሌ 2 ይመ. ነገዱ ከነገደ ዮሴፍ ነው::

11ኛ ናትናኤል

ናትናኤል የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው:: አገሩ ቃና ዘገሊላ ነበር ዮሐ.21÷2 ፊልጶስ ወደ ኢየሱስ ጠራው ዮሐ.1÷44 ቀናተኛ ስምዖንም ይባላል:: ነገደ ብንያም ነው የትውልዱ ቦታ ጌታ በተወለደበት አካባቢ ነው ምክንያቱም ሔሮድስ የቤተልሔምን ሕፃናት ባሰፈጀበት ጊዜ እናቱ ከበለስ ሥር ደብቃ አትርፋዋለች ጌታም ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ ሥር ሳለህ አውቅሃለሁ ብሎታል:: ናትናኤል ያስተማረበት ሀገር ሶርያ፣ ባቢሎን፣ ግብጽ፣ እስያ አስተምሯል ብዙ ዘመኑን ያሳለፈው በዚህ በሰሜን አፍሪካ ነው በትምህርቱ አረማውያን ስለቀኑበት ሁከት አሥነሥተው የመንፈስ ኃይማኖት ተቀበሉ ይለናል ብለው ለግብጽ ንጉሥ እንድርያኖስ ከሰሱት ንጉሡም በሠራዊት አስይዞ በማስመጣት ሐምሌ 10 ቀን በሰይፍ አስገድሎታል:: ነገዱ ከነገደ ብንያም ነው::

12ኛ የይሁዳ ምትክ ማትያስ

የሐዋ. 1÷15-26 ከሰባ ሁለቱ አርድዕት አንዱ ነው። ሐዋርያው ቅ.ጴጥሮስ «ከኛ ዘንድ እስካረገበት ቀን ድረስ ጌታ ኢየሱስ ከእኛ መካከል በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ ከእኛ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤ ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል አለ። የሐዋ. 1÷21-22 ማትያስ እንዲሰብክ ዕጣ የደረሠው በሳዕተ ሰብዕ የሚባሉ ወደ ሚኖሩበት አገር ነው። ማትያስን ያዙትና አይኑን አውጥተው እንደ እንስሳ ሳር ያበሉት ጀመር ማትያስ በእስር ቤት ለ40 ቀን ተቀመጠ ሳሩን ሳይበላ በያም አላለፈው። እንድርያስ ከእግዚአብሔር ተልኮ በተዘጋ በር ገባ ከእስር ቤትም ከ120 ሰዎች ጋር ማትያስን ይዞ ወጣ ተአምሩን ያዩ ሰዎችም አምነው ተጠመቁ ማትያስም ወደ ደማስቆ ገብቶ ስብከቱን ጀመረ ሰዎችም በብረት አልጋ በማስተኛት ከሥሩ ለ7 ቀን ያህል እሳት ለቀቁበት ሲመለሱ ጉዳት ሳይደርስበት በማግኘታቸው አምነው ተጠምቀዋል በመጨረሻ በሀገረ ይሁዳ ሲያስተምር ፊልሞን በተባለ ቦታ እድሜ ጠግቦ አርፏል በዓለ እረፍቱ መጋቢት 8 ቀን ይከበራል።

ሐዋርያት ከዕርገት በኋላ በአንድነት የሠሯቸው ሥራዎች

1ኛ ዮሴፍ የተባለ በርናባስን እና ማትያስን እጣ አጣጥሎ መምረጥ የሐዋ.1÷12-26

2ኛ በአይሁድና በአህዛብ መካከል በተነሣው ጭቅጭቅ ሰባቱን ዲያቆናት መርጠ መሾም ስማቸውም እስጢፋኖስ፣ ፊልጶስ፣ጵሮኮሮስ ፣ ኒቃሮን ጢሞና፣ ጰርሜና፣ ኒቆላዎስ ናቸው። የሐዋ. 6÷1-6

3ኛ የመጀመሪያውን ሲኖዶስ በ51 ዓ.ም ለሕዝብ አስተላልፈዋል ከተወሰኑትም ጥቂቶቹ

1ኛ ከጣዖትና ለጣዖት ከተሰዋ መስዋእት

2ኛ ደምን ከመብላት

3ኛ ታንቆ ከሞተ

4ኛ ከዝሙት መከልከል ናቸው። የሐዋ.15÷6-30

የሐዋርያት ሥልጣን ከመላእክት ጋር

ቅዱስ ዮሐንስ በክብር ደረጃ ከመላእክት እንደ ተስተካከለ ለማስረዳት በክብር የሠገደለት መልአክ በክብር እንዲተካከለው ሲገልጽለት መልአኩ እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ክርስቶስ ምሥክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ ብሎታል ራዕይ 19÷9-10 ፣22÷8-9 «የብቃትም መመዘኛ ጣሪያው መልአክ በክብር እኔና አንተ አንድ ነን ከእንግዲህ ወዲህ ሰፈጣሪ ስገድ እስኪል ድረስ ሆኖ መገኘት ነው። ፈጣሪያቸው ክርስቶስ ለወዳጆቹ ለሐዋርያት የሠጣቸውን የሥልጣን ደረጃ የሚያስተባብር መሆኑን የሚያመለክተውን እንመልከት

1ኛ ቅዱስ ሚካኤል በአጋንንት ላይ ሥልጣን እንዳለው ራዕ. 12÷7-10 ሐዋርያትም በአጋንንት ላይ ሥልጣን እንዳላቸው ማቴ.10÷1-3

2ኛ ቅዱስ ሚካኤል ሠይጣንን እንዳዋረደው ራዕ.12÷7-10 ዳን.10÷10-22 ይሁ.8÷10 ቅዱስ ጳውሎስም አዋርዶታል የሐዋ.16÷16 -19

3ኛ መላእክት ያዘዙትን የማይቀበላቸውን ሁሉ እንደቀጡ ሉቃ.1÷19-22 ሐዋርያትም ያልተቀበላቸውን ለመቅጣት ሙሉ ስልጣን እንዳላቸው የሐዋ.13÷10-12

4ኛ መላእክት እንደቀሰፉ ማቴ.18÷10 የሐዋ. 12÷22-24 ሐዋርያትም ይቀሰፋሉ የሐዋ.5÷1-11

5ኛ የእግዚአብሔር ስም በመላእክት ነው። ዘፀ.23÷20 ስሙም በሐዋርያት ላይ ነው የሐዋ.9÷15 ሐዋርያት የመፍታትና የማሠር የማጽደቅና የመኰነን በማናቸውም ሰባዊ ፍጡር ላይ የመፍረድ ሙሉ ሥልጣን ከፈጣሪያቸው ተሠጥቷቸዋል ማቴ.16÷19-20፣18÷18 ፣19:28

ምዕራፍ 32

የሰብዓ ሁለቱ አርድኢት ታሪክ

ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ ሁለት ሁለትም አድርጐ ላካቸው ሉቃ. 10÷1-16 ሰብዓውም ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንትስ እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት ርሱም አጋንንት ስለተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ ስማችሁ ግን በሰማይ ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ ብሎ የሚመጣውን ተስፋ አብስሮአቸዋል። ሉቃ. 10÷17-20 በገድለ ሐዋርያት 72 ተብለው ሲቆጠሩ በወንጌሉ 70 ተብለዋል ልማደ መጽሐፍ ነው። የተረፈውን ትቶ ሲቆጥር እግዚአብሔር ለአብርሐም ዘርህን ባሪያዎች አድርገው ለአራት መቶ አመት ያሰጨንቋአቸዋል ብሎታል ዘፍ.15÷14 የጐደለውን ሞልቶ ሲቆጥርም ለሙሴ እንደነገረው የእስራኤልን ልጆች በግብጽ ምድር የተቀመጡበት ዘመን 430 ዓመት ነው። ዘጸ.12÷40 እንዲሁም ሰሎሞን እንደሰው ሁሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የተፀነሰ ሲሆን የጐደለውን ሞልቶ በመቍጠር አስር ወር ተፀነስኩ ይላል ጥበ.7÷2 ምሳሌዎቻቸውም ሙሴ የመረጣቸው ሰባ ሊቃናት ናቸው ዘጎ.11÷16 ኤልዳድ ሞዳድ ዘጎ11÷26 ሰባውና እነዚያ ከሕዝባው የቀሩ በሠፈር የነበሩ ሁለቱ ነቢያት የአንድ ቀን ነቢያት መሆናቸውን ታሪካቸው ይናገራል። ትንቢታቸውም ምግብን በተመለከተ ጊዜያዊ የአንድ ቀን ነው እንደ ዛሬ ተናግረው በማግስቱ ተፈጽሟል እንዲሁም በሌላ ሰባ ቍጥር ምሳሌ ወደ ግብጽ የወረዱ ሰባ ሰዎች ዘፍ. 46÷27 የሰው ዕድሜ ሰባ መዝ.89÷10 ይቅርታ የሚደረግባቸው ጊዜያት ሰባት ጊዜ ሰባ ማቴ.18÷22። ስለዚህ ሰባሁለት ቋንቋ ተገለጠላቸው።

የሰብዓ ሁለቱ አርድኢት ሥም

1ኛ ማርቆስ ሊቀ አርድኢት መጀመሪያ ስሙ ዮሐንስ ነበር የሐዋ. 12÷12 ሚያዝያ 30 ይመልከቱ።

2ኛ ሉቃስ፡- ሉቃስ በመጽሐፍ ቅዱስ ስሙ ተጠቅሶ የሚታየው በቍላ. 4÷14 ፊልሞ. 24 2ኛ ጢሞ.4÷11 ላይ ብቻ ነው በነዚህ ጥቅሶች ላይ ሉቃስ ባለመድኃኒት የጳውሎስም ታማኝ አረዳት እንደነበር እንመለከታለን

የሐዋ.28÷30-31 ጳውሎስ ታስሮ ሳለ ያንጊዜ የሐዋርያት ሥራን ወንጌልን ጽፏል። የተጻፈለትም ለቴዎፍሎስ ነው ሉቃ.1÷1 የሐዋ.1÷1 ወንጌሉ የተጻፈው በ60 ዓ.ም ነው። ምዕራፉ 24 ቍጥሩም 1149 ነው። ወንጌሉን ከጽንሰት እስከ ዕርገት የሐዋርያትን ከዕርገት ጀምሮ እስከ ዘመነ ሐዋርያት ያለውን ጽፎአል ጥቅምት 22 ቀን በሰይፍ ተሰይፎ አርፎአል።

3ኛ. እስጢፋኖስ የሐዋ. 6 እና 7 ፤22÷20 ጥቅምት 17 ይመልከቱ።

4ኛ ጳውሎስ በዕብራይስጥ ስሙ ሳኦል በሮማዊው ስሙ ጳውሎስ የሐዋ. 13÷9 በጠርሴስ ተወለደ የሐዋ. 21÷39 ድንኳን መስፋትን ተማረ የሐዋ. 18÷3 ሕግንም ከገማልያል ተማረ የሐዋ. 22÷3፤26÷4-5 እስጢፋኖስ ሲሞት የሐዋ.7÷59-60 ፤8÷1-3፤9÷1-8 በኋላ አምኖ በሐናንያ ተጠመቀ የሐዋ. 9÷10-17፤22÷12-16 ዘጠኙን መልእክት ወደ ሐገር አምስቱን ወደ ሰው አሥራ አራት መልእክት ጽፎ በ67 ዓ.ም ሐምሌ 5 በኔሮን አንገቱን ተሠይፎ አርፏል።

5ኛ ጢሞቴዎስ የሐዋ. 16÷1 2ጢሞ.1÷5፤3÷14 ስንክ ጥር 23 ይመ.

6ኛ ሲሳስ የሐዋ.15÷22፤15÷40 ስንክ ጥቅምት 15 ይመ.

7ኛ በርናባስ የሐዋ.4÷36፤4÷26 ስንክ ታኅሣሥ 21 ይመ.

8ኛ ቲቶ የሐዋ.15÷1 2ቆሮ.7÷5 ቲቶ.1÷5

9ኛ ፊልሞና ፊል.2÷ቈላ.4÷8 ስንክ ሀዳር 27

10ኛ ቀሌምንጦስ ፊልጵ.4÷3 ስንክ ኅዳር 29

11ኛ አልዓዛር ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው የማርያምና የማርታ ወንድም ዮሐ.11÷1-49፤12÷1-19 መጋቢት 17 አርፎ መጋቢት 20 ክርስቶስ ከአሥነሣው በኋላ በኤጲስ ቆጶስነት 40 ዘመን ኑሮ ግንቦት 27 ቀን አርፏል።

12ኛ ስምዖን ዘለምጽ በቢታንያ ይኖር የነበር በቤቱም ማርያም ክርስቶስን ሽቱ የቀባችበት ማቴ.26÷6 ዮሐ.12÷3 ሉቃ.7÷49

13ኛ ዘኬምስ ሉቃ. 19÷1-10

14ኛ ቆርኔሌዎስ የሐዋ. 10÷3 -35 ስንክ ኅዳር 23

15ኛ አጋቦስ የሐዋ.11÷28 ስንክ የካ.4

16ኛ ጢባርዮስ (ጤርጥዮስ) ሮሜ.6÷22 ስንክ. መስ.21

17ኛ አግናጤዎስ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱ በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ማን ይበልጣል ብለው በጠየቁት ጊዜ እንደዚህ ሕጻን ካልሆናችሁ መንግሥተ ሰማያት አትገቡም ብሎ በፊታቸው ያቆመው ሕፃን አግናጤዎስ ነበር ማቴ.18÷1-7 ስንክ ታኅ.24

18ኛ አብሮኮሮስ ስንክ ጥር 20

19ኛ ማልኮስ ዮሐ.18÷10

20ኛ አንሲፎሮስ ስንክ መጋ.25

21ኛ ኤርስጦስ ሮሜ 16÷23

22ኛ ጋይዮስ ሮሜ.16 ÷23

23ኛ ኢያሶን ሮሜ.16፡1 ስንክ ግን.3

24ኛ ድዮናስዮስ የሐዋ.17፡34

25ኛ አናሲሞስ ቈላ.4÷8 ፊልሞ.1÷1 ስንክ የካቲት 21

26ኛ ፊልጶስ የሐዋ. 6÷5፤8÷26፤21÷8 ስንክ ጥቅ.14

27ኛ ጢሞና የሐዋ. 6÷5 ስንክ ጥቅ.26

28ኛ ጳርሚና የሐዋ.6÷5

29ኛ ኒቆላዎስ የሐዋ 6÷5

30ኛ ዮሴፍ ማቴ.27÷57 ሉቃ.23÷50

31ኛ ኒቆዲሞስ ዮሐ.3፡1፤7፡45-52፤19÷39 ስንክ ነሐሴ 1 ይመልከቱ

32ኛ ያዕቆብ ማቴ.13÷55 1ቆሮ.15÷7 ስንክ ሐም.18

33ኛ ይሁዳ ይሁ.1፡1 ማቴ.13፡15 ስንክ ሰኔ 25

34ኛ ስልዋኖስ 2 ቆሮ.1፡19፤ 1ጴጥ.5÷12

35ኛ አፍሮዲጡ ፊልጵ 2፡25፤4÷18

36ኛ ገማልያል የሐዋ.5፡34፤22÷3

37ኛ እንድራኒቆስ ስንክ ግን.22 ቅዳ. ጉር.

38ኛ ሐናንያ የሐዋ.9÷10-19 ስንክ ሰኔ 27 ጥቅ.4

39ኛ ጵርስቅላ

40ኛ አቂላ የሐዋ.18÷2፤ ሮሜ.16÷3 1ቆሮ.16÷19

41ኛ ቴዎፍሎስ ሉቃ.1÷1 የሐዋ.1÷1

42ኛ ዩልያን ሮሜ .16÷7

43ኛ ጳልያጦስ » 16÷9

44ኛ ኤርባኖን » 16÷9

45ኛ ስንጣክን » 16÷10

46ኛ ኤጤሌን » 16÷10

47ኛ ሄሮድዮና » 16÷11

48ኛ ጢሮፊሞስ » 16÷12

49ኛ እስክረጦስ »

50ኛ ሉቅዮስ »

51ኛ ሱሲ ጴጥሮስ » 16÷21

52ኛ ጵሮኮሮስ የሐዋ. 6÷5

53ኛ ኒቃሮናን » 6÷5

54ኛ አርስጥሮኮስ ፊልሞ 1÷24፤4÷1

55ኛ ኤጳፍራ » 1÷24 ቈላ.4÷12

56ኛ አስተራትዮስ

57ኛ ኢዮስጦስ ቈላ. 4÷11

58ኛ ኢኪላስ –

59ኛ ቀለዮጳ ዮሐ. 19÷25

60ኛ ቲቂቆስ 2ጢሞ 4÷12

61ኛ ፕሮፊሞስ » 4÷20

62ኛ ኤሌመን ሮሜ .16÷10

63ኛ ክርስቶፎሮስ

64ኛ አርንያኖስ

65ኛ ዩልያል ሮሜ.16÷15

66ኛ አርክቦንዮስ

67ኛ ኬፋ

68ኛ አድማጥስ

69ኛ ሮፎስ

70ኛ አለእስክንድሮስ

71ኛ መርአንዮስ

72ኛ ኤጴንጤስ

አንድ አንድ የስም መለዋወጥ ቢኖር አንድ ሲሞት አንዱ ይተካ ስለነበር በሣጥናኤል አዳም በይሁዳ ማትያስ እንደተተኩ ማለት ነው። መጽ ግንዘት ገጽ.12 ይመልከቱ።

ምእራፍ 33

36ቱ ቅዱሳት አንስት

ብዙዎች ሴቶች በገንዘባቸው እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር ሉቃ.8÷3 ኢየሱስ ሴቶችን በቃልና በድርጊት ይረዳ ነበር ማቴ.5÷27፣9÷18 ሉቃ.10÷38-42 የቅዱሳት አንስትን ስም ከመጻፋችን በፊት ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የተባለችውን ድንግል ማርያምን እንመለከታለን።

የእመቤታችን ከልደቷ እስከ እረፍቷ

1ኛ እመቤታችን ነሐሴ 7 ቀን 5 ሺህ 484 ዓ.ዓ በዘመነ ዮሐንስ ረቡ ዕለት ተፀነሰች

2ኛ ግንቦት 1 በ5ሺህ 485 ዓ.ዓ በዘመነ ማቴዎስ ቅዳሜ ቀን ተወለደች

3ኛ በተወለደች በ2 ዓመት ከ7 ወር ከ9 ቀን ታኅሣሥ 3 በ5ሺህ 488 ዓ.ዓ ማክሠኞ ቀን በዘመነ ዮሐንስ ወደ ቤተመቅደስ ገባች

4ኛ በተወለደች በ14 ዓመቷ 11 ወር ከ5 ቀን መጋቢት 29 በ5ሺህ 5መቶ ዓ.ዓ በዘመነ ዮሐንስ እሁድ ዕለት ጌታን ፀነሰች

5ኛ እመቤታችን በተወለደች በ15 ዓመቷ 8 ወር ከ4 ቀን ታኅሣሥ 29 በ5 ሺህ 501 ዓ.ዓ በዘመነ ማቴዎስ ማክሰኞ ቀን ጌታን ወለደች

6ኛ እመቤታችን በተወለደች በ63 ዓመቷ ከ8 ወር ከ26 ቀን ጥር 21 በ5549 ዓ.ዓ ወይም 49 ዓ.ም እሁድ ዕለት ዐረፈች።

ወደ ኋላ ተመልሰን ክርስቶስ እርገት በኋላ ያለውን ታሪክ ስንመለከት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሐዋርያት ፣ የአርድኢት የአንስት መሪና አስተዳዳሪ እንደነበረች መጽሐፍ ያስረዳናል የሐዋ. 1÷13-15 የአስራ ሁለቱን ሐዋርያት ስም ከዘረዘረ በኋላ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር ይላል። ሴቶች ያለው 36ቱ ቅዱሳት ሲሆኑ ወንድሞች ያለውም ሰብዓ ሁለቱ አርድኢትን ነው። ለነዚህም ለመቶ ሃያ ቤተሰብ ጸሎታቸውን የምታሣርገው ርሷ ነበረች ስለዚህም ርሷ ባለችበት በሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል።

1ኛ ሰሎሜ፡-

ታሪክ፡ ማጣት ለተባለው ሰው ሦስት ሴቶች ልጆች ነበሩት አንደኛይቱ ማርያም ትባላለች ይህችውም ሰሎሜን የወለደችው ነች ሁለተኛይቱ ሶፍያ ትባላለች። ይህችውም ኤልሳቤጥን የወለደችው ናት ሦስተኛይቱም ሐና ትባላለች ይህችውም ድንግል ማርያምን የወለደችው ናት። ሰሎሜ በቤተልሔም ጌታችን ሲወለድ አዋላጅ የነበረችውና እንዲሁም በ3ዓመት ከመንፈቅ የስደት ጉዞ ጌታን በማዘል ድንግል ማርያምን የረዳቻት ናት ይህችውም እስከ ሕይወቷ ፍፃሜ ሐዋርያትን አገልግላለች ትንሣኤንም ከሴቶች ጋር አይታ ሰብካለች። በ50 ቀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብላ ጲያቆናዊት ሆና ተሾማለች ዕረፍቷም ግንቦት 25 ቀን ሥንክሣር ይመልከቱ።

2ኛ ኤልሳቤጥ -

ሉቃ.1÷5-25 ኤልሳቤጥ የካህኑ የዘካርያስ ሚስት ካረጀች በኋላ መጥምቁ ዮሐንስን የወለደች ርሷም የቅድስት ድንግል ማርያም ዘመድ ነበረች ጸንሳ ለች ማርያም በጐበኘቻት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ አስደናቂ ቃል ተናገረች ሉቃ.1÷39-46 ኤልሳቤጥም ከአሮን ወገን ነበች ከአሮን ሚስት ኤልሳቤጥ ጋርም ትመሰላለች ዘፀ.6÷23 ሉቃ.1÷5 የአሮን ሚስት ኤልሳቤጥ ለች አሪት ተሰርታለች የዘካርያስ ሚስት ኤልሳቤጥ ሣለች ወንጌል ሠራች በኤልሳቤጥ የተሠራች ሕግ በኤልሳቤጥ አለፈች ካህኑ ዘካርያስን

በካህኑ አሮን ያነፃፅሩ:- ሁለተኛም ከአረጀች በኋላ ልጅ መውለዷ ከሣሌ ትመሠላለች ዘፍ.21÷1-9፤ ሉቃ.1÷57-64 ዮሐንስን ከይስሐቅ ዘፍ.22÷7 ዮሐ.1÷29 ዘካርያስን ከያዕቆብ ያዕቆብ ልጆቹን ሠብስቦ ትንቢት እንደተናገረ ዘፍ.49÷1-28 ዘካርያስም በልጁ ላይ ትንቢት ተናግሯል ሉቃ.1÷76 የኤልሳቤጥ አረፍት የካቲት 16 ስንክ ይመ. ::

3ኛ ማርታ

የአላዛር እህት ቢታንያ በተባለው መንደር የምትኖር በብዙ ሥራ ስለባከነች ኢየሱስ መከራት ሉቃ.10÷38-41 ስለትንሣኤ ሙታን ያላትን እምነት ገለጠች ዮሐ.11÷20-27 ዕረፍቷ ጥር 18 ቀን ነው::

4ኛ ማርያም እንተ እፍረት

ዕረፍቷ የካቲት 6 ጌታችንን ሽቱ የቀባችበት መጋቢት 21 ቀን ነው::

5ኛ ማርያም መግደላዊት

ዕረፍቷ ነሐሴ 6 ቀን ነው::

6ኛ ማርያም የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት

ዕረፍቷ በጥር 18 ቀን ነው::

7ኛ ማርያም የማርቆስ እናት

እረፍቷ በጥር 30 ቀን ነው::

8ኛ ማርያም የቀለዮጳ ሚስት

እነዚህን አምስቱን ሰኔ 21 ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ይመ.

9ኛ ሐና ነቢይት የ84 ዓመት ባልቴት ርስዋም እንደ ስምዖን በብሉይ ኪዳን ስለተረዳች መሲሕን ትጠብቅ ነበር:: ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ ሕፃን ሆኖ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ አወቀችው ለሌሎችም መሰከረች ሉቃ.2÷36-38 ዕረፍቷ የካቲት 8 ቀን ነው::

10ኛ ዮሐና የኩዛ ሚስት ሉቃ.8÷2

11ኛ ሶስና ሉቃስ 8÷2

12ኛ ልድያ በመጀመሪያ ያመነች ሴት ነበረች የሐዋ.16÷13-15

13ኛ ፌቬን ሮሜ 16÷1

14ኛ ጣቢታ፣ የሐዋ.9÷36-40

15ኛ ማርያ ፣ ሮሜ 16÷6

16ኛ ጠርሲዳ፣ ሮሜ 16÷12

17ኛ ሮዴ፣ የሐዋ.12÷13

18ኛ ብርፍሲንያ (ሳምራዊት) ዮሐ.4÷7-43 የአባቷ ስም ሰላፍ የእናቷ ስም ሞሕያ የባሎቿ ስም 1. ሰንቴ 2. ዮካን 3.ሌዊ 4. ሄሉት 5.ራፍስያ በግእዝ በተጻፈው ተአምረ ኢየሱስ ገጽ 67 ይመ.

19ኛ የይዋኤል ልጅ መበለቲቱ ሰሚም በርሰዓ ይባላል የተነሣውም ዮናስ ይባላል ተአምረ ኢየሱስ ገጽ 150 ሉቃ.7÷11-17

20ኛ ከነናዊት ሴት ማቴ.15÷21-28

21ኛ ሰፍያ ዕረፍቷ ነሐ.3 ስንክ ይመ.

22ኛ ጴስ

23ኛ አሳጴስ

24ኛ አጋጴስ ዕረፍታቸው ጥር 30 ወይም ነሐሴ 1 ቀን ስንክ ይመ.

25ኛ ዮስቴና ስንክ መስ.21 ይመ.

26ኛ ዕንባ መሪና ነሐ. 15 ስንክ ይመ.

27ኛ አርሴማ መስ.29 ዕረፍቷ ታኅ.6 ፍልሰተ አጽሟ ስንክ ይመ.

28ኛ አርኒ

29ኛ ኢየሱጣ ነሐሴ.6 ቀን

30ኛ አሴኒ ጥር 29 ቀን

31ኛ ኢዮጰራቅስያ መጋ 26 ቀን

32ኛ ታአድራ ጥር 4 ቀን

33ኛ ቴክላ ስንክ ሐም.25 ቀን ይመ.

34ኛ ኢላርያ ጥር 21 ስንክ ይመ.

35ኛ ማርያም ግብፃዊት ሚያ.6 ስንክ ይመ.

36ኛ አትናስያ ነሐ. 2 ስንክ ይመ.

የጌታችን 120 ቤተሰቦች የተባሉ እኚህ ናቸው

የሐዋ. 1÷15 መጽ ግንዘት ገጽ 122

ምሳሌአቸውም ንግሥት ሳባ ለሰሎምን የሠጠችው 120 መክሊት ሲሆን ክርስቶስ የሰሎሞን ይህ ዓለም የሰባ መቶ ሃያ ቤተሰብ 120 መክሊት ንግሥት ሳባ ለሰሎሞን እንደሰጠች ክርስቶስ ከዚህ ዓለም መርጧቸዋልና 1 ነገ.10÷10 ዮሐ.15÷19

ለመዋዕለ ስብከቱ ይከተሉ የነበሩ 120 ቤተሰቦቹ

ሁላቸውም እንደ ነብዩ ቃል መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ለማስተማር በቅተዋል:: ኢዩ.2÷28 የሐዋ.2÷16

- ቅዱሳት አንዕስት በመዋዕለ ስብከቱ ሉቃ.8÷2 –
- እንዲሁም መስቀሉን ተሸክሞ ሲጓዝ ሉቃስ 23÷27
- በስቅለተ ክርስቶስ የተገኙ ሴቶች ማቴ.27÷55 ማር.15÷40-41 ዮሐ.19÷25
- በትንሣኤ ወደ መቃብር የሄዱ ሴቶች ማቴ.28÷1-10 ማር.16÷1 ሉቃስ.24÷1 ዮሐ. 20÷1
- በዘመነ ሐዋርያት ሴቶች ለብዙ ሥራ ታዛዥ እንደሆኑ 1ጴጥ.3÷1-6 ቆላ.3÷18 1ቆሮ.11÷9 1ጢሞ.2÷11-15 ኤፌ.5÷22 1ጢሞ.5÷1-2
- በሙሴ ሕግ የሴት መብት የተጠበቀ ነው ዘዳ.15÷12-23፤7÷17-24፤1÷5-17)
- ሴቶች ልጆቻቸውንም ያስተምሩ ነበር 2ጢሞ.1÷5

ምእራፍ 34

ታኅሣሥ 9 ቀን ተሣቱ (9) ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት

፱ቱ ቅዱሳን በ480 ዓ.ም ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ መጡ በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው ንጉሥ አልዓሜዳ ነው:: የስደታቸው ምክንያት በጉባዔ ኬልቄዶን የተከሰተውን አዲስ ትምህርት

በመቃወማቸውና በቢዛንታይንም ነገሥታት ሥቃይ ስለጸናባቸው ነው:: ቢዛንታይን የአንድ መንደር ስም ነው:: ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ንጉሡ አቀባበል በማድረግ በአክሱም ቤተ ቀጢን በሚባል የእንግዶች መቀበያና ትምህርት ቤት አርፈዋል:: ብዙም የኢትዮጵያን ባሕል ተምረዋል:: በኢትዮጵያ ውስጥም 5ነገሮችን አስፋፍተዋል:-

1. ቤተክርስቲያንን አቋቁመዋል
2. መጻሕፍትን ተርጉመዋል
3. ወንጌልን አስፋፍተዋል
4. ገዳማትን ተክለዋል
5. ሥርዓተ ምንኩስናን ሰርተዋል::

ዘጠኙ ቅዱሳን የመጡበት የተቀመጡበት ቦታ የስማቸው ትርጉምና የበዓላቸው ቀን

1. አባ <u>አረጋዊ</u> ትውልዳቸው ሮም ሲሆን አባታቸው ይስሐቅ እናታቸው አድና ትባላለች 3 ስምም አላቸው በወላጆቻቸው ገብረ አምላክ አባ ዘሚካኤል የምንኩስና በመባል ይጠራሉ:: ከመንፈሳዊ ሥራቸው የተነሣ 8ቱ ጓደኞቻቸው አረጋዊ ብለው ሰይመዋቸዋል:: የተቀመጡበት ቦታ ደብረ ዳሞ ይባላል:: የበዓላቸው ቀን ጥቅምት 14 ቀን ነው::
2. አባ <u>ጳንጠሌምን</u> አስተዳደጋቸው እንደ ነቢዩ ሳሙኤል በቤተ መቅደስ ነበር የመጡበት አገር ሮም ሲሆን የተቀመጡበት ቦታ አክሱም ሰሜን ምስራቅ መካነ ጸማእት ነው:: የስማቸው ትርጉም ልብስ ማለት ሲሆን የበዓላቸው ቀን ጥቅምት 6 ነው::
3. አቡነ <u>ይመዐታ</u> ብዙ የቆዩት በትግራይ ውስጥ ገርአልታ በሚባለው ልዩ ስሙ ጉሕ ተብሎ በሚጠራው ነው:: ይምዐታ ከአክሱም ተነሥተው ቅዳሴ ማርያምን እያዜሙ አብ ጉሕ ወልድ ጉሕ ወመንፈስ ቅዱስ ጉሕ ብለው ሲጨርሱ የጉሕ መንደር ደረሱ በዚህ የተነሳ ይኩን ስምኪ መካነ ጉሕ ብለው ሰየሚት የመጡት ቆስያ

ከሚባል ቦታ ሲሆን የተቀመጡበት ቦታ ገርአልታ ይባላል። የስማቸው ትርጉም ማታ የመጣ ማለት ነው። በዓላቸው ጥቅምት 28 ቀን ነዉ።

4. አባ ገሪማ የቀድሞ ስማቸው ይስሐቅ ሲባል ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ ይህንን ስም አግኝተዋል እግዚአብሔር በእሳቸው አማካኝነት ልዩ ልዩ ተዓምራት ስለገለፀ ይህ ስም ተሰጥቶአቸዋል። የስማቸው ትርጉም አስደናቂ የሚያስገርም ማለት ሲሆን የመጡበት ከሮም ነው። የተቀመጡበት ቦታ መደራ አደዋ ሰሜን ምስራቅ ነው። የበዓላቸው ቀን ሰኔ 17 ነው ስንክ.ይመ.
5. አባ ጽሕማ ከዘጠኙ ቅዱሳን ሽማግሌ ስለነበሩ ጸሎትና ቡራኬ የሚሰጡ አባት ነበሩ የመጡት ከአንጾኪያ ሲሆን የተቀመጡበት ቦታ ጸደያ ይባላል። የስማቸው ትርጉም ጢማም ማለት ነው። አረፍታቸው ጥር 16 ቀን ነው።
6. አባ አፍፃ የመጡበት የትውልድ አገራቸው እስያ ሲሆን አባታቸው አቡድራስ እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ። በ15 ዓመታቸው ዲቁና ተቀብለዋል። የስማቸው ትርጉም አፈ ንጉሥ ማለት ነው። የተቀመጡበት ቦታ የሀ ይባላል። የበዓላቸው ቀን ግን.29 ነው።
7. አባ ሊቃኖስ የመጡት ከቁስጥንጥንያ ሲሆን የተቀመጡበት ቦታ ደብረ ቆናጽል ይባላል። ከአክሱም በስተ ሰሜን የሚገኝ ኮረብታ ቦታ ላይ ነው። የስማቸው ትርጉም ሊቅ ማለት ሲሆን በዓላቸው ጎዳር 28 ቀን ነው።
8. አባ አሌፍ የስማቸው ትርጉም በእብራይስጥ1ኛ / መጀመሪያ/ የተገኘ ማለት ነው መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ከገቡት ቅዱሳን የመጀመሪያ ናቸው ይባላል የመጡት ከቂሣርያ ሲሆን የተቀመጡበት ቦታ ደብረ ሃሌ ሉያ አህሳዕ ለአክሱም ሰሜን ምሥራቅ ነው በዓላቸው መጋቢት 11 ቀን ነው።
9. አባ ጉባ የመጡበት አገር ኬልቂዶን ሲሆን የተቀመጡበት ቦታ ከአደዋ ከተማ ወጣ ብሎ ወደ አባ ገሪማ ገዳም በሚወስደው መንገድ

ላይ ነው። የስማቸው ትርጉም ተራራ ትልቅ ግርማው የሚያስፈራ ማለት ሲሆን በዓላቸው ግንቦት 29 ቀን ይከበራል።

የአበው ቅዱሳን ረድኤትና በረከት በሁላችን ላይ ይደር አሜን።

ምዕራፍ 35

የዘጠኙ ነገደ መላእክት ስም ዝርዝር

መልአክ፡ መላእክት የቃሉ ትርጉም መልእክተኛ ማለት ነው። የተፈጥሮ ሁኔታቸው መላእክት በፍጥረታቸው ረቂቃን መናፍስት ናቸው። ሥጋና አጥንት የላቸውም አያገቡም አይጋቡም። /ሉቃ.24÷39 ማቴ.22÷30 / ብዛታቸው የማይቆጠር ዕውቀታቸው ከፍ ያለ ኃይላቸውም ትልቅ ነው። /ራዕ.5÷11 ማቴ.24÷36 መዝ.102÷20/ የእግዚአብሔር ልጆች መናፍስት ቅዱሳን ጠባቂዎች ተብለው ይጠራሉ። / ኢዮ.1÷6 ዕብ.1÷6-14 ዘካ.1÷11 ዳን.4÷13/

1. ቅዱስ ሚካኤል / ዳን.10÷13-ፍ.ም 12÷1 ራዕ.12÷7 ይሁ.9 ሄኖ.10÷5፣ 5፣12 20÷1-3 ተረፈ ኤር. 11÷38/
2. ቅዱስ ገብርኤል /ዳን.8÷16 ፣9÷21 ሉቃ.1÷19 ሄኖ.6÷10 /
3. ቅዱስ ሩፋኤል / ሄኖ.10÷6 ፣6÷2፣27 ጦቢ.8÷2 ፣12÷15/
4. ቅዱስ ኡራኤል /ዕዝ.ሱቱ.2÷1-3 ፣ሄኖ.6÷2፣26÷34
5. ቅዱስ ፋኑኤል /ሄኖ.10÷8፣15
6. ቅዱስ ሠረቃኤል / ሱርያል/ ሄኖ.6÷6/
7. ቅዱስ አፍኒን ጸሎተ ንግሥ ሄኖ 20÷38
8. ቅዱስ ራጉኤል /ሄኖ.6÷4/
9. ቅዱስ ሳቍኤል ጸሎተ ነግሥ /ስንክ.ሐም.30/

ዳቸውም

ሱራፌል /ኢሳ.6÷2 /

ኪሩቤል /ራዕ.4÷6-11/

መናብርት /ዙፋኖች/ የሚባሉ /ዳን.7÷10/

4. ሥልጣናት (ኃይላት) የሚባሉ / ሮሜ.8÷38-39/
5. አጋዕዝት (ጌቶች) የሚባሉ /ቈላ.1÷15/
6. መኳንንት የሚባሉ
7. ቀደምት »
8. ሊቃናት »
9. መላእክት » ሰባቱ ሊቃነ መላእክት አገልግሎታቸውና ዋና ሥራቸው እግዚአብሔርን ማመስገን ነው:: /ኢሳ.6÷2-4 ራዕ.4÷8፣5÷12/ ሰው በኃጢአት ስለወደቀ ምእመናንን ያገለግላሉ:: / ዕብ.1÷14 / ንስሐ በሚገቡ ሰዎች ደስ ይላቸዋል:: /ሉቃ.15÷10/ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ይጠብቃሉ:: /መዝ.33÷7፣90÷11/

የመላእክት አገልግሎት

እነሆ መላእክት ያገለግሉት ነበር:: /ማቴ.4÷11/ ይኸውም እንደኛ ትምህርት ነው:: ዲያብሎስን ድል ብትነሱ መንፈላዊም ሥራ ብትፈጽሙ መላእክት ይገለጹላቸኋል ሲል ነው:: አገልግሎታቸውም ውኃን በመቅዳት እንጨትን በመስበር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ወደ ሰው ረድኤት በረከትን / ዮሐ.1÷52 የሐዋ.10÷3 / ከሰው ወደ እግዚአብሔር ጸሎትና መሥዋዕትን /ዘካ.1÷11-16 ራዕ.8÷3/ በማቅረብ ነው:: አገልግሎታቸውም በ5 ወገን ይጠቃለላል::

1. ለጽንሰቱ ክብር መልእኩ እንደወረደ /ሉቃ.1÷26-39 ማቴ.1÷20/
2. ለልደቱ ክብር » » /ሉቃ.2÷10-15 ዘፍ.28÷12/
3. ለትንሣኤው » » /ማቴ.28÷2 ማር.16÷5 ሉቃ.24÷4 ዮሐ.20÷12/
4. ለዕርገቱ ክብር /የሐዋ.1÷10/
5. ለዳግም ምጽአቱ ትንቢት ተናግረዋል:: /የሐዋ.1÷10/ አብረው እንደሚመጡ /ማቴ.16÷27፣24÷31፣25÷31 1ተሰ.4÷14 ይሁ.14/

ነገዳቸውም በ3 ይከፈላል::

1. 7ቱ ነገደ መላእክት /ራዕ.15÷8 ጦቢ.12÷15/
2. 12ቱ ነገደ መላእክት /ራእ.21÷12/

3. 99ኙ ነገደ መላእክት /ማቴ.18÷10-12 «ሀዲጎ ተስአ ወተሰአተ ነገደ » እንዳለ ቅዱስ ያሬድ መላእክት የስማቸው ትርጉምም መ: መልእክተኛ ላ: ላእላውያን እ: ዕቍባነ ሥጋ ወነፍስ ክ: ክቡራነ ስም ት: ትጉሃን እለ ኢይነውሙ ማለት ነው::

ምእራፍ 36

ቅዱስ መጽሐፍ

ቅዱስ መጽሐፍ ማለት የተቀደሰ የተለየ የቅዱሳት መጻሕፍት መዝገብ ማለት ነው:: አበው ነቢያትና ሐዋርያትም በእየዘመናቱ የመዘገቡአቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ፈጣሪያችን በፍጡራን እውቀት የማይመረመር ችሎታው እንዲህ የሚል አስፍረውልናል:: ቅዱስ መጽሐፍ ለመላእክትና ለሰዎች መመሪያ ነው:: እግዚአብሔር ለአብርሃም «በውነ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን» /ዘፍ.18÷14/ የሚለውን ቃል መልአኩ ገብርኤል ለእመቤታችን « ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን» ብሏታል:: /ሉቃ.1÷37/ ነቢዩ ኤርምያስም ለእስራኤል «እነሆ የሥጋ ለባሽ ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ በውኑ እኔን የሚያቅተኝ ነገር አለን» /ኤር.32÷27/ እነዚህን ቃላት የተናገረና ያናገረ እግዚአብሔር አምላክ በመላእክትና በሰዎች ይታመናል:: የቅዱስ መጽሐፍ ክፍሎች ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ናቸው:: ብሉይ ኪዳን ከ1400 -400 ከክርስቶስ ልደት በፊት በልዩ ልዩ ቦታዎች 40 በሚያህሉ ልዩ ልዩ ጸሐፊዎች እንደተጻፈ ይነገራል:: አዲስ ኪዳን ከ45-96 ዓ.ም በ8 ሰዎች ተጻፈ:: ቅዱስ መጽሐፍ በሙሉ ወይም በከፊል ከ1500 ቋንቋዎች በላይ ተተርጉሟል:: ደራሲው ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ይባላል /ኢሳ.34÷16/ የብሉይ ኪዳን መነሻ የሆነ ሙሴ ለሕዝቡ ያነብላቸው ነበር /ዘፀ.24÷7/ የብሉይ ኪዳን ዓላማ ስለ እግዚአብሔር መመስከር ነው:: ዮሐ.5÷39-46/ አዲስ ኪዳን በብሉይ ተተንብዮ ነበር:: /ኤር.31÷31-34 / ትንቢቱም ተፈጸመ /ሉቃ.22÷19 ዕብ.8÷13 2ቆሮ.3÷4-18/ የአዲስ ኪዳን ዓላማውም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምነው ምእመናን እንዲጸድቁ

ነው። /ዮሐ.20÷31/ ብሉይ ኪዳን ከዘፍጥረት እስከ ሚልክያስ በ5ቱ መጻሕፍተ ሙሴ አምሳል በ5 ይከፈላል። /ዘዳ.4÷2/

1. ሕግና ሥርዓት ከዘፀአት እስከ ዘዳግም ያሉት የሕግ መጻሕፍት ናቸው።
2. ዘፍጥረት ከኢያሱ እስከ ኢዮብ ጣቢትና ዮዲት የታሪክ መጻሕፍት ናቸው።
3. ጸሎት፡ ይኸውም መዝሙረ ዳዊት ነው።
4. ምክር፡ የ4ቱ የሰሎሞን መጻሕፍት ሚራክ እንበለ መኃልይ
5. ትንቢት፡ የአለትና የወደፊት ቃል ይህም ከኢሳይያስ እስከ ሚልክያስ ያሉት እንበለ ሰቄቃው።

አዲስ ኪዳንም በ4ቱ ወንጌላውያን አምሳል በ4 ይከፈላል።

1. ሕግ አራቱ ወንጌላት
2. ታሪክ የሐዋርያት ሥራ
3. ስብከት ከመልእክተ ሮም እስከ ይሁዳ
4. ራዕይ፣ ትንቢት ናቸው። ሰሎሞንም ብሉይና ሐዲስን በአንድነት ሲናገር «አሮጌው ከሐዲሱ ጋር በደኃችን አለ።» ብሏል /መኃ.7÷14/ ቍጥራቸውንም ዘርዝሮ ሲያስረዳ ስሳ አማንቱ ንግሥታት ወዙ ዕቁባት አዋልድ አለ አልቦን ጉልቍ ወአሐቲ እምኔሆን ርግብየ ፍጽምትየ ሲል ስሳውን አንድ ብሎ ሰማንያውን አመጣው። ዙ ወፎዱ ግለቱ ነው። ከእነዚህም ተለይቶ አንዲቱ ፍጽምት ርግቤ ናት። ያላት ወንጌልን ነው። ስፍር ቍጥር የሌላቸው አዋልድ ያላቸው፡- ድርሳናትን ተአምሮችንና መጻሕፍተ ታሪክን ነው። /መኃ.6÷8 ሉቃ.10÷35/ መጻሕፍትን ባለማወቅ እያጣመሙ የሚተረጉሙትን ክርስቶስ ገስጿቸዋል። /ማቴ.22÷29 / ጴጥሮስም እንደጌታችን ቃሉን በማጽናት አስረድቷል። /2ጴጥ.3÷16/

ተአምርን መቀበል እንዲገባ

በተአምር ብዙ ነገር ይሠራልና ጌታ ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ተአምር በደቀመዛሙርቱ ፊት አደረገ /ዮሐ.20÷30/ ዳግመኛም በስሜ ያመኑትን ይህቺ ተዓምራት ትከተላቸዋለች። /ማር.16÷17 ኢሳ.7÷14/ ባለው መሠረት እግዚአብሔር ለቅዱሳን በሚያስተምርበት ትምህርት በእምነታቸው መሠረት በሚፈጽሙት ምግባርና ትሩፋት እውነተኛ ለመሆናቸው የሚያደርግላቸው ተዓምር ወይም የሚገልጽላቸው ምልክት ነው። /የሐዋ.2÷43/ እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተዓምር ያደርግ ነበር። / የሐዋ.19÷11፣ 14÷10 ዕብ.2÷4/ እግዚአብሔር ሲመርጥ ይህ በትር ነው ይህ ጨርቅ ነው አይልም። እግዚአብሔርም ሙሴን «ይህቺንም ተዓምራትን የምታደርግባትን በትር ይዘህት ሂድ» አለው። /ዘፀ.4÷17 2ነገ.2÷8/

የቅዱሳንን ገድል መቀበል እንዲገባ

ቅዱሳን በገድላቸው ላመነ ከጌታቸው የሚያማልዱ ክብር ፀጋ የሚያሰጡ ስለሆነ ነው። «ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን እንደሚገባ አድርጉ ባይታገል የድሉን አክሊል አያገኝም»/ 2ጢሞ.2÷5/ እንዲሁም «መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» ይላል። /2ጢሞ.4÷7 ሮሜ.8÷35-37/ ጌታችን በዮሐንስ ወንጌል «ከምኩራባቸው ያወጡአችኋል» «ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል ይህንንም የሚያደርጉባችሁ አብንና እኔን ስላላወቁ ነው።» / ዮሐ.16÷2 ጥበብ 10÷12/

ድርሳንና ትርጉምን መቀበል እንደሚገባ

ይህውም ጌታ በወዳጆቹ አድሮ ያናገረው ምእመናን የሚቀበሉት ቃል ነው። «በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው ፣ ትምህርት አለው፣ መገለጥ አለው፣ በልሳን መናገር አለው፣ መተርጉም አለው » ብሏል። / 1ቆሮ.14÷26 ድር.ሚካ.ድር.ገብ.ይህን የመሰለ አዲስ ድርሰት ሁሉ

ራእ.10÷8-11/ መላእክት ለዳንኤል የተሰወረውን ሲተረጉሙለት ዳንኤል ለሰዎች ተርጉሞላቸዋል። /ዳን.9÷21-24፣ 10÷12፣ 12÷4/ ዳንኤል ለናቡከደነጾርና ለብልጣሶር ተርጉሟል። /ዳን.2÷2-48፣ 4÷4-31፣ 5÷1-30/ ዳንኤል ለመላእክት ሲሰግድ ሰው ለዳንኤል ሰግዷል / ዳን.8÷16፣ 2÷46/ ዳንኤላዊ ትውፊትን ቤተክርስቲያን ትቀበላለች። መጻሕፍትን ተርጉሞ ማስተማር እንዲገባ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴና ከነቢያት ጀምሮ ስለ ርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጉመላቸው። /ሉቃ.24÷27/ ያልገባውን ቃል ማስተርጉም እንዲገባ ደቀመዛሙርቱም ቀርበው ምሳሌውን ተርጉምልን አሉት /ማቴ.13÷36 / ያልተተረጉመ ቃል በተዘጋ ቤት ይመሰላል። ቄላ.4÷3

ትውፊት

ትውፊት ማለት ተወፈየ ተቀበለ ካለው ግስ የወጣ ሲሆን ቅብብል ማለት ነው። በመጻሕፍት ያልተጻፈ በቃልና በቅብብል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አለና። ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመሰለኛል። ሲል ተናግሯል። /ዮሐ.21÷25/ ዮሐንስም በ2ተኛው መልእክቱ ሲጽፍ « እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ በወረቀትና በቀለም ልጽፈው አልወድም ወደ እናንተ ልመጣ አፍ ለአፍም ልናገራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ» ብሏል /2ዮሐ.1÷12 3ዮሐ.1÷13/ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማጽናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል»/2ጢሞ.3÷16 ሮሜ.15÷4/

ለቤተክርስቲያን እስራኤል ዘነፍስ፡ እግዚአብሔር ያበቀለው በወንጌሉ ራስ። ድርሰታቸው ቀንድ ሰማይ የሚጠቅስ፡ ጭራውም ትርጓሜ ምድር የሚያብስ።

ፊት በብሉይ ኪዳን ኋላም በሐዲስ፡ አፍ እያስከፈተ መጽሐፍ የሚያጉርስ። እግዚአብሔር መምህር ሆኖ የአዳምን ዘር ሁሉ፡ በመንፈሱ ሲቃኝ ሲያስተምር በቃሉ።

ፊደልና ጥፊት በሰማይ እንዳሉ፡ ብሉይና ሐዲስ ይመሰክራሉ።
አንድ ስለሆነ የዓለሙ መምህር፡ የሰማይ ሥርዓት ተሰርቷል በምድር።

ምዕራፍ 37

የቀድሞ የዘወትር ጸሎት

1. በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ ስቡሕ ወውዱስ ዘኀረረ ኩሉ ዓለመ በሐቲ ቃል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት አምላክ አማልክት ዘሀሉ ወይሄሉ ወትረ በሰማይ ወበ ምድር ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ንሰግድ ለአብ ንሰግድ ለወልድ ንሰግድ ለመንፈስ ቅዱስ እንዘ ሠለስቱ አሀዱ ወእንዘ አሀዱ ሠለስቱ ይሜለሱ በአካላት ወይትወአሐዱ በመለኰት አ ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ አ ሥሉስ ቅዱስ መሐከነ አ ሥሉስ ቅዱስ ተማሃለነ ወሥረይ ለነ ኃጢአተነ ወረስየነ ድልዋነ ንክስት አፉነ ወንጸውእ ስመከ ወንበል በአኰቴት ተብሎ ጸሎት ሲጀመር ነበር። እስከ ዛሬ በጉባኤ ቤት ይጠቀሙበታል።
2. የሦስቱ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስን ስም ለሐዋርያት ያስተማራቸው ራሱ ጌታችን ነው። /ማቴ.28÷19/ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ በቅድስት ሥላሴ የሚለውን በእፄ ዘርዓ ያዕቆብ በ14ኛው መቶ ክ/ዘመን ምእመናን ሲጠመቁ ወይም ካህናት ሲያጠምቁ ፊታቸውን ወደ ምዕራብ መልሰው እክሀደክ ሰይጣን እያሉ እንዲጸልዩ አባ ዘጊዮርጊስ አስተምሯቸዋል።
3. ነአኵተከ ማን አንደደረሰው አይታወቅም ከቅዳሴ ሐዋርያት እንደተወሰደ ይነገራል።
4. አቡነ ዘበሰማያትን የተናገረው ጌታ ነው፡ /ማቴ.6÷9 ሉቃ.11÷1/ በሰላመ ገብርኤልን አባ ዘጊዮርጊስ ናቸው። ከሉቃስ የተወሰደ /ሉቃ.1÷26-38/ ጸሎተ ሃይማኖትን አርዮስን ለማውገዝ በኒቅያ የተሰበሰቡ 318ቱ ሊቃውንት ናቸው። ይህውም ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም እስከሚለው ድረስ ነው። የሠለስቱ ምእት ግሩም ቅዱሱ

ተመልከት በኋላ ግን ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ የሚለውን እስከ ፍፃሜ የደረሱ መቅዶንዮስን ለማውገዝ የተሰበሰቡ 150 የቍስጥንጥንያ ሊቃውንት ናቸው። የካቲት 1 ስንክ ይመ.

5. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስን ሦስት ጊዜ /ኢሳ.6÷2 ራዕ.5÷8/ ስብሐት ለአብንም በ1460 የነበረ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ነው። ከምግብ በፊት ምስጋና ይቀርብ ነበር። / 1ሳሙ.9÷23 ማቴ.15÷36 ሉቃ.14÷30/ ከበሉም በኋላ እግዚአብሔርን ይባርኩ ነበር። /ዘዳ.8÷10/
6. ሰላም ለኪን የደረሱ አፄ በዕደ ማርያም ናቸው። አፄ በዕደ ማርያም ከተማቸው ወሎ አምባሰል ከሚባል አውራጃ ግሩ ማርያም ከምትባል ከተማቸው በበዓለ ማርያም ከቀዳሾቹ አንዱ ቢጉድል ጻድቅ ንጹህ ንጉሥ ነበሩና ሊቀድሱ ቢገቡ ከመቅደሱ ውኃ ነበረውና ከውኃው ውስጥ እባብ ወጣ በዚህ ምክንያት ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ ማርያም እምነ ናስተበቍዓኪ እምአርዌ ነዓዊ ተማህፀነ ብኪ በእንተ ሃና እምኪ ወኢያቄም አቡኪ ማህበረነ ዮም ድንግል ባርኪ ብለው ውኃውን ቢባርኩት እባቡ ጠፍቷል።
7. ጸሎተ እግዝእትነ ማርያምን እመቤታችን ተናግረዋለች /ሉቃ.1÷46-55/
8. ውዳሴ ማርያምን ቅዱስ ኤፍሬም በዕድሜዋ ልክ 64 አድርጎ ደርሶታል። ስንክ ሐም.15
9. አነቀጸ ብርሃንን ቅዱስ ያሬድ ስንክ ግን.11
10. ይቄድስዋን ቅዱስ ኤፍሬም ደርሶታል።

<u>የመልክን ድርሰት ንጉሥ ሰሎሞን እንደጀመረ ይነገራል</u> ይኸውም በመኃልይው የጌታችንና የእመቤታችን መልክ ውበት ስለገለጸ ነው። /ጥቢ.16÷21/ ለእያንዳንዱም መልክ ሰላምታ ማቅረብ እንዲገባ ጳውሎስ ለወዳጆቹ ቅዱሳንም ጽፎላቸዋል። /ሮሜ.16÷1-16/

1. የመልክአ ማርያም ደራሲ አፄ ናዖድ ነው።

2. የመልክአ ኢየሱስ ደራሲ አባ አምደ ሐዋርያት የሚባል መነኩሴ ነው ዘሚካኤልም ይባላል/ ሕዝ.1÷28/ ዘኁ.12÷8
3. የመልክአ ሥላሴ ደራሲ አባ ስብሃት ለአብ የጣናው መምህር በ17ኛው መቶ ክ/ዘመን አጋማሽ ላይ በአፄ ኢያሱ ቀዳማዊ ነው። መርስኤ ኃዘን ወ/ቂርቆስ የታሪክ ዘመን ትዝታዬ ምንይልክ ዘመነ መንግሥት አዲስ አበባ 1936 ዓ.ም ከተፃፈው
4. የመልክአ መስቀል ደራሲ አቡቶ ዘሩፋኤል ነው።
5. የመልክአ ሥዕል ደራሲ አፄ ገላውዴዎስ ነው።
6. የመልክአ ቍርባን ደራሲ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ በአንክበር ሚካኤል ነው።
7. የቅኔ አገባብ ደራሲው አፄ በዕደ ማርያም እንደሆነ ይነገራል።
8. የመልክአ ሰማእታት ደራሲው መሰንቆ ድንግል የሚባል የመርጠ ለማርያም ካህን እንደሆነ ይነገራል።
9. የመልክአ ተክለሃይማኖት ደራሲ ከአፄ ገላውዴዎስ ጋር ምድረ አዳል ላይ በ1551 ዓ.ም ሰማዕትነትን የተቀበለው የደብረ ሊባኖስ አጨጌ አባ ዮሐንስ ከማ ነው። ወድቆ አይሰበር ዮሐንስም ይባላል።
10. የመልክአ ኖብ ደራሲ አባ ወልደ ክርስቶስ የሚባል ነው።
11. የመልክአ ኤጲስጣቴዎስ ደራሲ አባ ዝክሩ የሚባል መነኩሴ እንደሆነ ይነገራል።
12. የመልክአ ኤፆም ደራሲ አፄ ልብነ ድንግል እንደሆነ ይነገራል
13. የመልክአ እንጦንዮስ ደራሲ አባ አካለ ክርስቶስ የሚባል መነኩሴ እንደሆነ ይነገራል።
14. የመልክአ ኪዳነ ምህረት ደራሲ አባ ዘመለኮት የሚባል መነኩሴ እንደሆነ ይነገራል።
15. የመልክአ ዮሐንስ መጥምቅ ደራሲው አባ ዘሩፋኤል እንደሆነ ይነገራል። የመልክአ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ደራሲ አባ አምደ ሐዋርያት የሚባል መነኩሴ ነው።
16. ድርሳነ ሚካኤልንና መልኩን ሊቀ ጳጳሳት ዱማትዮስ ነው።

17. የመልክአ ገብርኤል ደራሲ አባ ዘመለኮት ነው።
18. የመልክአ ጊዮርጊስ ደራሲ አፄ ዘርዓያዕቆብ ነው።
19. የመልክአ ውዳሴና ሰቆቃወ ድንግል ደራሲ አባ ጊዮርጊስ።
20. የማኅሌተ ጽጌ ደራሲ ጽጌ ድንግል ነው።
21. የመልክአ ጉባኤ የሁሉንም መልክ በአንድ ላይ ሰብስቦ የያዘ ነው። አስተጋባኢው አይታወቅም።

ምእራፍ 38

ዐሥሩ መዓርጋት /ማቴ.13÷8/

ሀ. ባለ 30 ፍሬ የንጽሐ ሥጋ (ወጣንያን)
ለ. ባለ 60 ፍሬ የንጽሐ ነፍስ (ማዕከላውያን)
ሐ. ባለ 100 ፍሬ የንጽሐ ልቡና (ፈጻምያን) ምሳሌዎች ናቸው።

ሀ. የንጽሐ ሥጋ ማዕረጋት

1. ጽማዌ (ከኃጢአት ይርቃሉ የዓለምን ነገር ይረሳሉ ቅዱሳን መላእክትን ለማየት ይበቃሉ)
2. ልባዌ (በመንፈስ ቅዱስ መግቦት ይኖራሉ /ዘዳ.9÷9/ ቅዱሳን መላእክትን እስከመለየት ይችላሉ። /ትን.ዳን.9÷21/
3. ጣዕመ ዝማሬ (አመስግነው አይጠግቡም ድምጻቸው ሳይቀር ኃይል ይኖረዋል /የሐዋ.16÷25/)

ለ. የንጽሐ ነፍስ ማዕረጋት

4. አንብዕ (አንብዐ ንስሐ) የዕንባ ሐብት ነው። ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን ምረረ ገሃነምን እያሰቡ ያነባሉ። /ሮሜ.12÷11 የሐዋ 20÷31 ሉቃ.6÷21/
5. ኩነኔ ሥጋቸው ለነፍሳቸው ፈጽሞ ይገዛል። /1ቆሮ.9÷27 ገላ.5÷2 ሮሜ.6÷6/
6. ፍቅር ሁሉን የሚወድ ሃብት ነው። /ማቴ.5÷45-48 ሉቃ.6÷3 ሮሜ.12÷9 1ኛ ቆሮ.13÷3/ በዚህ ማዕረግ እንስሳት ሁሉ ይገዙላቸዋል። /መዝ.90÷13 ሉቃ.10፡17 1ነገ.17÷4/

7. ሑሠት በደመና በባህር ይጓዛሉ ብዙ ማዕረጋትንም በዚህ ማዕረግ ይፈጽማሉ /2ጴጥ.1÷4 2ኛ ነገ.2÷4 1ኛ ነገ.17÷18/ ሁሉንም የማወቅ ፀጋ ይኖራቸዋል /1ቆሮ.13÷12 የሐዋ.5÷3-9/

ሐ. የንጽሐ ልቡና ማዕረጋት

8. ንፃሬ መላእክት ከመላእክት ጋር ያመሰግናሉ ያዝሏቸዋልም /1ቆሮ.6÷2
9. ተሰጥሞ ዓሣ በባህር ሰጥሞ እንደሚኖር ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥመው ይኖራሉ ሕሊናቸው ፍፁም ደስተኛ ብሩህ ይሆናል። /2ቆሮ.6÷10 ፊልጵ.4÷12/
10. ከዊነ እሳት (ነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ) በብርሃን ይከበባሉ እግዚአብሔርን በንጉሥና በተለያየ አምሳያ ያዩታል /ማቴ.5÷8 ዘፍ.18÷1 ኢሳ.6÷1-8 ራዕ.4÷1 የሐዋ.7፡53/ ረቂቃን፣ ምሉዓን ፣ እሳታውያን እስከመሆን ይደርሳሉ። /ዮሐ.1÷40 / ቅዱሳን ሐዋርያት እስከ 10 ሰዓት ከርሱ ጋር ዋሉ የተባሉላቸው እስከ ዐሥረኛው ማዕረግ መብቃታቸውን ምሥጢሩ ይጠቁማል።

ከመጽሐፈ ስንክሳር አርኬ

ለዘፀሐፍ በክርታስ ወለዘአጽሐፍ እንዘ ይደርስ ለዘአንበቦ ወለዘተርጉሞ በልሳን ሐዲስ ወለዘ ሰምዓ ቃሉ በእዝነ መንፈስ በጸሎተ እሙ ማርያም አራቂተ ኩሉ እምባይስ ህቡረ ይምህረነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ለዓለመ ዓለም አሜን።

ምእራፍ 39

ዓመተ ዓለምሁልምንት ሺህ ነው /ዕዝ.ሱቱ.2÷36፣6÷5 ዘዳ.4÷32 መዝ.76÷5

ዓመተ አዳም ወሶጎ

ዓመተ አዳም ማለት አዳምና ሶጎ ዘመናትን ይቆጥሩበት የነበረ የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት ነው። ሊቀ ነቢያት ሙሴ ይህንን የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት ተከትሎ የአበውን ትውልድና ዕድሜ ሲጽፍ አዳም የኖረበት ዘመን 930 ዓመት ሆነ ሞተም ብሎ /ዘፍ.5÷3 / ይጀምርና አዳም በተፈጠረ በ1256

ዓመት በኖኅ ዕድሜ በ6መቶኛው ዓመት በ2ኛው ወር ከወሩም በ17ኛው ቀን መርከቢቱ በአራራት ተራሮች ላይ ዐረፈች ይላል ዘፍ.7÷24 :: ሙሴ በ2ኛው ወር ማየ አይህ ዘነመ፣ በ7ኛው ወር መርከቢቱ በተራራ ላይ ዐረፈች ብሎ እሁድን መነሻ በማድረግ ነው:: ምክንያቱም 2ወር 7 ወር ብሎ ለመጻፍ መሠረቱ አንድ ብሎ መጀመር ነውና:: ስለዚህ እሁድ መጋቢት 29 ቀን ጥንተ ዕለት ጥንተ ፍጥረት ጥንተ ዘመን መሆንዋ በዚህ ይታወቃል 2ኛ ወር የተባለው ግን ግንቦት ሲሆን 7ወር የተባለው ጥቅምት ነው:: ይህም ከግንቦት 17 ቀን እስከ ጥቅምት 17 ቀን ያለው የዕለታት ቍጥር 150 ይሆናል:: 150 ቀን ሲደመር ወርህ ሲሰፈር 5 ወር ይሆናል እንዲህ የሚሆነው በዓመተ አዳም ወኖኅ አቆጣጠር ሥርዓት እንጂ በሌሎች የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት እንዲህ ትክክል አይመጣም የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት በዓመተ አዳም ወኖኅ አቆጣጠር ሥርዓት የተመሠረተ ስለሆነ የየወሩ ምድብ ቀን 30 ሆኖ ይገኛል::

የኢትዮጵያውያን እና የምዕራባውያን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት

አዳም በገነት የኖረው ለ7 ዓመታት ከ1 ወር ከ17 ቀን ብቻ ነበር:: ኩፋ.4÷16 አዳም በድሎ ከገነት በተባረረ ጊዜ እግዚአብሔር ከ5 ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጁ ተወልዶ እንደሚያድነው ቃል ገብቶለት አጽናንቶታል:: ኢትዮጵያውያን የዘመን ቀመራቸው የሚጀምረው አዳም ከተሰደደበት ጀምሮ ሲሆን ምዕራብያውያን ግን አዳም ከተፈጠረበት አንስቶ ስለሚቆጥሩ በመካከሉ የ7 ዓመት ልዩነት ሊኖረን ችሏል::

የዘመን መለወጫ ወርና ዕለት መስከረም

የኖኅ ልጅ ካም ከወንድሞቹ ጋር ዕጣ በተጣጣለ ጊዜ አፍሪካ ደረሰው ካም ወደዚህ ምድር የገባው ልምላሜና አበባ ደምቆ አሸብርቆ በሚታይበት ሌሊትና መዓልት በሰዓት በሚተካከሉበት (ዕሪና መዓልት ዕሪና ሌሊት በሚሆንበት) በመስከረም ወር ነበር:: እግዚአብሔር ለእስራኤል ከግብጽ የወጣችሁበት ወር የዓመት መጀመሪያ ይሁናችሁ እንዳላቸው:: /ዘፀ.12÷1/ ሁሉ የካም ልጆችም ይህንን ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን ወር የዓመት

መጀመሪያ ይሁነን ብለው ርእሰ አውደ ዓመት አድርገው ሰይመውታል:: /ኢ.ሳ.30÷29 ይህ የመስከረም ወር በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በተለይ ከዘመነ ሥጋዌ በፊት በዓለም ሁሉ የዓመት መጀመሪያ እንደነበረ ይነገራል:: መስከረም የመጸው መባቻ ከመሆኑም በተጨማሪ ከላይ እንደተጠቀሰው

ምዕራፍ 40

መርሐ ኅልቈ ዘመን ዘኢትዮጵያ

ዓ.ም	ወንጌላዊ	የዘመን መለወጫ ቀን	አበ ቅቴ	መጥ ቅዕ	ጾመ ነነዌ	ዐቢይ ጾም	ደብረ ዘይት
፲፱፻፺፯	ማቴ.	ቅዳሜ	፳	፲	የካ.፲፬	የካ. ፳፰	መጋ ፳፭
፲፱፻፺፰	ማር.	እሁድ	፩	፳፱	የካ.፮	የካ. ፳	መጋ ፲፯
፲፱፻፺፱	ሉቃ.	ሰኞ	፲፪	፲፰	ጥር.፳፩	የካ. ፭	መጋ ፪
፪ሺ	ዮሐ.	ረቡዕ	፳፫	፯	የካ. ፲	የካ. ፳፬	መጋ ፳፩
፪ሺ፩	ማቴ.	ሐሙስ	፬	፳፮	የካ. ፪	የካ. ፲፮	መጋ ፲፫
፪ሺ፪	ማር.	ዓርብ	፲፭	፲፭	ጥር. ፲፯	የካ. ፩	የካ ፳፰
፪ሺ፫	ሉቃ.	ቅዳሜ	፳፮	፬	የካ. ፯	የካ. ፳፩	መጋ ፲፰
፪ሺ፬	ዮሐ.	ሰኞ	፯	፳፫	ጥር. ፳፰	የካ. ፲፪	መጋ ፱
፪ሺ፭	ማቴ.	ማክሰ	፲፰	፲፪	የካ. ፲፰	መጋ. ፪	መጋ ፳፱
፪ሺ፮	ማር.	ረቡዕ	አልቦ	፴	የካ. ፫	የካ. ፲፯	መጋ ፲፬
፪ሺ፯	ሉቃ.	ሐሙስ	፲፩	፲፱	ጥር. ፳፭	የካ. ፱	መጋ ፮
፪ሺ፰	ዮሐ.	ቅዳሜ	፳፪	፰	የካ. ፲፬	የካ. ፳፰	መጋ ፳፭
፪ሺ፱	ማቴ.	እሑድ	፫	፳፯	ጥር. ፳፱	የካ. ፲፫	መጋ. ፲
፪ሺ፲	ማር.	ሰኞ	፲፬	፲፮	ጥር. ፳፩	የካ. ፭	መጋ. ፪
፪ሺ፲፩	ሉቃ.	ማክሰ	፳፭	፭	የካ. ፲፩	የካ. ፳፭	መጋ. ፳፪
፪ሺ፲፪	ዮሐ	ሐሙስ	፮	፳፬	የካ. ፪	የካ. ፲፮	መጋ. ፲፫
፪ሺ፲፫	ማቴ.	ዓርብ	፲፯	፲፫	የካ. ፲፭	የካ. ፳፱	መጋ. ፳፮
፪ሺ፲፬	ማር.	ቅዳሜ	፳፰	፪	የካ. ፯	የካ. ፳፩	መጋ. ፲፰
፪ሺ፲፭	ሉቃ.	እሑድ	፱	፳፩	ጥር. ፳፱	የካ. ፲፫	መጋ. ፲
፪ሺ፲፮	ዮሐ.	ማክሰ	፳	፲	የካ. ፲፰	መጋ. ፪	መጋ. ፳፱
፪ሺ፲፯	ማቴ.	ረቡዕ	፩	፳፱	የካ. ፫	የካ. ፲፯	መጋ. ፲፬
፪ሺ፲፰	ማር.	ሐሙስ	፲፪	፲፰	ጥር ፳፭	የካ. ፱	መጋ. ፮
፪ሺ፲፱	ሉቃ.	ዓርብ	፳፫	፯	የካ. ፲፭	የካ. ፳፱	መጋ. ፳፮
፪ሺ፳	ዮሐ.	እሑድ	፬	፳፮	ጥር ፳፱	የካ. ፲፫	መጋ. ፲
፪ሺ፳፩	ማቴ.	ሰኞ	፲፭	፲፭	ጥር ፳፩	የካ. ፭	መጋ. ፪
፪ሺ፳፪	ማር.	ማክሰ	፳፮	፬	የካ. ፲፩	የካ. ፳፭	መጋ. ፳፪
፪ሺ፳፫	ሉቃ.	ረቡዕ	፯	፳፫	ጥር ፲፮	የካ. ፲	መጋ. ፯
፪ሺ፳፬	ዮሐ.	ዓርብ	፲፰	፲፪	የካ. ፲፭	የካ. ፳፱	መጋ. ፳፮
፪ሺ፳፭	ማቴ.	ቅዳሜ	አልቦ	፴	የካ. ፯	የካ. ፳፩	መጋ. ፲፰
፪ሺ፳፮	ማር.	እሑድ	፲፩	፲፱	ጥር ፳፪	የካ. ፮	መጋ. ፫
፪ሺ፳፯	ሉቃ.	ሰኞ	፳፪	፰	የካ. ፲፪	የካ. ፳፮	መጋ. ፳፫
፪ሺ፳፰	ዮሐ.	ረቡዕ	፫	፳፮	የካ. ፫	የካ. ፲፯	መጋ. ፲፬
፪ሺ፳፱	ማቴ.	ሐሙስ	፲፬	፲፮	ጥር ፲፰	የካ. ፪	የካ ፳፱
፪ሺ፴	ማር.	ዓርብ	፳፭	፭	የካ. ፰	የካ. ፳፪	መጋ ፲፱
፪ሺ፴፩	ሉቃ.	ቅዳሜ	፮	፳፬	ጥር ፴	የካ. ፲፬	መጋ. ፲፩
፪ሺ፴፪	ዮሐ.	ሰኞ	፲፯	፲፫	የካ ፲፱	መጋ. ፫	መጋ ፴
፪ሺ፴፫	ማቴ.	ማክሰ	፳፰	፪	የካ. ፬	የካ. ፲፰	መጋ. ፲፭
፪ሺ፴፬	ማር.	ረቡዕ	፱	፳፩	ጥር ፳፮	የካ. ፲	መጋ. ፯
፪ሺ፴፭	ሉቃ.	ሐሙስ	፳	፲	የካ ፲፮	የካ. ፴	መጋ. ፳፯
፪ሺ፴፮	ዮሐ.	ቅዳሜ	፩	፳፱	የካ ፯	የካ. ፳፩	መጋ. ፩፰
፪ሺ፴፯	ማቴ.	እሑድ	፲፪	፲፰	ጥር ፳፪	የካ. ፮	መጋ. ፫
፪ሺ፴፰	ማር.	ሰኞ	፳፫	፯	የካ. ፲፪	የካ. ፳፮	መጋ. ፳፫
፪ሺ፴፱	ሉቃ.	ማክሰ	፬	፳፮	የካ. ፬	የካ. ፲፰	መጋ. ፲፭
፪ሺ፴፲	ዮሐ.	ሐሙስ	፲፭	፲፭	ጥር ፲፰	የካ. ፪	የካ. ፳፱
፪ሺ፴፩	ማቴ.	ዓርብ	፳፮	፬	የካ. ፰	የካ. ፳፪	መጋ. ፲፱

ታሪክና ግሥ ባለብዙ ፍሬ የታመነ የመጻሕፍት ወሬ እሴብሉ ሶእግዚአብሔር ዘረድአኒ ወእዜምር ለስመ እግዚብሔር ልዑል «የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ለልዑል እግዚአብሔር ስምም እዘምራለሁ::» መዝ.12÷12 «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን አሜን::» 1ተሰ.5÷27-28 አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረስው::